# መዝገበ ታሪክ



ክፍል ፪

«ተዘከሩ መኳንንቲክሙ ዘነገሩክሙ ቃለ <u>እግዚአብሔር</u>»
ዕብ 13:7

«<u>የእግዚአብሔርን</u> ቃል የነገሩአችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ»
ዕብ 13:7

ከመምህር ጎሩይ <u>ኤርምያስ</u>

ጥቅምት 1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ታህሳስ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አንደኛ ዕትም 1995 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም 1997 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም 1999 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም 2000 ዓ.ም
አምስተኛ ዕትም 2001 ዓ.ም
ስድስተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ሰባተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ስምንተኛ ዕትም 2005 ዓ.ም
ዘጠነኛ ዕትም 2006 ዓ.ም

ይህን መጽሐፍ በእቲሳ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም በቅኔ መምህርነት ተመድቤ ሳስተምር በ1988 ዓ.ም አዘጋጀሁት፤ በልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም አሳተምሁት::

## ማስታወሻነቱ

ከ46 ዓመታት በላይ ጉባኤ ሠርተው በማስተማር እያሌ ምሁራንን ለቅድስት ቤተክርስቲያን ላበረከቱት ለእኔም በመንፈስ ቅዱስ አባቴና መምህሬ ለሆኑት ታላቁ የቅኔ ምሁር ለክቡር መምህር መንግሥቱ ዘለዓለም ይሁንልኝ::

በመጽሐፉ ሙሉ ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን ሙያዊ አስተያየት ለሰጡኝ የቅኔና የወንጌል መምህራን ለመምህር ዓምደ ወርቅ ደሴ እና መምህር ኢያሱ ገ/አልፋ፤ ለክፍል ፩ መጽሐፍ ሕትመትና እገዛ ላደረጉልኝ ለወንድሜ ፈታሁ ገ/ወልድና ለንግድ ማተሚያ ድርጅት ኃላፊዎች እንዲሁም በማሠራጨት ለተባበሩኝ በሙሉ፤ አስተያየት ለለገሱኝ እና ይህን ጽሑፍ በኮምፒውተር በመጻፍ ለተባበሩኝ ለወ/ት ውበነሽ አዲሱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

## ማውጫ


| ተራ ቁ | | አርእስት |
|---|---|---|
| 1 | | መግቢያ |
| 2 | ምዕራፍ | 1 መዝገበ ታሪክ ዘመጋቢት |
| 3 | " | 2 መዝገበ ታሪክ ዘሚያዚያ |
| 4 | " | 3 መዝገበ ታሪክ ዘግንቦት |
| 5 | " | 4 መዝገበ ታሪክ ዘሰኔ |
| 6 | " | 5 መዝገበ ታሪክ ዘሐምሌ |
| 7 | " | 6 መዝገበ ታሪክ ዘነሐሴ |
| 8 | " | 7 መዝገበ ታሪክ ዘጳጉሜን |
| 9 | የግዕዝ ቅኔያት | |




## መግቢያ

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፡-

ክርስቶስ ኢየሱስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የሚመሰገን፣ በዚህ ጊዜ ተገኘ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይባል በባሕርይ ሁሉን የሚያውቅ የሚመረምር እርሱ ግን የማይመረመር ሁሉን በከሀሊነቱ ያስገኘ ለርሱ ግን አስገኝ የሌለው ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ምንም ምን የሚሳነው የሌለ ዓለማትን ፈጥሮ የሚገዛ፣ በኋለኛው ዘመን ሰውን በኃጢአት ምክንያት ካት ቦታውን ልጅነት ክብሩን ያጣ ሰውን ወደ ቦታው ወደ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ከንጽሕት ድንግል ማርያም በማይመረመር ግብር ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ በድንግልና ተወልዶ በፈቃዱ ሞትን ሞቶ በትንሣኤው ድል ነሥቶ ለዓለም ፍጹም ድኅነትን የሰጠ፡፡ በክብር በምስጋና እንዳረገ እንዲሁ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በኃጥአን ሊፈርድባቸው በግርማ መለኮት በይባቤ መላእክት ዳግመኛ የሚመጣ ለኅልፈት የተፈጠረውን የሚያሳልፍ ለኅልፈት ያልተፈጠረውን በትንሣኤ የሚያጸና የጌቶች ጌታ የንጉሦች ንጉሥ፣ የአማልክት አምላክ ገባሬ ፍጥረታት /ዮሐ 1:1፣14፣ ዮሐ፡ 7:24፣ ሐዋ 1:11 ቆላ 1:14 20፣ዮሐ 5:20/ መሆኑን የምታሳውቅ የምታስረዳ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘች እውነተኛና ቀጥተኛ ሃይማኖት ናት፡፡

ይህች ሃይማኖት ለሰው ልጆች ድኅነት /ሕይወት/ መሠረት ናት፡፡ ስለዚህም ክርስቶስ መሠረታት ነቢያት በትንቢት ሐዋርያት በስብከት ገለጧት፣ ሰማዕታት በበላውያን ፊት መስክረው አንገታቸውን ለሰለት ሰውነታቸውን ለእሳት ሠጡላት፣ ጻድቃን ዓለምን ንቀው ራሳቸውን ክደው ተከተሉአት ተገዙላት/ ሊቃውንት ከመናፍቃን ተከራከሩላት መከራም ተቀበሉላት፣ አዎን የነርሱ ቤዛነት ተዋሕዶን በአጋንንት በመናፍቃን ከመዋጥ ታደጋት፡፡ ቤተክርስቲያን መከራውን ታግሠው ተቀብለው ይህችን ርትዕት ሃይማኖት ጠብቃ በማቆየትና ለተተኪ በማስተላለፍ ታላቅ ውለታ የዋሉ /በጎ ሥራ የሠሩ/ ነቢያት ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትንና ሊቃውንትን ሁሌም ስታስባቸው በጎ ሥራቸውንም ስትመሰክርላቸው ትኖራለች፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ከሊቃውንት ሲያያዝ በመጣ ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓቷ ላይ

በቀለያዩ መንገድ ትችት የሚያቀርቡ በተለይም እኒህን ራሳቸውን ለሃይማኖት አሳልፈው ቤዛ አድርገው የሠጡ ቅዱሳንን ማክበር ማክበሩን የሚቃወሙ፤ ባይረዱትም ተቀብለናል የሚሉትን ወንጌልን በሐዋርያትና ከተመራማሪዎች የክህደት መንጋጋ ከመቀረጣጠፍ ታድገው ያቆዩላቸውን ባለውለታዎቻቸውን መዘንጋታቸው ግልጽ ነው። በሃይማኖትና በበጎ ምግባር አርአያ የሚሆኑ ቅዱሳን ሃይማኖታቸውና በጎ ምግባራቸው ወንጌል በተነገረበት ሁሉ ለጌርላቸው ሊመሰክርላቸው እንደሚገባ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ እማን እብለክሙ በኀበ ተሰብከ ዝ ወንጌል በውስተ ኩሉ

ዓለም ያንብቡ ላቲ ዘገብረት ዛቲ ብእሲት ወይዘከርዋ እውነት እላችኋለሁ። በዓለሙ ሁሉ ይህ ወንጌል በተሰበከ በት ቦታ ይህች ሴት ያደረገችውን ደናገሩ ያሰቡአት ማቴ 26:13 ሲል ማርያም እንተ ዕፍረት ሽቱ በቀባችው ጊዜ ለሐዋርያት የተናገረውን፤ ቅዱስ ጳውሎስም መምህሮቻችሁንን አስቡ ዕብ 13:7 ያለውን ሳያነቡ ቀርተው ከሆነ ወንጌሉን ተሸክሞ ለመዞር እንጂ አንቦ ለመጠቀም ባለመታደላቸው 'የተማሩትውን አትበላም...' እንደተባለው ሆኑ ማለት ነው እጅግ ያሳዝናል። አንበውት ከሆነም እነርሱ ሊፈጽሙት ባለመቻላቸው ብና ሙሉ ቅናት አድርባቸዋል ማለት ነው። ለማንኛውም የቤተክርስቲያን ሥርዓቷ ምንም የማይወጣለት ተገቢና እውነተኛ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

የዚህም መጽሐፍ ዓላማ ቤተክርስቲያን በሃይማኖትና በበጎምግባራቸው የምታከብራቸውንና እንደ ወንጌሉም ቃል ገድላቸውን የምትመሰክርላቸውን ቅዱሳንና በዓላቸውን ማስታወቅ ነው። ከመስከረም 1 የካቲት 30 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት በዓል ተሠርቶላቸው የሚታሰቡትን ቅዱሳን እንዲሁም የጌታ፣ የእመቤታችንና የመላእክት በዓላት ታሪክ «መዘገበ ታሪክ ክፍል ፩» በሚል ርእስ ከዚህ በፊት ታትሞ መሠራጨቱ ይታወሳል። ይህም የዚያ ሁለተኛ /ቀጣይ/ ክፍል ሆኖ ከመጋቢት 1 እስከ ነሐሴ 5 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት የሚዘከሩትን የያዘ ነው ክፍል 1 መጽሐፉን ያነበቡ ምእመናን ታሪኩ የተፈፀመበት ዘመን እንዲካተት በጠየቁት መሠረት ከዚህ መጽሐፍ በስተመጨረሻ በተዘረዘሩ መጻሕፍት ዋቢነት ረቂቁን ዘመኑን እያካተትኩ በድጋሚ ጽፌዋለሁ። የክፍል 1 ታሪኮች ዘመንም በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተገልጿል።

እንበን እንድናስተውለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን።

አሜን።





## መጋቢት 5 ዕረፍቱ ለአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ

ሀገራቸው ንሒሣ (ግብጽ) ነው። አባታቸው ስምዖን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ልጅ አጥተው 30 ዘመን ሲያዝኑ ኖረዋል። አንድ ቀን አቅሌስያ ቤተእግዚአብሔር ገብታ ከሰዐሉ ሥላሴ ሥር ወድቃ ስትማፀን "ንሥኢ ወልደ ዘይትሌዐል ቀርነ አምኑሂ ሰማይ .. ከብሩ ከሰማይ ከፍታ የሚበልጥ ልጅ እነሆ ተቀበዪ" የሚል ድምጽ ሰማች። በዚህም መሠረት አባታችን መጋቢት 29 ቀን ተጸንሰው ታኅሳስ 29 ቀን ተወለዱ።

ዓይን በገለፁት ጊዜ ከሚታይ ነገር ላይ እንዲያርፍ እርሳቸውም በተወለዱ ጊዜ አፉፍ ብለው ተነሥተው "ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ዘአውጽአኒ እምጽ ልመት ውስተ ብርሃን» ብለው በማመስገናቸውና ኋላም ምድራዊ መብል መጠጥ ሳይመገቡ ሳይጠጡ ለምስጋና ተግተው በመኖራቸው መላእክትን ይመስላሉ።

ሦስት ዓመት ሲሆናቸው ቅዱስ ገብርኤል ከእመቤታችንና በገነት ካሉ ቅዱሳን ዘንድ አስባርኮ ገዳማውያን ካሉበት ምኔት ወስዶ ከበሩ አኖራቸው። አበምኔቱ አባ ዘመደብርሃን ምልክት ተነግሮት ቢሄድ ፍሡሐ ገጽ ሆነው አግኝቷቸዋል። አሳድጎ አስተምሮ ከመዓርገ ምንኩስና አድርሷቸዋል። ከዚህ በኋላ ሀብተፈውስ ተሰጥቷቸዋል። ባንድ ቀን እልፍ ዕውራን ሀንካሳን ፈውሰዋል። ኋላ ግን ኢጲስ ቆጶሳቱ ካህናቱ ዝናቸውን ሰምተው እየመጡ ግብር የሚያስፈቷቸው ቢሆን ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ ከጌታ ፊት አቀረባቸው። ብዙ በገድልህ በትሩፋትህ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም የሚድኑ ነፍሳት አሉና ከሰው ተለይተህ ወደ ጫካ ግባ። ኑሮህም ከ60 አናብስትና ከ60 አናምርት ጋር ይሁን አላቸው። ጌታዬ ምን ተመግበው ይኖራሉ? አሉት። "ዘኪድከ እበለ-እገሪ ይልሕሱ ወበውእቱ ይጸግቡ .. የረገጥከውን ትቢያ ልሰው ያው ምግብ ሆኗቸው ይኖራሉ" ብሏቸው ውሳጤ ገዳም ገብተው ከአናብስትና አናምርት ጋር ይኖሩ ጀመር። ዳንኤል ከአናብስት ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ አናብስቱ እንደ ድመት ከእግሩ በታች ሆነው እንደተገኙ የረገጡትን ትቢያ ይልሱ ይታዘዟቸውም ነበር።

በዚህ መልኩ 30 ዓመት ከቆዩ በኋላ ጌታ በአንድነት በሦስትነት ተገልጾ ምን ላድርግልህ ትሻለህ? አላቸው። መጀመሪያ ላሉበት መጸለይ ይህ ልና የምድረ ገዘታን ሰዎች ማርልኝ አሉት። 3000 ኃጥአንን ከሲኦል አውጥቶ ገነት አግብቶላቸዋል። ከዚህ በኋላ

"ሑር ምድረ ኢትዮጵያ ወበህየኒ ሀለውከ ነፍሳት ዘታወጽእሙ .. ወደ ኢትዮጵያ ሂድ" አላቸው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል በሠረገላ ነፋስ ጭኖ ምድረ ከብድ አድርሷቸዋል፡፡ ዳግመኛም ወደ ዝቋላ (ደብር ቅዱስ) ወስዷቸው ከዚያ ሆነው በንጽሐ ልቡና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃጢአት አይተው ከባሕሩ በራሳቸው ቆመው ይጸልዩ ጀመር፡፡ አርባ ቀን ሲሆናቸው መልአኩ መጥቶ "ዘገብረ ተዝካረከ ወዘጸውዐ ስመከ እምሕር ለከ ብሎሀል" አላቸው፡፡ መላ ኢትዮጵያን ካልማረልኝ አልወጣም ብለው መቶ ዓመት ሲጸልዩ ኑረዋል፡፡ ከመቶ ዓመት በኋላ ጌታ "ተንሥእ ወጻእ መሐርኩ ለከ ኩሉ ኢትዮጵያ .. ምሬልሀለው ውጣ" ብሏቸው ወጥተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ምድረ ከብድ ወርደው ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ሆነው ሰባት ዓመት እንደ ትኩል ዓምድ ሆነው፡ ዓይናቸውን ሳይከድኑ ሰባት ዓመት ቆመው ጸልየዋል፡፡ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ቁራ መስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አንቁሮ አሳወራቸው፡፡ ሁለት ሱባዔ ሲፈጽሙ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል መጥተው እፍ ብለው አድነዋቸዋል፡፡ ከዚያ ተነስተው ወደ ዝቋላ ሲሄዱ ሥላሴን በአምሳለ አረጋውያን ከጥላ ሥር አርፈው አገኟቸው፡፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ተማጽነናል አዝለህ አንድ አንድ ምዕራፍ ሸኘን አሏቸው፡፡ አዝለው ከሸኙአቸው በኋላ በአንድነት በሦስትነት ሆነው ታዩቸው፤ ደንግጠው ወደቁ፡፡ እንሥቶ ዝቋላ ወርደህ ጠላቶችህን ተበቀላቸው አሏቸው፡፡ በዘባነ መብረቅ ደርሰው ሰባቱን ሊቃነ መላዕክት አጋዥ አድርገው አልፍ አእላፍ አጋንንትን በመብረቅ አጥፍተዋል፡፡

አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አባ አንበሴ ዘሐዘሎ እና አባ ብንያም ዘግብጽ ዜናቸውን ሰምተው እናብስቶቻቸውን አስከትለው ሊጠይቋቸው መጡ፡፡ በሰባተኛው ቀን ተገለፁላቸው፡፡ እናብስቶቻቸው በርሳቸው እናብስት ተውጠው አዝነው ነበርና እናብስቶቻቸውን ጌታ ያዘዛላችሁ የእግሬን ትቢያ እንጂ ሥጋና ደም ነውን? ትፋ ብለው ካስተፏቸው በኋላ ቢባርኳቸው ተነሥተዋል እነርሱም ርኢነ መንክረ ኦ አባ እያሉ ተመልሰዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ምዕራብ ሀገር ወሰዳቸው፡፡ የዐረብ ንጉሥ በጣዖታቱ ያደሩ አጋንንት ፈርተው ሲሸሹ ጣዖታቱ ሲሰባበሩ አይቶ ሰውነታቸው የሐር ፈትል በመሰለ ፀጉር የተሸፈነ ነበርና አንተ ፀጉር ልብሱ ምንድር ነህ ሰው ነህን? አላቸው፡፡ አዎን ሰማይና ምድርን በፈጠረ በኢየሱስ ክርስቶስ የማምን ሰው ነኝ አሉት፡፡ አይሁድ ሰቅለው በገደሉት ሰው ታምናለህን? አላቸው፡፡ እፍርበት መስሎሀልን አንተም ብታምንበት የዘለዓለም ሕይወት ባገኘህበት ነበር አሉት፡፡ እሳት አንድዱና አቃጥሉት አለ፤ አነደዱ፡፡ ማንም ግድ ሳይላቸው



በፊቃዳቸው ከእሳቱ ገብተው ወጡ ከሠራዊቱ ብዙዎች አመን አሉ፡፡ በሰይፍ አስፈጃቸው፡፡ እርሳቸውንም ሊመታቸው ሲቃጣ መብረቅ ወርዶ ከነተከታዮቹ ፈጅቷቸዋል፡፡ ወዲያውም መላእክተ ጽልመት ነፍሶቻቸውን እጅ ሲያደርጉ አይተው ይህ ሁሉ በኔ ምክንያት አይደለምን? ብለው ከታላቅ ገደል እግራቸውን በገመድ አስረው ቁልቁል ተሰቀሉ፡፡ ሰይጣን ገመዱን በጠሰው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተቀበላቸው፡፡ ተወኝ በራሴ ልቁም አሉት፡፡ በራሳቸው ቆመው በጥርሳቸው ደንጊያ ነክሰው 30 ዘመን አልቅሰዋል፡፡ ጌታ ምሬልሃለሁ ብሏቸው ደንጊያውን ሲጥሉት አራት ጥርሶቻቸው በደንጊያው ላይ ተተክለው ቀርተዋል፡፡



በሌላ ጊዜ ሲመለሱ ጥርሶቻቸው በተተከሉበት ደንጊያ መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የሽቱ እንጨት ደማቸው ከነጠበበትም ወይን በቅሉበት አግኝተዋል።

እንዲህ ለሰማዕ ዕፁብ በሆነ ግብር 262 ዓመት በኢትዮጵያ ኖረው በ562 ዓመታቸው በተሰፋቸው ያመነውን በኪዳናቸው የተማፀነውን ጌታ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲምርላቸው ተስፋቸውን ተቀብለው በዚህ ዕለት በዕለተ እሁድ ዐርፈዋል። መላእክት በአክናፈ እሳት ኢየሩሳሌም ወስደው በየማነ ምስዋዕ ቀብረዋቸዋል።

ገብረ መንፈስቅዱስ የአምላክ አገልጋይ
ለኢትዮጵያ ብርሃን ነህ ፀሐይ
እናብስት አናምርት ሲታዘዙህ ኖሩ
የእግርህን ትቢያ ልሰው እያደሩ
ፈጣሪን በስምህ ስለተማፀኑ
ኃጥአን ከሲኦል ከገሃነም ዳኑ።

እንደሰማይ መልአክ ቢሆንም ኑሮህ
የአዳም ልጅ ነህና አንተም ሞትን ሞትህ
ምስጋና ቀለብህ ልብስህ የአምላክ ጸጋ
አንተን ለማወደስ ነፍሴ ሁሌም ትትጋ
የጻድቅ ሰው ጸሎት በነፍስም በሥጋ
ታሰጣለችና ለማያዩ ዋጋ።

ሮሜ 12:12 ፤ 15:30 ያዕ 5 :16

❖ ወደኢትዮጵያ የመጡት በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ስለሚታወቅ የነበሩት ከ9 – 14 ኛው ም.ዓ ድ/ል/ክ/ መሆኑ ነው።

## መጋቢት 8 – ዕረፍቱ ለማትያስ ሐዋርያ

ማትያስ ማለት ምትክ ማለት ነው። ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያት መቶ ሃያ ራሳቸውን ከእመቤታችን ጋር ሆነው በጽርሐ-ጽዮን – በማርያም እመ ማርቆስ ቤት – ለጸሎት ይተጉ ነበር። አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ ከእኛ ጋር የነበረ አስቆሮታዊ ይሁዳ ዳዊት “ወይኩና መዋዕሊሁ ኅዳጠ ወሢመቶሂ ይንሣእ ባዕድ – ዘመናቱ ጥቂት ይሁኑ ሹመቱንም ሌላ ይውሰድ” መዝ 108፥8 ብሎ ትንቢት ተናግሯልና ከኛ ጋር ከሚተጉ ወንድሞች አንዱን መርጠን ይሾም አለ። ዮሴፍንና ማትያስን አቁመው እኛ ባወቅን ዮሴፍንና ማትያስን መርጠናል። አንተ እግዚአ ማዕምረ ኩሉ ልብ አርኢ አሐደ እምእሉ ዘኀረይከ ዘይንሣእ ላዛቲ መልእክተ ሢመተ ሐዋርያት ዘኀ ደጋ ይሁዳ ይሑር ብሔር ... ኩላሊት ያመላለሰውን ልብ ያሰበውን መርምረህ የምታውቅ ሆይ ይህችን የሐዋርያት ሹመት ገንዘብ የሚያደርጋትን ከእኒህ ከሁለቱ የመረጥከውን ግለጽልን “ብለው ጸልየው ዕጣ ሲያጣጥሏቸው ለማትያስ ወጣ። የዚህ ጊዜ አሥራ ሁለተኛ ሐዋርያ ሆኖ ተቆጠረ። ሐዋ 1፥13 ፅ 20

ከበዓለ ሃምሳ በኋላ መዲናቸው ኢየሩሳሌምን ዓመት አስተምረው ዓለምን ተከፋፍለው ለማስተማር ዕጣ ሲጣጣሉ ለርሱ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ደረሰው። በዚህ ሀገር ያሉ ሰዎች እንደ አራዊት ሥጋ



የሚመገቡ ነበሩ፤ ከአደባባያቸው ገብቶ ሲያስተምር ይዘው ዓይኑን አውጥተው እንደላም ሣር እየመገቡ ከዘግ ቤት አስቀመጡት። በ40 ቀን ዓይኑ ምድሩ ሲለወጥ አይተው ሊመገቡት ነው። ከዚህ አስቀድሞ ግን ጌታ ሐዋርያው እንድርያስን ልኮለት ዓይኑን ፈውሶት ከእስሩ ፈትቶት ወጥተው ሲያስተምሩ ሊጣሏቸው መጡ። ወደ ጌታ ቢያመለክቱ ውኃ እስከ አንገታቸው አጥለቀለቃቸው ኋላ ግን ጸልየው አድነዋቸው አምነው ተጠምቀዋል። ባሕርያቸውም ተመልሶላቸው እህል የሚመገቡ ሆነዋል። ከዚህም የበለጠ ቤተክርስቲያን አሳንጾ ቀሳውስት ዲያቆናትን ሾሞ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር የሚመግባቸው ሆኗል። ካህናቱ ማትያስ በላዕለ – እኩያን ጌሬ፤ ሥጋ ወልድ ቅዱስ ሴሰዮሙ ወደሞ ክቡረ፤ ተወላጠ ሴሰይዎ ሎቱ ከመላህም ሣዕረ” እንዲል አርኬ።

ሠላሳ ዘመን ካስተማራቸው በኋላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማዳረስ ደማስቆ ወረደ። አረማውያን በብረት አልጋ አስተኝተው ሃያ አራት ቀን እሳት ሲያነዱበት ቆይተዋል። እርሱ ግን በውነቱ አምሮ ነጽቶ ደምቆ ደገኝ ነበር። በዚህ አምነው ተጠምቀዋል። በመጨረሻም በይሁዳ ከተሞች እየተዘዋወረ አስተምሮ በዚህ ዕለት በፈላሃን አርፏል።

ራሱን አዋርዶ ስለወንጌል ክብር
ማትያስ እንደላም ተመገበ ሣር።
እንዲሸጋገሩ ከሞት ወደ ሕይወት
ተማሩ ቢላቸው የወንጌልን ትምህርት
እንደእህል ቀቀሉት አቃጠሉት በእሳት።
እዩ አለማወቅ ልበ ደንዳናነት!

አሕዛብ ተጋግዘው በግፍ ሲያሰቃዩት
ይጸልይ ነበረ እንዲያገኙ ምሕረት።
ክፉውን በክፉ መመለስ ቀላል
ቢከብድም መታገሥ ዋጋ ያሰጣል።
ግፍ በጭንቅ ውስጥ መከራን መታገሥ
ሞኝነት አይደለም መድኃኒት ነው ለነፍስ።

ሮሜ 12፡ 12 1 ቆሮ 4:12 2 ቆሮ 4:18

## መጋቢት 10 – መስቀል

በዚህ ዕለት ጌታ የተሰቀለበት መስቀል በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች አማካይነት ሁለት ጊዜ ከተቀበረበት ወጥቷል። መጀመሪያ በንግሥት ዕሌኒ ከኢየሩሳሌም፥ ሁለተኛ በንጉሥ ሕርቃል ከፋርስ ወጥቷል። “ወበዛቲ ዕለት እንበለ ይዕዜ ጊሠመ፤ መስቀል ተረክበ እምዘተ ኅብዐ ወገብረ ሰላመ፤ በኢየሩሳሌም ቅድመ ወበፋርስ ዳግመ” እንዲል አርኬ።

የኢየሩሳሌሙ በክፍል 1 መጽሐፍ በገጽ 32 ተጽፏል። የፋርሱ ግን እነሆ። መሳፍንተ ፋርስ ግብጽ ዘምተው ድል ነስተው ሲመለሱ ከመካከላቸው አንዱ ኢየሩሳሌም ወርጄ አይሁድን ማርኬ እመጣለሁ ብሎ እግረ መንገዱን ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ አይሁድን ማርኮ ሲመለስ ንግሥት ዕሌኒ በኀልኀልታ ካሠራችው ቤተ መቅደስ ቢገባ

መስቀሉን እንደፀሐይ ሲያበራ አገኘው፡፡ ቢይዘው አቃጠለው፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለቱን ዲያቆናት አሸክሞ ሊላውንም ንዋያተ ቅድሳት ዘርፎ ወደሀገሩ ተመለሰ፡፡

የሮሙ ንጉሥ ሕርቃል ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፡፡ ግብር ገብቶ ቀኖና ይዞ አንድ ሱባኤ ሲፈጽም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ተረድቶ በአዋጅ ዘምቶ ድል ነሣው፡፡ መስቀሉም ያለበት ጠፍቶት ሲቸገር ሲቀብር ዲያቆናቱን ሲገድል በመስኮት ሆና ያየች ከኢየሩሳሌም የተማረከች አንዲት ብላቴና አሳይታው አውጥቶ በልብሰ መንግሥቱ ጠቅልሎ ወደቁስጥንጥንያ ወስዶታል፡፡

* ታሪኩ የተፈጸመው በ614 ዓ.ም ነው፡፡/1/

## መጋቢት 11 - ዕረፍቱ ለአባ አሌፍ ዘእም ፱ ቅዱሳን

## መጋቢት 12 በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ.መ

(1) ነሬ የቤ/ክ ታሪክ በዓ.መ ገጽ 145

በዚህ ዕለት ወደ በለዓም ተልኳል፡፡ ሀብተ መርገም የተሰጠው ነውና እስራኤል ከምድረ ግብጽ ወጥተው አርባ ዘመን በረሀ ለበረሃ ተጉዘው ሞአብ ሲደርሱ የሞአብ ንጉሥ ባላቅ ወልደ ሶፎር ግብጻውያንን በዘጠኝ መቅሰፍት በአሥረኛ ሞተ በኩር በአሥራ አንደኛ ስጥመት ያጠፋ፤ ጦር የማይመልሰው ጽኑ ጠላት ተነሥቶብኛል መጥተህ ርገምልኝ ብሎ እጅ መንሻ አሲዞ ላከበት፡፡ ዋሉ እደሩ አላቸው፡፡ ሌሊት ወደጌታ ቢያመለክት አትሂድ አለው፡፡ አልሆነም ሂዱ አላቸው፤ ሂዱ እጅ መንሻው ቢያንስበት መልእክተኞቹ ተራ ላከ፡፡ ዋሉ እደሩ ፈጣሪዬን ልጠይቅ አላቸው፡፡ ዋሉ አደሩ፡፡ ወደ ጌታ ቢያመለክት ሂድ ነገር ግን አትርገም አለው፡፡ ሂድ ብሎ አትርገም ማለት እንደምን ነው? ከሄድኩስ የማደርገውን አውቃለሁ ብሎ የሚረገመውን እያሰበ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰይፉን መዞ ለአህያው ታየት ፈርታ ቆመች፤ ሂጂ እያለ መላልሶ መታት፡፡ በሦስተኛው ከቅጽርና ከቅጽር መካከል ይዛው ገባች እግሩን ላጠችው፡፡ አሮጌ ነቢይ ብለሽ ነው እንዲህ የምትጫወቺብኝ? ወይኑ ጦር በያዝሁ በወጋሁሽ ሰይፍ ቢያዝሁ በቀላሁሽ ነበረ አለ፡፡ በሰው አንደበት "አኮኑ እድግትከ ዘትጼዕነኒ እምንዕስክ-ከልጅነትህ ጀምሮ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁ ምን? እስከ ዛሬ ሜዳውን ሩጪ ዳገቱን ውጪ ብትለኝ እንቢ ብዬ አውቃለሁ? አለችው፡፡ እውነትሽን



ነው አለ፡፡ በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገለጸለት፤ ከአህያው ወርዶ ሰገደለት እነሆ መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና ልቋቋምህ መጣሁ፤ ለምን አህያህን መላልሰህ መታሃት? ብሎ ገሠፀው፡፡ እርሱም በግንባሩ ተደፍቶ ከሰገደለት በኋላ ልመለስን? ብሎ ጠየቀ መሄዱን ሂድ ነገር ግን እግዚአብሔር የገለጸልህን እንጂ ሌላ እንዳትናገር እወቅ አለው፡፡ ሄደ፡፡ ባላቅ ደስ አለው፡፡ ስለመጣሁ ደስ አይበልህ የምናገረው እግዚአብሔር የገለጸልኝን ብቻ ነው አለው፡፡

ከዚህ በኋላ መሥዋዕት ሠውቶ ከመሥዋዕትህ ቁም አለው፡፡ ወደ ምሥራቅ ተሂዞሮ "ምንተ እረግም ዘእግዚአብሔር ኢረገመ፤ ምንተ ኢጼዕል ዘእግዚአብሔር ኢጸዐለ-እግዚአብሔር ያልረገመውን በምን ነገር እረግማለሁ እግዚአብሔር ያልሰደበውን በምን ነገር እሰድባለሁ" አለ፡፡ ርገምልኝ ብልህ ትመርቃቸዋለህን" አለው፡፡ የገለፀልኝን ብቻ እናገራለሁ አላልሁምን? አለው፡፡ ሁለተኛ መሠዊያውን ከፍ አድርጎ ሠርቶ መሥዋዕቱን ጨምሮ ሠውቶ ርገምልኝ አለው፡፡ አሁንም እያሟረተ ወደ ምሥራቅ ተሂዞሮ "ከተራሮች በላይ አየሁት ከኮረብታዎችም በላይ አስተዋልሁት እግዚአብሔር አምላኩ ከርሱ ጋራ ያለ ሕዝብ ከበታች ይኖራል" አለ፡፡ ባላቅም ርገምልኝ ብልህ ሁለተኛ ትመርቃቸዋለህን? ብሎ አዘነ፡፡ በሦስተኛ ከሌላ ኮረብታ ወስዶ ርገምልኝ አለው፡፡

"ሚ ይሤኒ ተዓይኒከ ያዕቆብ ወእሮ አብያቲከ እስራኤል - ያዕቆብ ከተማህ ምን ያምር? እስራኤል ቤቶችህ ምን ያምር" ብሎ አደነቀ አሞገሰ፡፡ እያይዞም "ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምእስራኤል" ብሎ የጌታን ሥጋዌ ተናገረ፡፡ ርገምልኝ ብልህ ሦስተኛ ትመርቃቸዋለህን? አለው፡፡ እግዚአብሔር የገለፀልኝን ብቻ እንድናገር አስታውቄህ የለምን? አሁንም የምትሻው ጥፋታቸውን ከሆነ ረግሜ ባላጠፋልህ መክሬ አጠፋልሀለሁ ደናግሉን ጣኦት አሳዝለህ መሥዋ ዕተ እርያ አሲዘህ ስደዳቸው፤ እንድረሰባችሁ ይሏቸዋል ለጣዖት ሰገዱ መሥዋዕቱን ብሉ ይበሏቸው፤ ይሰግዳሉ ይበላሉ በዚህ ጊዜ አምላካቸው ተቆጥቶ ያጠፋቸዋል ብሎ መከረው፡፡

እንዳለውም ደናግሉን ጣኦት አሳዝሉ መሥዋዕተ እርያ አሲዞ ሰደዳቸው፡፡ ተቀመባቸው፡፡ ለጣዖት ሰገዱ መሥዋዕታቸውን በሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቸነፈር ይፈጃቸው ጀመር፡፡ የይሁዳ ቤት አለቃ ዘምሪ ከባላቅ ቤት አለቃ ልጅ ከከስቢ ጋር ተጠቃቅሰው ከእልፍኝ ሲገቡ አንድ ብላቴና አይቶ ለፊንሐስ ወልደአሮን ነገረው፡፡ ሁለቱንም ከተኙበት በጦር ወጋቸው ጌታም ፊንሐስ ወልደአሮን አስተንፈሰካ ለልብየ-ብሎታል፡፡ መዓቱንም በምሕረት መልሶላቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለፊንሐስ 300 መዋዕለ ክህነት ተሰጥቶታል፡፡
ዘኁ ምዕ 22 እና 23

• ታሪኩ የተፈጸመው በ1280 ዓ.ም ገደማ ነው፡፡

መከራና ችግር የማይለውጠው
ጠላት ተመቅኝቶ የማያጠፋው
ቢታመም የሚድን ወድቆ ሚነሳው
እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ያለለት ሰው ነው፡፡
ያንን ምእመን በዓለም ምን ያስጨንቀዋል
ጌታ ከከበረው ማን ያዋርደዋል?

ሰው ለምን ይለፋል እያዘነ ገብቶ
ያለ አምላክ ፈቃድ አንዳች ሳይሆን ከቶ፡፡
በጎ በጎ አስበህ በጎ ከሰራህ
ሁልጊዜ ይኖራል እግዚአብሔር አብሮህ
እግዚአብሔርም ካለ ሁሌ በጎንህ
ከፊትህ ለመቆም ያፍራል ጠላትህ፡፡

መዝ 22፡4 ሮሜ 8:3

## መጋቢት 13 አርብዓ ሐራ ሰማዕት

የብስጥያ የጦር ሠራዊት ነበሩ፡፡ የብስጥያው መስፍን ቢሞት ንጉሡ ቁስጠንጢኖስ እልፍያኖስን መስፍን-ብስጥያ አድርጎ ሾመው፡፡ ለጊዜው ከክርስቲያን ጋራ እተባበራለሁ አብያተ ክርስቲያናትን እንጻለሁ ብሎ ተሹሞ ነበረ፡፡ ኋላ ግን የወርቅ የብር ምስል አቁሞ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ አለ፡፡ ብዙዎች ከመሞት መሰንበትን ሽተው ሃይማኖታቸውን ክደው ለጣኦት ሲሰግዱ እኒህ አርባው ሃይማኖታችን አንክድም ለጣኦት አንሰግድም አሉ፡፡ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አስገርፎ ውርጩ በውነት ከሚበጣጥስ ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ጣላቸው፡፡ ሠላሳ ዘጠኝ ቀን ሲመላቸው ከሁሉ አንዱ መከራውን ጸልቶ ሥቃዩን ተሰቆ ወጣ፡፡ በማግስቱ አርባ አክሊላት በሰማይ ረበው ሠላሳ ዘጠኙን ሠላሳ ዘጠኙ ሲቀዳጁ አንዲቷ ተንጠልጥላ ቀረች፡፡ይህን አይቶ አንድ አረማዊ አምና ዘሎ ገብቶ ተቀብሏታል፡፡ ከዚህ በኋላ እልፍያኖስ ጭንጭናቸውን ሰበሯቸው አለ፡፡ ቢሄዱ አርፈው ተገኝተዋል፡፡

• ታሪኩ የተፈጸመው በ4ኛው ም.ዓ ድ.ል.ክ ነው፡፡

ትጠሏ ቢመርም የተከለ ትዕግሥት
ፍሬዋ ጣፋጭ ነው እንደወይን እሸት
ረሀብ ጥም እርዛት ችግር ካለመጠው
ፀንቶ ከተገኘ ሁልጊዜ በዓላማው
የክርስቶስ ወዳጅ በቃ እርሱ እኮ ነው፡፡
መከራን መታገሥ ናፍቆ የማውን
መሰከረው ይሄ ነው የእውነተኛው ምእመን
የምን ተስፋ መቁረጥ ፈጣሪ ማማረር
ከቶ ምን አለና የሚያለፍ በዚህች ምድር

ትናንት የነበረው ዛሬ ካልታየማ
ዛሬም ያለው ነገ ካልተደገመማ
እንዲያው ሁሉም ነገር ከተለወጠማ
እንዳችም አይበጅም ተስፋ መቁረጥማ
መታገሥን ግን መልከም ይሆነናል ማማ
ችሎል ተስፋው ሲበን እንዳመድ ሲከስም
የታገሠ ከብርን ሳያገኝ አይቀርም፡፡

ሉቃ 22፡15 1 ጴጥ 2፡14 3፡14 ፣ 4፡12

## መጋቢት 21 ትንሣኤ አልዓዛር

በዓሉ የጌታ በዓል ነው፡፡ በዚህ ዕለት አልዓዛርን ከሞት እንሥቶታል፡፡ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘይደዊ ዘስሙ አልዓዛር



በቢታንያ ዘሀገረ ማርያ ወማርታ ይላል፡ አልዓዛር ሞተ፤ ቢሞት እኅቶቹ ማርያምና ማርታ ወዳጅህ ሞተ ብለው ላኩበት፡፡ ወያፈቅሮን እግዚእ ኢየሱስ ለማርያ ወለማርታ እኅታ ወለአልዓዛር ይላል ይወዳቸው ነበረ፡፡ ሁለት ቀን ካለበት ውሎ ንርብ ንሁ ንሑር ብሔረ ይሁዳ - ወደ ይሁዳ እንሂድ አላቸው፡፡ አይሁድ በደንጊያ ወግረው በእሳት ተኩሰው ሊገድሉህ ሲፈልጉህ እንሂድ ትላለህን? አሉት፡፡ አልዓዛር ዐርክነ ሞተ ወዳጃችን አልዓዛር ሞተ አላቸው፡፡ ቢታንያ ቀርበው አደሩ፡፡ ቢነጋ ማርታ መምጣቱን ሰምታ ከመንገድ ተገናኝታ ሰበሰ ሀሉከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ ከዚህ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበረ፡፡ አሁንም ጌታ (አብ) የለመንከውን እንዳይነሳህ አውቃለሁ አለችው፡፡ ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ - በኔ ያመነ ቢሞትም ይነሳል አላት፡፡

ማርያ(ም) ከቤት ነበረች፤ ናሁ መጽአ ሊቅነ ብላ ማርታ ነገረቻት፡፡ እየተቻኮለች ተነሥታ ወጣች፡፡ አብረዋት የነበሩትም ከመቃብሩ ሂዳ ልታለቅስ ነው ብለው እያለቀሱ ተከተሏት፡፡ እጅ ነስታ እሷም እንደ እኅቷ ሰበሰ ሀሉከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ አለችው፡፡ ወአንብዐ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ ይላል እንባውን አፈሰሰ፡፡ አይቴ ቀበርክምዎ - የት ቀበራችሁት? አለ፡፡ መለኮትስ ሁሉን ያውቃል እንዲህ ማለቱ ግን ሥጋን መዋሀዱን ለማጠየቅ ነው፡፡ ወሰደው አሳዩት መቃብሩ ዙሪያውን የታነጸ ከላይ በታላቅ ደንጊያ የተገጠመ ነበረ ደንጊያውን አንሡት አላቸው፡፡ ማርታ እግዚኦ ናሁ ወድአ ጼአ - ከሞተ አራት ቀን ነውና ፈጽሞ ተበላሽቶ ይሆናል አለች፡፡ ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ታያለሽ አላት፡፡ ወዲያውም አባቱን አመስግኖ አልዓዛር አልዓዛር ነዓ ጻእ አፍኣ - ና ውጣ አለው፡፡ ወወጽአ ውእቱ ምውት እንዘግኑዝ ወእሱር እደዊሁ ወእገሪሁ ይላል - እጅ እግሩ እንደታሰረ ወጥቷል፡፡ ለጊዜው ምትሐት መስሏቸው ነበርና ፍቱት ይሂድ አላቸው፡፡ ፈትተውት በመካከላቸው እየተመላለሰ አመስግኗል፡፡

ዮሐ 11፡1-45

ኋላም በቆጵሮስ ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ አርባ ዘመን አስተምሮ ግንቦት 26 ቀን በሰላም አርፏል፡፡

• ጌታ ከሞት ያነሳው በ33 ዓ.ም አስተምሮ ያረፈው በ73 ዓ.ም ነው

## ለ. አግብኦተ - ግብር በቤተ ስምዖን

ከበቅለቱ ስምንት ቀን አስቀድሞ ትዳሜ ከቤተ ስምዖን ግብር አገቡለት፡፡ አልዓዛርን ጨምሮ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ግዕድ ቀረበ፡፡ ማርታ ባጭር ታጥቃ ታገለግላቸዋለች፡፡ ወማርያስ ነሥአት ዕፍረተ

ልጥረ ዘናርዱ ጵስጥቂስ ዘዕፁብ ሤጡ ወቀብዐቶ ለእግዚእ ኢየሱስ ይላል ማርያም የከበረ ሽቱ ቀብታዋለች፡፡

ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ይህች ማርያም ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ፀጉሯ ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ነበረች፡፡ ውበቷን በመስታወት አይታ ይህ ሁሉ ማማር ከንቱ መሆኑን ተረድታ ኃጢአቴን እንዲያስተሰርይልኝ ሽቱ ገዝቼ ከመምህሬ ዘንድ ልሂድ ብላ በአሰበ ደነስ የሰበሰበችውን 300 ወቄት ወርቅ ይዛ ልትገዛ ስትሄድ ሰይጣን የምታውቀው ወዳጇን መስሎ ከጎዳና ቆይቶ ወዴት ትሄጃለሽ? አላት ዝም አለችው፡፡ እንግዳ ወንድ መጥቶብሽ ሽቱ ልትገዢለት አይደለምን? አላት፡፡ አዎን አለችው፡፡ ዳግመኛ ፍቅሩ ያላለቀለት ወንድ መጥቶብሽ ሽቱ ልትገዢለት ይሆናል አላት፡፡ አዎን አለች፡፡ ሦስተኛ ብዙውን በጥቂት የሚሸጥ ነጋዴ መጥቶብሽ ነው አላት፡፡ አዎን አለችው፡፡ ሁሉንም አዎን አልሽኝ እውነቱ የቱ ነው? አላት፡፡ እንግዳ ወንድ አልኸኝ ከዚህ ዓለም ልዩ የሆነ፣ ፍቅሩ ያላለቀለት አልኸኝ የሰው ፍቅር አገብሮት ሊሞት የመጣ፣ ብዙውን በጥቂት የሚሰጥ ነጋዴ አልኸኝ በጥቂት ትሩፋት ብዙ በረከት የሚሰጥ ክርስቶስ ኢየሱስ መጥቷል ለርሱ የምቀባው ሽቱ ልገዛ እሄዳለሁ ብላ ስሙን ብትጠራበት እንደጢስ ተኖ እንደትቢያ በኖ ጠፍቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ሐድናክ ከሚባል ነጋዴ ሄዳ ይትረከብኑ በነቢከ ቅብዐ አፈው ዘይደሉ ለነገሥት ለነገሥታት የሚገባ ሽቱ ካለህ ስጠኝ ብላ 300 ውን ወቄት ሰጠችው፡፡ ዳዊት ሰሎሞን ተቀብተውለት የተረፈ ጌታም ግብጽ ሲወርድ ጥጦስ ታቅፎት ሳለ ከልብሱ ላይ ያረፈ ወዙን ሲያጥበው ሽቱ የሆነው ተጨምሮበት የተቀመጠ መንክረ ጼና ሽቱ ነበር፤ ሰጣት፡፡ ይህን ገሥጻት አላስገባምም አላት፡፡ ጌታ መኑ ጉድጉደ አንቀጸ አፀድከ - ማን አለው፡፡ መድኃኒት የሚያስፈልግ ለበሽተኛ እንጂ ለጤነኛ ነውን፡ የሰው ልጅ መምጣቱ ኃጥአንን ወደንስሓ ሊጠራ ነውና ከፍተህ አስገባት አለው፡፡ ገብታ ከወደኋላው እያለቀሰች ሽቱውን ቀባችው፣ እግሩንም በእንባዋ አርሳ በፀጉሯ አበሰች፡፡

ይሁዳ (አስቆርታዊ) ለምንት ኢሤጥዎ ለዝንቱ ዕፍረት በሠለስቱ ምዕት ዲናር የሀብዎ ለነዳያን ለነዳያን ይሰጡት ዘንድ በ300 ወቄት ይሸጥ አልነበረምን? ብሎ ተቆጣ፡፡ የገንዘብ ሹም ነበርና ከአሥር አንድ የሚያገኘው ስለቀረበት እንጂ ለነዳያን አስቦ አልነበረም፡፡ ኋላም በሠላሳ ብር የሸጠው ይህን የቀረበትን ለማግኘት ነው፡፡ ነዳያን ሁልጊዜ ከንተ ጋር ናቸው፤ ይህች ግን እስመ ተሀቅበ ለቀበርየ ለምቀበርበት አስጠብቃዋለችና ተዋት አለው፡፡ እሷንም አማን እብለከሙ በኀበ ሰብከዎ ለዝቱ ወንጌል ይንግሩ ውስተ-ኩሉ ዓለም ዘገብረት ዛቲ ብእሲት ተዝከረ ላቲ ወይዝከርዋ - ወንጌል በተነገረችበት ቦታ ሁሉ ያደረገችውን ሊነግሩላት ይገባል ብሎ ኃጢአቷን አስተስርዮ አሰናብቷታል፡፡ ማቴ 26፥ 6-14



## መጋቢት 22 - ሆሣዕና

ወሶበ በጽሐ ቤተፋጌ ወቢታንያ ኀበደብረዘይት ዘስሙ ኢሊዎን ትዳሜን ከስምዖን ዘለምጽ ቤት ግብር ገብቶለት ዋለ፡፡ ዮሐንስ ወበሳኒታ ይላል በማግስቱ ደብረዘይት ሲደርስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ሑሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ - ከፊታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ ሰው ያልተቀመጠበት የአህያ ውርንጭላ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ ለምን ትፈታላችሁ የሚል ቢኖር በሉ እግዚኡ - ይፈቅዶ - ጌታው ይፈልገዋል በሉ ብሎ ላካቸው፡፡ ሄደው ጌታው ይፈልገዋል ብለው ፈትተው አመጡለት፡፡ ወረሀኑ አልባሲሆሙ ይላል ልብሳቸውን ጎዝጉዘውለት በዚያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ ደቀመዛሙርቱም ሰማይ ተከፍቶ ፀሐይ ከአህያው ፊት ሁና ስትሰግድ ምድሪቱም ብርሀት ጽድልት ስትሆን መላእክትም ከሰማይ ወርደው አህያውን ከበው ሲያመሰግኑት አይተው ልብሳቸውን ከመሬት እያነጸፉ ብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው እያሉ አመሰግነውታል፡፡

ኢየሩሳሌም ሲደርስ ከገጹ ብርሃን የተነሣ ከተማዋ ብርሀት ሆነች፡፡ ሕዝቡ የሆነውን ሊያዩ ወጡ፡፡ ሕፃናት ፀሐይ ስትሰግድለት መላእክት ከበው ሲያመሰግኑት አይተው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የሰሌን ዝንጣፊ ይዘው ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመእግዚአብሔር እያሉ አመሰግነዋል፡፡ ሆሣዕና ማለት በልዕልና ጸንቶ የሚኖር መድኃኒት ማለት ነው፡፡ ከምን አገኙት? ቢሉ ጌታ ወደ ግብጽ ሲወርድ እስሙናይን ሲደርስ ዕፀተመርት አግኝቶ ካለችበት ቦታ ተነሥታ ደብረዘይት እንድትተከል አዘዛት፤ አሚሃ ሰረረት ውስተ አየር ወተተክለት ሀየ ይላል በአየር በራ ደብረዘይት ተተክላለች ከዚያ ቆርጠው አምጥተዋል፡፡

ሕፃናቱ ሦስት አፍል ናቸው፡፡ የነርሱ ምስጋና ከመላእክት ምስጋና ተዋህዶ ኢየሩሳሌም ተናወጸች፡፡ ረበናተ አይሁድ ምን መጣብን ብለው ደንግጠው ቢወጡ ሕፃናቱን ሲያመሰግኑ አገኙ፡፡ እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ምስጋና የዮሴፍን ልጅ እንድታመሰግኑ ግን አስተማራችሁ? አሏቸው፡፡ እናንተ እውሮች ፀሐይ ስትሰግድለት መላእክት ሲያመሰግኑት አታዩምን? ዳዊትስ ስለኛ "እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሉከ ስብሐተ" መዝ 8፥3 ያለውን አላነበባችሁምን? አሏቸው፡፡ ግስተው የማይቻላቸው ቢሆን ሄደው ጌታን አዝዞሙ

ለሕፃናት ከመያርምጡ ዝም እንዲሉ ሕፃናቱን እዘዛቸው አሉት፡፡ እኒህ ሕፃናት ዝም ቢሉ ድንጊያዎች እያመሰገኑኝ መሰላችሁ? አላቸው፡፡ 'ወዲያው ደንጊያዎች ከደብረዘይት እየዘለሉ መጥተው ሆሣዕና' በአርያም ለአምላክነ ሆሣዕና ቡሩክ ለመድኃኒነ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ብለው አመስግነውታል፡፡ ወተደመረ ቃሉ ሕፃናት ወቃለ-አዕባን ምስለ ስብሐተ መላእክት እንዲል ዲድስ፡፡ መቅደሱን ሦስት ጊዜ ዞሮ ወገፍትአ ማዕዳቲሆሙ ለመወልጣን ይላል ሻጮችን ለዋጮችን መሸጫ መለወጫቸውን አፈራርሶ እነርሱንም በጅራፍ እየገረፈ አስወጥቷቸዋል፡፡ ማቴ 21፥ 1013

* ይህ ሁሉ የሆነው "ተፈሥሒ ወለተጽዮን ወተሐውዪ ወለተ ኢየሩሳሌም ነዋ ይመጽእ ንጉሥኪ የዋህ ወትሑት ተጽኢኖ ዲበእዋለ አድግ" ተብሎ በዘካርያስ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡ ዘካ 9፡9

## ከመጋቢት 23-28 - ሰሙነ ሕማማት

የዐቢይ ጾም ስምንተኛ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል፡፡ ጌታ የሰው ፍቅር አገብሮት ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውኛውን ኑሮ በአይሁድ እጅ ተይዞ ተገርፎ ተሰቅሎ መሞቱን የምናዘክርበት ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡ በእኒህ ስድስት ዕለታት ክደስታ ከጨዋታ ተለይቶ ሕማሙን ሞቱን እያሰቡ ሊያዝኑ ቀን ከሌሊት ከቤተ ክርስቲያን ሳይለዩ ሕማሙን ሞቱን የሚናገሩ መጻሕፍትን ሊያነቡ፤ ሊሰሙ መዝሙረ ዳዊት ውዳሴ ማርያም ከሰጊድ ጋራ ሊያደርሱ ይገባል፡፡ የመላእክት የጻድቃን የሰማዕት መልክአ ግን አይነበቡም፡፡ የቻለ ሁለት ሁለት ቀን ያልቻለ እስከ ዕርበተ ፀሐይ ሊጾም ይገባዋል፤ ምግቡ ኀብስት በጨው መጠጡ ጥሩ ውሃ ነው፡፡ በእኒህ ዕለታት ሥጋ የሚቆርጥ ወይን ጠጅ የሚያንቀረቅር ቢኖር ዕድል ፈንታው ጽዋ ተርታው ጌታን በመስቀል በመግደል ደስ ከተሰኙ አይሁድ ጋራ ነው፡፡ ሕሙም ድውይ ቢሆን ግን ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ተከቶ ሊጾም ይችላል፡፡ ይልቁንም ከቤት የደረሰ ሰውነቱን ያረከሰ ዕዳ ፍዳ ይጸናበታል፡፡ አሌ ሎቱ ለዘይገብራ ለዛቲ ኃጢአት በሰሙነ ሕማማት ቅድስት
እንዲል ፍ፡ት-ነገ-አንቀጽ 24፡5

## መጋቢት 23 - ዕረፍቱ ለዳንኤል ነቢይ

ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው፡፡ በምርኮ ፋርስ በፀሎን ይኖር ነበር፡፡ ንጉሡ



ናቡከደነጸር አንድ ቀን በሌቱ ጠጥቶ ከሰገነቱ ሲመላለስ የኩተማውን ሰፋት የሠራዊቱን ብዛት አይቶ እኔ ይህን ዓለም እንደ ሰም አቅልጬ እንደ ገደል ቀጥቅጬ ገዛሁት ከኔ ቀጥሎ የሚነግሠው እንደኔ ብርቱ ይሆን? ብሎ አሰበ፡፡ ሌሊት በሕልሙ ራሱ የወርቅ አንገቱ ደረቱ የብር ወገቡ የነሐስ ጭንና ጭኑ የብረት እግርና እግሩ የብረትና የሸክላ ቅልቅል ምስል ከራቱ ቆሞ ሲያየው ከረጅም ተራራ እጅ ሳይፈንቅለው የወረደ ደንጊያ አድቆት ተመልሶ ተራራ ሲሆል አየ፡፡ ስለደነገጠ ሕልሙ ጠፋው፡፡ ከበላው አብልቶ ከጠጣው አጠጥቶ የሚያኖራቸው መፈከራን ሕልም ነበሩት፤ አስጠርቶ ግሩም ሕልም አይቼ ሕልሙም ትርጓሜውም ጠፋኝ ንገሩኝ አላቸው፡፡ ንጉሥ ፍርድ ልበስ ሺህ ዓመት ንጉሥ የሴፍ ለፈርዖን ቢተረጉምለት ሕልሙን ነግሮት ነው፡፡ አንተም ንገረን እንተርጉምልህ አሉት፡፡ እኔማ ጠፍቶኛል፡፡ ይልቁንስ ጊዜው ሳያልፍ ንገሩኝ ነገሩ ከልቤ ይወጣል ይወርዳል ፈጠራ ፈጥራችሁ ብትነግሩኝ ወዮላችሁ አላቸው፡፡ እንኪያስ አይቻለንም አሉት፡፡ ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ በቅሎ አይደላችሁ አላስጠግችሁ ብሎ ያርክ የሚባል ሰይፍ ጃግሬውን ወስደህ ፍጃቸው አለው፡፡

እንደ በግ እየነዳ ሲወስዳቸው ዳንኤል አገኘው፡፡ ወዴት ትወስዳቸዋለህ? አለው፡፡ንጉሥ ሕልም አይቶ ጠፍቶት ንገሩኝ ቢላቸው አቃታቸው፤ ስለዚህ ፍጃቸው ብሎኝ ልፈጃቸው እወስዳቸዋለሁ አለው፡፡ ቀን ስጠኝና እኔ እነግረዋለሁ ተዋቸው አለው፡፡ ሦስት ቀን ሰጠው፡፡ ከሠለስቱ ደቂቅም ላከባቸው፡፡ ለነርሱ በሦስተኛ ቀን ተገለጸላቸው፡፡ ለርሱ ግን ዕለቱን ተገልፆለታል፡፡ ስለትሕትና ሰንብቶ በሦስተኛው ቀን ገብቶ ሕልሙን ከነትርጓሜው ነግሮታል፡፡ በዚህ ምክንያት በሹማምንቱ ላይ ሾሞታል፡፡

ከዚህ በኋላ ናቡከደነፆር አልፎ ብልጣሶር[፤] ብልጣሶር አልፎ ዳርዮስ ነገሠ፡፡ ዳንኤልን በጣም ይወደው ነበር፡፡ ባቢሎናውያን ቀንተው ነገር ሠሩበት፡፡ ምነው ለአምላኬ አትሰግድም? አለው፡፡ አይበላ አይጠጣ አይሰግ፤ ምን ብዬ እሰግድለታለሁ? አለው ካህናት ማዩቱ ይበላል ይጠጣል እያሉ ምግቡን በያይነቱ እየወሰዱ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ይዘው ይመገቡ ነበረና - እየበላ እየጠጣ? አለው፡፡ እስመ ብላ ቱንበታያለህ ብሎ መርጃ እንዲሆነው የኋሊት አመድ ነስንሶ ምግቡን ጠጁን ብርዙን አስቀምጦ በማኀተመ ንጉሥ አትሞ ሄደ፡፡ ቢመጡ ተዘግቶ አገኙ፡፡ በምስጢር በር ገብተው ተመገቡ፡፡ ንጉሡ ቤል ኃያል አምላክ ዳንኤልን አሳፈርኸውን አለ ... ዳንኤልም ዝ እሙር ዘሙኑ-ይህ የማን ዱካ ነው? እያለ በዘንግ አሳየው፡፡ የካህናት ማያቱን[፤] የምስቶቻቸውንና የልጆቻቸውን አሰር አየ፡፡ ለካስ ሲሚወቱብኝ ኑረዋል ብሎ በሰይፍ አስመትቷቸዋል፡፡

ከዚህ ሌላ መንፈስ ርኩስ ያደረበት ዐቢይ ዘንዶ ያመልኩ ነበር፡፡ ያ አይበላም አይጠጣም አልህ፤ ለዚህ ለሚበላው ለሚጠጣው አትሰግድምን አለው፡፡ ይህንንም ከፈቀድህ ጦር ጋሻ ሳልይዝ እገድለዋለሁ አለው ሂድ አለው፡፡ እንዳሰለመዱት በግ አርዶ ሥጋውን አወራርዶ ሰቡን ጸጉሩን ጨርቅ ገል ጨምሮ አጤሰለት፡፡ እያስካካ መጥቶ አፉን ከፈተ፤ ሰቡን በጋለ እሎሎ ጠቅልሎ ከአፉ ጣለለት፤ ተሰንጥቆ ሞቷል፡፡ ተረ.ዳን ምዕ 1. ሃይ.አበ ዘዮሐ አፈ. ምዕራፍ 67 ባቢሎናውያን ጸልተው ተመቅኝተው ንጉሥ ወዳጅህን ጠላትህን እንድናውቅ ለሦስት ቀን አዋጅ ይነገርልን አሉት፡፡ ነገረላቸው፡፡ በሦስተኛው ቀን በሦስት ሰዓት ዳንኤል መስኮቱን ከፍቶ ሲጸልይ አዋጅ አፍርሶ ሲጸልይ አገኘነው ብለው ለንጉሡ ነገሩት፡፡ የተፈረደበትን ሰው የሚመገቡ አናብስት ነበሩ፡፡ ወስደው ጣሉት፡፡ በማግስቱ ቢሄዱ ሳይበሉት አገኙ፡፡ ባይርባቸው ይሆናል ብለው ምግባቸውን አስቀሩባቸው፡፡ ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል አፋቸውን ስለዘጋ አልተተናከሉትም፡፡

ነቢዩ ዕንባቆም በኢየሩሳሌም ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአኩ ሰድ ሉቱ ዘንተ ምሳሐ ለዳንኤል ዘሀሉ ውስተ ግበ ባቢሎን ለዳንኤል ውሰድለት አለው፡፡ ዳንኤል የት አለ? ባቢሎንንም አላውቃትም አለው፡፡ ወነሥኦ በእሐቲ ሥዕርተ ድማሁ ይላል አንዲት ጠጉሩን ይዞ አደረሰው፤ ሳይከፍት ገብቶ መግቦት ወጥቷል፡፡

ንጉሡ ይወደው ነበርና ፈጣሪው አድኖት ይሆንን ብሎ ቢሄድ አናብስቱ እንደድመት ከእግሩ ወድቀው እሱ ቆሞ ሲጸልይ አገኘ፡፡ ዐቢይ አምላኩ ለዳንኤል-የዳንኤል አምላክ ገናና ነው ብሎ ና ውጣ አለው፡፡ ባቢሎናውያንን ቢያስጥላቸው ከአየር እየተቀበሉ ሰባብረዋቸዋል፡፡ ንጉሥም እምነ አሕዛብ እንዲያምኑ አዋጅ ነግሯል፡፡ ዳን 7፡ 1-28

ከዚህ በኋላ ሚጠተ እስራኤልን ሲሻ ቀናና ገባ፡፡ ከሚጠትም የበለጠ የሥጋዌ ነገር ተገልጸለት "እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ትትሐነጽ መቅደስ" ብሎ ትንቢት ተናግሯል፡፡ በዚህም ዕለት ዕረፍቱ ይነገራል፡፡

• መዋዕለ ትንቢቱ ከ 556-538 ዓ.ዓ ገደማ ነው፡፡
የመ.ቅ. መ.ቃ - ገጽ 208

## መጋቢት 25 - ምክረ አይሁድ

በዚህ ዕለት አይሁድ ጉባዔ አስፍተው ነገር አጽንተው ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ሲያደርግ፤ ሰንበትን ሲሽር፤ ሙሴንና አሪትን ሲያቃልል ለንጉሥ ግብር አትስጡ ሲል ሰምተነዋል ብለን አስመክረን ሰቅለን እንገድለው ብለው ምክር አጽንተዋል፡፡ (ዕለቱ ረቡዕ)



## መጋቢት 26 - ሕጽበተ እግር

እስራኤል ከግብጽ የወጡበትን በዓለ ፍሥሕ፤ ፋሲካ፤ በዓለ መጸለት እያሉ በየዓመቱ እርሾ የሌለው ቂጣ ጋግረው በጉን አርደው በመብላት ያከብሩት ነበር፡፡ ዘጸ 11፡ 32 ዐ 51

ጌታም በዚህ ዕለት ከደቀመዛሙርቱ ጋር አከብሮታል፡፡ ደቀመዛሙርቱ በአይቴ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለከ ፍሥሐ ትብልዕ-ፋሲካውን ትበላ ዘንድ በየት ብናዘጋጅልህ ትወዳለህ? አሉት፡፡ ከፊታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ የውሃ ማድጋ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ከገባበት ተከትላችሁ ይቤልከ ሊቅ አይቴኑ ጽርሕ ኀበ እበልዕ ፍሥሐ ምስለ አርዳእየ በሉት ያሳያችሁል ብሎ ጴጥሮስን ዮሐንስንና ያዕቆብን ላካቸው፡፡

ቢሄዱ የውሃ ማድጋ ተሸክሞ ሲሄድ አገኙት፡፡ ስምየን ዘለምጽ ነው፡፡ ተከትለው መምህር ከደቀምዛሙርቱ ጋር ፋሲካውን የምበላበት አዳራሽ ወዴት ነው? ብሎሃል አሉ፤ ደስ እለው ለምስቱም ነገራት፡፡

በዘጠኝ ሰዓት ጌታ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ሄደ፡፡ ከደርቡ ላይ ግምጃ እንጥፎለት ያን እየረገጠ ገብቷል፡፡ ይሁዳ ወደ ኋላ ቀርቶ ነበር፡፡ ስለምን ቢሉ በደብረዘይት ጌታ እሐዱ እምኔከሙ ያገብአኒ-ከናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል፡፡ እምኀሶ ሶበ ኢተወልደ ለውእቱ ብእሲ ለዚያም ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር ባላቸው ጊዜ ደቀመዛሙርቱ አዝነው መኑ ዘይከህድ እምኔነ ንገረነ ገሀደ-የሚክድ ማነው ገልጠህ ንገረን ቢሉት ከክራድዮስ ደንጊያ አንዱን አኔን አሳልፎ የሚሰጠኝ ማነው? ተናገር ብሎት በይሁዳ ራስ ሦስት ጊዜ ዞሮ ንጹሕ ደም የምታፈስ ይሁዳ ወዮልህ ብሎ መስክሮበት ይህ መሠርይ ብሎ ብሎ ደንጊያ ያናገርብኝ? በማኝ ያገኘኝ ብሎ ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ ከአይሁድ ጋር ይማከር ነበርና ስለዚህ ነው፡፡ መጥቶ ሊገባ ሲል እለእስክንድርስ የተባለው ጠባቂ እርሱ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሲገባ ብሩህ ገፅጠንት ይዞ ገባ፤ አንተ ግን በደም የተመላ ጽዋ ይዘሃል፤ ከእንገትህ እባብ ተጠምጥሞ ሊሰምህ ምላሱን ያወለበልባል፤ የያዝከው ደም ቢነጥብበት ጌታዬ ስለሚያዝንብኝ ቆየኝ ብሎ ምንጻፉን ካነሣ በኋላ አስገብቶታል፡፡

ከዚህ በኋላ ከማዕድ ተነሥቶ ወገቡን በዘናር ታጥቆ የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብ ውሃ በኩስኩስት ይዞ ቀረበ፤ ርዕሰ ሐዋርያት ነውና ከጴጥሮስ ይጀምራል፡፡ እግርህን አምጣ ልጠብህ አለው፡፡ አንተኑ እግዚእ ተሐጽበኒ እግርየ - አቤቱ አንተ እግሬን ታጥበኛለህ? አለው፡፡ የማደርገውን

ኋላ እንጂ አሁን አታውቀውም አለው፡፡ መቼም ቢሆን እግሬን አታጥበኝም አለ፡፡ እመ ኢሐፀብኩከ እገሪከ አልብከ ክፍል ምስሌየ - ካልጠብሁህማ ከኔ ጋር እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለህም አለው፡፡ እንዲህስ ከሆነ እጄንም እግሬንም ጨምረህ እጠበኝ አለው፡፡ ፈጽሞ የታጠበ ከእግሩ ሌላ አያሻውም አለ፡፡ አንትሙሰ ንጹሐን አንትሙ - እናንተ ንጹሐን ናችሁ፤ ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም አለ፡፡

አጥቦ ሲጨርስ ወሶበ ኦነ እንዘ ሊቅክሙ ወእግዚእክሙ ሐፀብኩክሙ እገሪክሙ እኔ መምህራችሁና ጌታችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብኋችሁ አርአያዬን ሰጥቻችኋለሁና እናንተም የወንድማችሁን እግር ታጥቡ ዘንድ ይገባል፡፡ ነገር ግን ከናንተ አንዱ ለሞት አሳልፎ ይሰጠኛል አለ፡፡ ማን ይሆን? እኔ እሆንን? አሉ ኅብስት ቆርሼ ከወጡ ጠቅሼ የምሰጠው እሱ ነው አላቸው፡፡ ወዲያውም ኅብስቱን ባርኮ ከአሥራ ሦስት ፈትቶ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ - ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚሠዋ ሥጋዬ ይህ ነው እንካችሁ ብሉ፤ ብሉ ተቀብሉ አቀበላቸው፡፡ ጽዋውንም አክብሮ ለውጦ ዝ ውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ዘይትከዐው በእንተ ብዙኃን ለኀድገተ-ኃጢአት - ስለብዙኃን የሚፈስ የሐዲስ ሥርዓት ደሜ ይህ ነው፡፡ ጠጡ ብሉ ሰጣቸው፡፡ ሥጋውን ደሙን በመብል በመጠጥ ማድረጉ መብል መጠጥ ያፋቅራልና ሰውና እግዚአብሔርን የሚያፋቅር የሚያዋህድ መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡ ከዚያውም ዘንድ በስንዴ በወይን ያደረገው ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡

ትንቢት - እምፍሬ ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኃ መዝ 4፡7
ቀዳሚ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወማይ ወይን ወሥርናይ ሲራ 29:28
ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንት ውእቱ ሕይወቱ ሲራ 34 ፡ 26 ተብሎ ተነግሯል፡፡

ምሳሌ፡- እምሳሌሁ ለወልደ እግዚአብሔር የተባለ መልከ ጼዴቅ በስንዴ በወይን ያስታኩት ነበረ፡፡ ዘፍ ዕ፲

የጌታም መቀበሉ እንደ ባለመኃኒት ለማስደፈር አንድም አርአያ ለመሆን ነው፡፡ እርሱ ሳይቀበል ደቀመዛሙርቱን ብቻ አቀብሏቸው ቢሆን ኖሮ ዛሬም ካህናት ምዕመናንን አቀብለው እነርሱ ሳይቀበሉ ይሄዱ ነበርና ተቀብላችሁ አቀብሏቸው ሲል ጥዒሞ አጣዕሞሙ ይላል ተቀብሎ አቀብሏቸዋል፡፡

ምን ደግና ርኀሩኅ ሊጋስም ቢሆን
ብሉ ብሉ ሚሰጥ ማነው ሥጋውን?
ካንተ በቀር ጌታ የዓለም መድኀን
ደምህን አፍስሰህ ጠጡ ማለትህ
አልነበረም እንዴ ፍቅር አንብሮህ?
ታዲያ እኛን ዛሬ ምንድር ይሆን ያልከን
በአንደበታችን ልጆችህ ነን እያልን

ነገር ግን ከፊትህ በልባችን ርቀን
ክቡር ስጦታህን መቀበል ሲያቅተን
ከላተኞች ናችሁ አላልከንም ይሆን?
አሁንም እባክህ ቸር እምላካችን
ዛሬ ነገ ስንል ሞት እንዳይወስደን
እብታን ለመቀበል ሥጋ ደምህን
አይቻልምና ያለርሱ መዳን

የሐ.6፡5



## መጋቢት 27 - ስቅለት

ሥጋውን በኅብስት ደሙን በወይን አስታኩቶ ተቀብሎ ሲያቀብላቸው አክርስና (የስምየን ዘለምጽ ሚስት) ዶሮ አሰናድታ አቀረበችለት፡፡ የተናገረው ሊፈጸም ግድ ነውና ኅብስቱን ቆርሶ ከወጡ ጠቅሶ ለይሁዳ ሰጠው፡፡ ሰይጣን ከኅብስቱ ጋር ተዋህደው ልቡ በቅናት ነደደ፡፡ ሥጋው ደሙ ሰይጣን ያርቃል እንጂ አያቢዝም ነበር፡፡ ዳሩ ግን ዕዳ ፍዳ የሚቀበልበት ነውና ሳይበቁ የሚቀበሉ ዕዳ እንደሚሆንባቸው ለማጠየቅ ነው፡፡

/2/ ወደእዜኒ ዘበልዖ ለዝንቱ ኅብስት ወዘሰትዮ ለዝንቱ ጽዋዕ እንዘ ኢይደልዎ ደይና ወመቅሠፍተ በልዐ ለርእሱ 1 ቆር 11:27

ሂድ ያሰብከውን ፈጽም አለው፡፡ ወጥቶ ሄደ፡፡ይሁዳ እንደወጣ ጌታ ዶሮውን በቃሉ ተናግር በእጁ ዳሶ ሕያው ከአደረገው በኋላ ይሁዳን ተከትለህ የሚያደርገውን እይተህ የሚናገረውን ሰምተህ ለደቀመዛሙርቴ ንገራቸው አለው፡፡ እየበረረ ወጥቶ ተከተለው፡፡ ከቤቱ ገብቶ ከሚስቱ ተኝቶ በዋጋ አሳልፎ ሊሰጠው መከረ፡፡ ሄዶም አይሁድን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ? አላቸው፡፡ ስሞ ሊያሳያቸው ተስማምተው ሠላሳ ብር ሰጡት፡፡ የተነገረበት ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ምን ተብሎ ተነግሯል ቢሉ ነቢዩ ዕንባቆም ለማስተማር ሲሄድ የይሁዳ አባት ከባልንጀሮቹ ጋር ከደንጊያ ላይ ተቀምጦ ባልንጀሮቹ ሲነሱለት እርሱ ተቀምጦ አሳለፈው፡፡ ሲያስተምር ውሎ ሲመለስ ከዚያው ተቀምጦ አገኘው፡፡ እንዳይነሳ ኮርቶ እንዳይቀመጥ ፈርቶ ተሸፋፍና አሳለፈው፡፡ "ዕብን ዲበ ዕብን ነበሮ ደንጊያ በደንጊያ ላይ ተቀምጧል፤ ከዚህም ሰው የሚወለደው ዘእቡሁ እልገቱ ዘእሙ ብእሲቱ ወዘእግዚኡ ሤጡ - አባቱን የሚሰልብ እናቱን የሚያገባ መምህሩን የሚሸጥ ይሆናል ብሎ ትንቢት ተናግሮበታል፡፡ ከቤቱ ገብቶ ለሚስቱ በግድ ካልተነሳህልኝ ብሎ እንዲህ አለኝ ብሎ ነገራት እሷም ደግ ያደረግህ መሰለህ? ታላቅ ሰው ሲመጣ ተቀምጦ ማየት ይገባልን? ብላ ገሠጸችው፡፡ ከዚህ በኋላ መገናኘቱን እንተው ብለው መክረው ሲኖሩ አንድ ቀን ፈቃደ ሥጋ አቸንፎት ተገናኛት፡፡ ይሁዳ ተጸነሰ፡፡ በተወለደ ጊዜ በሳጥን አድርገው ከባሕር ጣሉት፡፡ ስምዖን አስቆሮታዊ አግኝቶ አሳደገው፡፡

ካደገ በኋላ ያለበት ሀገር ሰዎች በአባት እናቱ ሀገር ላይ ሲዘምቱ እርሱም አብሮ፣ዘምቶ ነበርና አባቱን ከሰልፍ አግኝቶ ገድሎ ሰለበው፤ እናቱንም ከሰፈር ማረካት በግብርም አወቃት፡፡ አባቱን ይገድላል እናቱን ያገባል ያለው ተፈጸመ፡፡ አንድ ቀን ሲጫዋወቱ የዚህ ሀገር ሰዎች ዘመድ ዘመድ አይሉህምሳ? አለችው፡፡ ከባሕር ተገኘህ ይሉኛል አላት፡፡ አንተ ጉደኛው ነህን? ያ ገድለህ የሰለብከው አባትህ ነው እኔም እናትህ ነኝ አለችው፡፡

ከዚህ በኋላ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልናል ብለው ከጌታ ዘንድ ሄዱ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ እርሱን ከ12ቱ ሐዋርያት እርሷን ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቆጠራቸው፡፡ ዳሩ ግን ትንቢት እንደተነገረበት በፍቅረ ንዋይ ተስቦ በ30 ብር ሸጠው፤ ዘእግዚአ-ኄጡ ያለው ተፈጸመ፡፡

ያም ዶሮ ተመልሶ መጥቶ ያለቅስ ጀመር፡፡ ያየኸውን የሰማኸውን ንገረን አለው፡፡ አሳልፎ ሊሰጥህ ከአይሁድ ሠላሳ ብር ተቀብሏል፤ እነሱም ሾተል ጎመድ ይዘው እየመጡ ነው ብሎ ያየውን የሰማውን ሁሉ ነገራቸው፡፡ በክንፍህ በረህ ሰማየ ሰማያት ገብተህ እልፍ ዘመን ኑር አለው፤ በሮ በሮ ገብቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸው፡፡ በዚህች ሌሊት ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ "እቀትሎ ለኖላዊ ወይዘረው አባግዒሁ (ዘካ 13፥7) ተብሎ ተነግሯልና፤ ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው፡፡ ጴጥሮስ ሁሉም ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለ፡፡ አማን እብለከ ከመ በዛቲ ሌሊት ሥልሰ ትክህደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ-ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብሎታል፡፡

ወደጌቴሴማኒ(ን) ገብቶ ጴጥሮስን፤ ያዕቆብንና ዮሐንስን ጥቂት እልፍ አድርጎ ሰምንቱን ራቅ አድርጎ ይጸልይ ጀመር፡፡ ሲጸልይም አ አቡየ እመሰ ይትከሀል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ - ቢቻልስ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ነገር ግን ፈቃደ ዚአከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ አይሁን አለ፡፡ ደካማ ሥጋን እንደተዋሀደ ለማጠየቅ ነው፡፡ ወደደቀመዛሙርቱ ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው፡፡ አንድ ሰዓት እንኳ መትጋት ተሳናችሁን? ትጉሁ ወጸልዩ ከመኢትባእ ውስተ መንሱት - ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ አላቸው፡፡ ሁለተኛም ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው፡፡



በሦስተኛው ኑሙ እንከ ወአእርፉ እንግዲህስ ዕረፉ አላቸው፡፡ ተንሥኡ ንሑር ናሁ በጽሐ ዘያገብአኒ የሚያሲዘኝ ይሁዳ መጥቷል ተነሡ እንሂድ አላቸው፡፡ ይህንንም ሲናገር ይሁዳ ሾተልና ጎመድ ከያዙ አራት ቤት ጭፍራ ጋር ደረሰ፡፡ መኑ ተኀሥሡ ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው፡፡ ኢየሱስሃ ናዝራዌ አሉት አነ ውእቱ እኔ ነኝ አላቸው ገብኡ ድኅሬሆሙ ወወድቁ ዲበ ምድር ይላል - የኋሊት ወደቁ፡፡ ሁለተኛም እንዲሁ ሆነ በሦስተኛ የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እኒህን ተውአቸው አላቸው፡፡ ይሁዳ ቀርቦ በሀከ ረቢ .. መምህር ሆይ በላም ላንተ ይሁን ብሎ ሳመው፡፡ አ ይሁዳ በስዒምኑ ታገብእ ለወልደ እጓለ እመሕያው የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን? አለው፡፡ ሊይዙት ተረባረቡ ወበ መጥባሕት ለስምዖን ጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ የማልኮስን ቀኝ ጆሮ ቆረጠው ዋይ አለ፤ ጌታ አግብእ ለመጥባህትከ ውስተ ቤታ አለው፡፡ ያንንም በእጁ ዳሶ ፈውሶታል፡፡

ከዚህ በኋላ አስረው እየደፉ እያዳፉ ወደ ሐና ወሰዱት፡፡ ጳውሎስ የተባለው ሳውል በዚህ ጊዜ ጌታን ከሚያሰቃዩት አንዱ ነበር፡፡ ልቡን በጫማ ረገጠው፡፡ እንደበግ ከእጅህ ገብቼ ሳለ ለምን ይህን ያህል ክፉ ታደርግብኛለህ? ኋላ ግን ከክፋትህ ትፀፀታለህ፤ የበተንከው መንጋዬንም ትሰበስባለህ አለው፡፡

ሐና ምን እያልህ ታስተምራለህ? አለው፡፡ በውኑ በስውር የተናገርሁት አለን? የሰሙኝን ጠይቅ አለው፡፡ አንዱ ጭፍራ "ከመዝኑ ትትዋሥእ ለሊቀካህናት" ብሎ ፊቱን ፀፋው፡፡ ክፉ ከተናገርሁ መስክርብኝ በጎ ስለተናገርሁ ግን ስለምን ትመታኛለህ? አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ቀያፋ ወሰዱት፡፡

ጴጥሮስ ከሩቅ እየተከተለ መጥቶ ከሊቀካህናቱ ግቢ ተቀምጦ ነበር፡፡ ዳጃፍ ጠባቂዋ በለሲዳ "አ አረጋዊ ብእሲ አንተሁ እምገሊላዊ ብእሲ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አይደለህምን? አለችው፡፡ ደንግጦ ኢየአምር ለውእቱ ብእሲ - አላውቀውም አለ፡፡ ሁለተኛ የማልኮስ ወንድም ኮልሰብ - "ከርሱ ጋር በአትክልቱ ቦታ አላየሁህምን?"፤ አለው አላየኸኝም ብሎ ካደ፡፡ ሦስተኛ አንዲቷ መጥታ "አንተኑ ረድኡ ለገሊላዊ ኢየሱስ ቃልከ የዐውቀከ - የኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆንህ ንግግርህ ያስታውቃል" አለችው፤ አላውቀውም እያለ

ይምል ይገዛት ጀመር፡፡ ወዲያው ዶሮ ሲጮኽ "ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለውን አስታውሶ አምርሮ አለቀሰ፡፡

ጌታም ሌሊቱን ሲደበድቡት አድረው መከራ ሲያጸኑበት ሌሊት ተሠወራቸው፡፡ ከሕዋረ ሰሎሞን ሲደርስ የይሁዳን ዘመድ ልጇን ታቅፋ አግኝቷት "አይሁድ እኔን ሊፈልጉ መጥተው ቢጠይቁሽ ከርሱ ምን አላችሁ? በያቸው" ብሏት ከዓምዱ ስር አረፍ አለ፡፡ አይሁድ ተከታትለው መጥተው "አላየሽውምን? አሏት፡፡ በእጇ አመለከተቻቸው፡፡ ይዘው እያዳፉ አመጡት፡፡ "አንቺ ሴት አትንገሪ ብልሽ ጥቂት ራሴን እስካሳርፍ መታገሥ አቃተሽን? በዳግም ምጽአቴ እሥነስቼ እስክፈርድብሽ ደንጊያ ሁኚ" አላት፤ ደንጊያ ሆና ቀርታለች፡፡

በነግህ አስፈርደው ሊሰቅሉት ወደ ጲላጦስ ወሰዱት፡፡ ይሁዳ እሱ በተአምራት ይድናል እኔም ብሬን እንደያዝኩ እቀራለሁ ብሎ ሽጦት ነበርና ይህን ሲያይ አሪት "ኢትቅትል ብእሴ ጻድቀ" ያለችውን ተላልፈ ንጹህ ያም አሳልፈ በመስጠቴ መልካም አላደረግሁም፤ ብራችሁን እንኩና ፍቱት አላቸው፡፡ እኛማ የፈለግኸውን ሰጥተንሃል የፈለግነውን አግኝተናል አሉት፡፡ ከእግራቸው በትናት ሄዶ ከዛፍ ተሰቀለ፡፡ ወደኋላ ሸሸችው፡፡ ከሌላ ዛፍ ሄደ፡፡ ገመድ አስሮ ሊታነቅ ሲንጠላጠል በቃል ሰብአዊ" ማረኝ ብትለው ይምርህ የለምን? ንስሕ ከመእንትከ ጴጥሮስ - እንደ ጴጥሮስ ንስሓ ግባ" አለችው፡፡ እርሷን ትቶ ከሌላ ዛፍ ሄዶ ተሰቀለ፤ ገመዱ ተበጥሶ ከመሬት ወደቀ፡፡ ሰውነቱ ቆስሎ በአርባ ቀኑ ሞቷል፡፡

አይሁድም ጌታን ይዘው ከጲላጦስ ሲገቡ ከሀውደ ምኩናን ስድስት አርማህ (ጦረኞች) ቆመው ነበር፡፡ መለስ ብሎ ሲያያቸው እንደግንድ ተረብርበው ሰገደሉት፡፡ ከኢየሱስ ወዳጆች ተመሳጥረው ነው፡፡ በእሥር በእሥር ኃያላን ይያዙ አሉ ተያዙ፡፡ ሲያያቸው አሁንም እነርሱን አቸንፈው ሰገዱለት፡፡ በአስራ አምስት በአስራ አምስት አሲያዟቸው፡፡ ዘጠናው ስድስቱን ግቆም ተስኗቸው ተንተው ወድቀዋል፡፡

ጲላጦስ ፍርሀት ፍርሀት አለው፡፡ "በውኑ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?" አለው፡፡ "አንተ ትቤ - አንተ አልህ" አለ፡፡ አይሁድ "ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ያደረገ፣ ሙሴንና ኦሪትን ያቀለለ፣ ሰንበትን የሻረ፣ ለቄሣር አትገብሩ ያለ ሀላዊ እንጂ ንጉሥ አይደለም" አሉ፡፡



"ይህን ያህል ሲከሱህ አትሰማምን? "አለው፤ ዝም አለ፡፡ "ብየ ሥልጣን እቅትልከ ወአሕዩከኒ ልገድልህ ወይም ላድንህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው፡፡ "እምአይቴ ለከ ሥልጣን ትቅትለኒ ወታሕይወኒ እምኢተውህበ ለከ እምሰማይ ከሰማይ ካልተሰጠህ በቀር ልትገድለኝ ወይም ልታድነኝ ሥልጣን ከወዴት አለህ?"አለው አይሁድን እኔስ አንድ ሰንኳ በደል አላገኘሁበትም፡፡ ገርፌ ልፍታው አላቸው፡፡ ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ መላ አይሁድን ሲያውክ የነበረ አይሰቀልም ትላለህን? አሉት፡፡ ገሊላዊ ከሆነማ ገሊላ ግዛቱ የሄሮድስ ነውና ወደርሱ ውሰዱት አለ፡፡

ሄሮድስም ዜናውን እየሰማ ሊያየው ይመኝ ነበርና ደስ አለው፡፡ ዳሩ ግን ቢያናግረው የማይናገር ሆነ፡፡ አስተአክዮ ይላል አስክፍቶ "አይቻልም እንጂ ቢቻልስ ሁለት ሞት ይገባዋል" ብሎ ወደ ጲላጦስ መለሰው፡፡ ከዚያ በፊት ጲላጦስና ሄሮድስ ተጣልተው ይኖሩ ነበር፣ አሁን ግን በጌታ ምክንያት ተነጋግረዋል፡፡

ጲላጦስ ጌታን አዝና ሲያየው ሄሮድስ ብዙ እንዳስገረፈው አውቆ አዘነ፡፡ "ይህን ሰው ወደኔ ሦስት ጊዜ አመጣችሁት፤ እኔ ግን መርምሬ ሰንኳ ለሞት ለግርፋት የሚያበቃ ጥፋት አላገኘሁበትም፣ አሁን ግን ለበዓል አንድ እስረኛ ልፈታላችሁ ልማድ ነውና ገርፌ እፈታዋለሁ አላቸው፡፡ "አኮ ዘንተ አላ በርባንሃ - በርባንን እንጂ ይህን አይደለም" አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሚስቱ ከአብሮቅላ "ድዳ የነበሩ ልጆችህን መካራና ዳርታን እንደበታቸውን ከፍቶላቸዋልና ከፉ እንኳ እንደተናገረው እወቅ "የሚል መልእክት ደረሰው፡፡ አይሁድ በሥራዩ ነው ሲሉ ጌታ ከርታሱን ተቀብሎ የተጻፈውን ደምስሶ "ዋጋሽን በመንግሥተ ሰማያት እከፍልሻለሁ ልጆችሽንም ከስግዕት አቆጥርልሻለሁ" ብሎ መልሶታል፡፡

ይህን አይቶ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፡. እነርሱ ግን እመአሕየውኮ ለዝንቱ ኢኮንከ ዐርኮ ለቄሣር - ይህን ከፈታህ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ስቅሎ ስቅሎ - ብለው ይፍጃጁ ጀመር፡፡ ውኃ በኩስኩስት አስመጥቶ ንጹህ አነ እምደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ - ብሎ እጁን ታጠበ፡፡ አይሁድ ግን ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን አሉ፡፡ ይህም ሊታወቅ ዛሬ አይሁድ ሲወለዱ ደም ጨብጠው እንደሚወለዱ ይነገራል፡፡

ከዚህ በኋላ ከጲላጦስ ተቀብለው ከግንድ አስረው አራት ከአርባ አትርፈህ አትግረፍ ትላለችና ሠላሳ ዘጠኝ ገርፈው ዘነጋሁኝ እያሉ እየተቀባበሉ አራቱ ጭፍሮች 6666 ጊዜ ገርፈውታል፣ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር።

የሾህ አክሊል ጎንጉነው ከራሱ ደፍተው በመቃ ቢመቱት ራሱ ሰባ ሶስት ጊዜ ተበሳስቷል። መስቀሉንም ሦስቱን እንጨቶች ዕፀ አውልዕ፣ ዕፀ ወይን፣ ዕፀ ዘይትን እና አራቱ ዕፀው በለስን አንድ ወገን አድርገው ቁመቱ ሰባት ክንድ ከስንዝር፣ ወርዱ ሦስት ክንድ ከስንዝር አድርገው ሠሩ። ዕፀ በለሱ ሰሎሞን ንስር አልገዛለት ብሎት ግልገሉን ከግንብ ውሥጥ ዘግቶበት ሳለ ንስር ከገነት እምጥቶ ግንቡ ላይ ጥሎት ግንቡን ሰብሮ ግልገሉን ከወሰደ ፀኋላ በአትክልት መካከል ተተክሎ ቆይቶ ቤተመቅደስ ሲሰራ እንደባርያ የሚገዙለት 700 አጋንንት ሊቆርጡት ሲሉ እንደእሳት ፈጅቷቸው እርሱም ለመቃንም፣ ለመድረክም አልሆን ብሎት ሳይቆርጠው ትቶት ከደጃፍ ወድቆ የነበረና የሀገራችን ንግሥት ማክዳ ጥበቡን ልታይ ወደርሱ በሄደች ጊዜ ዘንዶ ስታስገድል ደሙ ቢነጥብባት እንደ ፍየል ሰኮና ሆኖ የነበረውን ቀርፎ የጣለላት በዚህም ምክንያት ሰሎሞንና እርሷ በአንድ በአንድ ብር ለብጠው ከቤተ መዛግብት ያስቀመጡት ከርሱም በኋላ የተነሡ 28 ነገሥታት ተአምር እያደረገላቸው በአንድ በአንድ ብር እየለበጡት የቆየ ነው:: ሠላሳውን ብር ለይሁዳ ሰጥተው ግንዱን ለመስቀል አድርገውታል።

በስድስት ሰዓት ቀይ ግምጃ አልብሰው ግራ ቀኝ ፊት ኋላ ሆነው እየገፉ እያዳፉ ወስደው በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ሰቀሉት። በቀራንዮ መስቀሉም ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው። ትንቢት "ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር" ተብሎ ተነግሯል። መዝ 73፡12

ምሳሌም፡- እስራኤል መና ከደመና እያወረደ ውኃ ከጭንጫ እያፈለቀ ይህንን እየመገበ ደጋ ደጋውን ሲወስዳቸው "ሐመይዎ ለእግዚአብሔር ወይ ቤሉ ይክልኑ እግዚአብሔር ሠሪዐ-ማዕድ በገዳም ይዝብጥ ኰኵሐ ወያው ኀዝ ማየ" መዝ 77፡19 እንዲል-ቆላተ ዮሳፍጥ ከሚባል በረሀ አውርዶ መናውንም ውኃውንም ከወትሮው አብልጦ ሰጣቸው። ፉሩ ግን እባብ ጎናቸውን እየቀደደ ይፈጃቸው ጀመር። ሙሴ ወደጌታ ሲያመለክት እርዌ ብርት ሥርተህ ተራዳ



ላይ ሰቅለህ አይተው ይዳኑ አለው። እንዳለው ሆኗል። ተራራው የቀራንዮ ተራዳው የመስቀል ብርት የጌታ እባብ የዲያብሎስ ቁስሉ የኃጢአት በረሀ የሲኦል፣ አይተው አምነው የዳኑ የሐዋርያት የምእመናን፣ አይተው ያልዳኑ የአይሁድ የመናፍቃን ምሳሌ።

ሲሰቅሉትም መኀናፀፊያውን፣ኩፋሩን፣ ጠፈሩንና መነሳነሱን ለአራት ተካፍለውታል። ቀሚሱን ግን ሰብአ ሰገል የገበሩለት ስፌት የሌለው ሥረጽ ሲያድግ የሚያድግ ገባሬ ተአምር ነውና ኢንስጥጥ ወኢንግምድ አላ ንትፋሰስ ላዕሌሁ ለዘረከቦ ይርከቦ ብለው ዕጣ ተጣጥለውበታል።

ሰቀሉ ምስሌሁ ክልዔተ ፈያተ አሐደ እምለፌ ወአሐደ እምለፌ ይላል ጥጦስን በቀኙ ዳክርስን በግራው ሰቀሉ። "ተኈለቈ ምስለ ጊጉያን" /ኢሳ 53፡12/ ተብሎ ትንቢት ተነግሯልና። ጲላጦስም ከራሱ በላይ በቀረው ስንዝር ያህል "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" ብሎ በዕብራይስጥ በጽርዕ በሮማይስጥ ጻፈበት።

በተሰቀለም ጊዜ ሦስት በሰማይ (ጠፍር) አራት በምድር ሰባት ተአምራት ታይተዋል። በላይ የፈጣሪያችንን ዕርቃን አናሳይም ብለው ፀሐይ ጨልሟል፣ ጨረቃ ደም ሆኗል፣ ከዋክብትም ረግፈዋል። በምድርም አዕባን ተፈትተዋል፣ መቃብራት ተከፍተዋል፣ ከ500-1000 የሚሆኑ ሙታን ተነሥተዋል፣ የቤተመቅደስ መጋረጃ ከሁለት ተከፍሏል። መከራው እጅግ ጽኑ ነው፣ ሕማማቱንም ሊቃውንት በቁጥር 13 ብለው አስቀምጠዋቸዋል።

እነርሱም 1. ተአስሮ ድኅሬት
2. ተስሕቦ በሀብል
3. ወዲቅ ውስተምድር
4. ተከይዶ በእግረ አይሁድ
5. ተገፍዖ ማዕከለ ዓምድ
6. ተጸፍዖ መልታህት
7 ተወክፎ ምራቀ ርኩሳን
8. ተኮርዖተ ርክስ
9. አክሊለ ሦክ
10. ፀዊረ መስቀል
11. ተቀንዎ በቅንዋት
12. ተሰቅሎ በዕፅ እና
13. ሰረበ ሐሞት ናቸው።

እነዚህን ትኩሳቱን አብርዱልኝ ከመከራው አስታግሱኝ ሳይል በትሕትና በትዕግሥት ተቀብሏል። "ኦ ትዕግሥት ዘኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ በቅድሙ እለይረግዝዎ" እንዲል ቅዳ. ግር ቁጥ 126 ይህማ አንዲት ቃል ስንኳ አልተናገረም ማለት አይደለምን? ቢሉ

የትዕቢት የፍርሃት ቃል አልተናገረም እንጂ አሠሩን ለሚከተሉ አብነት ሊሆን ሰባቱን አጽራሐ መስቀል ተናገሯል።

እነርሱም

1. አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወለምንት ኀደገኒ
2. አባ ሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ እስመበዘኢየአምሩ ይገብሩ ሉቃ23-33 በመላእክት ያመጣዋል። አካሉ ደም ለብሶ እርቃኑን ተሰቅሎ አይተውት ደንግጠው እንዲሸሸ ተነጹ። ቅዱስ ሚካኤል ዝም አለ! ቅዱስ ገብርኤል ግን ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው ሰይፉን መዘዘ። ባያውቁ ነው ሰ ይፍህን መልስ አለው። "ሚካኤል አርመመ ወገብርኤል ተደመ" እንዳለ ቅዱስ ያሬድ ቸርነቱን እያደነቀ ቢለቀው የቤተመቅደስን መጋረጃ ከሁለት ከፍሎ ምድርን ሰንጥቆ ገባ እስከ ምጽአት ሲወርድ ይኖራል። ሰቤ ከልዐቶ ምሕረቱ ለአብ ወጊሩቱ ለወልድ ወትዕግሥቱ ለመንፈስ ቅዱስ ዘበጠ ለመንጠላዕተ ምኩራብ ወረሰዮ ክልዔ ክፍለ "እንዲል ሃይ አበ ዘአትና ክፍል 9
3. ነዋ ወልድኪ ወነያ እምክ ዮሐ 19፡26 ጌታ በተሰቀለ ጊዜ እመቤታችን ዮሐንስ ነግሯት እየወደቀች እየተነሳች መጥታ ከእግረመስቀሉ ሆና ስታለቅስ ገናግ ሐሞት ሲያጠጡኝ በጦር ሲወጉኝ ብታይ በኃዘን ትሞት የለምን? ብሎ እናቱ ሆይ ልጅሽ እነሆ አላት! ዮሐንስንም እነኋት እናትህ ልጅ ሁናት ብሎ አደራ አቀባበለ። ይህም ለጊዜው ለዮሐንስ ቢሆን ፍጻሜው ለሁላችን ነው።
4. ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ማቴ 27፡46 አይሁድ ኤልማስ ቢል ኤልያስ ያለ መሰሏቸው ኤልያስ መጥቶ ሳያድነው ይሙት ብለው ሀሞት ነኁ አጠጥተውታል። ዲያብሎስም አምላኬ ካለማ ዕሩቅ ብእሲ ነው ብሎ ነፍሱን ከሥጋው ሊለይ በድፍረት ቀረበ። ጌታ በአውታረ ነፋስ ወጥሮ መኑ አንተ መኑ ዝንቱ እያለ አስቀባጥሮታል።
5. ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተገነት ሉቃ 23፡43 በቀኙ የተሰቀለው ጥጦስ ሰባቱን ተአምራት አይቶ አምላክነቱን ተረድቶ ተዘከረኒ እግዚእ በውስተ መንግሥትከ ተዘከረኒ እመጻግም ምጽአትከ እያለ ሲማፀነው ዳክርስ ለራሱ ጻዕረ ሞት ይዞት ያስጨንቀዋል አድነን ትለዋለህን? አለው። እርሱም እኛ ብንሰቀል በኃጢአታችን ነው እርሱ ግን ለቤዛ ዓለም ብሎ ቢሰቀል አምላክን አትፈራውምን ብሎ ገሠጸው። ጌታም ራሱን ወደ ጥጦስ ዘንበል አድርጎ ወደ ግብጽ ስንወርድ የነገርኩህ ሁሉ ተፈጽሟል ! ከሞት በቀር የቀረ የለምና ሂድ ገነት ግባ ብሎ በደሙ አትሞ ላከው።ወእግዕዝ ለሱራፌ ዘየዐቅብ ፍኖተ ሕይወት ወአእተተ እምእዴሁ ኩናተ እሳት ይላል ጠባቂዋ ሱራፌ ፈርቶ እየሸሸ አንተ ማነህ? ወዴት ትሄዳለህ?



አለው። አምላክ ሰው ሆኖ ተሰቅሎ በሞቱ ዓለምን አዳነ ለእኔም ደመማኅተሙን ሠጥቶ ላከኝ አለው። አዳም ነህን አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ነህን? አለው። አይደለሁም እጄን በሰው ደም ነክሬ የኖርሁ ሽፍታ ነኝ። ሰባቱን ተአምራት አይቼ አምላክነቱን ተረድቼ ብማፀነው ለዚህ ክብር አበቃኝ ብሎ 5493 ዘመን ተዘግታ የነበረች ገነትን በደመ ማኅተሙ ከፍቶ ገብቷል።



6. አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተእዴከ ሉቃ 23፡46
7. ተፈጸመ ኩሉ ዮሐ 19፡30 በነቢያት የተነገረው በመጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ደረሰ ተፈጸመ ሲል ነው፡፡ እኒህን ተናግሮ ራሱን ወደቀኝ ዘንበል አድርጎ ቅድስት ነፍሱን በሥልጣኑ ከክብርት ሥጋው ለየ፡፡

በሲኦል የነበሩ ነፍሳት በአካለ ነፍስ ወርዶ የተወጋ ጎኑን ቀኝ ክንዱን አሳይቷቸው ይኸው ጥምቀት ቁርባን ሆናቸው ዲያብሎስ በዕ ብኑ ሩካም ጽፎ ያኖረውን የዕዳ ደብዳቤ አጥፍቶላቸው ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአውረሰነ መንግሰቶ ሰማያዊተ እያሉ እያመሰገኑ ወጥተው ገነት ገብተዋል፡፡ “”ወኀደገ ሥጋሁ ሰቁለ ዲበዕፀ መስቀል ወነፍሱሰ ወረደት ውስተሲኦል ወፈወሰት ነፍሳተ እለሀለው ሀየ ወጌወወት ሲኦለ ወአግዐዘት ኩሉ ፍጥረታተ “እንዳለ አትናቴዎስ በሃይ.አበ.

ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ ለንጊኖስ የሚባል ሐራዊ ቀኝ ጎኑን በጦር ወጋው፡፡ ውኃና ትኩስ ደም መንታ ሆኖ ፈሰሰ፡፡ ደሙን መላእክት በጽዋዐ ብርሃን ተቀብለው በዓለሙ ሁሉ ረጭተውታል፡፡ ለንጊኖስ አንድ ዓይና ነበር[1] ደሙ ቢነጥብበት በርቶለታል፡፡ ኋላም ትንሣኤውን አይቶ መስክሮ በሰማዕትነት አርፏል፡፡ ወዘርዐየ ሰምዐ ኮነ ወጽድቅ ውእቱ ስምዑ እንዲል ዮሐ 19፡35

ወነሥኡ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ወገነዝዎ በመዋጥሕ ዘሰንዱናት ይላል በ11፡00 ሰዓት ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ ከጲላጦስ አስፈቅደው ሥጋውን ከመስቀል አውርደው ሽቱ እየረበረቡ በሐዲስ በፍታ ገነዙት፡፡ ሲገንዙትም ወአንበሰበሰ አዕይንቲሁ ይላል ዓኖቹን ገልጽልጽ አድርጎ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እያላችሁ ገንዙኝ ብሏቸው እንዲሁ እያሉ ገንዘውታል፡፡ አክብራችሁ ስማችሁ እንደገነዛችሁኝ እኔም አከብሬ በሰማያዊ ሰንቁ መንበር እኖራችኋለሁ ብሎም ተስፋቸውን ነግሯቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ በሦስተኛ ቀን የሚነሣ ነውና የኤልሳዕ አጽም ሙት እንዳነሳ ከነቢያቱ የአንዱ አጽም አነሣው እንዳይሉ ዮሴፍ ለራሱ ባሠራው ሰው ባልተቀበረበት አዲስ መቃብር ቀብረውታል፡፡ ዮሐ. 19፡ 41



ምላክ እንደአንግዳ ወደዓለም ቢመጣ
ይንና ወተቱ ብርዙ ሳይታጣ
ስታዋች አይሁድ አሉት ሐሞት ጠጣ፡፡
ዝና እንዳትቀር በገሃነም ነፍስ
ላም በበደለ ሞተ ክርስቶስ፡፡
መስቀል ተሰቅሎ ያልእንዳች ጥፋት
ሕያዋን አምላክ እንደምን ይሙት?
ሚሰገዱለትን ፈርተው መላእክት
ይሁድ በእንጨት ሰቅለው በጦር ሲወጉት
በችንካር ቸንክረው ደሙን ሲያፈሱት
ሬታ ደም ብትሆን ፀሐይም ጽልመት
ዋከብት ቢረግፉ ብትርድ መሬት
ይበዛም ቢያንስ እንጂ እሪ ቢል ፍጥረት፡፡
ች ከና መቃብር ምሕረት የሌላት
ንቱን ጻድቅ ውጣ እልበቃሽ ያላት
ጣላት ጌታዋ ዛሬስ ይውጣላት
ንቺ ተንከራታች ድንግል የኔ ቤዛ

በልጅሽ መሰቀል መከራሽ ቢበዛ
እንባሽ ጎርፍ ሆኖ ሲወርድ እንደዋዛ
ውበት ደምግባትሽ ሲረግፍ እንደጤዛ
ማነው አይዞሽ ያለሽ የቱ ልብ የገዛ
አንቺው ቻልሽው እንጂ ልብሽ በኀዘን ፈዛ፡፡
ጻድቅ ተኮንኖ ኃጥኡ ሲጸድቅ
ሐቀኛ አልቅሶ ውሸታም ሲስቅ
ቀማኛው ሲደሰት ሲጋስ ሲሳቀቅ
ምን አልሽ ይሆን ዓለ ም ምንተናግረሽ ሐቅ?
ምድራቱ ዝም አትበይ መስክሪ ሀቁን
ጎባጣውን ማቅናት ማንሣት ምውቱን
ያሸልማል እንጂ ያሰቅላልን?
ምስጋና ይድረሰው ክብር ይግባው አሚን
በሞቱ ገድለው ጨካኙ ሞትን፡፡
ሲኦል ጠም አደረቸ ኢጋንንት አፈሩ
ምርኳቸው ተነጥቆ ባዷቸውን ቀሩ፡፡

ኢሳ 25፡8 ፤ ቆሮ 15፡54 ፤ ጴጥ 3፡18

## ሰ- ዕረፍቱ ለአባ መቃርስ ዘየዐቢ

ቃርስ (መቃርዮስ) ማለት ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ ሃገራቸው ሳሱዊር ነው፡፡ አባታቸው አብርሃም እናታቸው ሣራ ባላሉ፡፡ አባታቸው ካህን ነበር፡፡ የተወለዱት በብስራተ ኪሩብ ው፡፡

ለ መጠን ሲያደርሱ ግድ ብለው ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ጭተው አጋቧቸው፡፡ በድንግልና ለመኖር ይሹ ነበርና አመመኝ ብለው ከቤተ እግዚአብሔር ገብተው ከዚያ ሰነበቱ፡፡ ሲመለሱ ሽራት ሞታ አገኙ፡፡ እርሷን በድንግልና ሳለች የወሰዳት እኔም በእዚሁ እንድኖር ፈቅዶ ነው ብለው ደስ አላቸው፡፡

ባት እናታቸውም ብዙ አልቆዩም ተከታትለው አረፉ፡፡ ኀዘናቸውን ጨረሱ በኋላ ያለውን ሀብት ንብረት ሁሉ ሰጥተው መጽውተው ማዕ ነቅስና ተቀብለው ከቤተእግዚአብሔር በዓት ሠርተው ተቀመጡ፡፡ ይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ግብራቸውን ጠልቶ ሞታቸውን ሽቶ ብ አነሳባቸው፡፡ ለሀገሩ ባላባት አንዲት የደረሰች ልጅ ነበረችው

በዝሙት ጸነሰች፡፡ ልጄ ምነው እንዲህ አደረግሽ ብሎ አዘነ፡፡ ሰይጣን ለጸሁ ምክንያት አድርጎ መርጧታልና ቤተእግዚአብሔር እጅ ልነሳ ብሄድ አባ መቃርስ እንዲህ አደረገኝ አለች፡፡ ተቆጥቶ ሄዶ እጅ እግራቸውን አስሮ ይገርፋቸው ጀመር፡፡ ይህን ያህል የምትገርፈኝ ምን በደልሁህ? አሉት፡፡ በደልህንማ አንተው ታውቃለህ ብሎ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አብዝቶ ገረፋቸው፡፡

ይህም አልበቃ ብሎት በሰንሰለት አስሮ እየጎተተ ሲወስዳቸው ሁለቱ መላእክት በእምሳለ ወራዙት ቀርበው ምን አጥፍተ ነው፡፡ አሉት፡፡ ልጄን አስነውሮ እኔን አሳፍሮ ነው አላቸው፡፡ ይህንንስ እንደማያደርግ እናውቃለን፤ ባይሆን እስክትወልድ ድረስ ልብሷን ቀለቧን ይሰጣል በዋስ አሰናብተው አሉት፡፡ ማን ይዋሰዋል? አለ፡፡ ሕማማቸውን አይቶ ያዘነ አንድ መንገደኛ እኔ እዋሳለሁ ብሎ አስለቀቃቸው፡፡

ከቁስላቸው ሲድኑ መልአኩ መጥቶ ለዚያች ሴት ቀለቧን ልብሷን አትሰጥምን? አላቸው፡፡ ቅርጫት እየሰሩ ሸጠው ሲሰጧት ቆዩ፡፡ የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ ምጥ ፀንቶባት አራት ቀን ተጨነቀች፡፡ እናቷ ልጄ ጌታን ያስቀየምሽው ነገር እንዳለ አለቻት፡፡ የአባቴን ቁጣ ፈርቼ እንጂ የጸነስኩት ከአባ አይደለም አለች፡፡ ያን ካህን በከንቱ አስቀይመነዋል አሁንም ሳትሞት እንማጸነው ብለው ሲሄዱ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው ይህማ ውዳሴ ከንቱ ሊሆንብኝ ነው ብለው ከበዓታቸው ወጥተው ሲሸሹ መልአኩ በከንቱ ነጥቆ ገደመ አስቄጥስ አድርሷቸው ይህ ቦታ የአንተና ልጆችህ ነው፡፡ እንዲህ አድርግ እንዲህ አታድርግ ብሎ ሥርዓት ሠርቶባቸዋል፡፡

አጋንንት እየተፈታተኑ ቢያስቸግራቸው መልአኩ መርቶ ከአባ እንጦንስ አገናኛቸው ሥርዓተ ምንኩስና ተምረው ተመለሱ ኋላም አባ እንጦንስን ገንዘው ቀብረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን መከራውን በትዕግሥት ሰይጣንን በጸሎት ድል ነሥተውታል፡፡ አንድ ቀን አጋንንት ከበዓቱ ደጃፍ እሳት አንድደው ፍህሙን እየታፈኑ ይጥሉባቸው ጀመር፡፡ ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ቢያማትቡባቸው እንደ ጢስተነው እንደ ትቢያ በነው ጠፍተዋል፡፡ ኋላም ጌታ ስነገድላቸው እንዲገለጽ ብዙ ደቀመዛሙርትን አመጣላቸው፤ ሥርዓተ ምንኩስና አስተምረዋቸዋል፡፡



በዘመናቸው በሀገረ አውሲም ትንሣኤ ሙታን የሚል መናፍቅ ባሕታዊ ተነሥቶ ምእመናንን ሲያስተምር ሄደው ወንድሜ የዘሩት ሲበቅል የተከሉት ሲጸድቅ አላየህምን ብለው በምሳሌ አስተምረው አንድ ሙትም አሥነስተው አሳይተው አሳምነውታል፡፡ በመጨረሻም በስማቸው የተማጸነ ከዕዳ ከፍዳ እንደሚድን ተስፋቸውን ተቀብለው በተወለዱ በ97 ዓመታቸው በዚህ ዕለት አርፈዋል፡፡

- የነበሩት በ4ኛው ም.ዓ. ድ-ል-ክ ነው፡፡

ቅዱስ መቃርዮስ የመንፈስ አርበኛ
በጸሎት ድል ነሣው የሰውን ደመኛ፡፡
የዓለም ብልጽግና ማለፉን አስቦ
በትኅርምት ኖረ በአራዊት ተከቦ፡፡
የጠላት ፈተና መሆኑን ተረድቶ
ሲገርፉት ዝም አለ በትዕግሥት ፀንቶ፡፡

በአምላክ ዘንድ ከፍ ቢል ክብርና ሞገሱ
የሚያነጋግረው መልአክ ነበር ለርሱ፡፡
ያለኃጢአቱ ሰውን ማስቀየም
የኋላ የኋላ ያመጣል መረገም፡፡
በመልካም እንድትኖር ሳያገኝህ ፍዳ
ፈጽሞ አታስብ ማንንም ልትጎዳ፡፡

ኢሳ1፥16 1 ተሰ 5፥15 2 ቆሮ 13፥7

## መጋቢት 28 ሀ. ቀዳም ስዑር

ዐባይ ሰንበት፣ ቀዳም ስዑር ትባላለች፡፡ ዐባይ ሰንበት መባሏ ጌታ በጥንተ ፍጥረት ከእሑድ እስከ ዓርብ ስድስቱን ቀናት ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛዋ በቀዳሚት አልፈጠረም፡፡ ዕረፋባት ሲል ሥራውን ፈጽሞ አርፎባታል፡፡ ወአእረፈ እግዚእነ እምኩሉ ዘአኀዘ ይግበር እንዲል ዘጸ 20፥11

5500 ዘመን ሲፈጸምም ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውኛውን ኖሮ የማዳኑን ሥራ ዐርብ በመልዕልተ መስቀል ፈጽሞ በአዲስ መቃብር አርፎ ውሉባታልና ስለዚህ ነው፡፡

ስዑር መባሏም ደቀመዛሙርቱ ዓርብ ሕማሙን ሞቱን አይተው እሞታለሁ ብሉን ሕማሙን ሞቱን አየን፤ እነሳለሁ እንዳለንስ ትንሣኤውን ሳናይ እንቀራለን ብለው ከምግብ ተከልክለው ሲያዝኑ ውለዋል፡፡ ስዑር መባሏ ብትሻር አይደለምን ብለው ሲሰሩባት ተድላ ደስታ ሲያደርጉባት የሚውሉ ቢኖሩም እውነታው ግን እንዳልነው ሕማሙን ሞቱን እያሰብን የምንጸምባት የምናዝንባት ስለሆነ ነው፡፡ በነግህ ካህናት የነግህ ተግባራቸውን አድርሰው ገብረ ሰላመ በመስቀሉ

እያሉ በዘመነ ኖህ ርግብ "ሐጸ ማየ አይኅ" "ኅትነ ማየ ድምሳሴ" ስትል ቈጠማ የወይራ ቅጠል ይዛ እንደተገኘች "ሐጸ ማየ ኃጢአት" "ኅትነ ማየመርገም" ሲሉ ቈጠማ ለምእመናን ያድላሉ፡፡

## ለ. ዕተፍቱ ለቈስጠንጢኖስ ጻድቅ (272 - 337 ዓ.ም)

ሀገሩ በራንጥያ (ቁስጥንጥንያ) ነው፡፡ አባቱ ቁንስጣ ይባላል፡፡ የበራንጥያ ንጉሥ ነበረ፡፡ መንግሥት ለማዳረስ ወደ ሰርቪያኒስ ሔደ፡፡ ዕሌኒን ከባህር ተጥላ አግኝቷት ሚስቱ አደረጋት፡፡ አረሚ ቢሆንም ቅሉ ክፋት የለውም ነበር፡፡ ዕሌኒ ግን አረሚ በመሆኑና ልጇን ልታስጠምቅ ባለመቻሏ ታዝን ነበር፡፡ ዳሩ ግን ጌታ ዓምደ ቤተክርስቲያን እንዲሆን መርጦታልና ከእናቱ ትምህርተ ክርስትና እየተማረ ከክርስቲያን ጋር እየተባበረ መንፈሳዊ ሆኖ አደገ፡፡

አካለ መጠን ሲያደርስ አባቱ ሥርዓተ መንግሥት አውጥቶለት ዘውድ ደፍቶለት በሁለት ዓመቱ አረፈ፡፡ በብራንጥያ ሰባት ዓመት ከነገሠ በኋላ ሮማውያን ንጉሥ መክስምያኖስ አገዛዝ አጽንቶብናልና መጥተህ አድነን ብለው ላኩበት፡፡ ሲያስበው ውሎ ሌሊት በሕልሙ "በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዖ ለጸርከ - ጠላትህን በዚህ ትእምርተ መስቀል ታቸንፈዋለህ" የሚል ጽሑፍ የተቀረጸበት የብርሃን መስቀል አየ፡፡ ምን ይሆን እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው አድርገህ አሠርተህ ያዝ ታቸንፈዋለህ አለው፡፡ ከዘውዱ ጀምሮ እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ በሁሉ ላይ መስቀል አስቀርጾ ገጥሞ ድል አድርጎታል፡፡

ከዚህ በኋላ ሮምን ጠቅልሎ መግዛት ጀመረ፡፡ በዓመቱ "አብያተ ጣዖታት ይትዐፀዋ ወአብያተክርስቲያናት ይትራኀዋ" ብሎ አውጆ በመክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ ዘመን የፈረሱ የተተከሉ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ፤ የተዘረፉ ንዋያተ ቅድሳትን መለሰ፤ አብያተ ጣዖታትን አፈረሰ፤ ርስት ጉልታቸውን ለቤተክርስቲያን ሠጠ፡፡ ይህም በቤተክርስቲያን ታሪክ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ከተደረጉ አስተዋጽኦዎች አንዱና ታላቁ ነው፡፡

በኑረ ሰይጣን አርዮስ የተወገዘበት፤ እምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ጸሎተ ሃይማኖት፤ የተረቀቀበት ሌሎችም ድርሳናት የተጻፉበት



የመጀመሪያው የሊቃውንት ስብሰባ (ጉባኤ) በኒቅያ የተደረገው በርሱ ዘመነ መንግሥት በርሱ ፈቃድና ጥረት ነው፡፡ ሙሉ ታሪኩ በክፍል 1. ገጽ 63
በመጨረሻ ቦነ በዓል ለማየት ኒቆምድያ ደርሶ ሲመለስ ታመመ በሊቀጳጳሳቱ በአባ ሶል ጴጥሮስ ተጠምቆ በተወለደ በ65 ዓመቱ በዚህ ዕለት ዐርፏል፡፡ ቈስጠንጢኖስ ጥምቀት ነጭ ልብስ ናት፡፡ ደኃ ብበድል ፍርድ ባገድል አሳድፋታለሁ እያለ ያስብ ነበር፡፡ በፍጻሜ ዘመኑም መጠመቁ ስለዚህ ነው፡፡ ይልቁንም አብያተ ክርስቲያናትን ከማሠራት ክርስቲያንን ከጥፋት ከመታደግ የበለጠ አለን? ደኃ ብበድል ፍርድ ባገድል ላልከው ግን ፈቃደ እግዚአብሔር ጠይቀን ሕግ እንሠራልሀለን ብለው ፍትሐ ነገሥትን፤ ግሩም ቅዳሴንና ሕንፃ መነኮሳትን ጽፈው ቢሰጡት እንጂ ሠለስቱ ምዕትን ድኃ ብበድል ፍርድ ባገድል እናንተ መከራ ተቀብላችሁ የምትገቡባትን መንግሥተ ሰማያትን ልወርስ እችላለሁን መንግሥቴን ትቼ ገዳም ገብቼ እንድኖር አሰናብቱኝ እናንተ የወደዳችሁትን አንግሡትችሁ ኑሩ ብሎ ሕልቀተ ወርቁን፤ ሕለተ ወርቁንና አክሊለ ወርቁን ሰጥቷቸው ነበር፡፡ ከብሩንም አባ ብሶይ አይተው መስክረዋል፡፡ በዓታቸውን ዘግተው ሲጸልዩ ቈስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ ሰላም ለከሙ አ ብፁዓን መነኮሳት አላቸው፤ አንተም እንጂ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሟልና ብፁዕ ነህ አሉት፡፡ ከሄደ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ነግረዋቸዋል፡፡
ዜና አበው

ደግ እናት ዕሌኒ በእምነቷ ጽንታ
ደግ ልጅ አስገኘች የሚሆን እለኝታ
ሰላም ለጠማው ሕዝብ ለሚሻ ጽጥታ
ታላቅ ሰው እንዲሆን አምላኩ መርጦት
ለቤተክርስቲያን ሙሴሶ ሆናት፡፡
የሰማዕታቱ ደም እንደጎርፍ ፈሶ
ተቢያ ሆኖ አጽማቸው በምድር ተነስንሶ

እልቀረም በከንቱ ቈስጠንጢኖስ ነግሦ
አይተን ደስ ተሰኘን ጠላት ተደምስሶ
መንግሥት የእግዚአብሔር እውቆ መሆኑን
እገለገለበት ፈጣሪ አምላኩን፡፡
ሰዎች እንታቢይ በሹመታችን
በሀብት እንመካ አይጠፋ መስሎን
በጎ ልንሠራበት ነው የተሰጠን፡፡

## መጋቢት 29 - ብስራት (በዓለ ትስብእት)

ታሪኩ በክፍል 1 መጽሐፍ ገጽ 110 ተጽፏል

## ለ. ትንሣኤ

"ሞተ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ" ሃይ. አበ. ዘአትና. እንዲል:: በፈቃዱ ሞቶ በውዱ ተቀብሮ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በገዛ ሥልጣኑ በዘመነ ማርቆስ እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ተነስቷል:: "ወተንሣእኩ በሥልጣነ - ባሕቲትየ" እንዳለ ቅ-ቄርሎስ

የተቀበረ ዓርብ በሠርክ የተነሣ እሁድ በመንፈቀ ሌሊተ ከሆነማ 3 ቀን 3 ሌሊት በመቃብር ቆየ መባሉ እንደምን ነው? ቢሉ ዕለተ ዓርብ ከሦስት ተከፍሏል:: ከነግህ እስከ ቀትር ሰዓቱ አራት ነው:: ብርሃን ሆኗል፣ ቀትር ከነ ሌሊተ ወጸልመ ኩሉ ዓለም እንዲ ሉቃ 23 : 44 አንድ ሌሊት:: ከዘጠኝ እስከ ሠርክ ሰዓቱ አራት ነው ብርሃን ሆኗል:: ሁለተኛ ቀን፤ ሌሊቱ ሁለተኛ ሌሊት፣ ቅዳሜ ቀኑ ሦስተኛ ቀን ሌሊቱ እስከ መንፈቀ ሌሊት ሦስተኛ ሌሊት ነው:: ያውስ ቢሆን የተቀበረ በሠርክ ነው:: እስከዚያ ያለው ስለምን ተቆጠረ ትለኝ እንደሆነ ሕማሙ ሞቱ ቁጥሩ ከዚያው ነውና::

ትሣኤውን በሦስት ቀን ያደረገው በ2 ወይም በ4 ያላደረገው ስለምንድር ነው? ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው:: ትንቢት - እርሱ ባለቤቱ "እስመ በከመ ነበረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ከማሁ ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ውስተ ልበ ምድር ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ" ብሎ ተናግሯል:: ማቴ 12:40

ምሳሌም ዮናስ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ አድሮ ወጥቷል:: ከርሠ አንበሪ የመቃብር ዮናስ የጌታ ምሳሌ ነው:: ትንቢቱን ባወቀ ተናገረ ምሳለውንም ባወቀ አስመሰለ ፍጻሜው ግን ኃጢአትን በምድር፣ መርገምን በመስቀል፣ ሞትን በሲኦል፣ ጥፋትን በመቃብር ማጥፋቱን ለማጠየቅ ነው:: "አስተኀፈረ ኃጢአተ በዲበምድር መሠዐረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ወነሠተ ሙስና በውስተ መቃብር" እንዲል:: ሃይ. አበመቃብሩን ሲጠብቁ የነብሩ አራት ጭፍች መግነዝ ፍቱልኝ



መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በአካለ ብርሃን ሲነሣ፣ መላእክት ከእግሩ እንደሻሽ ተነጽፈው ሲያመሰግኑት ደንግጠው ሲቻኮሉ ወደ አይሁድ ሄደው ተነሣ አሏቸው:: ቢሄዱ መቃብሩን ተከፍቶ አገኙት:: ልብሳቸውን እየቀደዱ ይጮኹ ጀመር:: 400 ወቄት እንሰጣችሁ ተኝተን ሳለ ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ አሏቸው::

ደቀመዛሙርቱ አይሁድን ፈርተው ተሸሽገው ነበር:: ማርያም መግደላዊት ግን ሽቱ ይዛ እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ይላል ጎህ ሳይቀድ ሄደች:: ሌሎችም ተከታትለው ከመቃብሩ ደረሱ:: ጌታችንን ወስደውታል እያሉ ሲያለቅሱ መልአኩ ለምንት ተኃሥሣሁ ለሕያው ምስለምውታን ተንሥአ ኢሀሎ ዝየሰ ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ትፈልጉታላችሁ? ተነሥቷል ከዚህ የለም፤ ይልቁንስ ተነሥቷል ገሊላ እቀድማችኋለሁ ያላችሁን አስቡ ብላችሁ ለደቀመዛሙርቱ ንገሯቸው አላቸው:: ሄደው ተናገሩ:: ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ሄዱ:: በደሮ ለጴጥሮስ ይላል ዮሐንስ ቀድሞ ደረሰ:: ነገር ግን ርዕስ ነውና ከውጭ ሆኖ ጠብቆ ከጴጥሮስ በኋላ ገባ፤ መግነዙን እንጂ እርእሱን አላገኙም፤ በእውነት ተነሥቷል እያሉ ተመለሱ::

ማርያም መግደላዊት ግን የደረሰበትን ሳላውቅ አልሄድም ብላ ቆማ ታለቅስ ነበር:: ጌታ ከወደኋላዋ መጥቶ ምን ሆነሽ ታለቅሺአለሽ? አላት:: ጠባቂ መሰሏት ጌታዬ አንተ ወስደኸው ከሆነ ሽቱ እንድቀባው ያደረግህበትን አሳየኝ አለችው:: ማርያም ብሎ ስሟን ሲጠራት ጌታ መሆኑን ተረድታ መምህር ሆይ ብላ እጅ ልትነሳው ቀረበች:: ኢትልክፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረኩ ኀበ አቡየ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት:: ይህ ሴቶች ሥጋ ደሙን መቀበል እንጂ ማቀበል አለመቻላቸውን ያጠይቃል:: ኋላ ቶማስን ጎኑን ያስዳስሰዋልና:: ዮሐ 20:27 ሄደሽ ለደቀመዛሙርቴ ተነሣ ብለሽ ንገሪያቸው አላት፤ ሄዳ አብስራቸዋለች:: ዮሐ 20:11-17

በእመቤታችንም ያመጣዋል:- በነግህ ብትሄድ ደንጊያው ተገልብጦ መግነዙ ተቀምጦ አገኘች:: ምርር ብላ ስታለቅስ ጌታ ሰማያዊ ግምጃ ተጎናጽፎ አካሉ እንደ ፀሐይ አብርቶ መጥቶ ብታለቅሺ ብታለቅሺ አትደክሚምን? አላት:: አይሁድ መስቀል መግደል እንዳይበቃቸው ሥጋውን ወስደው ኀዘን ጨመሩብኝ አግኝቼው ቢሆን በተጽናናው ነበር አለች:: በውኑ በጦር የተወጋ ጎኑን፣ በችንካር

የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን፣ በአክሊለ ሦክ የተቆራረሰ ራሱን ስታዪ ትጽናኛለሽ? ይልቁንስ አይሁድ በልጅሽ ተማምለውብታል፣ አንቺ ግን ከኀዘንሽ ተጽናንተሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ አላት፡፡ ነገሩን የምታውቅ ትመስላለህና እባክህ ያለበትን አሳየኝ አለችው፡፡ ፍጹም ኀዘኗን አይቶ አይሁድ የሰቀሉት አንቺም የምታለቅሺለት አንድ ልጅሽ እኔ ነኝ አላት፡፡ ደስ አላት እናቴ ሆይ አይሁድ መነሣቴን ሊያስተባብሉ ከዚህ ይመጣሉና ምክንያት አገኘን እንዳይሉ ወደ ደቀመዛሙርቴ ሂጂ ብሏት ሄዳለች፡፡
ላሐ-ማርያም ሉቃ 24:10





ጲላጦስ ጌታ በመስቀል ሆኖ የተደረጉትን ሰባት ተአምራት አይቶ ደግ ሰው አሰቅያለሁ ብሎ አዝኖ ሳለ ጌታ በሕልሙ ሞቼ የቀረሁ መሰለህን? ግረኝ ብትለኝ እምርህ የለምን ሲለው አየ፡፡ በነግህ አይሁድ መጥተው ሥጋው ተሰርቋልና ጠባቂዎችን አስጠርተህ መርምርልን አሉት፡፡ ሲመረምራቸው አንዱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሠረቁት፤ ሁለተኛው አሥራ አንዱ ሁሉ ሠረቁት፣ በሦስተኛው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ወሰዱት አሉ፡፡ አራተኛውን እውነቱን ንገረኝ ብሎ ቢገሥፀው ከእንቅልፍ ስንነቃ ከውኃ ጉድጓድ ተጥሎ አገኘነው ፤ ይህንንም ያደረጉ ደቀመዛሙርቱ ይሆናሉ ብለን እንጂ ሲወስዱትስ አላየንም አለ፡፡ አራቱንም ከግዞት ቤት አስገብቶ የመቶ አለቃውን ከነጭፍሮቹ አስከትሎ ከመቃብሩ ሄደ፡፡ መግነዙን አይቶ ደቀመዛሙርቱ ወስደውትስ ቢሆን ይህንንም ባልተውት ነበር ብሎ መግነዙን ይዞ ያለቅስ ጀመር፡፡ እኔስ ጌታ እንደተነሳ ይህም መግነዝ ዕውር እንደሚያበራ አምናለሁ ብሎ መቶ አለቃውን ቢዳስሰው የጠፉች አንድ ዓይኑ በርታለታለች፡፡ ወዲያውም ዮሴፍ ኒቆዲሞስን ጠርቶ አስመሰከራቸው፡፡ አይሁድ እነርሱ ከኛ እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የላቸውም፣ አንተ ተነሣ የምትለው ግን ያውልህ ከጉድጓድ ወድቆልሀል አሉት፡፡ ከመቶ አለቃው ጋር ተሸክሞ አምጥቶ ከመቃብሩ አግብቶ ደንጊያውን ገጥሞ ጌታዬ ሆይ የአንተ ክብርህ የአይሁድ ሐሰታቸው በዚህ ሙት ይገለጥ ዘንድ እለምንሀለሁ ብሎ ለመነ፡፡ ሙቱ ተነሥቶ በጌታ ቀኝ የተሰቀለ ጥጦስ መሆኑን የጌታንም ክብር መሰከረ፡፡ አይሁድ ፈርተው እየተዟዟሁ ይሸሹ ጀመር ያዟቸው አትልቀቁአቸው ብሎ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ በኀሙድ አስገርፏቸዋል፡፡

ወዲያውም ተነሣ ብሎ ከሄሮድስ ላከበት፡፡ እሱም መግነዙን፣ ዓይኑ የበራለትንና ከሞት የተነሣውን አያቸው ዘንድ ላክልኝ ብሎ ላከበት፡፡ እውነት መስሎት ላከለት፡፡ ሰዎቹን በሰይፍ አስመትቷቸው በሰማዕትነት አርፈዋል፡፡ እርሱንም በሐሰት ከቄሳር አጣልቶ ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር በሰይፍ አስመትቶት በሰማዕትነት አርፏል፡፡ ግብ. ሕማ

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱ ቀለዮጳና ኒቆዲሞስ ከኢየሩሳሌም 60 ምዕራፍ ወደምትርቅ ወደ ኤማሁስ የርሱን ነገር እየተጫዋወቱ ሲሄዱ ከወደኋላቸው ተከትሎ ይህ የምትሉት ነገር ምንድነው? አላቸው፡፡ ቀለዮጳ አንተ ለኢየሩሳሌም እንግዳ ነህን? ናዝራዊው

ኢየሱስን አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው እንደሰቀሉት አልሰማህምን? እኛማ ወልደ አምላክነቱን አምነን ተከትለነው ነበር፤ ዛሬም በነግህ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሄደው ሥጋውን አላገኙም፣ ተመልሰው መጥተው ተነሥቷል አሉን፡፡ ይህንንም ጴጥሮስና ዮሐንስ ሄደው አይተዋል አሉት፡፡ እናንተ ዝንጉአን ብትሆኑ እንጂ እሱማ እንዲሞት እንዲነሣ ነቢያት ትንቢት ተናግረውለት የለምን እያለ መጻሕፍትን ይተረጉምላቸው ጀመር፡፡

ከሚሄዱበት ሲደርሱ መሽቷል ከእኛ ጋር እደር ብለው ግድ አሉት፡፡ ማዕድ ሲቀርብ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ሰጥቶ ተሰወራቸው፡፡ ወተከሥታ አዕይንቲሆሙ ይላል ጌታ መሆኑን አውቀው ወደኢየሩሳሌም ተመልሰው ለሐዋርያት ነገሩ፡፡ ወዲያውም ጌታ ከዝግ ቤት እንዳሉ በማይመረመር ጥበቡ ከመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለከሙ አላቸው፡፡ ምትሀት መሰሏቸው ታወኩ፡፡ በጦር የተወጋ ጎኑን በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን አሳይቷቸዋል፡፡ በዚያውም ላይ ንሥኡ መንፈስ ቅዱስ ለእለ ኀድግሙ ኃጢአት ይትኀደግ ሎሙ ወለእለ ኢኀደግሙ ኢይትኀደግ ሎሙ ብሎ በምድር ያሠሩት በሰማይ የታሠረ በምድር የፈቱት በሰማይም የተፈታ ይሆን ዘንድ ሀብተ ክህነት ሠጥቷቸዋል፡፡ ሉቃ 24፡ 1-43

በመቃብር አድሮ ሦስት ሌሊት ሦስት ቀን
ሳይል መግነዝ ፍቱ አንሡ ደንጊያውን
ብርሃን ተጎናጽፎ ሲነሣ መድኀን
ሊያስቀረው አልቻለም ሞት ይዞ እርሱን፡፡
አይሁድ እርሱን ሰቅለው ደስ ሲላቸው
ከሙታን ቢነሣ ፍርሀት ዋጣቸው፡፡
በብርሃን ሲተካ የሌቱ ጽልመት
መላእክት ከበው ሲያመሰግኑት
ሙታን ናቸውና የአይሁድ ሠራዊት
ያንኮራፉ ነበር ተኝተው መሬት፡፡
ገና ወላጆቹ ዋሉ ተደስተው
በገዛ ሥልጣኑ ጌታ አምላካቸው
ከሙታን ተነሥቶ አይተውት በዓይናቸው
እምነቱ በአምላኬ ታላቅ ነው የጸና
ሞቼ ብቀበርም እነሣለሁና፡፡
አግዐዝካለሁ ጌታ ፈጣሪዬ
ኋላ እንድታነሣኝ በጎ ግብር አዝዬ
አንተኑ ጌታዬን አባቴን መሰዬ፡፡

## መጋቢት 30 - ዕረፍቱ ለሶምሶን መስፍን

ሶምሶን ማለት ሐዲስ ለእግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ ትውልዱ ከነገደ ዳን ነው፡፡ አባቱ ማኑሄ እናቱ እንትኩይ ይባላሉ፡፡ እንትኩይ ዕፁተ ማህፀን ሁና ስታዝን ትኖር ነበር፡፡ አንድ ቀን እንጨት ስትለቃቅም የታዘዘ መልአክ መጥቶ ደግ ልጅ ትወልጃለሽ፣ የወይን ጠጅ



ከመጠጣት ርኩስም ነገር ከመብላት ተጠበቂ፤ ለባልሽም ንገሪው፣ ሕፃኑ ለእግዚአብሔር የተለየ ነውና በራሱ ላይ ምላጭ አያርፍበትም አላት፡፡ ለባሏ ነገረችው፡፡ ሁለተኛ ሲገለጥልሽ ንገሪኝ አላት፡፡ ሁለተኛ ተገልጾ ደግ ልጅ ትወልጂያለሽ አላት፡፡ ቆየኝ ባሌን ልጥራ ብላ ጠርታ አመጣችው፡፡ ለርሷ የነገራትን ሁሉ ነገረው፡፡ የፍየል ጠቦት አርዶ ሥጋውን አወራርዶ መሥዋዕት አቀረበ፡፡ መልአኩ በዘንጉ ቢነካው ተቃጥሎለታልል፤ እሱም በጢሱ ዐርጓል፡፡ መልአክ አይተው አያውቁም ነበርና ወዮልን እንሞታለን አላት፡፡ እኛ ከሞትንማ ልጁን ማን ይወልደዋል? አንሞትም አለችው፡፡ ወዲያውም ሶምሶን ተፀነሰ፡፡

ተወልዶ ባደገ ጊዜ ኃያል ሆነ፡፡ በአሥራ አምስት ዓመቱ ከአባቱ ጋር ወደ ኢሎፍሊ ሄደ፡፡ በመንገድ ተለይቶ ዱር ቢገባ ግሩም አንበሳ አገኘው፡፡ በጡጫ መትቶ ገድሎታል፡፡ ሲመለስም አስታውሶ ቢያየው አንሁብት በአፉ ውስጥ ማር ሰርተው አገኘ፡፡ ማሩን ቆርጦ ከአባት ከእናቱ ጋር ተመግቦታል፡፡

በኢሎፍሊ ያያት ቆንጆ ነበረች፡፡ አባቱን አጋባኝ አለው፡፡ ተስፋ ከተነገረላቸው ከእስራኤል ሴቶች እንጂ ከአሕዛብ ሴቶች አታገባም ብሎ ከለከለው፡፡ እርሱ ግን ወድጃታለሁና አጋባኝ ብሎ ግድ አለ፡፡ አጭቶ አጋባው፡፡ ሠላሳ ያህል ሚዜዎች ተመርጠው ሲያጫዋውቱት ካገኛችሁት ሠላሳ መጎናፀፊያ ሠላሳ ቀሚስ እሰጣችኋለሁ፡፡ ካላገኛችሁት ግን እናንተ ትሰጡኛላችሁ ብሎ "እምአፈበላዒ ተረክበ መብልዕ ወእምአፈ ሐሱም ተረክበ ጥዑም ከበላተኛ አፍ መብል ከክፉም አፍ ጣፋጭ ተገኘ" የሚል ምሳሌ ነገራቸው፡፡ ሦስት ቀን ሲያስቡ ቆይተው የማይሆንላቸው ቢሆን ሚስቱን ጠይቀሽ ንገሪን ብለው አስጨነቋት፡፡ ጠይቃ ነገረቻቸው፡፡ በቀጠሮ ቀርበው ምሳሌህን እንንገርህ አሉት፡፡ እሺ አለ፡፡ "ከአንበሳ የተፈራ ከማር የጣፈጠ ምን አለ? ከአንበሳ አፍ ማር አግኝተህ በልተሀል" አሉት፡፡ "እምኢያሥራህክምዋ ለዕጎልትየ እምኢረከብክዋ ለምሳሌየ - ሚስቴን ባታስጨንቋት ኖሮ ምሳሌየን ባላገኛችኋት ነበር" ብሎ ተናዶ ወደ ጌዳ ወጣ፡፡ ሠላሳ ያህል ነጋድያን ሲያልፉ አግኝቶ ጭንጭናቸውን ሰብሮ መጎናጸፊያና ቀሚሳቸውን ገፎ አምጥቶ ሠጣቸው፡፡ በዚህም አዝና ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

ከሦስት ወር በኋላ የበግ ሙከት ይዞ ቢመጣ አማቱ ሚስትህንማ ቀረህ ብለን ለሚዜህ ዳርናት፡፡ ከወደድህ ታናሿን አግባ አለው፡፡ ወደኋላ ተመልሶ 300 ቀበሮ ያዘ፣ 150 ጭራሮ አዘጋጅቶ አንዱን በሁለቱ ቀበሮዎች ጅራት እያሰረ በእሳት እያቀጣጠለ ለቀቃቸው፡፡ ቀበሮዎቹ ደንግጠው ሜዳ ለሜዳ ሲሮጡ የኢሉፍላውያንን አዝመራ አቃጥለውት ዋሉ፡፡

የሀገሩ ሰው ስምሶን ያደረገው መሆኑን ሲያወቁ በአማቱ ፈርደው አማቱን ከሀብት ከንብረቱ ጋር ቤት ዘግተው አቃጥለውታል፡፡ ሶምሶን ይህን ባታደርጉ ኖሮ ጠቢ ከእናንተ ነበር አላቸው፡፡ አርባ ሆነው ገጠሙት፡፡ ጭንጭናቸውን ሰብሮ በዓተ ኤጣም ገብቷል፡፡ ሄደው እስራኤልን ሶምሶንን ይዛችሁ ስጡን አሏቸው፡፡ ነገሩት እጅ እግሬን አስራችሁ ከሜዳ ጣሉኝ አላቸው፡፡ ጣሉት፡፡ ሲይዙት ሲጠጉ የታሰረበትን በጣጥሶ ተነሳ፡፡ የአህያ መንጋጋ አገኝቶ ቢወረውር ባንድ ጊዜ 1000 ሰው ፈጅቷል፡፡ ወዲያው ውኃ ጥም ተሰማው፡፡ ወደጌታ ቢያመለክት ከአህያው መንጋጋ አፍልቆ አጠጥቶታል፡፡ በጋዛም ሳለ ካደረበት ቤት ሸምቀው ሲጠብቁት መናራቸውን አውቆ ወጸረ ራግዛተ ጋዛ በመትከፉ ይላል ከነደርቡ ተሸከሞ ወስዶ ገደል ከቷቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ በሴራቅ ደሊላ የምትባል ሴት ለመደ፡፡ ኢፍላውያን ወርቅ ብር እንሰጥሻለን ኃይሉ የሚደከምበትን ጠይቀሽ ንገሪን አሏት፡፡ ጠየቀችው በሰባት አውታር ብታሠር እደከማለሁ አላት፡፡ አሥራ ሶምሶን ኢሉፍላወያን መጡብህ አለችው፡፡ በጣጥሶት ተነሣ፡፡ አታለልከኝ እውነቱን ንገረኝ አለችው፡፡ በሰባት ምራን ብታሠር እደከማለሁ አላት፡፡ አሥራ ሶምሶን ኢሉፍላውያን መጡብህ አለችው፡፡ ጎማምዶት ተነሣ፡፡ አሁንም ዋሸሽኝ ንገረኝ እንጂ አለችው፡፡ ሰባቱ ቁንዳላዎቼን ከምድር በካስማ መትተው ቢያሲዟቸው እደከማለሁ አላት፡፡ እንዲሁ አድርጋ መጡብህ አለችው፡፡ ነቃቅሉት ተነሣ፡፡ ከኃይሉም ጽናት የተነሣ ካስማዎቹ የደረሱበት አልታወቀም፡፡

በመጨረሻ እወድሻለሁ ትለኛለህ እንጂ አትወደኝም ብላ ወተሀወከት ነፍሱ እስከ ለሞት ይላል ነፍሱ እስከትታወክ ድረስ አስጨነቀችው፡፡ ኃይሌ በጸጉሬ ነው፣ እስመ ናዝራዊ ሐዲሱ ለእግዚአብሔር የተባልሁ እኔ ነኝ ከተወለድሁ ጀምሮ አልተላጨሁትም አላት፡፡ በወይን ጠጅ



አስክራ አስተኝታ ጸጉሩን ቆርጣ ቆርጣ ከጣለችው በኋላ ሶምሶን ኢሉፍላውያን መጡብህ አለችው፡፡ ኃይል ተነስቶት መነሳት አቃተው፡፡ በዚህ ጊዜ ኢሉፍላውያን ይዘው ሁለት ዓይኑን አጥፍተው እየጎተቱ ወሰዱት፡፡ ባቁላ ሲያስፈጩት ኖረዋል፡፡

ጸጉሩ እያደገ ኃይሉ እየተመለሰ ሄደ፡፡ አንድ ቀን በዓል አድርገው ሳለ ያን ዕውር አምጡት ያጨውተን አሉ፡፡ አንድ ብላቴና እየመራ አምጥቶ ከመካከል አቆመው፡፡ ሁለቱን ሙሰሶዎች በቀኝ በግራ እጁ ይዞ ኦ እግዚኦ እስእለከ አሐተ ስእለተ ሀየንተ ክልዔሆን አዕይንተየ ትፃእ ነፍስየ ምስለ ኢሉፍላውያን ስለሁለቱ ዓይኖቼ ነፍሴ ከኢሉፍላወያን ጋር ትወጣ ዘንድ እለምንሀለሁ ብሎ አንዱን ሙሰሶ በቀኝ እጁ ሁለተኛውን ሙሰሶ በግራ እጁ ቢመታው ከፎቅ የነበሩትም ከምድር ያሉትም ሁሉም አንድ ሆነው ጠፍተዋል፡፡ በሕይወተ ሥጋም ሳለ ካጠፋቸው ጠላቶቹ ያን ጊዜ በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉ፡፡

መጽ. መሳፍንት ከምዕራፍ 13 - 16 በሙሉ፡

• <u>የነበረው በ1300 ዓ.ም ገደማ</u> ነው፡፡

_____ //_________

## ምዕራፍ 2

### ሚያዚያ 1 - ዕረፍቱ ለአሮን ካህን

አሮን ማለት ደብረ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ የሊቀ ነቢያት

ሙሴ ታላቅ ወንድም ነው፡፡ ሲራ 45:6 ትውልዱ ከነገደሌዋ ነው፡፡ አባቱ ጌታ እስራኤልን ከምድረ ግብጽ ሲያወጣ ሙሴን መስፍን አሮንን ካህን አድርጎ አስነስቷቸዋል፡፡

ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ እስራኤል ሲበድሉ ጌታ በቸነፈር ገሥጻቸው፡፡ ሙሴ ወደጌታ ቢያመለክቱ ወንድምህ አሮን ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ የታመሙትን ባንድ ወገን ያልታመሙትን ባንድ ወገን አድርጎ ይጠንላቸው አለው፡፡ ወነሥአ ኤፋደ ቅኔሁ ዘጸሎት ከተረ መዓተ ወአንሥዐ መቅሰፍተ ይላል እንዳለው አድርጎ ቢያጥንላቸው የታመሙት ድነዋል ያልታመሙት ተጠብቀዋል፡፡

ልጆቹ ናዳብ፣ አብዩድና አልዓዛርም እንደርሱ በክህነት ጌታቸውን ያገለግሉ ነበርና ደቀቀ ቀዓት እስከ መቼ ክህነትን ከነልጆቹ ይዞ ሲገዛን ይኖራል? ብለው ተመቀኙት፡፡ ሙሴን እኛም ከሌዊ ወገን ተወልደናልና ሹመን አሉት፡፡ አሮን የተሾመ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ እናንተም ከእግዚአብለሔር አግኝታችሁ ተሾሙ እንጂ እኔ አይቻለኝም አላቸው፡፡ ይህማ ለወንድሙ ማድላቱ ነው፡፡ ብለው ከሁለት መቶ የሚበልጡት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንተ ብርት ይዘው ሊያጥኑ ገቡ፡፡ ጢሱ ሲያርፍባቸው ልብሳቸው ምንም ሳይሆን እነርሱ እሳት እንደለበለበው ግንድ ሆነው ሙሴ አሮን አውጥተው ጥለዋቸዋል፡፡ በሙሴም ተነስተው የነበሩ ዳታንና አቤሮን ከነሀብት ንብርታቸው መሬት ውጣቸዋለች፡፡ ምክር ሊያጸና ወዲያ ወዲህ ይል የነበረ ቆሬም የደረሰበት አልታወቀም ጠፍቷል፡፡



እስራኤል ኃጢአታችንን እያሳሰቡ ይህን ሁሉ መከራ የሚያመጡብን ሙሴ አሮን ናቸው ብለው ሊወግሯቸው ደንጊያ ይዘው መጡባቸው፡፡ ከደብተራ ኦሪት ገቡ፡፡ ወድያውም የብርሃን ዓምድ ከምድር እስከ ሰማይ ተተከለ፡፡ በዚህ ፈርተው ተመልሰዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታ ክህነት ከቤትህ እንዳይወጣ ምልክት አሳይልሀለሁና ወንድምህ ሙሴ የ12ቱን ነገድ በትራቸውን ሰብስቦ በምሽት ከደብተራ ኦሪት አግብቶ በነግህ ያውጣው አለው፡፡ ሙሴ እንደታዘዘው ሰበሰበ፡፡ አሮንም የአባቱን የሌዊን በትር አምጥቷል፡፡ 12ቱንም በምሽት አግብቶ በነግህ ቢያወጣው የእርሱ ለምልማ አብባ አፍርታ ተገኝታለች፡፡ ዘኁ 16:17 እና 18 (ምሳሌነት አለው፡፡ በክፍል 1 ገጽ 95 ተመልከት፡፡)

እንዲህ እያሉ ሐቅለቃዴስ ሲደርሱ እስራኤል ዋዕየ ፀሐይ ተሰምቷቸው ውኃ ውኃ ብለው ሙሴና አሮንን አስጨነቁአቸው፡፡ ደንጊያውን በበትር ሲመቱት ውኃ ፈለቀ፡፡ ለወትሮው ንሴብሖ ደግመው ንሥኦ ዘወሀበከሙ እግዚአብሔር . ኪያሁ ሰብሑ - የሰጣችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ ብለው ይሰጧቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ተናደዋልና ይህን ሳያደርጉ ሳያመሰግኑ ሰጧቸው፤ እስራኤልም ሳያመሰገኑ ጠጡት፡፡ በዚህ ጌታ አዘነ፡፡ ታመሰግኑኝ ዘንድ ካላመናችሁብኝምና ምድረ ርስት አትገቡም አላቸው፡፡ ይኸውም አልቀረ ሙሴ በሞአብ አሮንም በደብረ ሖር ዐርፈዋል፡፡ ዘኁ20፡ 1-29

### ሚያዚያ 5 - ዕረፍቱ ለሕዝቅኤል ነቢይ

- የነበረው በ1500 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡

ሕዝቅኤል ማለት ጽኑዕ ጽኑዐ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው፡፡ አባቱ ቡዝ ይባላል፤ ካህን ነበር፡፡ ቁጥሩ ከአራቱ ዐበይት ነቢያት ነው፡፡

እስራኤል ተማርከው ፋርስ ባቢሎን በወረዱ በ30 ዓመት ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶታል፡፡ ሕዝ 1:1-3 ከዚህ በኋላ ክህነትን ከትንቢት

አንድ አድርጎ ይዞ ሃያ ዓመት አስተምሯል፡፡ የጌታን ከእመቤታችን መወለድና እመቤታችንም ቅድመ ጸኒስ፣ ድኅረ ጽንስ፣ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወለድ ድንግል መሆኗን በራዕይ አይቷል፡፡ ሕዝ 44፡ ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ እስራኤል አምላካቸውን ዘንግተው በቃላቸው አዘው በእጃቸው ሠርተው ላቆሙት ምስል የሚሰግዱ የሚሠው ቢሆን ገሠጻቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ጸልተው ተመቅኝተው በደንጊያ ወግረው ሮኣሳት ተኩሰው ገድለውታል፡፡

> መዋዕለ ትንቢቱ ከ 592 – 570 ዓ.ዓ ነው፡.

## ሚያዚያ 6 - የአዳምና ሔዋን መታሰቢያ

ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ዘፍ 1፡26 ይላል ጌታ ከእሑድ ዓርብ ነግህ 21 ዱን አስራወፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (ከነፋስ፣ እሳት፣ ውኃና መሬት) ከሦስቱ ግብራተ ነፍስ (ለባዊነት ነባቢነት እና ሕያውነት) የ30 ዓመት ጎልማሳ አድርጎ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ፈጠረው፤ ባሕርዩ ባሕርየ መልአክ ወሰብእ ነውና ማዕከላዊ ነህ ሲል ነው፡፡

ሰውም ማለት ሰባት ባሕርያት ያሉት ፍጹም ፍጡር ማለት ነው፡፡ ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ነውና፡፡ እስመ ትልቀ ሳብዕ በጎበ ዕብራውያን ፍጹም ወእቱ እንዲል ሃይ. አበ ፍጹምነቱም በአርአያ እግዚአብሔር በመፈጠሩ ነው፡፡ በፍጥረት ላይ የሰለጠነ ሆኖ መፈጠሩም ፍጹም ያሠኘዋል፡፡ "ወሢሞ ንጉሠ ካህነ ወነቢየ ወመጋቢ፤ ላዕለ ኩሉ ዘፈጠረ እንዲል ስንክሳር ይህም ሲታወቅ መላእክት ከእግዚአብሔር ታዘው በየብስም በባሕርም ያሉትን እንስሳት አራዊት ወደርሱ እያመጡ እሱ ስም አውጥቶላቸዋል፡፡ ኩፋ. 4፡ 1-3

ከዚህ በኋላ ወይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ሠናየ ለእጓለእመሕያው ይንበር ባሕቲቶ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድአ ይላል፡፡ የሰው ልጅ ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፡፡ ረዳት እንፍጠርለት ብሎ እንቅልፍ አመጣበትና ፍጹም ሳይተኛ ፍጹምም ሳይነቃ ከጎኑ



አንድ አጥንት ወስዶ በሥጋ መልቶ የ15 ዓመት ቆንጆ አርጎ ሴትን ፈጠረ፡፡ ወእምጽአ እግዚአብሔር ድቃስ ላዕለ አዳም ወኖመ ወነሥአ አሐደ አጽመ እምገቦሁ ወለእንተ ነሥአ አጽም ረሰያ ብእሲተ ወእምጽአ ኀበ አዳም አዳምም ዛቲ አጽም እምአጽምየ ወሥጋ እምሥጋየ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት ብሎ ሚስት አደረጋት፤ ስሟንም ሔዋን አላት፡፡ ሔዋን ማለት እመ ሕያዋን ማለት ነው፡፡ ዘፍ 3፡20

ይህም የሆነ በሳምንቱ ዓርብ በሦስት ሰዓት ነው፡፡ እስኪግርስ
አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀኗ ገነት ገቡ፡፡ በዘመነ ኦሪት ወንድ በአርባ ቀኑ ሴት በሰማንያ ቀኗ ዕጉለ ርግብ ዘውገ ግዕነት ይዘው ቤተመቅደስ መግባታቸው፣ ዛሬም እንዲሁ በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ለጥምቀተ ክርስትና ቤተክርስቲያን መግባታቸው ስለዚህ ነው፡፡ ኩፋ 4፡9-10

በገነትም የታዘዙላቸውን ፍሬ እየተመገቡ 7 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን ተቀመጡ፡፡ ኩፋ4፡16 በዚህ ጊዜም እንስሳት አርደህ ብላን አልበህ ጠጣን ሲሉ አራዊትም እጅ ሊነሡ ከአዳም ዘንድ ሄዱ፡፡ እርሱም ሁሉን መርቆ ሰደዳቸው፡፡ እየተደሰቱ ሲመለሱ ዲያብሎስ ከጎዳና ቆይቶ ይህ ሁሉ ደስታ ምን ተገኘቷል? አላቸው፡፡ አርደህ ብላን አልበህ ጠጣን ብንለው መርቆ ሰደደን አሉት፡፡ ጌታችሁ አዳም ምን ይመስላል አላቸው? ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራል አሉት፡፡ ያችን ዕፀ ቀርጦ ማን ከእፉ ባደረገልኝ ብሎ አሰበ፡፡

በሌላ ቀን እጅ ሊነሱ ሲሄዱ አግኝቷቸው አስከትሉኝ አላቸው፡፡ አይሆንም ብለው ትተውት ሄዱ፡፡ አብርል አዝርል የተባሉ ድምፀ መልካም አዕዋፍም ጌታችን አዳም መልከመልካም ነው አንተ ግን መልከ ጥፉ ነህ ብለውት አለፉ፡፡ በመጨረሻም የግመል ወሣብሬ ታህል የነበረችው እባብ መጣች፡፡ አስከትዪኝ አላት፡፡ መልከ ጥፉ ነህ አይሆንም አለችው፡፡ መልከ ክፉ ካልኖረ መልከ መልካም በምን ይታወቃል፣ በዚያውስ ላይ ካንቺ ከመልከመልካሟ ጋር ሆኜ መልከ ክፉነቴ አይታወቅም አላት፡፡ በውዳሴ ከንቱ ተጠልፋ እሺ ብላ አስከተለችው፡፡

ከዳገት ሲደርሱ ይህ መንገድ ካላወቁበት ያደክማል፣ እንተዛዘል አላት፡፡ እሺ አለች፡፡ አዘላት፡፡ ጥቂት እልፍ አድርጎ በጽሐ ፍዳ

ተባርዮ ዘጸርኩኪ ጹርኒ ተራሽ ደረሰ እዘዴኝ አላት፡፡ አዘለችው፡፡ ከእካሏ ተዋሕዶ እያክለፈለፈ ወሰዳት፡፡

አዳም መላእክት አሌፋት አስተምረውት ነበርና ሲጸልይ አገኘው፡፡ ቀርቦ በሐከ አ አዳም ንጉሠ ሰማያት ወምድር - የሰማያትና የምድር ንጉሥ ሰላም ላንተ ይሁን ብሉ ሰላምታ አቀረበ፡፡ እርሱ ግን ፍልጥ አርዌምድር የምድር እንጂ የሰማይ ንጉሥ አይደለሁም ወግድ አለ፡፡ ወደ ሔዋን ቢሄድ ሥራ ፈትታ እግሯን ዘርግታ አገኛት፡፡ ድል እንደሚነሳት አወቀ፡፡ ቀርቦም በሐኪ አ ሔዋን ንግሥተ ሰማያት ወምድር አላት፡፡ ለካስ የሰማያትም ንግሥት ነኝ ብላ ደስ አላት፡፡ በእንተ ምንት ይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኵሉ ዕፀው ዘውስተገነት በገነት ካሉ እንጨቶች ሁሉ እንዳትበሉ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ለምንድር ነው? አላት ያዘነ የተቆረቆረ መስሎ ኸረ ዕፀበለስንም አትበሉ ያለን ሞትን እንዳንሞት ነው አለች፡፡ ለእመ በላዕክሙ እምትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ እንዲል ዘፍ 3:3 አኮ ሞተ ዘትመውቱ አላ አምላከ ትከውኑ - አምላክ ትሆናላችሁ እንጂ አትሞቱም ወባሕቱ የአምር እግዚአብሔር ከመ ሶበበላዕክሙ እምኔሃ ይትከሠታ አዕይንቲክሙ ወትከውኑ ከመአምላክ ዳሩ ግን ከርሷ በበላችሁ ጊዜ አይኖቻችሁ እንዲገለጹ እንደ አምላክም እንድትሆኑ እግዚአብሔር ያውቃል ለዚህ ነው አላት፡፡ ወአፍተዋ ከመትብላዕ እምውእቱ ዕፅ ይላል አስጎመጃት፡፡ በልታ አዳምን አበላቸው፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ልብሰ ብርሃን ተጐናጽፈው ሳይተፋፈሩ ይኖሩ ነበረ:: በዚህ ጊዜ ግን ጸጋቸውን ተገፋፋ፤ ተፋፍረው በበለስ ቅጠል ሥጋቸውን ይሸፍኑ ጀመር፡፡ እባብ ከአራዊት ሁሉ የተረገመ በሆዱ የሚሳብ አፈር የሚመገብ የሰው ልጅ ራስ ራሱን የሚቀጠቅጠው እንዲሆን ፈረደበት፡፡ አዳምና ሔዋንንም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ፈርዶ ከገነት አስወጥቶ በደብር ቅዱስ አኖራቸው፡፡ ተመልሰውም እንዳይገቡ "ወአዘዘሙ ለኪሩቤል ወሱራፌል ዘውስተ እዳዊሆሙ ሰይፈ እሳት እንተ ትተመያየጥ ከመይዕቀቡ ፍኖተ ዕፀ ሕይወት"(ዘፍ 3:24) ይላል፡፡ ሰይፈ እሳት የያዙ ኪሩቤል እንዲጠብቋት አድርጓል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አዳም እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ታህል ቦታ ባንቺ ምክንያት አጣሁ ብሉ ሔዋንን ፊት ነሳት፤ ደንግጣ ሸሸች፡፡ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶለምን አበረርኻት? በርሷ ምክንያት እግዚአብሔር ጌታዬን ገነት ቦታዬን አጣሁ አለ፡፡ በርሷ ምክንያት



ብታጣም መታረቂያህ እርሷ ናትና ታረቃት አለው፡፡ እርሱ ግን ኢትከወነኒ ናዛዚተ - በፍፁም መታረቂያዬ አትሆኝኝም ብሉ ሳይታረቃት ቀረ፡፡ ከዚህ በኋላ በጸሎት ጊዜ ሲጸልይ መልአኩ አዳም የቀመኛን ጸሎት እግዚአብሔር አይሰማም ምን ያረግልሀል አለው፡፡ ሄዶ ታርቆ አምጥቷታል፡፡

ሔዋን ከጌታ መታረቅ ሽታ አዳም እግዚአብሔር ግረን ብንለው ይምረናልና ሱባኤ ይዘን እንለምነው አለች፡፡ እርሱም አንቺ እያለሽ በምን ይሆናል አለ፡፡ ከእንግዲህ ከፊታድህ አልወጣም አለች፡፡ ከዚህ በኋላ "ምቅዋሞን (ምጽላዮን) ለአንስት ለባሕቲቶን" የምትል ሕግ እንድትሠራ አውቀው እጅግም ሳይራራቁ እጅግም ሳይቀራረቡ ለየብቻቸው ሆነው ከባሕር ገብተው ይጸልዩ ጀመሩ፡፡ በሠላሳ አምስተኛ ቀን ዲያብሎስ እንግዲህማ ሊታረቁብኝ አይደለምን ብሉ መልአከ ብርሃናዊ መስሉ አዳም ጌታ ምሬሀለሁና ውጣ ብሉሀል አለው፡፡ አንተ ማነህ? አለው መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አለው እርሱም ከዚህ በፊት የፍጡር ቃል ሰምቼ ተጐድቻለሁና አልወጣም አለ:: ወደ ሔዋን ሄዶ አንቺ ሔዋን ባልሽ አዳም ቀድሞ አትብላ ያለውን በልቶ ፈጣሪው ተጣላ አሁን ደግሞ ታርቄሀለሁ ውጣ ቢለው አልወጣም አለ እኔ ምን ገዶኝ ለራሱ ይባሰው እንጂ አላት:: አንተ ማነህ? አለችው፡፡ መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላት ወጥታ ሄዳ አዳም ጌታ እንኳ በ35 ቀን በ1 ቀንስ ይምር የለምን ውጡ ካለንማ እንውጣ እንጂ አለችው፡፡ እርሱ ግን አይሆንም የፍጡር ቃል ሰምቼ አልወጣም አለ፡፡ እኔስ እሄዳለሁ ብላ ወጥታ ሄደች፡፡ መልአኩ አትለያት ብሉት ነበርና እርሱም ወጥቶ ተከተላት ከእግረ ገነት ሲደርሱ ሰይጣን እኔ ማንኝ እውቃችሁኝ? አላቸው መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላልሁምን? አሉት፡፡ ምን ገብርኤል ነኝ ባላጋራችሁ ነኝ እንጂ ብሉ ጉሥምሙን ቢያሳያቸው ደንግጠው ወደቁ፡፡ በሦስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል ወስዶ በደብር ቅዱስ አስቀመጣቸው ሲሄድም ምግቡን እንዲወስዱለት በገነት ያሉ አዕዋፍን አዞለት ሄዷል፡፡

አዕዋፍም በአፋቸው በእግራቸው አንድ አንድ ሁለት ሁለት ዘላላ እየወሰዱ 12 ዋሻ ሞሉለት፡፡ ከአዕዋፍም አብርል አዝርል የሚባሉ አዳም በገነት ሳለ ቋንቋቸውን ለምዶ ነበርና እንሂድ ሲባባሉ ፀምቶ ሠጡለት ፍሬ ስንቁን ይዞ እየሮጠ ተከትሏቸው እኩል ከእግረ ገነት ደረሰ፡፡ ዳሩ ግን ገነት በእሳት ተቀጽራ ነበርና እነሱ ላይ ላዩን በረው ሲገቡ እርሱ መግቢያ አጥቶ ከዚያው ቆሞ ቀረ፡፡ ዲያብሎስ

አይቶት ደገሞ እዚህ ምን አመጣው? እንደውም ካልገደልኩት አላርፍም ብሎ ቤት የሚያህል ደንጊያ አንስቶ ሜነበት:: ወተደብተረት ይእቲ ዕብን ላዕለ ርዕሰ አዳም ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ -ይላል ደንጊያው እንደ ድንኳን ሆናለት ሦስት ቀን ሦስት ሌት ቆይቶባታል:: በሦስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል አንሥቶለት የያዘውን ፍሬ በደሙ ለውሶ መሥዋዕት አቀረበ:: ጌታም በገሙስ ዕለት ወበ መንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅከ ውስተ መርሀብከ ወእትቤዘወከ በደሙ መስቀልየ ወበሞትየ ብሎ 5500 ዘመን ሲፈጸም የልጅ ልጁ ከምትሆን ከእመቤታችን ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቶታል:: ... ቀሌምንጦስ

አዳም ይህን ተስፋ ካገኘ በኋላ እያረሰ በምድረ ኤልዳ ተቀመጠ:: ኩፋ 5:6 ሚስቱ ሔዋንን በግብር አወቃት፤ ቃኤልን ወለደችለት፤ በሁለተኛ ሩካቤ አቤልን ወለደችለት:: መገደል በቃኤል መሞት በአቤል ተጀምሯል:: ዘፍል 1 ገጽ 130 ተመልከት:: አዳም በአቤል ሞት ምክንያት 4 ሱባዔ ዘመን አዝኗል:: ኩፋ 5:12 ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ናሁ ወልድከ አቤል ተገለመ ዕዋየ ለከት እለው፤ ከንዘሉ ተጽናና ወንድ ልጅም ተወለደለት ስሙን ሴት አለው:: ምትክ ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ አዳም የ230 ሔዋን የ215 ዓመት ዕድሜ ሰዎች ነበሩ:: ከሴትም በኋላ ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን ወልደዋል::

ጊዜ ዕረፍቱ ሲደረስ አዳም ልጁ ሴትን ባልሞት እንድባርካቸው ልጆችህን አምጣ አለው:: አምጥቶ በፊቱ አቆማቸው:: ዓይን ዓይናቸውን እያየ ያለቅስ ጀመር:: እነርሱም አባታችን ከእኛ እንዴት ትለያለህ እንዴትስ ከአፈር ትገባለህ? እያሉ አለቀሱ:: እግዚአብሔር ይባርካችሁ ብሎ ባረካቸው መረቃቸው:: ሴትንም ልጄ ፈጣሪህን እንዳታስቀይም እወቅ ቃኤል በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነውና አንተ ከርሱ ልጆችህም ከልጆቹ እንዳትተባበሩ ተጠንቀቅ ኋላ ግን ምድር በንፍር ውኃ ትጠፋ ዘንድ አላትና ሥጋዬን በቤተመዛግብት አስቀምጠው ብሎት በ930 ዓመቱ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ዐረፈ:: ዘፍ5:5

ሥጋውንም መላእክት እያሳዩአቸው ሽቶ ቀብተው ገንዘው ዕጣን ወርቅ ከርቤውን አድርገው በቤተመዛግብት አኑረውታል:: በጥፋት



ውኃ ጊዜም ኖኅ ከመርከብ ይዞት ገብቷል:: ሲወጣም ይዞት ወጥቶ ለሴም ሰጠው:: ሴምም ከዛም ወገን የተወለደ መልከጼዴቅን ከወንድሞቹ አስናብቶ በገዳከል ምድር ቀራንዮ አስቀብሮታል:: ጌታም በቀራንዮ መሰቀሉ ቅሉ በዚህ ነው::

• የአዳም መቃብር ሕይወቱ ከ5500 - 4570 ዓ.ም ነው::

ሰላም ላንተ አዳም ወደ ፍጥረታት
ለአምሳሉ ልጁ ነህ ለሰዎች አባት::
ከሁሉ አስቀ አምላክ በወደህ
ስለርስት በአምሳሉ ሰጠህ
የሕይወት አስተንፋስ እና ዕውቀ
በፍጥረት ሁሉ ላይ አሠለጠነው::
ለትዕዛዙ እንቢ አለመስማት ከቶ
ዕንወጠን እርቀው ለመናገር ስቶ
ወደ ሕይወት ወለሰ እርሱ ሞትን ሞቶ::
እናታችን ሔዋን ደድረሽ ሰማታ
የሞት ሁሉ እናት ነሽና አሰኝታ::
ዕገዛን ሰትቶሉ ዕውት ፍሬሽ
እኛ ድንግልን በመወለድ ከበርሽ::

የድካታችን ምንጭ ናትና ልጅሽ
ምክንያት ሴሊት መጣል ተረልኝ::
ሞትና መተብር ሰለው የመጣው
አዳምና ሔዋን በለሰ ሰለተው ነው
ለገል እርገም ከእንገዚህ እንተው::
እነርሱም አለቃለው ገለሉ ተቀተው::
ድኾው ሰብረር አሉ በአምላክ ደምድነው::
ሞትል ደመቀበን ሞትና መቅበርን
የኛው ማማማም ነው ሰለለ ኃጢአትን
ለሰለሁ ተዋረን ሔዋን ከአዳም
በሕይወት ለመኖር በገያልና ዓለም
ንሴሐ እንገባ እንሸርል ሳምም::

ማቴ 3:2 ሉቃ 13:10 ፣ 15: 11

## ለ- ዳግማይ ትንሣኤ (ፈጸምን)

ዳግም ትንሣኤ የበዓላት ሁሉ ርእሰ ቀንም ነው:: ስለሆነም ቤተክርስቲያን እስከ ዳግም ትንሣኤ ድረስ ያለውን ጊዜ ዘመነ ትንሣኤ ብላ የሰየመችው ሲሆን በተለይ ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ሰማንተኛው ቀን እሑድ ድረስ ያሉትን ዕለታት ልዩ ስያሜ ሰጥታ እንደ አንድ ዕለት ታከብራቸዋለች::

የዕለታቱም ስያሜ እንደሚከተለው ነው

ሰኞ - አብርሃም
ማክሰኞ - አልዓዛር
ኀሙስ - አዳም
ዓርብ -
ቅዳሜ - አንስት
እሑድ - ፈጸምን (ዳግማይ ትንሣኤ)

በዚህ ዕለት የሚደረሰው ምስጋና ከዕለተ ትንሣኤ ምስጋና ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡ ታሪኩም - ጌታ የተነሣ ዕለት ደቀመዛሙርቱን ከዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለክሙ ባዕቸው ጊዜ ከአስራ አንዱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ የተባለው ዲዲሞስ ከነርሱ ጋር አልነበረም፡፡ ሲመጣ ርኢናሁ ለእግዚእነ ጌታን አየነው አሉት፡፡ ሑሩ ወመሀሩ እንደሚላቸው ያውቃልና እነሱ አየን ብለው ሲያስተምሩ እኔ ሰማሁ ልል ነውን ብሎ እመኢርኢኩ አደዊሁ ወአገሪሁ ኀበ ቀነውዎ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን ካላየሁ - ወእመ ኢወዲይኩ አጽባእትየ ውስተ ቅንዊቲሁ ወእመ ኢያባእኩ እዴየ ውስተገቦሁ ወኢገሠሥኩ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን በጦር የተወጋ ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም አለ፡፡

ወእምድኅረ ሰሙን መዋዕል ይላል በስምንተኛው ቀን ቶማስ ባለበት በዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለክሙ አላቸው፡፡ ቶማስ ጎኑን ካልዳሰስኩ ብሎ ነበርና ሀብ እዴከ ወአብእ ውስተ ገቦየ ወገሥሥ እጅህን አምጣና ወደጎኔ አግብተህ ዳሰኝ ወኢትኩን ናፋቄ አላ እመን እመን እንጂ አትጠራጠር አለው፡፡ ቢዳስሰው ከእሳት እንደገባ ጅማት ኩምትርትር አለ፡፡ እግዚእየ ወአምላኪየ ጌታዬ አምላኬ ሆይ አለ፡፡ እስመ ርኢከኒሁ አመንከኒ ብታየኝ አመንክ ብፁዓንስ እለእንዘ ኢይሬእዩኒ የአምኑኒ - ንዑዳን ክቡራንስ ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው፡፡ ብሎ ፈወሰታል፡፡ ይህች ጎኑን የዳሰሰች እጁ ዛሬም ሕያዊት ሁና በሕንድ አገር ከታቦቱ ጋራ ትኖራለች፡፡ በዓመት በእመቤታችን በዓል (በአስተርእዮ) ሲያጥኑ ሲገቡ ቀድሳ ታቆርባለች፣ የሚሾመውን ወጥታ ቀኝ እጁን ትይዘዋለች፡፡ እንዲህ እያለች እስከምጽአት ድረስ ትኖራለች፡፡ ትር፡ ወን

## ለ. ማርያም ግብጻዊት

ሀገሯ እስክንድርያ ነው፡፡ አባት እናቷ ሲያርፉ በደግነታቸው ይቀና የነበረ ሰይጣን እርሷን ፍቅረ ዝሙት አሳደረባት፡፡ 27 ዓመት በሴት አዳሪነት ኖረች፡፡ ጌታ ሊያድናት ቢወድ ማስተዋልን ሰጣት፡፡ አንድ ቀን ቅዱሳን መካናትን እጅ ሊነሱ የሚሄዱ መንገደኞች አግኝታ ተከተለቻቸው፡፡ መርከብ ሲሳፈሩ እርሷ ገንዘብ አልነበራትምና ሥጋዋን ፈቅዳለት ተሳፍራ ተሻገረች፡፡

ጎልጎታ ከመቃብር እግዚእ ምእመናን ሲገቡ እርሷ መግባት ተሳናት፡፡ ከስዕለ ማርያም ሥር ወድቃ ስታለቅስ ቆይታ እመቤታችን ዋስ ሆናት ገብታ ተሳለመች፡፡ ደስ ብሏት እመቤቴ በሥጋ እንደተዋስሽኝ በነፍሴም ዋስ ሁኚኝ እድን ዘንድ የማደርገውን አስታውቂኝ ብላ ተማፀነች እመቤታችንም በስዕሏ አድራ ከሰው ተለይተሽ ገዳመ ዮርዳኖስ ገብተሽ ኑሪ አለቻት፡፡



ከመንገድ ወጥታ ስመ እግዚአብሔር ጠርታ ጥቂት ሣንቲም አገኘች፡፡ ሁለት ኅብስት ገዝታ ያን ይዛ ዮርዳኖስን ተሻግራ የሰው ድምፅ ከማይሰማበት በረሀ ገብታ 47 ዓመት ኖረች፡፡ የያዘችው ሁለት ኅብስት ምን በልታ ትኖር ነበር? ቢሉ በበረሀ ምን ይገኛል እንደበግ ሣር ነጭታ ውኃ ተጎንጭታ ትኖር ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ዞሲማስ የተባለ መነኮስ እመቤታችን አነሳስታ ልካው ቢሄድ ከሩቅ አያት፡፡ ዕርቃኗን ነበረችና ተነሥታ ሮጠች፡፡ እሱም በረከት ቀረብኝ ብሎ ተከትሏት ሮጠ፡፡ ጥቂት ከተሯሯጡ በኋላ መለስ ብላ አ ዞሲማስ ለእመፈቀድከ ከመ ትትናገር ምስሌየ ውግር ሊተ ጸርቀ ዘእትከደን ቦቱ እስመ አነ ዕርቅት - ከኔ ጋር ልትነጋገር ከወደድህ ዕርቃኔን ነኝና የምለብሰው ጨርቅ ጣልልኝ አለችው፡፡ መደረቢያውን ጣለላት፡፡ ያን ለብሳ መጥታ እጅ ተነሳሱ፡፡ ከዚህ በኋላ ታሪኳን ነግራ ለዓመቱ ሥጋውን ደሙን አምጥቶ እንዲያቀብላት ተማጽና ተሰናበተችው፡፡

በዓመቱም ሥጋውን ደሙን አምጥቶ አቀበላት፡፡ የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ መጥተህ ጠይቀኝ አለችው፡፡ ቢሄድ ዐርፋ ሥጋዋን ግሩም አንበሳ ሲጠብቀው በራሷም አ ዘሲማስ ቅበራ ለማርያም - ቅበራት የሚል ተጽፎ አገኘ፡፡ እሱ ሥጋዋን ሲገንዝ አንበሳ መቃብሯን ቆፍሮለት ቀብሯ ተመልሷል፡፡ <u>"አባዕኩ ለኪ ስብሐተ ተአምር ዘይሤለስ በበኅምሳ፣ ሀየንተ ጽጌያት ኅምሳ ለሰዕልኪ አክሊለ ርዕሳ፣ ተወኪፈኪ ማርያም እንጽሕኒ እምአበሳ፣ ከመ እንጻሕኪያ ለግብጻዊት እምርኩሳ፣ እስከመቃብራ ከሪየ ዘይጥሀር አንበሳ፡፡" እንዳለ ደራሲ</u>

* የነበረችው በ5ኛው ም.ዓ ድ፡-ል፡-ክ ነው የቤ/ክ መዝ. ቃ አማርኛ፣

ግብጻዊት ማርያም ባሕታዊት እናት<br>
የድንግል ማርያም ወዳጅ ነሽ በእውነት<br>
መንደላቀቅ ሳለ በዓለም ተደሰቶ<br>
በበረሀ መኖር ከሰው ተለይቶ<br>
ለአዳም ልጅ በምድር ይቻል ይሆን ከቶ?<br>
በእምላክ ቸርነት ግን ላንቺ ተችሎሽ<br>
አርባ ስምንት ዓመት በበረሀ ኖረሽ<br>
መራር የንስሐ ዕንባ እያነባሽ፡፡

ጠላት ዲያብሎስን ከናሚካሪው<br>
በንስሐ ጦርሽ አንበረከክሽው<br>
የዓለም ሀሳብንም አንኮታኮትሺው<br>
የሰው አዋራጁ ነወና ጣዪው<br>
የቀድሞ በደልሽ በዕንባሽ ተደምስሳ<br>
መቃብር ቆፈረ ግሩሙ አንበሳ<br>
የኛም ኃጢአታችን ይፋቅልን ዘንድ<br>
በንስሓ እንቅረብ ወደ ወልድ ዋሕድ፡፡

* "ንስሓስ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ፡፡ ወለዘማኒ ከመ ድንግል"
"ንስሐ የበደለውን ያልበደለ፡፡ አመንዝራውንም እንደ ድንግል ታደርጋለች"
አረጋዊ መንፈሳዊ ድር 26 እና 29

## ሚያዝያ 7 - ዕረፍቱ ለኢያቄም ጻድቅ

ዮናኪር፣ ሳዶቅ ተብሎም ይጠራል።

ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ከቤተ ዳዊት ነው። አባቱ ቅስራ ይባላል። ከነገደሌዊ ወገን የሆነች ሐናን አግብቶ በይሁዳ ከተማ ይኖር ነበር። ነገር ግን ሐና ዕፁተ ማኅፀን ሁና ልጅ አጥቶ ብዙ ዘመን ሲያዝን ኖሯል። ኋላ ግን ጌታ ኀዘኑን አይቶ ጸሎቱን ሰምቶ ልምላሜ ሙቀት ከተለየው በኋላ በብስራተ መልአክ እመቤታችንን ሰጥቶታል። እመቤታችንም በተወለደች ጊዜ ታድሶ እንደ መላ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ሕማም ድካም ሳይሰማው ኖሮ በዚህ ዕለት ዐርፏል። ያረፈውም እመቤታችን ገና በቤተመቅደስ ሳለች ነው። ነገ ማር

| | |
|---|---|
| ኢያቄም ይድረሰህ የጸጋ ምስጋና | ጌታም ጽናትህን ትዕግሥትህን አይቶ |
| የጽድቅ የትሩፋት አበጋዝ ነህና። | አስደሰተህ ላንተ የልጅ እናት ሰጥቶ። |
| ፍቅርና የዋሃት ትዕግስት ጓደኞችህ | የአምላክን እናት ለመውለድ የበቃህ |
| ኀዘንህን ሁሉ አስወገዱልህ። | ኢያቄም ሆይ አንተስ የጻድቃን ራስ ነህ። |
| ጸልየህ ተስዕህ ባይሰማህ ለጊዜው | ልክ እንደኢያቄም እንደደገ አባት |
| ከቶ አልሞከርከም አምላክን ልትከዳው | ጸንተው ደጅ ቢጠኑት ያስመኝታት |
| በትዕግስት ኖርክ እንጂ እየተማጸንከው | ፈጣሪ አይነሳም የጽቅን በረከት። |

ሉቃ 18፥7 ሉቃ 21፥36

## ሚያዝያ 15 ፀዓተ ነፍሱ ለዮሐንስ መጥምቅ

ዜና ዕረፍቱ በክፍል 1 ገጽ 15 እንደተገለፀው ንጉሥ ሄሮድስ ኢይከውነከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ ብሎ ቢገሥፀው በሰይፍ አስመትቶታል አንገቱም ከንፍ አብቅላ አ ሄሮድስ ኢይከውነከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ ብለው በራ ሄዷለች። በዚህ ጊዜ ጌታ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በደብረዘይት ነበርና ቀርባ ስገደችለት ባለሽበት ፀንተሽ አስተምሪ አላት። 15 ዓመት አስተምራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች። * ያረፈችው 945 ዓ.ም ነው።



## ሚያዝያ 23 - ዕረፍቱ ለቅዱስ ማር ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

ጊዮርጊስ ማለት ኮከብ ብሩህ፣ ሐረገወይን፣ ፀሐይ ማለት ነው። [illegible] በልዳ እንደሆነ ሀገሩ ልዳ ነው። አባቱ [illegible] (አንስጣስዮስ) ይባላል። በልዳ መስፍንነት ተሹሞ ይኖር ነበር። እናቱም ቴዎብስታ (አቅሌስያ) ትባላለች። ማርታ ድስያ የሚባሉ እኅቶች ነበሩት።

አሥር ዓመት ሲሆነው አባቱ ሞቶ ሌላ መስፍን ተሾመ ደግ ክርስቲያናዊ ነበርና ከቤቱ ወስዶ እያስተማረ አሳደገው። እርሱም ፈረስ መጋለብ ቀስት መወርወር ለመደ። [illegible]

እንዲህ እያለ አድጎ ሃያ ዓመት ሲሞላው መስፍኑ የ15 ዓመት ቆንጆ ልጅ ነበረችውና እርሷን አጋብቶ ሀብቱን ወርሶ ይኑር ብሎ ድግስ ሲያሰናዳ ሳለ ጌታ ቅዱስ ጊዮርጊስን ለዚህ አላበቃውምና የመስፍኑን ነፍስ ወሰደ። እርሱም ገንዘቡን ወርሶ ወደ ቤሩት ሄደ። [illegible]

[illegible]

አላቸው፡፡ ይህስ አይሁን ባይሆን ከገደልከው በአምላክህ እናምናለን አሉ፡፡ ከከተማ አውጥቶ በጦር ወግቶ ገደለው፡፡ ይህን አይተው በእግዚአብሔር ስም አምነው ተጠምቀዋል፤ አውሬውን ከገደለበትና ከመሀል ከተማ ሁለት አብያተክርስቲያን ሠርተዋል፡፡

በዚህ ጊዜ የፋርሱ ንጉሥ ዱድያኖስ ሰባ ነገሥታት ሰብስቦ ሰባ ጣዖታት አቁሞ ይሰግድ ያሰግድ ነበረ፡፡ የአባቴን ምስፍና ተቀብዬ ልምጣ ብሎ እጅ መንሻ ይዞ ብላቴናቹ አስከትሎ ቢሄድ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ ብሎ አውጆ ሕዝቡም ለጣዖት ሲሰግዱ አገኘ፡፡

ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናዒ ነውና አዘነ፡፡ ወርቅ ብሩን ለነዳያን መጽውቶ ብላቴናቹን አሰናብቶ ነገሥታቱ ከተሰበሰቡበት ገብቶ እኔ ውእቱ ክርስቲያናዊ ወእአምን በእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ፡፡ ዱድያኖስ ሦስት ዓመት ሙሉ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ ሲል እንዲህ ያለኝ አንድ እንኳ የለም፡፡ ለመሆኑ የማን ልጅ ነህ? ሀገርህስ ዴት ነው? አለው፡፡ ከኔ ጋር ምን ኅብረት አለህና አባቴን ሀገሬን ትጠይቀኛለህ? አለው፡፡ ሌሎች ያወቁት ነበርና የዞሮንቶስ መስፍን ልዳ ልጅ ነው አሉት፡፡ አንተማ የእኛ ነህ በ10 እህጉር ላይ እሾምሃለሁ የኔን አምላክ አጵሉንን አምልክ አለው፡፡ ሹመት ሽልማትህ ላንተ ይሁን እኔ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስን አልክድም አለ፡፡ ተቆጥቶ በእንጨት አሰቅሎ ሥጋውን በመቃጥን አስተፈተፈው፡፡ ረጃጅም ችንካሮች ያሉበት የብረት ጫማ አጫምቶ ሂድ አለው፡፡ ችንካሮቹ እግሮቹን በሳስተው ወጡ ደሙ እንደ ውኃ ፈሰሰ፤ አጥንቱ ደቀቀ፡፡ መሄድ አቅቶት አጎንብሶ ሄዷል፡፡ <u>"ሰላም ለመከየድከ በአሣዕነ ሐፂን ዘተጸዕረ፤ እስከነሠርከ ድቡተ ሶበ ሰእንከ ሰጊረ"</u> እንዲል፡፡ መከራው ቢፀናበት እ እግዚእየ ኢትግድፋ ለነፍስየ እስከ አስተኀፍር ለዝንቱ ዕልው ይህን ከሀዲ እስካሳፍረው ድረስ ነፍሴን አትውሰድ ብሎ ወደጌታ አመለከተ፡፡ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ፈወሶታል፡፡ ሄዶ ኀፈር አ ዕልው አለው:: በሰባ ችንካር አስቸንክሮ በእሳት አስተኩሶ አናቱን በመዶሻ አስቀጥቅጦ በሆዱ ላይ የደንጊያ ምሰሶ አሳስሮ እንዲያንከባልሉት አደረገ፡፡ የማይሞት ሆነ ሥጋውን በመጋዝ አስተልትሎ ጨው ነሰነሰበት፤ ሥጋው ተቆራርጦ ወደቀ፡፡ ከዝግ ቤት ትተውት ሄዱ፡፡ በመንፈቀ ሌሊት ጌታ በእጁ ዳሶ አስነስቶ ገና ስድስት ዓመት ስለ ስሜ ትጋደላለህ ሦስት ጊዜ ትሞታለህ፡፡ በአራተኛው ታርፋለህ አለው፡፡

ሲነጋ ከንጉሥ ሄዶ አንተ ከሀዲ አፈር አምላኬ አዳነኝ አለው፡፡ በሥራይ የሚያቸንፍልኝ ባገኝ ቤቱን በወርቅ እመላለታለሁ አለ፡፡ አትናስዮስ የተባለ መሠርይ መጥቶ ንጉሥ ሺህ ዓመት ንገሥ ጠላትህ ይደምሰስ አለው፡፡ በምን እውቀዋለሁ አለው፡፡ ላም አስመጥቶ በጆሮዋ ቢያንሾካሾክባት ከሁለት ሰንጥቃለች፡፡ ለጊዜው እርሱንም እንዲህ የሚያደርግለት መስሎት ደስ



አለው፡፡ ሆድ በጥብጦ አንጀት ቆራርጦ የሚገድል መርዝ ቀምሞ አስማተ ሰይጣን ደግሞ ሰጠው፡፡ ስመእግዚአብሔር ጠርቶ ቢጠጣው እንደጨረቃ ደምቆ እንደአበባ አሸብርቆ ተገኝቷል፡፡ ጠንቋዩ ማረኝ ብሎ ከእግሩ ወደቀ፡፡ መመለሱን አይቶ የቆመባትን መሬት በእግሩ ረግጦ ውኃ አፍልቆ ወደጌታ ቢያመለክት ሐዋርያው ቶማስ በአካለ ነፍስ መጥቶ አጥምቆት ጥር 23 ቀን አንገቱን ለሰይፍ ሰጥቶ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

እሱን ግን በመንኮራኩር አስፈጭቶ ከጥልቅ ጉድጓድ ጥሎት ደንጊያ አትሞበት ተመለሰ፡፡ ጌታ የተፈጨ ሥጋውን በእጁ ዳሶ መንፈሱን መልሶ አንሥቶታል፡፡ እግረ መንገዱን አሕዛብን እያስተማረ ከንጉሥ ቀረበ፡፡ አንተ መስሀት አፈር አምላኬ ከሞት አነሳኝ አለው፡፡ ተበሳጭቶ በብረት አልጋ አስቸንክሮ ከበታቹ እሳት አንድዶበታል፡፡ እሳቱም ደሙ ቢነጥብበት አልም ድርግም ብሎ ጠፍቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ክርስቶስ አምላክ ነው ትላለህ ምን አድርገህ ታሳየናለህ? አሉት የሰመለሙትን ዕፅው አድርቆ የደረቁትን አለምልሞ፤ ከሞቱ 430 ዘመን የሆናቸው ሙታንን አሥነስቶ አሳይቷቸዋል፡፡ በረሀብ በጽም ይሙት ብሎ የሚላስ የሚቀመስ ከሌላት ደኃ መበለት ቤት እንዲታሰር አዘዘ፡፡ ከምሶሶው ጋር አሠሩት፡፡ ራበኝ አብዪኝ አላት፡፡ የምትሰጠው ብታጣ ወደደጅ ወጣች፡፡ ስትመለስ የታሰረበት ሙሰሶ ለምልሞ 15 ክንድ ያህል ከጣራው አልፎ፤ ካጠገቡ እንጀራ የተመላ መሶብ ተቀምጦ እንሉ ዘይቱ በየዕቃው መልቶ አገኘች፡፡ ናሁ አምላክ ገሊላውያን ተመሲሎ ሰብእ ወረደ እምሰማይ ወቦአ ውስተ ቤትየ የገሊላውያን አምላክ ሰው መስሎ ከሰማይ ወርዶ ከቤቴ ገብቷል፡፡ አለች፡፡ አገልጋዩ እንጂ እርሱን አይደለሁም አላት፡፡ ጆሮው የማይሰማ ዓይኑ የማያይ እፉ የማይናገር ሐንካስ ልጅ ነበራት፡፡ ሰው እንዳያየው ሸሽጋ ታኖረው ነበር፡፡ አምጥታ ጭኑን ብታስነካው ዓይኑ በርቶለታል፡፡ ጌታዬ ጆሮውንም አፉንም እግሩንም ፈውሰው አለችው፡፡ ይህ ጊዜው ገና ነው አላት፡፡ እርሱንም ቅዱስ ሚካኤል ከእስር ፈቶት መበለቲቱን ከነልጇ አጥምቆ እያስተማረ ወደንጉሥ ተመለሰ፡፡

ንጉሥ ዱድያኖስ የሚያደርገው ጠፋው፡፡ በመንኮራኩር ፈጭታችሁ ደብረ ይድራስ ወስዳችሁ ንዙት አለ፡፡ ፈጭተው ወስደው ቢነዙት ሥጋው ያረፈበት ሣር ቅጠሉ ደንጊያው እንጨቱ ሁሉ ጊዮርጊስ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለእግዚአብሔር እያሉ አመስግነዋል:: ጌታም ሦስተኛ ከሞት አንሥቶታል ጭፍሮቹን ተከትሉ አምላኬ ከሞት አዳነኝ አላቸው፤ ደንግጠው ከእግሩ ሥር ወደቁ፡፡መሬቱን ከእግሩ መትቶ ውኃ አመንጭቶ ቅዱስ ዮሐንስ አጥምቋቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ንጉሥ ልሹምህ ልሸልምህ ለአጵሉን ስገድ አለው፡፡ ከሾምከኝማ ሌላ ምን እሻለሁ እሺ እሰግዳለሁ አለ፡፡ እንኪያስ እስከዛሬ ባስከፋሁህ ይቅር

ዐለኝ ብሎ ከእሌኖኝ አስጥቶ ወጣ። ንግሥቲቱ አለእስክንድርያ ትባላች። ስሙ እንዴሌዎስ ወርቶ ሊያመሰግን ስምታ ምን ማለት ነው፡፡ ይህን ምክንያት አድርጎ አስተምሮ አሳምኗታል፡፡

ሲነጋ ጊዮርጊስ ለአጽሙን ሊሰግድ ነውና ከአደባባይ ተሰብሰቡ ብሎ አዋጅ አስነገረ፡፡ ሃያ መበለት ልጇን አትፋ ሁለት ይሁን ጊዮርጊስ ለአጽሙን አይሰግድም እያለች ታለቅስ ነበር፡፡ ልጆቿን ከዚህ አትሩጡ አላት፡፡ አኖረቻቸው፡፡ ተንሥቶ መለኮቱን አድርስ አለው፡፡ ተነሥቶ ቆመ፡፡ ከቤተ ጣዖት ገብቶ አጵሎንን የክርስቶስ አገልጋይ ጊዮርጊስ ይጠራሃል በለው አለው፡፡ ገብቶ በጠራው ጊዜ ያደረ ሰይጣን እሺ ሊቀ ወደ ሊቀ እያለ እየጮኸ ሕዝቡን ተከትሎ መጥቶ ከፊቱ ቆመ፡፡ ሕዝቡ በዚህ አንጻር እንዲህ ጆሮውን አፉን ተፈውሷል፡፡ ወደ አንተ አምላክ ነህ አለው፡፡ በመንፈሳዊ በሰማያዊ እንጂ አምላክ አይደለሁም አለ፡፡ እንዲያስ ፋታንንና አብርሃን የሠራች ምድር ትዋጥህ አለው፡፡ ምድር አፏን ከፍታ ውጣለች፡፡

ንጉሥ እንዲያደንቁለት የሰበሰባቸው ሁሉ የሚያደንቁለት ሲሆን ለብዙን ቀድ እንደ እሳት እየፈለፈለ ከእሌኖች ወጣ፡፡ ንግሥቲቱ ምን ሆንክ? አለችው፡፡ እንዲህ አድርጎብኝ አለች፡፡ እኔማ እንጂ ነገሬሽ አልነበረም ጊዮርጊስን አስክሬ ያሠቃየው አይደለምን ትምህርቱን ሰምቼ ተአምራቱን አይቼ ከክርስቶስ አይመለሰምን? አለችው፡፡ ሁኒርን ይዞ እየተተተ ወስዶ ከንጉሡ ፊት አቁሞ ፍረዱኝ አላቸው፡፡ ትቀጣ አላት፡፡ ወርቃቿን አውልቃ በሰይፍ አስመትተሽ ደሟ ጥምቀት ሆኗት ወርዳለች፡፡ “ሰላም ለኪ ንግሥት ከመሬት እንዳ ትምህርቱን አስመነ፤ ብፅዕ መጥምቀት ከደሙ ተጠመቀች ወሪሆ” እንዲል አስተማርዋን ተከትላ አርፋለች፡፡

ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው ያመኑ ብዙ የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ እነሱንም በሰይፍ አስመታቸው፡፡ እሱንም በሰይፍ ሲቀጡት ይሰውት ሲጸል መላእክት ሥጋውን ተቀብለው ከሆነ በሊልያስ ቃል ከቦታዩ ወርዶ ወሰዳቸውን የሰባት እሳት እነሆን ወዳሪያን ትዕዛዛቸው ብሎ ወርዷል እሳተ፡፡ ወዲያውም ንጉሥ ዳብር አስቀድቶ ከአፍራሽ ተቀኝቶ ሲበላ ሲጠጣ እሳት ከሰማይ ወርዶ ነደቀደቀችባቸው፡፡ ሁለቱም ገድሉን የዳረ ያዳረ፤ መታሰሩን ያደረገ፤ በሞቷ ሲተከርስቲያን ያዝ፤ በመከራ ሆኖ በደሚ የቀማው ሁሉ በሥጋው ፈርእትን በብዙ ምልዕትን የሚያገኝ ይሁን ብሎ ለምኖ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰማያት ተከፍቶ ምድር ተናወጸች፡፡ ጌታ መላእክቱን ነቢያትን ሐዋርያትን አስከትሎ መጥቶ ሰላም ለከ ኦ ፍቁርየ ጊዮርጊስ ሰላም [illegible] ማቴ 11፡11/ ያለውን እንደፈጸምከ በማህበረ ሰማዕት እምቅድሜሁ ማኅበረ ሰማዕት ሐሰ እምትድሜከ ወእምድኅሬከ



እንዲሁ ከማኅበረ ሰማዕት የሚመስለህ የሚስተካከለህ የለም” ብሎ ተናገረውን ነገርታል፡፡ ቀናርቹ ግን ይህን ሊያዩ ሊሰሙ አልታደሉምና ከወደቁበት ተኝተው ያንከራታ ነበር፤ ቀስትቦ የታዘዛችሁትን ፈጽሙ አላቸው፡፡ በሰይፍ መትተውታል፡፡ በመቁረጥም ጊዜ ደም፤ ውኃና ወተት ከአንገቱ ፈሷል፡፡ ጊዜው ዘጠኝ ሰዓት ነበረ፡፡ ዕድሜውም 27 ዓመት ነበር፡፡

ጌታም ስለ ሰባት ዓመት ተጋድሎው ሰባት አክሊላት አቀዳጅቶታል፡፡ በሰማይም ከሳ ነፍስ ማዕምንት ለእሙ ወጽአት እምሥጋ ትሰግድ ትድሙ ለሥሉስ ቅዱስ ወካዕበ ለትድበት ድንግል ወላዲትየ ወእምዝ ይሰድዋ ኀበፍቁርየ ጊዮርጊስ ከሙ ትሰግድ ሎቱ ብሎ ክብሩን ነገርለት ነፍስ ሁሉ እጅ ትነሳዋለች፡፡



ገድል ያለመለመው የወንጌል ተክል
የጊዮርጊስ ስሙ ጥዑም እምአስካል
አይደርቅ አይጠወልግ ሁሌም ያብባል፡፡
ሹመት ሽልማቱን ክብሩን ሁሉን ትቶ
ታቦር ተገረፈ ለአምላኩ ክብር ተንቶ፡፡
ኧረ እንደምን ቻለው ያን ሁሉ መከራ
ተቆልቶ ተፈጭቶ እንደእንጎል ሲዘራ፡፡

እኔስ ይጨንቀኛል ገድሉን ሳስበው
ሰባት ዓመት በገድል ይኖራል ወይ ሰው?
ዛሬስ እንኳንስ ሰው እጅግ ያሳዝናል
ግና ምንም ሳይሆን ክሩን ይበጥሳል
ሰው ጌታውን ሲክድ ለሥጋ እያወ
ጊዮርጊስ ለአምላኩ እስከሞት ታመነ
አክሊልን የሚያበሩ ደሙ ለሰው

ማቴ 10 : 39 ራእ 2 : 10

## ሚያዝያ - 27 ዕረፍቱ ለፊቅጦር ሰማዕት

ሀገሩ እንጸኪያ ነው፡፡ አባቱ ኅርማኖስ እናቱ ማርታ ይባላሉ፡፡ የቅዱስ ፋሲለደስ የእህት ልጅ ነው፡፡ ንጉሡ ኑማርያኖስ ተንባላትን ሊወጋ ሲዘምት እርሱም አብሮ ዘምቷል፡፡ በጦርነቱ ንጉሥ ሞተ፡፡ ፊቅጦር በተሰለፈበት ጠላት ድል ነሥቶ ድንበር አስፍቶ ወደከተማ ቢመለስ የንጉሡ ፈረስ አቅራቢ የነበረ አግሪጳዳ (ዲዮቅልጥያኖስ) የንጉሡን ሴት ልጅ አግብቶ መንግሥት ወርሶ አገኘ፡፡ በዚህ አዝኖ ከፋም በጎም ሳይናገር ብዙ ጊዜ ተቀመጠ፡፡ ኋላ ግን ዲዮቅልያኖስ አብያተ ጣዖታት ይትራኀዋ ወአብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ ብሎ ሃይማኖት ሲያስክድ ለጣዖት ሲያሰግድ የወንድሞቼን መንግሥት መንጠቁ አንሶት ደግሞ እንዲህ ይለናልን ብሎ ሊጣላው ሰይፍ መዞ ቢሄድበት ሸሽቶ ወደማጀት ገባ፡፡ እርሱንም ቅዱስ ፋሲለደስ ስለ ክርስቶስ ልንሞት እንጂ ልንገድል አይገባም ተው አለው፡፡ ንጉሥም በአማላጅ በአጓዳጅ ታረቀው፡፡
እሱም እጁ ከምጽዋት እንደበቱ ከጸሎት ሳይለይ ሲኖር ቴዎድያዳ ከሁለት ልጆቿ ጋር ክርስቶስን አልክድም ለጣዖትም አልሰግድም ብላ በሰማዕትነት ሞተች፡፡ ንጉሥ ቀብር ከልክሉባት ሥጋዋ ከአደባባይ ወድቆ ዋለ አደረ ይህ ፊቅጦር ከወደቁበት አንሥቶ ቀበራቸው፡፡ መሳፍንቱ በዚህ ምክንያት ከንጉሥ አጣሉት፡፡ ጠርቶ ምነው እንዲህ አደረግህ አለው የወደቀን ማንሳት የሞተን መቅበር ምን ጥፋት አለው ይልቁንስ አንተ እስከመቼ እንዲህ ስትል ትኖራለህ? አለው፡፡ ወገኖቹን ፈርቶ በድብቅ አፋን እንደፈረሰ አስለጉሞ ወደ እስክንድርያ አጋዘው፡፡ ሹሙ ሀርሜኔዎስ ራሱን እስኪስት ድረስ አስገረፈው፡፡ ሥቃዩ ቢጸናበት ወደጌታ አመለከተ፡፡ የታዘዘ መልአክ በአካለ ነፍስ ወስዶ ጌታ ያዘጋጀለትን መካነ ዕረፍት አሳየው፡፡ ጌታ እንጂ ሑጥቁት ሀማር ብዙ ክቡር በአንድ ሞት የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣልና ብሎ በጥብዓት የሚጋደል ሆነ፡፡ ያም በደንጊያ እስወግር በእሳት አስተኩሶ የማይሞትለት ቢሆን ወደ እንዲናው ላከው፡፡ ቢያሥሩት ተፈትቶ ቢገድሉት ተነሥቶ ያገኙታል፡፡ በችንካር ቸንክረው ሰቅለው ተዉት፡፡ ይህን ታይ የነበረች የ15 ዓመት ብላቴና እሰይ እሰይ እልል እልል አለች፡፡ ምነው ለሞተ ሰው ዋይ ዋይ ይባልለታል እንጂ እልል ይባላልን አሏት፡፡ መላእክት ሰማያዊ አክሊል ሲያቀዳጁት እየሁ አለች፡፡ እንግዲህማ ብዙዎችን ሲያምንብን አይደለምን ብለው በሰይፍ መትተውታል፡፡

• በ4ኛም. ዓድ፦ል፦ክ መጀመሪያ ላይ ነው

ፊቅጦር ምዕመኑ ለአምላክ ክርስቶስ
ተወካፌ ሕማም አርክ ጊዮርጊስ
ከኃጥአን ጋራ ከሚኖር ተዋዶ
መሞትን መረጠ ስለጽድቅ ተሰዶ፡፡
እንደፈረሰ በሐብል ቢለጎም አፋን
በእምነቱ ጽናት መሰከረልን
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን፡፡

አመቻችቶ ሰጥቶ ለችንካር እጆቹን
እሰቦ እለቀሰ የጌታ ሥቃዩን
ሰለሰው ልጅ ብሎ የተቀበለውን፡፡
ሞቱ ለጻድቅ ሰው ነውና ሕይወቱ
መላእክት ዘመሩ ጻድቃን ተደሰቱ
እልል እልል አለች ሕፃኗም ከፊቱ

መዝ 115፡



## ሚያዚያ 30 - ዕረፍቱ ለማርቆስ ወንጌላዊ

ማርቆስ ማለት ንህብ፣ አንበሳ፣ ካህን ማለት ነው፡፡ ንህብ የተባለ ንህብ ሁሉን እንድተቀስም እርሱም አስቀድሞ ከጌታ ኋላም ከሐዋርያት ስለተማረ ነው፡፡ አንበሳም የተባለ አንበሳ ላህምን እንደሚሰብር እርሱም በአምሳለ ላህም በአምሳለ ጣዖዋ ተሠርተው ሲመለኩ ነበሩ የግብጽን ጣዖታት አጥፍቷልና ነው፡፡ ካህን የተባለም ወአምጽኡ ማሬ ዘድዮስ ባለው ሄዶ ነው፡፡ ሐዋ 14፡13 ቀዳሚ ስሙ ዮሐንስ ነው፡፡ ሐዋ 12፡12 ቁጥሩም ከ72ቱ አርድዕት ነው፡፡ አባቱ አርስጦቦሉስ እናቱ ማርያም ይባላሉ፡፡ ይህች ማርያም ሑጌታ ያመነች ወንጌልን የተቀበለች ጌታም ካረገ በኋላ ቤቷን ለሐዋርያት ቤተጸሎት አድርጋ የሰጠች እነርሱንም በተልዕኮ ያገለገለች ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ ናት፡፡ ሐዋ 12፡12

ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያትን እየተከተለ ይማር ያገለግል ነበር፡፡ በርናባስንና ጳውሎስን ተከትሎ አንጾኪያ ወርዶ አስተምሯል፡፡ ሐዋ 12፡25

ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ተከትሎ ሮም ወረደ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ከፍጹምነት መድረሱን አውቆ ጵጵስና ሾሞ ከሀገረ ስብከቱ ግብጽን ክፍሎ አስተምር ብሎ ሠጠው፡፡ እሱም ወደ ግብጽ ሲሄድ ከከተማው በር ሲደርስ የጫማው ጠፈር ተበጠሰበት፡፡ አንያኖስ የሚባል ጫማ ሰፊ አግኝቶ ስፋልኝ ብሎ ሠጠው፡፡ ሲሰፋ እጁን ወግቶት ኢስ ታኦስ ብሎ ጮኸ አሐዱ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ የጠራኸውን ታውቀዋለህን አለው፡፡ ሲሉ ሰምቼ እንጂ ያስተማረኝ የለም አለው፡፡ ፈቃዱን አይቶ አስተማረው፡፡ ከነቤተሰቦቹ ከነጎረቤቶቹ አምኖ ተጠምቋል፡፡

"የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ" እንዲሉ አንያኖስን ጳያሔ ፍኖት አድርጎ ያስተምር ጀመር፡፡ ሕዝቡም ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አመኑ ተጠመቁ፡፡ ካመኑም ዘንድ ጣዖታቱን አፈራርሰው አብያተ ክርስትያናት ሠርተዋል፡፡
ነነውተ ጣዖቱ በጠላትነት ተነሱበት፡፡ ምዕመናን አባታችን ልናጣህ አንሻምና ቀጣቸው እስኪበርድ ወደሌላ ሄደህ ቆይ አሉት፡፡ እረኛ የሌለው መንጋ እንዳይሆኑ አንያኖስን ኢጲስቆጶስ ልጆቹን ቄስ ዲያቆን አድርጎ ሹሞላቸው በባርቃና በአቅራብያዋ ባሉ 5 አህጉር እየሰበከ ቅዱስ ጴጥሮስን ለመጠየቅ ወደሮም ሄደ፡፡ ከዚያ ሆኖ ወንጌሉን በልሳነ ሮማይስጥ ጽፎታል፡፡ ዘመኑም በአብነት መጻሕፍቶቻችን ጌታ ካረገ 11ኛ ሲፈጸም 12ኛ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሳር በነገሠ በ4ኛ ዓመት (45-46 ዓ.ም) ነው፡፡

በመዝገበ ቃላት ግን በ60 ዓ.ም ተብሎ ተጽፏል።

የቲት ዓመታትን ቆይቶ ቢመለስ ምእመናን በዝተው አገኘቶ ደስ አለው ገበሬ የዘራው በትሉ የተከለው እድቶ ሲያይ ደስ እንደሚለው በግል ትጉሔን ከርሱ ጋር ሲያከብር እኒያ ዓላውያን መመለሱን ሰምተው ሊጣሉት መጡ ምእመናንም አባታችን ሽሽ አሉት ኖላዊ ሔር ይሜጡ ነፍሶ በእንተ አባግዒሁ ዮሐ 10:11 እንዲል መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጉቹ ይሰጥ የለምን አይሆንም አልሸሽም አለ። እንደ ላም በአንገቱ ገመድ አስረው በረሀ ለበረሀ ሲጉትቱት ዋሉ። ሥጋው በእሾህ በጋሬጣ ተበሳ። ወደ ጌታ ቢያመለክት ለርሱ ተገልጾ ሥቃይህን አይቼ ልመናህን ሰምቼ ላረጋህ መጣሁ። ስለ ተቀበልከው መከራ ክብርህን ከ12ቱ ደቀመዛሙርቴ አንድ አደርጊሃለሁ። በስምህ የተማጸነን እምርልሃለሁ። ብሎ ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ በቃሉ አቅርንት በስብሐት መላእክት አሳርጓታል። በዚህ ጊዜ የሰባ ዓመት አረጋዊ ነበር። ዘመኑ እንደአብነት መጽሐፍቶቻችን ተቀውዲዮስ ቀሣር በነገሠ በ11ኛ ዓመት እንደ መዝ ቃላ ግን በ67 ዓም ነው።

እኒያም ሥጋውን እናቃጥላን ብለው እንጨት ሲረበርቡ ዝናብ ሲያርከፈክፍ ታላቅ ነጉድጓድ ሆነ ምድር ተናወጸች ወሐይም ብርሃኗን ከለከለች ያን መጥበን ብለው ሸሽተዋል ኋላ ግን ምእመናን ብርሃን መብራት ተከቦ አግኝተው ተብረውታል። ሰላም ለማርቆስ ለማርያም እጓለ [illegible] ከመጸብሐ እመ እውእቱ ፈቀደ ለእሳት [illegible] መብረቅ ለሥጋሁ ከለላ እንዘ አርከ፤





# ምዕራፍ 3

## ግንቦት 1 ልደታ ለማርያም እግዝእትን

እመቤታችን በፈቃደ አምላክ በብስራተ መልአክ ነሐሴ 7 ቀን ተጸነሳለች። በማኅፀንም ሆና ብዙ ተአምራት አድርጋለች። ሁለቱን ለአብነት ያህል እናያለን።

1 ሐና በርሴባ የምትባል አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት ልትጠ ይቃት መጥታ ሳለ እግዚአብሔር በቸርነት ጉብኘሽ ብላ ማኅፀናን በዳሰሰችበት እጇ የጠፋ ዓይናን ብታሽው በርቶላታል። ሌሎችም እንዲሁ ሆዷን እየዳሰሱ ድነዋል

2 ሐና የምትወደው ሳምናስ የሚባል የአጉቷ ልጅ ሞቶ በቤተሰብ ልማድ የአልጋውን ሸንኮር ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ሙቱ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ሰላም ለኪ ኦ እምሒውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የአምላክ አያቱ ሐና ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎ መስክሮ ተመልሶ አርፏል።

ከዚህ በኋላ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ቀድሞ ከእኒህ ወገን የሆኑ

ዳዊትና ሰሎሞን እርባ እርባ ዘመን ገዙን አሁን ደግሞ እነዚህ የወለዱት ሊገዛን ነውን ብሎ በጠላትነት ተነሡ ቅዱስ ገብርኤል እያቄምን ሐቅለ ሊባኖስ ይዘሀት ሂድ አለው ይዟት ሄደ። ጊዜዋ ደርሶ ነበርና በዚህ ዕለት ነቢያት ትንቢት የተናገሩላት ምሳሌ የመሰሉላት እያቶቿ ቴክታ በጥሪቃ በጨረቃ አምሳል ኢያቄምና ሐናም በርግብ አምሳል ያዩአት እመቤታችን ተወለደች። በሊባኖስ መወለዷም ሰሎሞን ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ መኃ 4:9 ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው።

የተወለደችው በ 16 ዓ.ዓ ነው።

መዝገበ ርኀራኄ ድንግል ማርያም
ወልዳ የሠጠችን የዓለምን ሰላም
ለመላእክት እኅት እናት ናት ለሁሉም።
ክብርት ናትና አምሳል የሌላት
ድንግል ተወለደች በመልአክ ብስራት።
ድንግል ስትወለድ በአምላክ ቃልኪዳን
የሊባኖስ ጋራ ተመላች በብርሃን
ሐሤት አደረግን በፍጹም ደስታ
ምስጋናም አቀረብን ለአምላክ በዕልልታ

የድንግል መወለድ ከእያቄም ከሐና
ለጠበቀው የኖርን ተስፋችን ነውና።
በመድም ባታጣ ወዳጅ ቢኖራት
ሐና ምትወልድበት አልተገኘም ቤት።
እንኳን ቤት በረቱን አይሁድ ነፍገዋት
በደብር ተወለደች የአምላክ እናት
አባቷ ሰሎሞን በቃለ ትንቢት
ንዒ እምሊባኖስ እንትየ መርዓት
ብሎ እንደዘመረ እንዳወደሳት።

መኃ 4:9

## ግንቦት 5 እረፍቱ ለኤርምያስ ነቢይ ከ626 - 515 ዓ.ዓ

ኤርምያስ ማለት እግዚአብሔር የሚያውቀው ጎሩይ እምከርሠ እሙ ማለት ነው:: ቁጥሩ ከአራቱ ሀበይት ነቢያት ነው አባቱ ኬልቅያስ ይባላል በዓናቶት የሚኖር ካህን ነበር:: ከኢዩአስ ዘመነ መንግሥት እስከ ሚጠተ እስራኤል ድረስ አስተምሯል::

ንጉሡ ኢኮንያን ይባላል ሦስት ወር እንደነገሠ ናቡከደነጸር ከፋርስ መጣ እሱን አሥሮ ሕዝቡን ማርኮ ሲሄድ ወንድሙ ናታን ከመንገድ ቆይቶ እነኤ ብታነግሠኝ እስራኤልን አስገዛልህ ነበር ብሎ ሹመት ለመነ:: ስሙን ባትከዳኝ ሲል ሴዴቅያስ ብሎ ከምርኮ በቀሩት ላይ ሹሞት ሄዷል:: እርሱም 8 ዓመት ሲገብር ኖሮ ቅጽሩን ካስፋ አንባውን ካጸና በኋላ አልገብርም አለ:: አስቀድሞ በሞአባውያን መንፈቅ ያህል አስከበበው ኋላም እርሱ ሁለት ዓመት ከበበው:: ወደ እግዚአብሄር አመልክትልኝ ብሎ ወደ ኤርምያስ ላከ ከሕዝብህ ጋር ትማረካለህ አለው አንተማ በጐ ተናግረህልኝ አታውቅም ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ከጥልቅ ጉድጓድ አስጣለው:: ጌታ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ በአቤሜልክ አድሮ አውጥቶታል:: ኤር 38: 7- 11 እስራኤል ረሀብ የሚጐዳቸው ቢሆን ንጉሣችንን በምክንያት እናድናለን ብለው እንደ ሞተ ሰው ገንዘው በአልጋ አድርገው ዋይ ዋይ እያሉ ይዘውት ሲወጡ ናቡከደነጾር የሰውን ብዛት አይቶ ምንድር ነው ብሎ ጠየቀ:: የእስራኤል ንጉሥ ሞቶ ሊቀብሩት ይወስዱታል አሉት እሱንማ አጥቤ ገንዤ ልቀብረው ይገባኝ ነበር:: ያም ባይሆን ልሳመው አምጡት አለ:: አስመጥቶ መገነዙን ፈትቶ ቢያየው ቁልጭ ቁልጭ ይላል:: ምነው ሳምንህ ከዳኸኝ አሁንስ እንጂ እኔን ከዚህ አስቀምጠህ ወዴት ልትሄድ ነበር አለው ዝም አለ መሳፍንቱን ፍረዱኝ አላቸው እችላለሁ ብሎ አይዋጋ ወይ አልችልም ብሎ አይገባ ሞት ይገባዋል አሉ ፍርድ አላወቃችሁም ሞቱ ለብእሲ ዕረፍቱ ሞትማ እረፍት ነው ብሎ ሰባት ልጆቹን በሰደፍ አስመትቶ እሱን ሁለት ዓይኑን አውጥቶ በፈረስ ጭራ አስሮ እያስጐተተ ባቢሎን አወረደው ጫን ባቁላ ሲፈጭ ከወፍጮ ስር ልቡ ፈርሶ ሞቷል::

ለኤርምያስ አቤሜልክና ባሮክ የሚባሉ ምድያማውያን ደቀመዛሙርት ነበሩት ከዚያ በፊት የምርኮን ነገር ሲናገር እየሰሙ ኢታርአየን ሙሾ ወብድወታ ለኢየሩሳሌም የኢየሩሳሌምን ጥፋት ኢታሳየን እያሉ ያለቅሱ ነበር:: ጊዜው ሲደርስ ባሮክን መቃብረ ነገሥት አስጠብቀው አቤሜሌክንም ለድውያን የምንቀባው አጽቀ በለስ አምጣ ብሎ ላከው እርሱ ግን ከሕዝቡ ጋር ተማርኮ ፋይስ ባቢሎን ወርዷል::

አቤሜሌክ በለሱን ቆርጦ በሙዳይ አድርጐ ሲመለስ ከጥላ ስር አረፍ አለ ወዲያውም እንቀላፍቶት ተኛ በተኛ በ66 ዓመቱ ነቅቷል ሲነሣ ጥለው ከተኛበት ጊዜ ጥቂት እልፍ ብሎ ነበርና ዘገይቻለሁ ብሎ ፈጥኖ ሊሄድ ቢሞክር መንገዱ ጠፋው:: ቁሞ ሲመለከት መልአኩ በአምሳሉ አረጋዊ ከተራራ ሲወርድ አየ:: ሄዶ አይቴ ሀለው ኤርምያስ ወአኃውየ እነ ኤርምያስ ወዴት አሉ አለው:: አንተኑ ነግዳ ለኢየሳሌም ለኢየሳሌም እንግዳ ነህን እነ ኤርምያስ ያሉ ባቢሎን በስደት ኢየሩሳሌምም ከጠፋች 66 ዓመት አለው አሪት ሽማግሌውን አክብር ብላኛለች እንጂ ጆጁ ጀጃዋ ብልህ በወደድሁ ነበር ለድውያን የምንቀባው በለስ አምጣ ብሎ ልኮኝ ይኸው ቅጠሏ አልጠወለገም ደሟም ይንጸፈጸፋል አለው እንተን ከመከራው ሠውሮህ ነው ብሎ በወራቱ አስረድቶ ወስዶ ከባሮክ አገናኘው አንገት ለአንገት ተቃቅፈው ተላቅሰዋል:: ኋላም ቀናና ቢገቡ እስራኤል ከምርኮ ሊመለሱ አራት ዓመት እንደቀራቸው ተገለፀላቸው ይህን ጽፈው ዐጽቀበለሱ ጋር ታዞ ቢመጣ ንስር አንገት ላይ አሥረው ላኩለት::

ኤርምያስ ሰው ሞቶበት ሊያስቀብር ሲሄድ ከፈረስ ግንብ አጠገብ እስከሬኑ አሳርፎ ሳለ ንስሩ በስሙ ጠርቶ ጣለለት ነገሩንም እንዲረዳለት ሙቱን በእግሩ ረግጦ አንስቶታል ሙቱም በወረቀቱ የተጻፈውን መስክሮ ተመልሶ አርፏል:: ጽሁፉም ከምርኮ ለመመለስ አራት ዓመት ቀርቷልና ከአሕዛብ የተጋባችሁ ተፋቱ ያላገባችሁ ተጠበቁ የሚል ነበር:: ብዙዎቹ እግዚአብሔር የተናገረውን አያስቀር ብለው ያገቡ ተፋቱ ያላገቡትም ተጠበቁ:: የቀሩት ግን ሚስቶቻችንን አንፈታም ከሀገራችንም አንቀርም አሉ:: አራት ዓመት ሲፈጸም ኤርምያስ በፈቃደ እግዚአብሔር እስራኤልን ሰብስቦ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ:: እነሊያም ከኋላ ከኋላ ተከተሉት:: ባሮክና አቤሜሌክ ሊቀበሏቸው ወጥተው የአሕዛብን ሴቶች አይተው ምነው እንዲህ አደረግህ አሉት ሚስቶቻችንን ማን አፋቱን ሀገራችንንስ ማን ነሥቶን ብለው መጡ አላቸው ኃያላኑን መርጠው

አሳደዋቸዋል:: ከዚያም ቢመለሱ ንቃችሁን ጠልታችሁን ሄዳችሁ የለምን ብለው አባረሯቸው:: ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ሀገር አቅንተው ተቀመጡ:: ምድሪቱንም ሠመርናሃ /ወደድናት/ ሲሉ ሰማርያ ብለዋታል::

ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ኤርምያስ የፈረሰውን ቤተመቅደስ አሠርቶ ንዋያተ ቅድሳቱን አሰናድቶ ዳግመኛ እግዚአብሔርን በድለው ይህን የመሰለ መከራ እንዳያገኛቸው ሲያስተምራቸው ቆይቶ በዚህ ዕለት ሕዝቡን ሰብስቦ የሥጋዌን ነገር ሲናገር የአምላክን ልጅ አምላክን አየሁት ይለናልን ብለው በደንጊያ ወግረው ገድለውታል:: ተረ.ኤር 11:54 ዕብ 11 37

## ግንቦት 7 ዕረፍቱ ለአትናቴዎስ ሐዋርያዊ

አትናቴዎስ ማለት ሞት ሕልፈት የሌለበት ሕይወት ማለት ነው:: ሐዋርያ የተባለው አንድ ቀን ከጴጥሮስና ከጳውሎስ መቃብር ሄዶ ሰላም ለክሙ ብጹዓን ሐዋርያት እያለ ሲጸልይ ለከሂ ይበሉክ ሐዋርያ አንተንም እንጂ ሐዋርያ ይሉሀል የሚል ጽምጽ ስለሰማና እንደሐዋርያት መከራ የተቀበለ የተሰደደ በትምህርቱ መናፍቃንን ተከራክሮ የረታ በተግሣጹ በድርሰቱ ለቤተክርስቲያን ዓምድ ስለሆነ ነው::

ሀገሩ መኑፍ ነው:: አባት እናቱ አረማውያን ነበሩ የአባ አለ እስክንድሮስ ደቀመዘሙር ነው:: የአረማዊ ልጅ ከሆነማ እንደምን ደቀመዝሙሩ ሆነ ቢሉ አንድ ቀን አለእስክንድሮስ በመንገድ ሲሄድ ይህ አትናቴዎስ ከሕፃናት ጓደኞቹ ጋር እሱ እንደ ሊቀጳጳስ ሆኖ ጓደኞቹ እንደምእመናን ሆነው አጥምቀን እያሉ እያጠመቃቸው ሲጫወቱ አይቶ ቆሞ ይመለከታቸው ጀመር:: ተከታዮቹ አባታችን ከሕፃናት ምን ቁም ነገር ይገኛልና ቆመህ ታያቸዋለህ አሉት እንዲህ መስሏቹሀልን እኒህ ሕፃናት የሚሰሩት ኋላ ጌታዐአድሮ የሚሰራውን ነው ይህ ብላቴና አባቱ በሕፃንነቱ ይሞታል እናቱ አምጥታ ትሰጠኛለች እኔም ቀጥሎ የሚሾም እሱ ነው አላቸው::

ይኸውም አልቀረ አባቱ በዘመነ ረሀብ ሞተ እናቱ እንደወደድህ አድርገው ብላ አምጥታ ሰጠችው እያስተማረ አሳድጐ ከበታቹ ሾመው:: እርሱ ካለፈ በኋላ በርሱ ቃል በመንበሩ ሾመውታል 20ኛ ሊቀጳጳሳት ነው:: ተሹሞም ሳለ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል ብዙ ድርሰት ደርሷል:: ከብዙውም አንዱ የቅዳሴ እግዚእ ለውጥ ሆኖ በሰንበት በክረምትና በደብረታቦር የሚቀደሰው ቅዳሴ ነው ብዙ ሕሙማንን ፈውሷል፣ በለበሰው ልብስም ሙት አንሥታል:: ከትህትናውም ብዛት እንግዳ ሲመጣበት እንደ ብላቴና ዝናሩን ነጥቆ ወገቡን ታጥቆ እግር ያጥብ ነው::

ንጉሥ ቁስጠንጢኖስ ዘየበቢ አርፎ ልጁ ቁስጠንጢኖስ ዘይንእስ ነገሠ:: የአርዮስ ወዳጅ የነበረ አውሳብዮስ ሄዶ ንጉሥ ብዙ ስለነበሩ አስወጥተውት እንጂ ይአርዮስ ሃይማኖት እውነተኛ ነበረች:: አለው እሱም ነገሩን ተቀብሎ አትናቴዎስን ከመንበሩ አስወጥቶ ሰደደው 7 ዓመት በስደት ኖሯል:: ተሰዶም በብሔረ ዐረብ ሳለ ዐረባውያን አምልኮ የሚፈጽሙበት ምኩራብ ጣዖት ነበረ:: ቆሞ ሲያየው ቆይቶ ወደ ጌታ ቢያመለክት የሰው እጅ ሳይነካው ፈርሶ የኮረት ክምር ሆነ ምን መጣብን እያሉ ሲታወኩ ነገሩ ከወደእግዚአብሔር የተደረገ መሆኑን አስረድቶ አሳምኖ አጥምቋቸዋል ቀሳውስት ዲያቆናትንም ሾሞላቸዋል:: ስንክሳር

ከሰባት ዓመት በኃላ ቢያከራክረኝ እከራከራለሁ ቢገድለኝም እሞታለሁ እንጂ እስከ መቼ በስደት እኖራለሁ ብሎ ከንጉሥ ቀረበ:: በገዛ እጁ ይሙት ብሎ አውሳብዩስን በአዲስ መርከብ የምርቶ ምግቡን ቀዛፊውን ሰጥቶ እሱን ግን ምግብ ቀዛፊ ሳይሰጠው በነቀዘ መርከብ አድርጎ ወደ እስክንድርያ ላካቸው አውሳብዮስ መርከብ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል:: እሱ ግን መላእክት መንፈሳዊ ምግብ እየመገቡት በአዲስ መርከብ አሳፍረው አድርሰውት ወደ መንበሩ ተመልሷል::

ከዚህ በኋላ አርዮሳዊው ቁስጠንጢኖስ ዘይንዕስ ሞቶ ዩልዮስ የተባለ ከሀዲ ነገሠ ሊገድለው ሲያስፈልገው ሸሽቶ ገዳመ አክሚም ገባ መሸሹ ግን ሞት ፈርቶ ሰማዕትነት ጠልቶ አይደለም ወሶበ ያሰድዱክሙ እምዛቲ ሀገር ጉዩ ኀበ ካልዕታ ማቴ 10:25 ያለውን አስቦ እርሱም እኔን ገድሉ በኔም ምክንያት የብዙኃን ደም ፈስሶ እዳ ፍዳ እንዳይሆንበት ብሎ ነው:: እሱም አልቆየም ሞተ ምእመናን አባታችን ጠፋብን ብለው ለአባ እንጦንስ ነገሩ ገዳመ አክሚም አለላችሁ አላቸው በአጀብ አምጥተው ወደ መንበሩ መለሱት ከዘህ በኋላ በሰላም ሲያስተምር ቆይቶ በተሾመ በ47 ዓመቱ በዚህ ዕለት አርፏል:

ቢቶ አትናቴዎስ ደግ ሐዋርያው
ለቤተክርስቲያን የመርቅ ዓምድ ነው
ርእሰ ጳጳሳት ክቡር ሰው ቢሆን
ቀርቦ እግር አጠበ የእንግዶቹን
ታዲያ ጻድቅ ቢባል ያስዋልን
እስኪ ልብ በሉት ትሕትናውን
በመናፍቃን ምክር ቢሰደድ ካገር
ዞሮ አስተማረ ወንጌልን በምር
ንፍሰን በማያረክ በትእግሥ ትምህርቱ
ከሕዝብ መንደር ጠፍተው ማእታቱ
በክብር ክፉ አለች የእምነት ታቦቱ
የሾህ ግንድ አርዮስ ከሀዲት ፍሬውአላው
ጻድቃንን ሲያሳጣ ሥጋቸውን ቆርጦ
ኋላም እንዳያመክ ጉቶው አቆጥቁጦ
በምስጢር ምግቡ አትናቴዎስ ልጦ
ከሥሩ ሳለው ገዝገዞ ቆራርጦ
እስኪ እንደአባታችን ያኮረን ትህትና
ራስን ማዋረድ ክፉ ያደርጋልና

1ጴጥ 5፡6

## ግንቦት 8 ዕርገት

የተነገረው ትንቢት የተመሰለው ምሳሌ ይፈጸም ዘንድ ጌታ በተቀበረ በሶስተኛው ቀን ፀሰንፀተ ክርስቲያን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተነሥቷል ተነሥቶም አርባ ቀን ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳን አስተምሯል:: ጉባኤ ሠርቶ ያስተማራቸው ሶስት ቀን ነው:: በትንሣኤ በአግብአተ ግብርና በጥብርያዶስ ወዘንቱ ሣልሱ ለእግዚእን እንዘ ያስተርእዮሙ ለአርዳኢሁ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን እንዲል ዮሐ 21፡ 1 በየቀኑ ግን ለአንዱ ለሁለቱም ሳይገለጽላቸው አያውልም አያድርም ነበር:: በ40ኛው ቀን አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ከሰማይ ኃይል እስክታገኙ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ ብሏቸው እስከ ቢታንያ አውጥቶ እስከ በትርያርክነት ያለውን መዓረግ በአንብሮተ እድ ሾሟቸው ዐርጓል:: ሉቃ 24 50

ከአርባ ዝቅ ብሎ በ39 ከፍም ብሎ በ41 ያላደረገው በ40 ቀን ያደረገው አዳም በ40 ቀን አግኝቶ ያጣትን ልጅነት እንደመለሰ ለማጠየቅ ነው:: ማረጉም ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ ነው:: ስለምን



ቢሉ ተለየ ተለወጠ ላሉት እንዳይመቻቸው አንድም ቅዱሳን ማረጋቸውን ገነት መንግሥት ሰማያት መግባታቸውን ለማጠየቅ ነው ዐርገ ከመያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሐን እንዲል መቅ ወን

ክርስቶስ ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት
ከሞት በተነሣ በአርባ ዕለት
መላእክት እጅበው እያወደሱት
በእልልታ ዐረገ በቃለ አቅርንት
ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ
ልዑል ጌታ አረገው አክብሮ በጸጋ
በእጁ ባርኳቸው ሐዋርያትን
ጌታ ወደ ሰማይ ሲያርግ በሥልጣን

ጠብቆ አባቸው መንፈስ ቅዱስን
ቅዱሳን መላእክት ለርሱ እየዘመሩ
ጌታ በክብር ሲያርግ ቆመው የነበሩ
ያዩ ሐዋርያት ምንኛ ይከብሩ
ሰብበን ሳንቀር ከሞት ተነስተን
ወደ ሰማይ መንግሥት ማረጋችንን
በርሱ የክብር ዕርገት አውቀን ተረዳን
እርሱ ዐርጎ ለኛ አብነት ሆነን

1 ተሰ 4 17

## ግንቦት 9 ዕረፍታ ለቅድስት ዕሌኒ /ከ 255 328 ዓ.ም/

አየሁዳዊት የሮሓ ሴት ነች:: ተርቢኖስ የሚባል ባል ነበራት ነጋዴ ነበርና ለንግድ ሄዶ ሶስት አራት ዓመት ኑሮ ሲመለስ ባልንጀሮቹ ከግዕበል ከሞገድ ድነን እንደወጣን ሚስቶቻችን ሌላ ወንድ ሳይለምዱ ብናገኛቸው መልካም ነበር አሉ:: በሃይማኖት የጸናች ከገቢረ ኃጢአት የራቀች መሆኗን ያውቃልና እኔስ እንኳን ከግዕበል ተርፍሁ እንጂ ሚስቴን በዚህ አልጠረጥራትም አላቸው ያንተ ሚስት ፍጥረቷ ከሔዋን ልጆች አይደለምን ሴት ጥንቱንም ምክንያተ ስሒት አይደለችምን አሉት በፍጹም አታደርገውም አለ አንዱ አሁን እኔ ቀድሜ ሄጄ ለምጃት ለምዳኝ ብመጣስ አለ እሱም ባይሆንልህስ ቢሆንልኝስ ጥሪቴን እሰጣለሁ ጥሪቴን እሰጣለሁ ተባብለው ተወራርደው ሄደ::

ከቤቱ አቅራቢያ ደርሶ ከተርቢኖስሚስት አገናኙኝ አለ:: ስንኳ ሰው ፀሐይ አይቷት አያውቅም አሉት አገልጋይን አስጠርቶ እመቤት ዕሌኒን ላነጋግራት እፈልጋለሁ ንገሪልኝ አላት ገብታ ብትነግራት ፊት ነሳቻት ተመልሳ አልሆነልህም አለችው:: ገንዘብ ልስጥ ይላል ፀይልኝ አላት ነገረቻት ተቆጥታ በያዘችው መታቻት:: ደጓን እያዘራች ወጥታ አይሆንም ስልህ እንቢ ብለህ አስመታኸኝ አለችው እንኪያስ ይህን ገንዘብ ላንቺ ልስጥሽ ሁለቱ የሚተዋወቁበትን ነገር አምጥተሽ ስጪኝ አላት:: ይህንንስ

አደርግልሀለሁ አንተም ንጋድ'ያን መጡ የብስ ሬገጡ ብለህ አሰውራ አለችው አስወራ ገብታ ንጋድያን መጡ የብስ ሬገጡ እየተባለ ነው ሰውነትሽን ታጠቢ ሽቱም ተቀቢ አለቻት። ስታጥባት ከአንገቷ ያሠረላትን ዕንቁ ረስታው ገባች። ወስዳ ሰጠችው ከመደብር ሄዶ ለምጃት ለምዳኝ መጣሁ ብሎ የያዘውን ዕንቁ አሳየው እውነት መስሎት ልመርምር ሳይል ጥሪቱን አስረክቦ ባዶ እጁን ገባ።

ዕሌኒ ማዘኑን መቆጣቱን አይታ ወንድሜ ምን ሆነህል እንደወትሮህ ደስ አላለህም አለችው ይህን ያህል ዘመን የደከምሁበት ጥሪቴን ማዕበል ሲወስድብኝ ምነው አላዝን አላት ይህማ እግዚአብሔር ያየነውን ቢነሣን ያላየነውን ይሰጠን የለምን በዚያውም ላይ ከዘመዶቻችን ተበድረን እንደወትሮህ ነግደህ እንኖራለን አለችው። እኔስ አበድሬ በኖርኩበት ሀገር ተበድሬ አልኖርም አንቺን ግን ሁሉ ይወድሻል እንዳልሽው ሆነሽ ኑሪ ብሎ በነገሩ ይወርፋታል። ተነሥቶ ሲወጣ እኔስ ካንተ ተለይቼ ወዴት እቀራለሁ ብላ ተከተለችው።

ማዮን አስጠርቦ ይዞ መርከብ ተሳፍረው ሲሄዱ እንቴ ምነው ሳምንሽ ከዳሽኝ ሰወድሽ ጠላሽኝ አላት አንተን ጠልቼ ማንን ወድጃለሁ አንተን ከጂ ማንን ለመድሁ አለችው እንኪያስ ይህንን ለእገሌ ማን ሰጠው አላት ሠራተኛዋ መጥታ ነገረችኝ አይሆንም አልኳት ኋላ ገላዬን ስታጠብ ረስቼ ገብቼ ነበር እሷ ወስዳ ሰጥታው ይሆናል እንጂ እኔስ መልኩን እንኳ አላየሁትም አለችው አድርገሽው ከሆነ ሥራሽ ያጥፋሽ ኣላደረግሽውም እንደሆነ ሥራሽ ያውጣሽ ብሎ በሣዮን ከቶ ከባሕር ጣላት ማዕበል እየገፋ ወስዶ ጽንፈ በራንጥያ አደረሳት የበራንጥያ ንጉሥ ቁንስጣ ከባህር ዳርቻ ቆሞ ነበር የነጋዴዎች ወርቅ ይሆናል ብሎ አስወጥቶ ቢከፍተው ቁልጭ ቁልጭ ስትል አገኛት ውበቷን አይቶ አላዋቂ ነውና የክርስቲያን እመቤት ማርያም አንቺ ነሽ? አላት የከፋኝ የቤት እመቤት እንጂ የርሷን የእግሯ እጣቢም አልሆንም አለችው ሥርዓተ አሕዛብ የሚያስተምሯት ሽቱ የሚዘግቡላት ደንገጡሮች ሰጥቶ መንፈቅ ያህል የጠራ የለሰለሰ ሲመግባት ቆይቶ በመንፈቁ ተገናኛት ልጅ ወለደች። ስሙ ቈስጠን ጢኖስ ተባለ እናቱ ከባሕር ተገኝታለችና ሐመልማል ማለት ነው።

እስከ አራት ዓመቱ ነገረ ሃይማኖት እያስተማረች አሳደገችው ጥምቀት ግን አባቱ አረማዊ ነበርና እንዳይጣላው ብላ



አላስጠመቀችውም ወደ ሀገሯ ይዛው ከተመለሰች በኋላ አድጉ አካለ መጠን ሲያደርስ ጥበቡን ኃይሉን ሰምቶ አምጥቶ አንግሦት በሁለት ዓመት አረፈ እሱ በበራንጥያ ዲዮቅልጥያኖስ በሮም ተከታትለው ነግሠዋል። የዲዮቅልጥያኖስ ነገሥና እንደምነው ቢሉ ቀዳሚ ስሙ ⁑ገሬሻ ነው ሀገሩ ላዕላይ ግብጽ ነው ከሮሙ ንጉሥና ከኑማርያኖስ ቤት የፍየል እረኛ ሆኖ ሲያገለግል ይኖር ነበር። ንጉሡ ሕንጥርብያ፣ ፍንጥርብያ፣ የሚባሉ ሴቶች ልጆች ነበሩት ታላቂቱ ሕንጥርብያ ድምፃዊ ነበርና ሲያንጐራጉር በገና ሲደረድር እየሰማች በሐጸዝሙት ተነደፈች አባቷ ጠላት ተነሥቶበት ዘምቶ በዚያው ሲሞት ስመ መንግሥቱን ዲዮቅልጥያኖስ ብላ አግብታ አነገሠችው ከስምንት ዓመት በኋላ ታናሽቱ ፍንጥርብያም ቢትወደዱ መክሰምያኖስን አግብታ በእንጸኪያ አነገሠችው።

ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ በ20 ቈስጠንጢኖስ በነገሠ በ19 መክሰምያኖስ በነገሠ በ 8 ዓመት ዲዮቅልጥያኖስ በአባ ባጋግዮስ ምክንያት አብያተ ጣዖታት ይትራኀዋ አብያተ ክርስቲያናት ይተአጸዋ ብሎ አዋጅ ነገረ። አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ መጻሕፍት ተቃነጹሉ፣ ምእመናን በግፍ ታረዱ ተሰደዱም ኋላ ግን ዲዮቅልጥያኖስ ዓይኑን ታውሮ ተሰቃይቶ ሞቷል። /ገድ. ጊዮ/ መክሰምያኖስንም እርሱ ድል ነስቶታል። እንደምን ቢሉ ከሞት ከስደት የተረፉ ምእመናን መጥተህ አድነን ብለው ላኩበት። ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ሌሊት በራእይ «በዝ ትእምርተ መስቀል ትሙውዖ ለጸርከ» የሚል ጽሑፍ የቀረጸበት መስቀለ ብርሃን እየ ምን ይሆን እያለ ሲያሰላስል የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው ምስል አሠርተህ ያዝ ታሸንፈዋለህ አለው። ከዘውዱ ጀምሮ እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ መስቀል አስቀረጸ። ከዚህ በኃላ መክሰምያኖስ መጣብህ ብለውት ቢገጥመው አቸንፎታል። መክሰም ያኖስም ሲሸሽ የቴብር ወንዝ ድልድይ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል። ከዚህ በኃላ ሮምን አንጾኪያን ጠቅልሎ የሚገዛ ሆነ በዓመቱም /በ313 ዓ.ም/ አብያተ ጣዖታት ይትዐጸዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትራኀዋ ብሎ አዋጁን በአዋጅ መልሶታል።

ዕሌኒ ቀድሞ ልጅ ሳለ ደገኛ ሃይማኖተኛ ይሆንላት ዘንድ ብፅዓት ገብታ ነበርና በዘመኑ ቀና ሃይማኖት ስለቆመ ደስ ብሏት ብጽዓቷን ለመፈጸም በ327 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ወርዳ መስቀሉን

ከተቀበረበት አስወጥታ አብያተ ክርስቲያናት አሠርታ በዓመቱ /በ328 ዓ.ም/ በዚህ ዕለት አርፋለች::

> ዲዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ በ305 /6/ ዓ.ም መንግሥታቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ነበር፣ ቆስጠንጢኖስም የተዋጋው በመክስምያኖስ ተተክቶ ከነበረ ሌላ መክስምዮኖስ ነው የሚል ታሪክም ይነገራል::

## ግንቦት 11 ቅዱስ ያሬድ

ያሬድ ማለት ሙራድ ማለት ነው:: ብሔረ ሙላዱ አክሱም ነው ትውልዱ ከዘርዐ ሌዋውያን ነው:: አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ይባላሉ:: አባቱ ካህን ነበር የተወለደው በ505 ዓ.ም ነው ለትምህርት ሲደርስ ይስሐቅ ለሚባል መምህር ሰጡት ከሱ ፊደል አጥንቶ መዝሙረ ዳዊት ሊማር ለእናቱ ወንድም ለርሱ አጐቱ ወደ ሆኑት ወደ መምህር ጌዴዎን ሄደ አንዲት ቀለም እንኳ ሳያጠና ሰባት ዓመት ተቀመጠ::

አንድ ቀን ቀለም አጥፍቶ መምህሩ ተቆጥተው በበትር ገረፉት የፀብ አይደለም «ወኢትዘብጥ አሐደኒ ዘእንበለ ሕጻን በእንተ ትምህርት ወግተሣጽ ከመ በዝንቱ ይተዐቀብ» /ፍት.ነገ.አ.11ክ1/ እንዲል ለተግሣጽ ነው:: ሸሽቶ ሲሄድ መንገድ አድክሞት ዋዕየ ፀሐይ ተሰምቶት ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ:: ትል ዛፉ ላይ ለመውጣት ሽታ ስድስት ጊዜ እየወጣች ስትወድቅ በሰባተኛው ወጥታ ስትሄድ አየ እኔስ እስከመጨረሻ ብተጋ ትምህርቴ ይገለጽልኝ የለምን ብሎ ተመልሶ መመህሩን ይቅርታ ጠየቀ ከዚህ በኃላ ጌታ ኅሊናውን ንጹሕ ልቡናውን ብሩህ አድርጐለት ባንድ ቀን ብሉይ ሐዲስ ወስኖ ተገኝቷል::

ከጊዜያት ባንዱ ጌታ ሶስት አዕዋፍ ከገነት ልኮለት በቃል ሰብአዊ ሲያነጋግሩት ተመስጦ መጣበት ጌታ በመንበረ ጸባዖት ሆኖ በቃለ አቅርንት በስብሐተ መላእክት ሲመሰገን ሰማ:: ጳጳሱ ንጉሡ ካህናቱ መሳፍንቱ ለጸሎት ተሰብስበው ሳሉ በሶስት ሰዓት ከመላእክት የሰማው ተገልጾለት ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብረ ለደብተራ ብሎ



በዜማ አመስግኗል:: ከዚያ በፊት በዜማ ምስጋና የለም ነበርና ሁሉም ተደንቀው ሲሰሙት ውለዋል:: ይህን ድርሰቱንም ከአርያም የሰማሁት ነው ሲል አርያም ብሎታል:: በሚያዜምም ጊዜ ያለፈ ያገደመው የመጣ የወረደው ሁሉ በተመስጦ ይሰማው ነበር:: አዕዋፍም ክቡር ንዑድነቱን አውቀው ግዕየ ፀሐይ እንዳይሰማው በክንፋቸው ይጋርዱት ነበር::

ንጉሥ ዐጼ ገብረ መስቀል ከፍቅር የተነሣ ከቤተመንግሥታቸው ያኖሩት ነበር አንድ ቀን ከፊታቸው ቆሞ ሲያሰማቸው ተመስጠው ሳይታወቃቸው በያዙት ጦር እግሩን ወጉት እሱም በተመስጦ ያደርስ ነበርና ለጊዜው አልታወቀውም ኋላ ግን ተሰማው የደምህን ካሳ ምን ልስጥህ አሉት ወርቅ ብር አልሻም ወደ ገዳም እንድሄድ ያሰናብቱኝ አላቸው:: መለየቱን ባየወዱም ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ምለውለት ነበርና አሰናበቱት:: ወደቤተክርስቲያን ገብቶ እጁን በታቦተ ጽዮን ላይ ዘርግቶ ቅድስት ውብዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን ግዕረገ ሕይወት የሚለውን የእመቤታችንን ምስጋና ንባቡንና ዜማውን ሰተት አድርጐ ተናግሮታል:: በዚህም ጊዜ አንድ ክንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብሎ ታይታል:: ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ተከዚን ተሻግሮ በጸለምት ከገዳማተ ሰሜን በአንዱ በጾም በጸሎት ተወስኖ ኑሮ በዚህ ዕለት ዘገብረ ተዘካርየ ወተዝካረ ጌዴዎን መምህርየ ወተዝካረ አዳም አቡየ ምንት እንከ አሰቡ ብሎ ጌታን ጠይቆ ጌታም በተሰፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማጸነውን እስከ 10 ትውልድ ድረስ ምሬልሀለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮት ተሠውሯል::

የድርሰቱንም ነገር ከዚህ ይናገሩታል:: የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች አምስት ናቸው እነርሱም ድጓ፣ ጾመ ድጓ ፣ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ናቸው::

1. ድጓ - እስትጉቡዕ /የተሰበሰበ/ ማለት ነው:: ከብሉይም ከሐዲስም ከአዋልድም ይጠቅሳል፣ የጌታን የእመቤታችንን፣ የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታትን ክብር ይናገራልና ድርሰቱን በዮሐንስ ጀምሮ በዮሐንስ ፈጽሞታል:: ዓለም በዘመነ ዮሐንስ ተፈጥራ በዘመነ ዮሐንስ ለማለፏ ምሳሌ ነው:: ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ጾመድጓ፣ ፋሲካ ብሎ በአራት ዐበይት ክፍሎች ከፍሎታል:: በአራቱ ፀወርተ መንበር በአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ለዚህም በ22 ስነፍጥረት አምሳል 22 አርእስት ሰጥቶታል::

ከእነዚህም 12ቱ ምልክት አላቸው 10 ሩ ግን ምልክት የላቸውም ምልክት ያላቸው «ብዝኆ ወተባዝኆ» የተባሉ የሕጋውያን፥ ምልክት የሌላቸው በተፈጥሮአቸው ፀንተው የሚኖሩ የደናግል ምሳሌ ነው።

2. ጾመ ድጓ በዐቢይ ጾም የሚደርስ ነው ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኩራብ፣
ደብረ ዘይት፣ ገብር ኄር፣ ኒቆዲሞስና ሰሙነ ሕማማት ተብሎ በስምንት ተከፍሏል።

3. ምዕራፍ ማረፊያ ማለት ነው የደረሰው በጠለምት ነው ምዕራፍ
ዘዘወትር ምዕራፍ ዘዐቢይ ጾም፣ ብሎ በሁለት ክፍሎታል መሠረቱ መዝሙረዳዊት ሲሆን በውስጡ ብዙ ንዑሳት ክፍሎች አሉ።

4. ዝማሬ ምስጋና ማለት ነው። ዝማሬና መዋሥዕትን በደቡብ
ጐንደር ዙር አባ በሚባል ቦታ ደርሶታል። ኅብስት፣ ጽዋዕ፣ መንፈስ፡ አኰቴትና ምሥ ጢር ብሎ በአምስት ክፍሎታል። አምስት ክፍል መሆኑ ኅብስት ሥጋውን ጽዋዕ ደሙን ያመለክታልና የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ ነው።

5. መዋሥዕት - ምልልስ፣ ሰዋሰወ ነፍስ፣ ማለት ነው
ለአዕርጎ ነፍስ በፍትሐት ጊዜ የሚደርስ ነውና ያስ ይሁን ለሙት ድርሰት ደርሶ ማዘንን ከማን አገኘቶታል ቢሉ ከዳዊት ይሏል። ዳዊት ለሳአልና ለናታን ግጥም ገጥሞ አልቅሶላቸዋል። 1ኛ ሰሙ 1፡ 17- 27 በዘመነ ሐዲ ስም ዮሐንስ
ኤጲስቆጶስ ዘጳግስቆ ለሞተ ሰው ድርሰት እየደረሰ ያዝንላቸው ያለቅስላቸው ነበረ ድርሰቱ ግን የኔማ ጀግናው የኔማ ሳተናው ሸሸ ተበላሸ የሚል ሳይሆን በሞቱ ሞትን ያጠፋ ጌታ አምላክ ከሞተ ነፍስ ክርዳተ ገሃነም



እንዲያድነው ለሕይወት እንዲያበቃው የሚለምን ጸሎት ነው።
እስከ ድረስ የተገለጹት ድርሰቶቹ አምስቱ ጸዋትወ ዜማ በመባል ይታወቃሉ።
ከዚህ ሌላ የውዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ማርያም ምን ዜማ የደረሰ እሱ ነው። ማይኪራህ በሚባል ቦታ ሳለ እመቤታችን ቅዱስ ኤፍሬምን ከቂሳርያ አባ ሕርያቆስን ከብህንሳ በደመና ጠቅሳ እርሱ ካለበት አምጥታ አንተ ውዳሴዬን አንተ ቅዳሴዬን ነግራችሁት በዜማ ያድርሰው ብላቸው ነግረውት ውዳሴዋን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለውን በአራራይ የእሑድን በዕዝል፣ቅዳሴዋን በግዕዝና በዕዝል፤ አድርሶታል። ከዚህም አያያዞ 13 ቀን ቅዳሴያት ሁሉ በዜማ አድርሷል። ቅኔንም አምልቶ አስፍቶ ባይናገረው እንጂ ደራሲው እርሱ ነው። ዜማውም ሶስት ዓይነት ነው፤ ግዕዝ ዕዝል አራራይ፣ ግዕዝ የአብ ዕዝል የወልድ አራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።



ለቤተ ክርስቲያን ያሬድ በጥበብ
የምታበራለት ፅንቀን ነህ ኮከብ::
መዝሙርና ቅኔ ያወረሰከን ሀብት
ጉድፍ ሳያገኘው ብልና ዝገት
ይኸው ዛሬም አለ እንዳማረበት
እሱ መቼም እያልቅ አይጉድልም ቅንጣት
የአዳም ልጆች ሁሉ ቢከፈፈሉት
ምድራዊ ስትሆን ሥጋን የለበስህ
አይተንህ ደስ አለን በማኅሌትህ
ከመላእክት ጋር ተካክሉ ክብርህ::
ቤተክርስቲያንን አጉናጸፍካት

የማያረጅ ካባ ጥዑም ማኅሌት
ለአምላክህ ስትዘምር እያሸበሸብህ
በዋዕየ ፀሐይ እንዳይዝል ሥጋህ
የሰማይ መላእክት በክንፍ ጋረዱህ::
ልብን የሚመስጥ የማይሠለቸ
ያሬድ ባንተ መዝሙር ኢትዮጵያም ከራች::
እንደ ቅዱስ ያሬድ በጥዑም ዜማው::
ፈጣሪ አምላክን እናገልግለው::
ሃሌ ሃሌ እያልን እናመስግነው::
ለዚሁ ነውና የተፈጠር ነው::

3ኛ መቃ 2:11 ሃይ አብ ዘአትና /ወዘለንተዝ ፈጠር ለእጓለ እመሕያው ከመይትለአኮ በእምሳለ መላእክት/

## ግንቦት 12 - ዮሐንስ አፈወርቅ /ከ344 /7/ - 404 /7/ ዓም/

ዮሐንስ ማለት: ፍሥሐ ወሐሤት ፣ ርኅራኄ ማለት ነው:: ሀገሩ አንጾኪያ ነው:: አባቱ አስፋኒዶስ /ሱፋንዩ/ እናቱ አትናስያ ይባላሉ:: አቴና ወርዶ ጥበብ ሥጋዊ ከተማረ በኋላ ጥበብ መንፈሳዊ ሊማር ቅዱስ ባልልዮስ ከነበረበት ገዳም ገባ:: «ወከነ ሲሲቱ መጠነ ሲሲተ ዖፍ» ይላል እፍኝ ገብስ ከነኃሠሩ እስከ መመገብ ድረስ ደርሶ ብዙ ትሩፋት ይሠራ ጀመር::

እርሱ ካለበት ገዳም ሲሲኮስ የሚባል ደግ ባሕታዊ ነበር:: ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ ከበዓቱ ገብተው ጴጥሮስ መራኁቱ መንግሥተ ሰማያት ዮሐንስ ወንጌል ሲሰጡት አይቶ እንዲህ ያለ ራዕይ አየሁ ብሎ ነገረው:: ምን ይሆን ብሎ ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ውሉ ሌሊቱን ለሰጊድ ለጸሎት ሲተጋ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ከፊቱ ቆመ:: ደንግጦ ወደቀ፤ መልአኩ አንሥቶ ጌታ አዞሀልና የአንጾኪያው ሊቀጳጳስ የሚልህን አይሆንም አትበል አለው:: በማግሥቱ የአንጾኪያው ሊቀጳጳስ መጥቶ ቅስና ልሹም አለው:: አይሆንም አለ:: ኋላ ግን መልአኩ የነገረውን አስቦ ተሹሟል::

ከዚህ በኋላ ቁስጥንጥንያ ወርዶ አንድ ቀን ምእመናን ቅዳሴ በሚያስቀዱስበት ሥጋውን ደሙን በሚቀበሉበት ጊዜ ፀሐይ ከአንዲት ሴት ላይ ጨረሯን ፈነጠቀችባት፤ ኤጲስቆጶስ ንስጥሮስ ነው:: ልጄ የሠራሽው ኃጢአት ምንድር ነው? አላት ከፍቅረ ቤተክርስቲያን የተነሣ የመንጸት ጊዜዬ ሳይፈጸም መጥቻለሁ እንጂ ሌላ ከሰው የተለየ የሠራሁት ኃጢአት የለም አለችው:: በልቡ



የጌታን አምላክ ወልደ አምላክነት የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ይነቅፍ ነበርና ድንግል ማርያም አምላክን የወለደች ብትሆንስ ለሴቶች ይህን የደም መፍሰስ ባስቀረችላቸው ነበር ብሎ ዕርቃኗን አስቅሎ ክርስቶስን አምላክ ወልደ አምላክ ድንግል ማርያምንም ወላዲተ አምላክ የሚል የተረገመ ይሁን እያላችሁ ትፋባት አለ:: እየሄዱ ይተፉባት ጀመር:: «ወሀሉ አሚሃ ዮሐንስ ጠርዘቤጠር» ይላል ዮሐንስ ከዚያ ቁሞ ነበረ በተራው ቀርቦ እኔስ ወልደ እግዚአብሔር እንዲህ ባለማኅፀን ከእመቤታችን በኀቱም ድንግልና እንደተወለደ አምናለሁ ብሎ:: የሴቲቱ እድፈት ሳያስጸይፈው የእመቤታችንን ንጽሕናና ቅድስና እያሳበ አካሏን ቢስም ከአፉ ላይ እንደ ወርቅ ተቀስሞበታል:: በቤተ መቅደስ የነበረች ስዕለ ማርያምም «ለምእመናን ትምህርቱ እንደማር የጣፈጠ ለከሀዲ ግዘቱ እንደ ጦር የጸና እንደ ሰይፍ የተሳለ በእውነት አፈወርቅ ልሳነ ወርቅ» ብላ በቃል ሰብአዊ መሰከረለታለች:: «ሰበ ሰዓመ ኃፍረተ ትክት ቅድመ መዋዕለ ንጽሕ ሱባዔ፤ ተአምረ ፍቅርኪ ያርኢ ወያስተኀፍር ጸላዔ፤ማርያም ስዕልኪ ለዮሐንስ ጽጌ ትንሣኤ፤ ወደሰቶ ወአእኰተቶ ቅድመ ገጸ ኩሉ ጉባዔ፤ አፈወርቅ እንዘትብል ጊዜያተ ክልዔ:: እንዳለ ደራሲ::

ከዚህ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር በአንጾኪያ ሊቀጳጳስነት ተሾመ:: ተሹሞም ሣለ ብዙ ተግሣጻት ጽፏል ብዙ ድርሳናት ደርሷል:: ንጉሡ አርቃዴዎስ ይባላል:: ወዳጁ ነው:: ሊጠይቀው ሄዶ ሳለ መምህር አንተን ሳገኝህ ነገሩ ይጠፋኛል ነገሩን ሳገኘው አንተን አጣሀለሁ፤ ከልቤ ሲወጣ ሲወርድ የሚኖር ነገር አለ፤ ወንጌላዊ «ኢያእመራ እስከ አመ ትወልድ ወልደ ዘበኵራ የበኩር ልጇን እስክትወልድ አላወቃትም» /ማቴ 1: / ያለው:: ከወለደች በኃላ ወንዶች ሴቶችን በሚያውቁበት ግብር አውቋታል ማለት ነውን አለው:: ይህስ አይደለም ጌታን ጸንሳ ሳለች ሥጋዌው በብዙ ኅብረ ትንቢት የተነገረለት በብዙ ኅብረ አምሳል የተመሰለለትን ጌታ እንደጸነሰች ለማጠየቅ መልኳ እየተለወለጠ ይታየው ነበረ፤ ከወለደችው በኋላ ግን በአንድ ኅብረ መልክዕ ታይታዋለችና ስለዚህ ነው ብሎ ተረጉመለት በዚህም ጊዜ ከግድግዳ ላይ የነበረች ስዕለ ማርያም ካለችበት መጥታ ሦስት ጊዜ በራሱ ላይ ዞራ «ሠናየ ተናገርከ ዮሐንስ አፈወርቅ ዮሐንስ ልሳነወርቅ» ብላ አወድሳው

ከቦታዋ ተመልሳለች:: ንጉሡም ለመታሰቢያ ሁለት ልሳናተወርቅ አሠርቶ በግራ በቀኝ አድርጎላታል::

በዚህም ላይ ንጉሡ አርቃዲዎስ ንግሥቲቱ አውዶክስያ ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸው ነበርና ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ እንዳትሞትብን ብለው እርሱን አጥምቅልን አሉት ሲሄድ መልአከ ሞት ከመንገድ ተገናኘው ወዴት ትሄዳለህ? አለው:: የአርቃዲዎስን ልጅ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ ላመጣ እሄዳለሁ አለው:: ቆየኝ ላጥምቃት ብሎት ሄደ:: ካጠመቃት በኋላ ረስቶት በሌላ መንግድ ተመለሰ:: የካህናት የመዓረጋቸውን ደግነት ለማጠየቅ /17/ ወዲያ ወዲህ ሳይል 10 ዓመት ቆሞ ቀይቷል:: «እምነ አፉሁ ዘወርቅ ሰሚኦ ግዘተ፤ እንበለ ይዕርግ ላዕለ ወእንበለ ይረድ ታሕተ፤ መልአከ ሰማይ ቆመ ዐሠርተ ዓመተ» እንዲል እርኬ::

በአሥረኛ ዓመቷ ለባልታጨች ልጃችንን መርቀልን ብለው ላኩበት ቀድሞ በሄደበት መንገድ ቢሄድ መልአከ ሞትን ቆሞ አገኘው :: ምነው ከዚህ ቆመሀል? አለው:: አንተ ቆይ ካልከኝ ጊዜ ጀምሮ ወዲያ ወዲህ ሳልል ቆሜአለሁ አለው:: አጥፍቻለሁ ሂድ የታዘዝከውን ፈጽም አለው:: ከዚያ ሲደርስ ሞታ ሲላቀሱ አገኘ:: ነገሩን ነግሮ አጽናንቷቸው ተመልሷል::

ንግሥቲቱ አውዶክስያ መፍቀሪተ ንዋይ ነበረች:: በዓመት 3 ጊዜ የምታፈራ ለከተማ ቅርብ የሆነ ርስት ያላት መበለት ነበረች ርስቷን ነጠቀቻት:: መጥታ ለርሱ ነገረችው መልሺላት አላት አምለልስም አለች:: ርስተ ምድር ነጥቀሽ ርስተ ሰማይ ታገኚ መሰለሽ? ብሎ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዳትገባ ሥጋውን ደሙን እንዳትቀበል ከምእመናን እንዳትገናኝ አወገዛት:: እርሷም በበኩሏ እሱ በነውር ምክንያት የሻሩቸውን ኤጲስ ቆጳሳት በብስባ ታሥሮ ይጋዝ ብለው እንዲፈርዱበት አደረገች:: ታሥሮ ወደ ደሴተ አጥራክስያ ተጋዘ:: የሮሙ ንጉሥ አርያኖስ ዜና ገድሉን ስነ ጽድቁን እየሰማ ሲያደንቅ ይኖር ነበርና ባትመልሰው ጠቤ ካንተ ነው ብሎ ከአርቃዴዎስ ላከ:: መልሱ ብሎ አስመለሰው ያች ግን ሰይጣን አነሣስቷታልና ሁለተኛ አሥራ አጋዘችው በዚያው አርፏል:: እሷም አልተጠቀመችም እሱ ካረፈ በኋላ ጽኑ ደዌ አደረባት:: ከመቃብሩ ሄዳ በድያለሁ ይቅር በለኝ እያለች ብዙ መከራ ተቀብላ ተፈውሳለች::



የሐንስ አፌወርቅ ሊቀጸለባት
ጠቢብ ተጋፊጊ ምሁር ደግ አባት::
እውነተኛ መምህር ፊት አይቶ አያደላ
ንግሥትን ገሠጻት ደጋዋን በድላ::
በእግዚአብሔር ፊት ብትከብርላት ነፍሱ
በግያዊ መልአክ ታዘለት ለርሱ::
ቃሉ የማፈጠ ትምህርት እውን
አቃጥሉ ፈጀቸው መናፍቃንን::
በስንፎች መሀል አንዳች ሳያፍር
ቆሞ ሲመሰክር የድንግልን ክብር
ድንግል በሥዕሏ አድራ በቋንቋው
አፌወርቅ ብላ አወደሰችው
እንዳይቀየሙት ነገሥት መናፍንት
በሞቱ ቻል ከግል የደጋን ጩኸት
ጌፊዎችን ሁሉ ገሥጾ በእውነት
ይቫለኛል አለ መጥር በክብት
ጌታ እንዳልጉዳ እውነትን ተርቆ::
የቀናውን መንፈስ አላደር በክር::

አባ እፍሺ - /ከዘጠኙ ቅዱሳን/

## ሐ. ፍልሰተ ሥጋሁ ለአቡነ ግር ተክለሃይማኖት

ዜና ዕረፍታቸው በገጽ እንደተገለጸው ጌታ በ57 ዘመን ደቀመዛ መዛሙርትህ ቤተክርስቲያን አንጸው ሥታህን ወደዚያ ያፈልሱታል:: ብሎ ብሎ ነግሯቸው ነበረ:: ጊዜው ሲደርስ 19 ቀን ለአቢ ምኔት ለአባ አባ ሕዝቅያስ ተገልደው ጌታዬ የነገረኝ ተስፋ ሊፈጸም ጊዜው ደርሷልና በሩቅም
በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቴን ሰብስበህ በ12 ሥጋዬን አፍልሱ፤ እኔም ከቅዱስ ሚካኤል ጋር እመጣለሁ፤ ምልክት ይሆንህ ዘንድ ስትገባ መብራቶቹን አጥፉ እኛ ስንመጣ ይበራል አሉቶ:: እንዳሉትም ደቀመዛሙርቶቻቸውን ከሩቅም ከቅርብም ሰብስበ በዚህ ዕለት ሥጋቸው ካረፈበት ከመካነ አስቦ ቢገቡ እንደ ሽቱ መዓዛው እምር አገኘተው ተሸክመው ወደ ቤተመቅደስ ከቅዱስ ሚካኤል ጋሮ መጥተው ከመንበሩ ተቀመጡ፤ ቢመጡም የጠፉት መብራቶች በርተው ተገኝተዋል እኒያም በዕልልታ በደስታ አጽማቸውን ከእግረ መንበር አኑረውታል:: ታሪኩ የተፈጸመው በ1349 ዓ.ም ቀን ነው::

## ግንቦት 14 አባ ጳኩሚስ /ከ290 - 346 ዓ.ም/

ሀገራቸው ጽርዕ ነው:: በገዳመ ዳውናስ በ 6 ሺህ መነኮሳት ተሹመዋል:: ቀን ለማስተማር ለአገልግሎት ሌሊት ለበጊድ ለጸሎት ተግተው ይኖሩ ነበርና ሱታፌ ማኅበረ መላእክት ተብለዋል:: በጸሎታቸው ጥቂት ትምክህት ነበረባ ቸው:: አንድ ሌሊት ሲሰግዱ

ላባቸው የቆሙበትን ምድር አራሰው ጌታ ተገልጾ አሁን ይህ ሁሉ ስገደት ይህ ሁሉ ጸሎት ለማን ብለህ ነውሕ አላቸው ጌታዬ ላንተ ብዬ ነዋ አሉት በማገሥቱ በችንካር ተቸንከር በመስቀል ተሰቅሉ ታያቸው:: ጌታዬ አሁን ደግሞ መስቀልህ ለማን ብለህ ነውሕ አሉት ላንተ ብዬ ነዋአላቸው:: ይህ ሁሉ ትናንት በተናገርኩት አይደለምን ደግ አላደረግሁም ብለው ተጸጸተዋል:: በሚጸልዩም ጊዜ ጉንትና ሲኦል በዓይነልቡና ይታያቸው ነበር አንድ ቀን ባያቸው በወደድሁ ነበር አሉ:: የታዘዘ መልአክ ነጥቆ ወስዶ ጸድቃንን በገነት ሲያመሰግኑ ኃጥአንን በሲኦል ዋይ ዋይ ሲሉ አሳያቸው:: ከዚህ በኋላ መላ ዘመናቸውን ስለኃጥአን ሲያዝኑ ሲያለቅሱ ኖረዋል:: ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ ኀዘንህን አየሁልህ ልመናህንም ሰማሁልህ በስምህ የተማጸነውን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም አድንልሃለሁ ብሎ ተስፋቸውን ነግሯቸው በዚህ ዕለት ዐርፈዋል::

## ግንቦት 16 ኢያሱ ሲራክ

ኢያሱ ማለት መድኃኒት፣ ሲራክ ማለትም ጠቢብ ማለት ነው:: ሲራክ የጥበብ ስሙ ነው አባቱ አልዓዛር ይባላል:: መጽ ሲራ 5:1 ጌታ ጥበብ ገልጾለት የጥበብ ሁሉ መገኛዋ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ዓለም ሳይፈጠር ጥበብ ከርሱ ጋር ነበረች ብሎ ስለጥበብ ተናግሯል:: ሲራ 1:1 ከመሳፍንት ሙሴን ከነገሥታት ዳዊትን ከነቢያት ኤልያስ ኤልሳዕና ኤርምያስን አብነት እያደረገ ታላቅ የጥበብና የምክር መጽሐፍ ጽፏል መጽሐፉም ከ 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው::

ከምርኮ መልስ ከ 470 ዓ ዓ ወዲህ የተነሣ መሆኑን መጽሐፉ ያመለክታል

## ግንቦት 17 ኤጲፋንዮስ ኤጲስቆጶስ /ከ 315 - 403 ዓ.ም/

ወላጆቹ አይሁዳውያን ነበሩ አባቱ ሞቶ እናቱ እርሱንና እኅቱን የምታሳድግበት አጥታ ስትቸገር እርሱ ያላቸውን አንድ አህያ ሊሸጥ



ይዞ ሲሄድ ክንዱና ፊላታዎስ የሚባል ደግ ሰው አገኘው:: ዋጋውን ሲነጋገረው አህያው ዘሎ ኩላሊቱን ረገጠው ፣ ወደቀ ፊላታዎስ የክርስቶስ ኢየሱስን ስም ጠርቶ ቢጎትተው ተነሣ:: አህያውንም ውደቅ ቢለው ወድቆ ቀረ:: ኤጲፋንዮስ በስሙ የወደቀውን የምታነሣበት የቀመውን የምትጥልበት ኢየሱስ ማነው? አለው:: ኢየሱስማ ለቤዛ ብዙኃን ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ዕውር ቢያበራ ሙት ቢያስነሣ ወገኖቹ አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው ሰቅለው የገደሉት አምላክ ወልደአምላክ ነው:: አለው ይህን በልቡ አኑሮ ባየው እየተደነቀ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

ከዚህ በኋላ ባለጸጋ አጐት ነበረው እሱንም እኅቱንም ወስዶ አሳድጎ ሀብቱን አውርሷቸው ዐረፈ:: አንድ ቀን ከአባ ሉክዮስ ጋር በመንገድ ተገናኝተው እየተጨዋወቱ ሲሄዱ አንድ ችግረኛ ስመ እግዚአብሔር ጠራባቸው:: አባ ሉክዮስ ወርቅ ብር የለውምና የለበሰውን አውልቆ ሰጠው:: ወዲያው መልአክ ከበረዶ የነጻ ልብስ ሲያጎናጽፈው አይቶ አባቴ አምላክህን አመልከው ዘንድ ሃይማኖትህን አስተምረኝ አለው:: አስተምሮ አጥምቆታል:: ከፍጹምነትም እንደሚደርስ አውቆ መዓርገ ምንኩስና አሰጥቶታል በዚህ ጊዜ የ17 ዓመት ወጣት ነበረ:: ከዚህ በኋላ በጾም በጸሎት ተወስኖ በትኅርምት የሚኖር ቢሆን ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶት ሕሙማንን የሚፈውስ ሆኗል፣ ሙትም አንሥቷል::

መምህሩ አባ ኢላርዮን መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት ጌታ የብዙኃን አባት እንድትሆን መርጦሀልና፣ ቆጵሮስ ሂድ ተሾምልን ቢሉህ አይሆንም አትበላቸው አለው:: ከበዓቱ መውጣቱን ከመምህሩ መለየቱን ባየወድም ፈቃደ እግዚአብሔር ነውና ሁለት ብላቴኖች አስከትሎ ሄደ:: ጌታም ለቆጵሮሱ ኤጲስቆጶስ ሁለት ብላቴኖች ያስከተለ ሁለት የወይን ዘለላ የያዘ ኤጲፋንዮስ የሚባል ገዳማዊ ወደ ገበያ ይመጣል እሱን ሹመው አለው:: ቢሄድ ሁለት የወይን ዘለላ ይዞ ሁለቱን ብላቴኖች አስከትሎ ሲገበያይ አገኘው ኤጲፋንዮስ የምትባል አንተ አይደለህምን አለው:: አዎን አለ ጌታ ያዘዘኝ አለና ተከተለኝ ብሎ ወስዶ ሾመው:: በሶስተኛው ቀን ቅስና ሰጠው ኋላም እርሱ ሲሞት ኤጲስቆጶስነት ተሹሟል:: ተሹሞም ሳለ ብዙ ድርሳናት ደርሷል ብዙ ተግሣጻት ጽፏል::

ንግሥቲቱ አውዶክስያ የአንጺት መበለት ርስት በመንጠቋ ምክንያት የሐንስ አፈወርቅ አውግዞ ከማኅበረ ምእመናን ለይቷት

ነበርና የሃይማኖት ሕጸጽ ሳይኖርብኝ በከንቱ አውግዞኛልና መተቱሀ እያልኝ ብላ ላከችበት ሄደ፣ ተይ ያለሽን ተዪው አላት ይህንንስ አልተውም አለች እንግዲያውስ የሺቀጻጻሉን ቃል ልታከብሪ በተገባሽ ነበር አላት ይህንን ካልከማ አብያተ ክርስቲያናትን አዘጋቼ አብያተ ጣዖታትን አስከፍታለሁ አለችው:: ከርሱ ዘንድ ሄዶ ወንድሟ ጥቂት ጊዜ ምእመናን ከመከራ አረፉ ስንል በዚህ ምክንያት ደግሞ መከራ ቢመጣባቸው ደግ ነውን ተወው አለው:: ርበተ ምድር ነጥቃ ርስተ ሰማዩ ታገኛለችን አይሆንም አብያተ ማኦታትንም ብታስከፍት ለርሷ ይበሳታል አለ::

ተመልሶ ከንጉሥ ሊሰናበት በገባ ጊዜ ኢሲፋንዮስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከሹመቱ ሻረው ከመዓረጉ አዋረደው ብላ በሐሰት አስወራች::

ዮሐንስን ሊሰናበት ሲሄድ ምነው እንዲህ አደረግኸኝ? አለው ኧረ ምንም አላደረግሁብህም አለ:: መሄድማ ትሄዳለህ ከመንበርህ ግን አትቀመጥም በመንገድ ትሞታለህ አለው:: እርሱም በበኩሉ መመለስማ አይቀርም ትመለሳለህ ነገር ግን ሁለተኛ ተግዘህ ትሞታለህ አለው:: የጠብ አይደለም የዮሐንስ ሞት ለኢሲፋን ዮስ የኢሲፋንዮስ ሞት ለዮሐንስ ተገልጾላቸው ነው እንጂ ይኸውም አልቀረ ዮሐንስ አፈወርቅ በዕርቅ ከተመለሰ በኋላ ሁለተኛ ተግዞ በዚያው ዐርፏል:: ኢሲፋንዮስም ጥቂት ቀን ተጉዞ ሳይደርስ ከመንገድ በዚህ ዕለት ዐርፏል:: 11 ቀን ተጉዘው በ28 ደረሱ፣ በሃይማኖት ሕጸጽ በምግባር ጻጉዕ የሻራቸው ሁለት ዲያቆናት አናስቀብርም ብለው መቃብር ከልክለውት 40 ቀን ተቀመጠ ይህንንም ያህል ቀን ሲቆይ መዓዛው አልተለወጥም ነበር::ኋላ ግን አንድ ዲያቆን ቢማጸነው እኒያን በተአምራት አጥፍቶ ተቀብሯል::

ነበር መንፈሳዊ ኤጲፋንዮስ
ታማኝ ባለሟሉ ለመንፈስ ቅዱስ
ኻኝ በልጅነቱ በመነትነቱ
በድጊድ ተቀማ በጾም በመንነቱ
ለግጸትን አብዝቶ ቢገልም ጉልበቱ
ያረሐቸው ነበር ሕዝቡን በስብከቱ

አምላኩ ክርስቶስ ነውና ብርታቱ::
ከሞተ በኋላ ሥጋው ሆኖ በድን
ጻድቃን የመሰሉ ተንኮለኞችን
ተጣቸው ለሕዝቡ ትምህርት እንዲሆን
ፈጣሪ ተጣልቶን እንዳንሆን እጉል
አይበጀንምና ይቅርብን ተንኮል

ምሳ 10 :29 ፥ 12: 2

## ግንቦት 18 በዓለ ጰራቅሊጦስ

ጌታ በሚያርግ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን እንትሙስ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ሉቃ 24:49 ብሏቸው ነበርና:: ተናግሮ የማያስቀር ምሉ የማይከፋ ነውና ባረገ በ10ኛው ከተነሣ በ50ኛው ቀን ጰራቅሊጦስን ሰዶላቸዋል::



ጰራቅሊጦስ ማለት መንፈስ ጽድቅ መንፈስ ሕይወት ባሕርያዊ እስትንፋስ አካላዊ ሕይወት አካላዊ እስትንፋስ ማለት ነው ስለምን ቆይቶ በ10ኛው ቀን ላካላቸው ቢሉ በ10ኛ መዓረግ የነበነ እኛ ነበርንና ወደ ክብራችን ወደ መዓረጋችን እንደመለሰን ለማጠየቅ ነው ዳግመኛም 10ሩን ቃላት ቢጠብቁ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ መሆኑን ለማጠየቅ ነው::

"ወአስተርአይዎሙ ልሳናተ እሳት ክፉላት ከመ እሳት ዘይትከፈል" ይላል በአምሳለ እሳት አድሮባቸዋል:: ወዲያውም የሚያውቁት አንደበታቸው የማያውቁት ተገልጾላቸው ቀድሞ ከሚናገሩት ከዕብራይስጥ ቋንቋ ሌላ 71 ቋንቋዎች ተገልጸውላቸው ምሥጢር የሚተረጉሙ ሆነዋል:: ከአይሁድ ወገን አኩሌቶቹ ይህ ነገር ምን ይሆን? አሉ አኩሌቶቹ "እሉስ ጻዕፈ ጸግቡ - ጉሽ ጠጅ ጠጥተው ሰክረው የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራሉ "አሉ:: ቅዱስ ጴጥሮስ ሀሣባቸውን አውቆ እኮ ከመትትሐዘብዎሙ አንትሙ ስኩራን እሙንቱ ዘትበሉ ሰክረዋል የምትሉ እናንተ እንደምትጠረጥሯቸው አይደለም እስመ ነግህ ብሔሩ ወሶቤሁ ሠለስቱ ሰዓት - ጊዜው ማለዳ ሰዓቱም ሶስት ሰዓት ነውና፣ ዳሩ ግን እሰወጥ እምነመንፈስ የ ዲበ ኩሉ ዘሥጋ (ኢዩ 2: 28) ተብሎ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ይህን ያደረገ እናንተ ጸልታችሁ ተመቅኝታችሁ የሰቀላችሁት ክርስቶስ ኢየሱስ ነው እኛም ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት ምሳሌ የመሰሉለት አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ፣ ከሙታን ተለይቶ ለመነሣቱ ለማረጉ ዳግመኛም በክብር በምስጋና ለመምጣቱ ምስክሮች ነን አላቸው ምንተ ንግበር እኃዊን እውን ምን እናድርግ አሉ "ነስሑ ወተጠመቁ በስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከክፋታችሁ ተመልሳችሁ በስሙ ተጠመቁ አሏቸው "ወተወሰኩ በይእቲ ዕለት መጠነ ሠላሳ ምዕት ነፍስ " ይላል ሶስት ሺህ ሕዝብ አምነው ተጠ ምቀዋል:: ሐዋ 2:1-41 ይህ የተፈጸመ በ33 ዓ.ም በዚሁ ቀን በዕለተ እሑድ ነው:: ዕለቱን ሊቃውንት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተሠጠበት፣ ወደ የሀገራቸው በተመለሱ ጊዜ በአሕዛብ መካከል የሚያስተዋውቋትንና የሚመሰክሩላትን 3000 ምእመናን ያገኘችበት ዕለት ስለሆነ የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ሲሉ ጠርተውታል::

4. ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ እመቤታችን ከሌሎች ቅድሳት አንስት ጋር አብራቸው ለጸሎት ትተጋ ነበር ሐዋ 1:14፥2:1

ሰንበተ ክርስቲያን ክብርት ልለት ናት
መንፈስ ቅዱስ ለሰው የተሰጠበት
ጌታ ጉብኝቷቸው በቅዱስ መንፈሱ
ሐዋርያት ፀሑ ከብልየት ታደሱ
ምሥጢር ለመተርጉም በዕውቀት ጉለመሱ
ሃይማኖታቸውን በግልጽ መሰከሩ
የአይሁድን ግልምጫ ሞትንም አልፈሩ
ለቤተክርስቲያን የጴጥሮስ ስብከት
ሦስት ሺህ ነፍሳትን አተረፈላት
ተመለሱ ብሎ ጴጥሮስ ሲመክራቸው
ሊገሥጻቸውም በክፋ ሥራቸው
ከአይሁድ መካከል የበዛቁጥራቸው

አሁንም ተጸጸቱ ስለበደላቸው
በክርስቶስ እምነው በስሙም ተጠምቀው
የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለው
ከዓለም ክፋ ሥራ ከክፋት ርቀው
በፍቅር በአንድነት መከራን ታግሠው
በጎ እየሠሩ ቢጎውን ተናግረው
ወንጌልን በአንደበት በሥራም መስክረው
ለአምላክ ታምነው ኖሩ በመላ ዕድሜያቸው
ለምእመናን ሁሉ በጐ አብነት ሆነው::

# ግንቦት 19 ኤስድሮስ ሰማዕት

ሀገሩ አንጾኪያ ነው :: አባቱ በድላአን እናቱ ሶፍያ ይባላሉ:: እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰውን የሚያከብሩ ደጋጐች ነበሩ:: በድላአን የንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ሊቀሐራ ነበረ:: ዲዮቅልጥያስ በነገሠ በ20 ዓመት ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ይፈጃቸው ጀመረ:: በድላአን ፈጣሪዬን ክጄ ለጣኦት ሰግጄስ አልኖርም ብሎ ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን ይዞ ከአድባራት ባንዱ ተቀመጠ:: ዲዮቅልጥያኖስ አስፈልጎ አምጥቶ በሰይፍ አስመታው ኤስድሮስ በዚህ ጊዜ የ12 ዓመት ልጅ ነበረ:: ይሀስ ምንም አያውቅም ብሎ ከእናትና ከእኅቱ ጋር አጋዘው::

አሥራ ስምንት ዓመት ሲሞላው በሌላ ስፍራ ያለ ዐላዊ ኢራንራነኑ ልብከ ወኢመክርከኑ ትተመየጥ እምሃይማኖትከ አልተመለስክምን አለው ፈጣሪውን የከዳ ለጣኦት የሰገደ ይመለስ እንጂ እኔማ ፈጣሪዬን አውቄ ሃይማኖቴን ጠብቄ የምኖር ነኝ አለው:: ከግንድ አሰቅሎ ሥጋውን በእስዋጠብርት አስተፈተፈው እናቱ አንተ ርጉም አንተ ጎሰም እያለች ደሙን እየታፈነች እረጨችበት:: እኅቱም አፎምያ ትባላለች በደንጊያ ፊት ፊቱን ትጠብሰው ጀመረች:: ሰይፍ ጃግሬው ሁለቱንም በሰይፍ መታችው:: እሱንም ጎኑን አስቀድዶ በእሳት አቃጥሉ ለሰማይ አዕዋፍ ለምድር አራዊት ራት ይሁን ብሎ ከዱር አስጣለው:: ጌታ ከሞት አንሥቶ ከንጉሥ ፊት አቀረበው ከሠራዊቱ 800 አመነ በአመላኩ ለኤስድሮስ እያሉ አንገታቸውን ለስለት ሰውነታቸውን ለእሳት ሰጥተው በሰማዕትነት አርፈዋል::

እሱንም ከብረት አልጋ አስተኝቶ ከበታቹ እሳት አስነደደበት አሁንም ከሞተ በኃላ ተነሥቶ መሠከረ ከዚህም በኋላ የወፍጮ ደንጊያ በአንገቱ አሳስሮ ከባሕር አስጣለው፣ ደንጊያው ሠጠመ እርሱ ወጣ::



በመጨረሻ ሥቃዩ ይጽናበት ብሎ ግንድ ላይ በችንካር አስቸንክሮ ተወው:: ጌታ በስምህ የተማጸነውን ምሬልሀለሁ አንተ ከገባሀበት መካን ዕረፍት አስገባልሀለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮት ከ 17 ዓመት ተጋድሎ በኋላ በዚህ ዕለት ዐርፏል::

➢ ከታሪኩ እንጻር መዋዕለ ሕይወቱ ከ292- 329 ዓ.ም መሆኑ ነው::

ሰማዕቱ ኤስድሮስ ላዕከ ቃል ፍጹም
የመልካም ዛፍ ፍሬ ጣፋጭ ነው መልካም
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን
ለዓለም ሲመሰክር ሲያስተምር እምነትን
በምቾት አይደለም ሳይቀምስ መከራን
እንደ ሐዋርያት ሠጥቶ እንጂ ነፍሱን

አንገቱን ለስለት ለችንካር እጁን
ኤስድሮስ ለአምላኩ በአሕዛብ ፊት
እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀሰማዕታት
እስከ ሞት ድረስ ነው የታመነለት
የሰማዩን መንግሥት የክብርም መውረሻ
በርሱ መታመን ነው እስከመጨረሻ

ማቴ 40 22፤ 2413

# ግንቦት 21 ደብረ ምጥማቅ

ከሠላሳ ሶስቱ የእመቤታችን በዓላት አንዱ ነው:: ደብረ ምጥማቅ በምኔተ ገምኑዲ አቅራቢያ የምትገኝ ቦታ ናት:: እመቤታችን በስደት ሳለች ጌታ በዚህ ቦታ በስምሽ ዐባይ ቤተክርስቲያን ይታነጻል ስሙንም ደብረ ምጥማቅ ይሉታል ብሎ ነግሯት ነበር:: ይኸውም አልቀረ:: በዚሁ ቦታ በእመቤታችን ስም ቤተክርስቲያን ታንጾ ስሙ ደብረ ምጥማቅ ተብሏል::

በዚህም ዕለት እመቤታችን ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርታ ከጉልላቱ ላይ በመንበረ ብርሃን ተቀምጣ መላእክት ሊቃነ መላእክት ከበው ሲያመሰግኗት፣ ነቢያት ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት እጅ ሲነሷት ታይታለች:: እስከ አምስት ቀንም ምእመናኑን አረማውያኑን አንድ ወገን አድርጋ ስትባርክ ሰንብታለች:: ከዚህ በኋላ ምእመናንም አረማውያንም በየዓመቱ እነዚህን አምስት ዕለታት በደብረ ምጥማቅ ተሰብስበው የሚያከብሩ ሆነዋል::

# ግንቦት 24 ሀ. ዕንባቆም

ዕንባቆም ማለት ጠቢብ ለባዊ ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ነው ወእብሰለ ተብሲለ ከመ ይስድ ምሳሐ ለአለ የአጽዱ ይላል ንፍሮ ቀቅሎ ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰድሎቱ ዘንተ ምሳሐ ለዳንኤል ዘሀሉ ውስተ ግበበ ባቢሎን ባቢሎን በጉድጓድ ለተጣለ ለዳንኤል

ውስድለት አለው። ሸንኢል ወዴት አለ ባቢሎንንም አላውቅም አለ ወነሥእ በአሐቲ ሥዕርተ ድማሁ ይላል አንዲት ጠጉሩን ይዞ አድርሶት ሳይከፍት ገብቶ ማግቦት ሳይከፍት ወጣ፣ መልአኩ እንዳመጣው መልሶታል ተረ.ዳን

ከዚህ በኋላ እስራኤልን ሲያስተምር ቆይቷል የጌታም ሰው መሆኑ ተገልጾለት እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእም አህጉረ ይሁዳ እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ከይሁዳም ሀገሮች ብሎ ትንቢት ተናገሯል።

> መዋዕለ ትንቢቱ ከ 609-606 ዓ.ዓ

## ሊ. በአተ ግብጽ

ጌታ ተወልዶ 2 ዓመት ሲሆነው ሰብአ ሰገል እጅ ሊነሡ እጅ መንሻ ሲሰጡ "እይቴ ሀሎ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ እያሉ ቢመጡ ሄሮድስ መንግሥቱን የሚነጥቀው መስሎት" ሊገድለው አስቦ ሕፃናቱን ሰብስቡ ብሎ በዚያ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ለዮሴፍ "ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሑር ብሔረ ግብጽ" አለው። ማቴ 2:13 እመቤታችን ደንግጣ ልዋል ልደር..ሰቅል ዕሩቋን ልጇን አዝላ ዮሴፍ ሰሎሜን አስከትላ ሽሽት ጀምራ በዚህ ዕለት ምድረ ግብጽ ገብታለች።

ቅዱሳት መጻሕፍት ደርሰው ወንዙን ተሻግረው ካለፉ በኋላ ጌታ በእግሩ ድንክ..ድንክል እያለ ሲሄድ ከአንዱ ደንጊያ ላይ አሠረ እግሩ ተቀረጸ። እናቱ ....ህ በዚህ ቦታ በስምሽ ዐቢይ ቤተክርስቲያን ይታነጻል ደብረ ...... /.../ ይባላል። ብሏታል። ገዳመ አስቄጥስንም ከሩቅ አሳይቶ በዚያ ቦታ ላይ እንደመላእክተ ሰማይ በንጽሕና የሚያገለግሉኝ ወዳጆቼ ይኖሩበታል ብሏታል።

በማግስቱም ወደ ምዕራብ ሲደርሱ የዮሴፍን በትር ከሁለት ሰብሮ ከመሬት ተክሎ ቢጠጉ ጥዑም ውኃ አፍልቆ አለምልሞ ጥዑም መዓዛ ያላቸው ዕፀው አድርጎ በለሳን /በለ ሰን/ ይባላሉ፣ ለሜሮ ጥምቀት መቀደሻ ይሆናል። ብሏታል፡ እስሙናይን ከሚባል ቦታም ሲደርሱ እንጨቶችና ተራሮች ሰግደውለታል። "ምዕረ ትትፌሣሕ ሶበ ተንዘን ለሕጻን ወላዲቱ፣ ርእያ ዘንብረ ተአምረ ውስተ ደወለ ግብጽ አመበአቱ፣ እንፈርዐ አድባር ወሰገዱ ሎቱ" እንዳለ ደራሲ።

> የእመቤታችን መዋዕለ ስደት ከ 02 - 05 ዓ.ም ድረስ ነው ሙሉ ታሪኩን በዚህ መጽሐፍ ክፍል 1 ከገጽ 38-41 ተመልከት።

## ግንቦት 25 ቅድስት ሰሎሜ



ሰሎሜ ማለት ሰላማዊት ማለት ነው። ለእመቤታችን የእኅቱ ልጅ ናት ማጣት እያቷ ነው፤ ማርያምን ሰፋያንና ሐናን ወልዷል ማርያም ሰሎሜን፣ ሰፋያ ኤልሳቤጥን ሐና እመቤታችንን ወልደዋል። ነገረ ማር፣ ስንክ እመቤታችን የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ዮሴፍ እንትሽን አዋልጂያት አላት። ብትመጣ ብፋህ ሐፃን ታቅፋ አገኘቻት ሕማመ ምጥ ሳይሰማሽ በሴቶች የሚደርሰው ሳይደርስብሽ እንደምን ወለድሽው? አለቻት። በማይመረመር ጥበቡ በድንግልና ፀንሼ በድንግልና እንድወልደው አደረገኝ አለቻት። ካላየሁ አላምንም ብላ ልትዳስሳት እጇን ዘረጋች፣ በእሳት እንደተለበለበ ግንድ ሆኖ ቀረ። የጌታዬ እናቴ እመቤቴ በእውነት ትንቢት የተነገረለትን ሱባኤ የቆጠረለትን አዳኝ እንደወለድሽ አምኛለሁና ይቅር በይኝ ብላ አለቀሰች እኔንማ ምን አድርገሽኛል? ይለቁንስ የማይመረመር ግብሩን ልመርምር ብለሻልና እርሱን ይቅር በለኝ በይው አለቻት። እያለቀሰች ሰውነቱን ብትዳስሰው ተፈውሶላታል። አመስግናዋለች።

ከዚህ በኋላ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ እመቤታችንን እያገለገለች ኖራለች። በስደቱም ጊዜ ሕፃኑን አዝላ ከርሷ ጋር ተሰዳለች። "ነበ ሐጸበት በማይ አልባሲሁ ወአባሉ፤ለሕፃን ድንግል ገኩ ሰሎሜ ዘተንገለ" እንዳለ ደራሲ።

ጌታም በመዋዕለ ስብከቱ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቆጥሯታል። በስቅለቱ ጊዜ ከእመቤታችን ጋር ከመስቀሉ ሥር ሆና ታለቅስ ነበር። ዮሐ 19:25 በተነሣም ጊዜ በሌሊት ወደመቃብሩ ከሄዱ ሴቶች አንዷ ነበረች። ከዕርገት በኋላ ከሐዋርያት ሳትለይ ሐዋርያትን በተልእኮ ስታገለግላቸው ኖራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች።

ሰላም ሰሎሜ ክብርት መብዕት
የጌታ አገልጋይ ሐዋርያዊት
ጌታ አምላክ ክርስቶስ እንቺን ለክብር መርጠሽ
በከንድሽ ታቀፍሽው አዘልሽው በጀርባሽ
ድንግል ማርያምን የአምላክን እናት
ሊያዩአት ተመኝተው አበው ሳያዩአት
በቅንነት ሆነሽ ያገለገልሻት

ታድለሽ ነው እኮ ተመርጠሽ በእውነት
በነዘኗ ጊዜ አዝነሽ ከርሷ ጋራ
ሲጨንቃት ተጨንቀሽ ተቀበልሽ መከራ
ድንግል በልጇ ሞት ስታለቅስ በምር
አብረሽ ተገኝተሻል በመስቀሉ ሥር
ፍቅሯ አገብሮሽ የልጇም ፍቅር

ዮሐ 19 25

## ግንቦት 26 ቶማስ ሐዋርያ

ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው። ቀዳሚ ስሙ ዲዲሞስ ነው ዲዲሞስ ማለት ጨለማ ማለት ነው። ቁጥሩ ከ12 ሐዋርያት ነው።ማቴ 10:3 ዮሐ 20:24 ሐዋ 1:13.

[illegible] ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ያየው በ8ኛው ቀን እሁድ ሲሆን ያመነውም በጦር የተወጋ ጐኑን ደሶ ነው::___ገጽ ተመልከት የእመቤታችንንም ትንሣኤ ሾርገቿን አስቀድሞ ያየ እርሱ ነው____ገጽ ተመልከት

ሀገረ ስብከቱ ሕንደኬ ነው:: ለምክንያት ይሁነኝ ብሎ በ30 ብር ተሾጦ ከመስፍኑ ብሔሩ ከሉክዮስ ቤት እያገለገለ ይኖር ነበር:: ምን ምን መሥራት ትችላለህ? አለው:: ሕንፃ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ እችላለሁ አለው እንኪያስ ሠርተህ ቆየኝ ብሎ ብዙ ወርቅና ብር ሠጥቶት አሕዛብ ምኩሀን ናቸውና እንዲህ ያለ ጠቢብ አገኘሁ ለማለት ወደ ንጉሥ ሄደ:: እሱም ሕንጻ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ ከዚህ የበለጠ አለን ብሎ ለነዳያን መጸወተው:: ከዚያውም ዘንድ አስተምሮ አሳምኗቸዋል:: የሉክዮስም ሚስት አርሶንዋ ከነልጆቿ ከነአገልጋዩቿ አምና ተጠምቃለች::

ሉክዮስ ከሄደበት ሲመለስ ያነጽከው ሕንጻ የቀረጽከው ሐውልት ወዴት አለ? አለው በወርቅና በብርህ ያነጽኳቸው ሕንጻዎች እነኚህ ናቸው ብሎ ያመኑቱን ደኃዎቹን አሳየው ይህ ከፋ ባሪያ ተጫወተብኝ ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ቆዳውን አስገፍፎ ስልቻ አሰፍቶ በአሸዋ መልቶ አሸክሞ ገበያ ለገበያ ሲያዞረው ሚስቱ አርሶንዋ አይታ በድንጋጤ ወድቃ ሞተች:: ሚስቴ የሞተች ባንተ ምክንያት አይደለምን ካዳንካት እኔም በአምላክህ አምናለሁ አለው:: ጌታ ቁስሉን እንደ ውኃ አቀዝቅዞለት ካለችበት ሄዶ ስልቻውን ቢያስነካት ተነሥታለች በዚህም ሉክዮስ አምኖ ተጠምቋል::

ከዚህ በኋላ ስልቻውን ተሸክሞ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ሙት እያነሣ ደውይ እየፈወሰ አሕዛብን አሳምኖ አጠመቀ:: ቀንጠፍያ ሲደርስ አንድ ሽማግሌ ሰባት ልጆቹን ገድለውበት ሲያዝን አግኝቶ ስልቻውን እያስነካ ሰባቱን አስነሥቶሲታል:: በኢናስም የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይተው ከንጉሱ ሚስት ከንግሥቲቱ ጀምሮ እስከ ተራ ገባር ድረስ ያሉት ሁሉ አምነው ተጠመቁ:: ኋላ ግን ካህናተ ጣኦቱ ጥቅም የሚቀርባቸው ቢሆን በተንኮል ከንጉሥና ከመኳንንቱ አጣልተው በዚህ ዕለት አንገቱን በሰይፍ አስመትተውታል::

- ሰማዕትነት የተቀበለው በ 72 ዓ.ም ነው

ንዑድ ክቡር ሰው ነው ተማስ የኛ አቡን
በእጁ የዳሰሰ የአምላኩን ጐን
ዘመዱ ወገኑ ሲሆን አምላያው

እንደምን በሰው ላይ ይጨክናል ሰው?
አምላክ ክርስቶስን ቢሰብካላቸው
አቤት ክፋታቸው መጨከናቸው
ስልቻ አደረጉት ቆዳውን ገፈው
የቆሰለው ሥጋው በጨው ታጥቦ ታሽቶ

የቆዳው ስልቻም በአሸዋ ተሞልቶ
ተሸክሞ ሲዞር በመከራው ፀንቶ
ክብሩን መሰከረ ስልቻውን ነክቶ

የሞተው ተነሥቶ ጉባጣውም ቀንቶ
ስትወልድ በምጧ አዝና አልቅሳ ሴት
ከወለደች ኋላ ደስ እንደሚላት
ጻድቅም ስለጽድቅ የሚሞተው ሞት
የዘላለም ደስታን ያስገኛል ሕይወት

ዮሐ 16 21



ምዕራፍ 4

## ሰኔ 9 ሳሙኤል ነቢይ

ሳሙኤል ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው:: 1ሳሙ 1:20 አንድም ካህን ተአማኒ ማለት ነው:: 1ሳሙ 2:35 ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው፣ አባቱ ሕልቃና እናቱ ሐና ይባላሉ የተወለደው የአርማቴም ሰጸ በሆነች በመሴፋ ሲሆን የብፅዓት ልጅ ነው:: ጡት ሲተው እናቱ አፋ እህል ሳይለምድ ሆዱ ዘመድ ሳወድ ወስዳ ለቤተእግዚአብሔር ሠጥታዋለች::

ሊቀካህናቱ ዔሊ ካህናቱ አፍኒን ፊንሐስ ይባላሉ:: አፊኒን ፊንሐስ ጽዩአነ ምግባር ነበሩ ጌታ ዔሊን ልጆችህን ሥራ ቅጻ አለው:: እነሱ ተመክረው የማይመለሱ፣ ዔሊም ከእግዚአብሔር ይልቅ ለልጆቹ አድልቶ ከሹመታቸው ልሻራቸው ከመዓርጋቸው ላዋርዳቸው የማይል ቢሆን ጌታ አስቀድሞ ለሳሙኤል በራዕይ አስታውቆ ቁጣውን በሞተ እስራኤል ጀምሮ በጼዋ ጽዮን፣ በሞተ አፍኒን ፊንሐስ ጀምሮ በሞተ ዔሊ ፈጽሞ ሳሙኤልን ሊቀካህናት አድርጎ ሾመው::

ክህነት ከምስፍና አንድ አድርጎ ይዞ 40 ዘመን አስተዳድሯቸው አረጀ:: ኢዩ ኤል አብያ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት:: ካህናት አድርጎ ሾማቸው:: ደኃ የሚበድሉ ፍርድ የሚያጓድሉ ቢሆን እስራኤል "አንተሰ ልህቀ ከመ ኢትመግበነ ወደቂቅከኒ ኢሖሩ በፍኖትከ" አንተ እንዳታስተዳድረን አረጀህ ሸመገልህ፣ ልጆችህም አሠርህን አልተከተሉም በዚያውም ላይ በኢያቢስ ዘገለዓድ ባሉ 2 ነገድ ተኩል ወንድሞቻችን ናያስ አምናዊ ቀኝ ቀኝ ዓይናችሁን ገብሩልኝ ይላልና ቅን ፍርድ የሚፈርድልን ከጠላት የሚታደገን ንጉሥ አንግሥልን አሉት ጌታ ከሙሴ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ካህናትን መሳፍንትን አስነሣ እንጂ እንደ አሕዛብ ንጉሥ አንግሦላችኋለን ተው አይሆንም አላቸው ጌታ "ስምዮሙ ቃሎሙ ዘይቤሉከ -የሚሉህን ስማቸው" አለው :: ሳኦል ወልደቂስን ቀብቶ አንግሦላቸዋል:: ለእርሱም እንዲገዙ ሥርዓት ሠርቶባቸዋል:: ኋላም ሳኦል ቢበድል የዕሴይ ልጅ ዳዊትን ቀብቶ አንግሦላቸዋል:: ዳዊትን ከቀባ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ በዚህ ዕለት ዐርፏል::

- የነበረው ከ በ1100 ዓ.ዓ ገደማ ነው::

## ሰኔ 11 ገላውዴዎስ ሰማዕት

ገላውዴዎስ ማለት ዕንቈጳዘዮን ማለት ነው:: ሀገሩ አንጾኪያ ነው:: አባቱ አብጥልማዎስ የንጉሥ ኑማርያኖስ ወንድም ነው:: እንደ ዮሴፍ እስራኤላዊ መልከቀና እንደ ዮፍታሔ እንደ ጌዴዎን ኃይለኛ ነበረ:: የሀገሩም ሰዎች ከመውደዳቸው የተነሣ ስዕሉን ስለው ከአደባባይ አቁመው ያደንቁለት ነበር::

ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ሲፈጅ እርሱ ከቅዱስ ፊቅጦር ጋር ለአንብቦ መጻሕፍት ይተጋ ነበር:: ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና በአምሳለ አረጋዊ መጥቶ ልጆቼ ይህ ንጉሥ ምሕረት የሌለው ጨካኝ እንደሆነ አታውቁምን አሁንም ቢሰማ ይጣላቿሀልና መሰላችሁ እደሩ አላቸው:: በነገሩ ጠላትነቱን አውቀው አ አቡሃ ለሐሰት ረሀቅ እምኔነ ወገድልን አሉት እርእያውን ለውጦ በአምሳለ ገብር ጻሊም ሆኖ ባማችሁኝ አገኙኝ ብሏቸው ሄዶ ንጉሥን ገላውዴዎስና ፊቅጦር ባሉ መንግሥትህ ይጸና መሰሉሃልን አለው:: ካሉበት አስጠ ርቶ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ አላቸው አይሆንም ይህን አናደርግም አሉት ከዚያ እንዳይቀጣቸው ቤተሰቦቻቸውን ፈርቶ ፊቅጦርን ወደ እስክንድርያ ሰደደው እርሱንም ወደ አንጺናው ላከው::

የአንጺናው መስፍን አርያኖስ ምነው ወንድሜ ንጉሥ የወደደውን ወደህ የጠላውን ጠልተህ በግዛትህ በሹመትህ ተደላድለህ አትኖርምን አለው:: አንስ ኢመጻዕኩ ኀቤከ ከመታስሕተኒ በቃልከ ወዳንተ የመጣሁት በሐሰት ቃልህ ልታስተኝ ነውን? አለው:: ለማስፈራራትም ቢሉ ተቆጥቶም ነው ቢሉ የያዘውን ጦር ቢጥልበት ጉኑን ወግቶት በሰማዕትነት ዐርፏል::

> ሰማዕትነት የተቀበለው በ304 ዓ.ም አካባቢ ነው::

ቅዱስ ገላውዴዎስ የአንጾኪያ ወርቅ
ሰማዕተ ክርስቶስ ሐዋርያ ጽድቅ
ሰይጣን ቸግገሌ መስሎ ሊያስተው
ጸሎቱን እንዲተው ሲሸነግለው
ወገድል* ብሎ በእምነት ድል ነሣው
ሊቀጡ ሲወስዱት አሥረው እጆቹን
ሽንገላውን ሰምቶ ቀጣ ዛቻውን
ሳይታለልለት ሳይፈራው ሹሙን

ወዲህ የመጣሁት አይደለም ልሞኝ
በሐሰተኛ ቃልህ እንድታስተኝ
ይልቅ አንካ እንተቱን በቢደፍህ ቅጣኝ
እኔ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ
ብሎ አስመችቶ ሰጠው እንተቱን
ወደ ፈጣሪው ዘንድ ናፍቆ መሄድን
ከዓለም ኑሮ ይልቅ ፈጥኖ ከሚበን
የሚሻል ነውና ከአምላክ ጋር መሆን



## ሰኔ 12 በዓለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ.መ

### ሀ. ዕረፍታ ለቅድስት አፎምያ

ሀገሯ ኪልቅያ ነው:: ባለቤቷ አስተራኒቆስ ይባላል፣ መስፍነ ኪልቅያ ነበረ፣ ታሞ ሞቶ ከሀብቷ ከንብረቷ እየሰጠች እየመጸወተች በጾም በጸሎት ተወስና ትኖር ነበር:: ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ደግ መነኩሴ መስሎ አጋንንትን መነኮሳይያት አስመስሎ መጥቶ ከደጅ ሆኖ አስጠራት:: ከቤት ገብታችሁ በቅዱስ ሚካኤል ስዕል ፊት ጸልዩልኝ አለቻቸው እኛማ በነግህ ጸልየናል፣ እንደው አንቺ ግን ይህ ሁሉ ጾም ጸሎት ምን ያደርግልሻል? ሲበዛ ያለ ጊዜ እንደሚገድል አታውቂምን ሀብትሽን ስጥተሽ መጨረስሽስ ስለምንድን ነው? በዚያው ላይ አንቺ ስትደክሚ የሚደግፍሽ ስታረጂ የሚጦርሽ ልጅ የለሽም፣ ሁለተኛ ማግባት ኃጢአት መሰሉሻልን? እነ አብርሃም እነ ዳዊት ከብዙ <u>ሴቶች</u> ብዙ ልጆች ወልደው የለምን? አሁንም ቤት ሠሪ ጉመን ዘሪ ልጅ ያስፈልግሻልና ባል አግቢ፣ አሺ በይኝ አላት አ አባ እስኬማከ ሠናይ ወቃልከሰ እኩይ አባ ቀብህ መልካም ነበረ ንግግርህ ግን ክፉ ነው አትጹሚ አትጸልዪ ያልከኝ ጌታ ምጽዋተ አበድር እመስዋዕት ብሎ የለምን፣ ሁለተኛ ባል አግቢ ማለትንስ ከምን አገኘኸው አርጋብ እንኳ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ከሌላ ወንድ አይቀርቡም ታዲያ ጥንቱን በንጽሕና ሊኖር የተፈጠረ ሰው ሁለተኛ አላገባም ቢል ዕዳ ፍዳ ሊሆንበት ነውን? ብላ ባሏ ታሞ ሳለ ያሠራላትን ስዕለ ሚካኤል አውጥታ ብታሳየው ሰኔ 12 ቀን መጥቼ ከተመካሸበት ከዚህ ግብሩስ ስዕሉ ጋር አጠፋሻለሁ ብሏት እንደትቢያ በኖ ጠፋ::

ሰኔ 12 ቀን በነግህ ብርሃናዊ መልአክ መስሎ መጥቶ ጾም ጸሎትሽ ስግደት ምጽዋትሽ ዐርጉልሻል፣ ያስሁት ሚካኤል በዚያ ዕለት ቅድመ እግዚአብሔር ይቆማልና መጥቼ አጠፋሻለሁ እንዳለሽ አውቂ ላድንሽ መጥቻለሁና ስገጅልኝ አላት አንተ ማነህ? አለችው

ሊቀመላእክት ሚካኤል ነኝ አላት:: የንጉሥ መልእክተኛ ያለማኅተም ይሄዳልን? በትረ መስቀልህ ወዴት አለ? አለችው:: መስቀል አሲዞ መሳል ልማድ ነው እንጂ እኛስ አንይዝም አላት ቆየኝ ስዕሉን ላምጣልህ ብላ ዘውር ስትል አርአያውን ለውጦ ደብረ ጽልመት መስሎ አነቃት ቅዱስ ሚካኤል እንደ ዓይን ጥቅሻ ፈጥኖ ደርሶ ቀጥቶ አምሉ ገዝቶ እመቀ እመቅ ጥሎታል:: እሷንም ብፅዕት ሆይ ጾም ጸሎትሽ ስጊድ ምጽዋትሽ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶልሻል ዕረፍትሽ ዛሬ ነው ብሏት ዐረገ::

ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ ሥጋውን ደሙን ተቀብላ ጳጳሱን ካህናቱን ወደ <u>ቤት</u> ጠርታ ተመለሰች ጳጳሱን በወርቅ ካህናቱን እንደመዓረጋቸው በብር በናስ መንበር አስቀምጣ አብልታ አጠጥታ ወርቅ ብሯን ለቤተክርስቲያን መሥሪያና ለድሆች ምጽዋት ያደርገው ዘንድ ለጳጳሱ ሠጥታ ዐርፋለች:: ስዕሉም ከእቅፏ ወጥቶ በሮ በሮ ያላንዳች መስቀያ በቤተመቅደሱ በር ተሰቅሎ ተገኝቷል:: ኋላም አብቦ አፍርቶ በአበባው በፍሬው ሕሙማንን የሚፈውስ ሆኗል::

| | |
|---|---|
| ቅድስት አፎምያ ባእምነቷ ጽንታ | እርሱ መቼም ቢሆን ጀምር ከጥንት |
| በጾም በትሩፋት ሰይጣንን ድል ነሥታ | የክህደት መፍለቂያ የሐሰት አባት |
| ገነት ገባች በክብር አክሊል ተቀዳጅታ | ቢመኝ የሚኖር ነው የሰውን መጥፋት |
| እውነት በመሰለች የሐሰት ትምህርት | ከምግባር ልምጥቶ ከእምነታችን |
| መምህር ሳይሆን መስሉ ሰውን ከሚያስት | በጉ እያስመሰለ ከፉ ከፉውን |
| ከሞት ሐዋርያ ከጽድቅ ጠላት | እኛን የርሱ ባሮች እንዳያደርገን |
| ነቅተን እንጠብቅ ጸንተን በእምነት | እስኪ እናፍርሰበት የሰይጣን ምክሩን |

ዮሐ 8:44 ኤፌ 6:11 ያዕ 4:8

## ለ. ዘተፈነወ ኀበ ባሕራን

ሀገሩ እስክንድርያ ነው በዘመነ በጥሊሞስ ልጁ አክሉብጥራ በግብጽ ኾኋል በሚባል ኮከብ ስም ቤተ ጣዖት አሠርታ ሕዝቡ በየዓመቱ መሥዋዕት እየሠው ተረፈ መሥዋዕቱን እየተመገቡ እየዘፈኑ እያጨበጨቡ ያከብሩ ነበር:: ሊቀ ጳጳሳት ኣ| እስክንድሮስ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ «አብያተ ጣዖታት ይተወጸዋ አብያተክርስቲያናት ይትራኅዋ» ብሎ ካወጀ በኋላ አፍርሶ ከቦታው ላይ ቤተክርስቲያን ሠርቶ ታቦተ ሚካኤልን አግብቶ የጣዖቱን በዓል



ተው ይህን እክብሩ ብሎ በየዓመቱ በዚህ ቀን በዓል እንዲሆን ሥርዓት ሠራላቸው::

ይህንንም በዓል ከሚያከብሩ ምእመናንን አንዱ የዚህ የባሕራን አባት ነበር:: ተፀንሶ ሳለ ሞተ በተወለደ ጊዜ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ከቤቷ ገብተው ሕፃኑን ባርከው ይህ ሕፃን የዚህን ባለጸጋ ሀብት ይወርሳል ሲሏት ባለጸጋው ጎረቤቷ ሰማ:: ነገሩን ከልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ኖሮ ሕፃኑ አሥር ዓመት ሲሆነው እናቱ ቀዳ የምታለብሰው ቆርሳ የምታጉርሰው አጥታ ስትቸገር ለርሷ ሃያ ወቄት ሠጥቶ ሕፃኑን ላሳድገው ብሎ ከቤቱ ወሰደው:: ወዲያውም በሣጥን ከቶ ከባሕር ጣለው ማዕበል እየገፋ ወስዶ ከወደቡ አደረሰው:: አንድ በግ ጠባቂ አግኝቶ ወርቅ መስሎት ከቤቱ ወስዶ ቢከፍተው መልካም ብላቴና ሆኖ አገኘ:: ልጅ ይሻ ነበርና ደስ አለው ከበላው እያበላ ከጠጣው እየጠጣ አሳደገው::

ከብዙ ዓመታት በኋላ ያ ባለጸጋ ለንግድ ሲሄድ መሸቶበት ከነርሱ ቤት አደረ:: ባሕራን ባሕራን እያለ ሲጠራው ሰምቶ ባሕራን ምን ማለቱ ነው? አለው ከባሕር የተገኘ ማለት ነው አለው:: መቼ አገኘኸው አለው፣ ጊዜውን ጠቅሶ ሲነግረው ለካስ አልሞተምና አለ:: ሲነጋ ከቤቴ የረሳሁት አለና የድካሙን ዋጋ ላንተ እከፍላለሁ ልጅህን ልላከው? አለው እሺ አለ:: «እንደደረሰ ግደሉት» ብሎ ጽፎ አትሞ ምልክት ነግሮ ስንቁን አሲዞ ወስአሞ በጉሕሉት ከመ ይሁዳ ይላል እንደይሁዳ በሽንገላ ስሞ ሰደደው::

ዘጠኝ ቀን ተጉዞ የአንድ ቀን ጎዳና ሲቀረው ቅዱስ ሚካኤል በአምሳለ ሊቀሐራ በፈረስ ተቀምጦ መላእክትን እንደ ሠራዊት አስከትሎ ከመንገድ ተገናኘው:: አንተ ጉብዝ ወዴት ትሄዳለህ? አለው እንዲህ ካለ ቦታ መልእክት ላደርስ ተልኬ እሄዳለሁ አለው:: እስኪ መልእክቱን አሳየኝ አለው ጌታዬ ለማንም አታሳይ ብሎኛል አለ:: ያም ባይሆን እንደተጠቀለለ አሳየኝ አለው:: አሳየው ወመልአክሰ ነፍሀ ውእተ ክርታስ ወደምሰሰ ኲሎ ዘጽሑፍ ውስተ ውእቱ ክርታስ ይላል እፍ ቢልበት የሞቱን ትእዛዝ አጥፍቶ የሕይወት ትእዛዝ ጽፎበታል:: ያን ይዞ ሄደ <u>ለቤቱ</u> ሹም ሰጠው ቢገልጸው ልጄን ዳሩለት ሀብት ንብረቴን አውርሱት ባሮቼ ይገዙለት የሚል አነበበ:: በቤታው ማኅተም ታትሟልና እንዲሁ አደረገለት::

ባለጸጋው ከንግድ ሲመለስ የዘፈን የጨዋታ ድምጽ ሰምቶ ብላቴናውን አገኝቶ ይህ ሁሉ ዘፈን ጨዋታ ምን ተገኝቷል? አለው:: የላከኸው ሰው ልጅህን አገብቶ ሀብትህን ወርሶ ይኸው አርባ ቀን ሙሉ ይዘፍናል አለው:: ደንግጦ ከፈረሱ ወድቆ ሞቷል:: ባሕራንም ይህ ሁሉ በቅዱስ ሚካኤል ረዳኢነት የተደረገለት መሆኑን በራዕይ ተረድቶ እምና መዓረግ ቅበና ተቀብሎ ቤተክርስቲያን አሳንጾ ሲያገለግለው ኖሯል::

የዋሁ ባሕራን የሌለው ተንኮል
በሚገን ታቹን ከባሕር ሲጣል
ውጦ እንዳያስቀረው ሞገድ ማዕበል
ጠብቆ አወጣው ቅዱስ ሚካኤል
ቅንጣት እንኳ ክፉት በደል ሳይኖረው
ሞት ታዞበት ቢሄድ ወደሚገድለው
መልአኩ ሚካኤል ከሞት ታደገው

ጠላቱን አዋርዶ ገብሬቱን ማዳን
መልአኩ ሚካኤል በእምነት ለጠራው
የደጋ ደጋፊ ረዳት ነው
ከችግር ከመከራ የሚታደገው::
አደራ ሚካኤል ቅዱስ ጉብኘኝ
ደካማ ነኝና ቸል አትበለኝ
በኃጢአቴ በሞገቱ የሚደርስብኝ
ለኔ ካንተ ሌላ ምን ዘመድ አለኝ

## ለ. ቅዱስ ላሊበላ/ ከ1180 - 1207 ዓ.ም/

ላሊበላ ማለት ንህብ እእመረ ጽጋሁ ማለት ነው:: በተወለደ ጊዜ ቤቱ በንብ ተከቦ ነበርና ሀገሩ ሮሃ ነው አባቱ ጃን ሥዩም ይባላል:: ትውልዱ ከዛግዌ ነገሥት ነው:: ያግረ የተዋበ መልክ መልካም ነበረና ያለፈ ያገደመው የወጣ የወረደው ሁሉ ይህንንስ ያንግሠው ይሉ ነበር:: ንጉሡ ሐርብይ /ሐርቤ/ /ገብረማርያም/ ይህን ሲሰማ ታናሽ ወንድሙ ቢሆንም ንጉሥ በመንግሥቱ ቢገዙበት ሲሰማ ታናሽ ወንድሙ ቢሆንም ንጉሥ በመንግሥቱ ቢገዙበት አይወድምና እንግዲህማ መንግሥቴን ሊነጥቀኝ አይደ ለምን ብሎ ይመቀኘው ጀመረ:: ይልቁንም ግብሯ የከፋ ክፉ እኅት ነበረችው:: ሆዱን በጥብጦ አንጀቱን ቆራርጦ ይገድለው ብላ መርዝ በጽዋ ሞልታ ላከችበት:: ተልኮ ያመጣው ዲያቆን ቀምሼ እሰጣለሁ ብሎ ቢጐነጭለት ጠምቧ ብሎ ሞቷል:: የሚንከባከበውም ውሻው ዲያቆኑ የተፋውን ልሶ ሞተ እርሱም ይህ ሁሉ የሆነ በኔ ምክንያት ነው:: ወዳጄ ሞቶ እኔ እቀራለሁን ብሎ የተረፈውን ጨለጠው ቅዱስ ገብርኤል ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ከጌታ ፊት አደረሰው:: የመላእክትን ምስጋና ሰምቶ ከነዚህስ ጋር ብኖር በወደድሁ ነበር አለ:: በግብር እምላካዊ የተሠሩ ሥረወ የሆኑ በዓታትን አሳይቶ እንዲህ ያሉ ሰሜ የሚቀደስባቸውን ማደሪያዎቼን ብታሠራ ክብርህ ከክብራቸው ምስጋናህ ከምስጋናቸው አንድ ይሆናል አለው::



ከዚህ በኋላ ከሠታቱን ኀቡዓቱን ሁሉ ሲያሳየው ቆይቶ በሶስተኛው ቀን ወደ ሥጋው መለሰው ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሰው አፈፍ ብሎ ተነሣ::

ሙቀት ሳይለይህ አይሆንም ብለን እንጂ ገንዘን ልንቀብርህ ነበር፣ ወዴት ቆይተህ መጣህ? አሉት:: እስመ ፍቅር ከመሞት ጽንዕት / / ፍቅር /እንደ/ እስከ ሞት የጸናች እንደሆነች አታውቁምን? የወዳጄ ፍቅር አገብሮኝ ከደረሰበት ደርሼ መጣሁ አላቸው:: የበለጠ የሚጠሉት የሚቃወሙት ሆነዋል::

ወንድሜ ጥፋቴን እንቴ ሞቴን ከተመኙልኝ ከእንግዲህ ከዚህ ምን ያስቀምጠኛል? ብሎ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖርን መርጦ በረሀ ገብቶ በዓት ሠርቶ ተቀመጠ:: እንዲህ ሆኖ ሲኖር የታዘዘ መልአክ ነገ በዚህ ጊዜ እንዲህ ያለች ብላቴና ትመጣለችና እንዲህ በላት አለው ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ እንጂ ይህንንስ አላደርገውም አለ፣ የፈጣሪህን ፈቃድ መተላለፍ ይቻልሃልን? አለው እሺ አለ::

በማግሥቱ ባለው ጊዜ መስቀል ክብራ እንጨት እየለቃቀመች ካጠገቡ ደረሰች:: መልአኩ እንዲህ ብሎ ስላገኘ ነገረኝ አላት:: ሄዳ ለአባቷ ነገረች:: ጥሪው አላት ጠርታ አመጣችው የመልኩን ቀናነት የቃሉን ጥዑምነት አይቶ ለዚህስ ሊድሩለት ይገባል ብሎ ድሮለታል::

ከዚህ በኋላ እንደ አብርሃም እንደ ሳራ ተዋደው ለበጐ ምግባር ተግተው የሚኖሩ ቢሆኑ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ሰማዕተ ሐሰት አስነስቶ ለባል የታጨቸውን ሴት ግድ ብሎ አገባት ብሎ ከንጉሥ አስከሰሰው:: ንጉሡ አስጠርቶ አርባ አስገረፈው:: ከቤት ሲገባ መስቀል ክብራ ወንድሜ ንጉሥ በሰላም ነው ያስጠራህ? አለችው፣ እኔማ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻለኛል ብዬ በረሀ ወድቄ አልነበረምን እንግዲህም ከዚያው እኖራለሁ እንጂ ከሰው ጋር አልሆንም፣ ከወደደሽ ተከተይኝ አላት ተከተለችው በረሀ ገብተው በዓት ሠርተው ተቀመጡ:: ንጉሥ ሠራዊቱን ልኮ ያስፈልገው ጀመር:: ጠባቂ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ኢየሩሳሌም ሄደህ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነሥተህ ትመለሳለህ አለው፣ ይህችስ እንቴ እንደምን ትሆናለች አለ:: ለርሷስ ሚካኤል አለላት ብሎ በአምሳለ ወሬዛ ሆኖ እየመራ

ወሰደው መስቀል ክብራንም ቅዱስ ሚካኤል በእምሳለ ወሬዛ ሠናይ አርአያሁ ሆኖ ከሴቶች ገዳም ወስዶ አደራ ሰጣት::

ላሊበላም ቅዱስ ገብርኤልን እየተከተለ ሲሄድ ደክሞት አረፍ ካለበት በክንፍህ ነቅተህ ሰማየ ሰማያት እንዳደረስከኝ በክንፍህ ነጥቀህ ኢየሩሳሌም አታደርሰኝምን አለው:: ክብር የክብር ክብር እንድታገኝበት ብዬ እንጂ ነው ብሎ በክንፉ ነጥቆ አደረሰው:: ቅዱሳት መካናትን አይቶ እጅ ነሥቶ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ሲደሰት ጌታ በብሩህ ደመና ተገልጾ ክብርህ ወንጌልን ለመስበክ ዓለምን ከዞሩ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ የተካከለ ይሁን፣ በተስፋህ የጸናውን ቢከዳንህ የተማጸነውን ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም አድንልሀለሁ፣ መቃብርህን እጅ የነሣ ጎልጎታ መቃብሬን እጅ እንደነሣ ይሆንለታል፣ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለታል:: ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ መስቀል ክብራ ካለችበት አደረሰው::

በዚያ ሌሊት ጌታ ንጉሡን መንግሥትህን ለወንድምህ ስጥተህ ብልየት ኀልፈት የሌለበትን ሰማያዊ መንግሥት ፈልግ አለው:: መንግሥቱን ለላሊበላ ለቆ በረሀ ወድቆ ከፍጹምነት ደርሶ ዓርፏል::

እሱም መንግሥቱን ከያዘ በኃላ በየሀገሩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠርቷል:: በከተማውም ላይ 11 አቢያተ ክርስቲያናት ከቋጥኝ አስፈልፍሎ አሠርቷል:: ሲሠራም ፈቃደ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማጠየቅ አንድ ክንድ ያህል ተቀርጾ ያደረው በማግሥቱ 2 ክንድ ያህል ሆኖ ይገኝ ነበር:: አብያተ ክርስቲያናቱም

1. ቤተ አማኑኤል
2. ቤተ መድኃኔዓለም
3. ቤተ ማርያም
4. ቤተ ሚካኤል
5. ቤተ ገብርኤል
6. ቤተ መስቀል
7. ቤተ ጎልጎታ
8. ቤተ ጊዮርጊስ
9. ቤተ መርቆሬዎስ
10. ቤተ ሊባኖስና
11. ቤተ ደናግል ናቸው::

እንዲህ አብያተ ክርስቲያናት ሲሠራ አጥቶ እስከ መቸገር ደርሶ ገንዘቡን ለድኃ ሲመጸውት ለጸሎት ሲተጋ ኖሮ በዚህ ዕለት በክብር ዐርፏል::እልመከኑን የሚባል ልጅ የነበረው ቢሆንም መንግሥቱን የወረሰው ግን የወንድሙ ልጅ ነአኩቶ ለአብ ነው::

ቅዱስ ላሊበላ ካህን ወንጉሥ — ጽድቁ ድንቅ ቢሆን ሥራውም የሚገርም
ለኢትዮጵያ ክብር ነው ሞገስ — ስሙን ስታዘክር ትኖራለች ዓለም::
ከፋዎች ቢሆኑ ወገኖቹ በምድር — እርሱ ቅቢ ግሩን ሥጋ እየበላ
የማይመለሱ የማይነኩ ከነውር — ደኃ ጥሬ አጥቶ በረሀብ ሲቆላ
ውሎና አዳሩ ሆነ ከእራዊት ጋር — አልቻለው ብሉ አይቶ ማለት ቻላ
ባለማወቃቸው ሰዎች ቢጠሉት — መጽውቶ ጨረሰው ሀብቱን በጠቅላላ
መላእክት ወዳጆች ጓደኞች ሆኑት — ለድኃ መራራት ማዘን ለምስኪን
ጥበብ ማስ ተዋልን ፈጣሪ ሠጥቶት — የሚያሠጥ ነውና በቀኝ መቆምን::

ሔራ 4. 1ማቴ 25፣ 40 ያዕ 2.16



## ሰኔ 17 አባ ገሪማ ዘመደራ

ቀዳሚ ስማቸው ይስሐቅ ነው አባታቸው ሰናንያስ ንጉሥ ሮም ነበር:: ከልጅነታቸው ጀምረው መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ በዲቁና ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ አድገዋል፤ ኋላም የአባታቸውን መንግሥት ወርሰው ሰባት ዓመት ገዝተዋል::

ከዚህ በኃላ አባ ጰንጠሌዎን ዘጾማዕት ምድራዊ መንግሥት ያልፍ ይጠፋ የለምን? የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደእኔ ና ብለው ላኩባቸው ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ አክሱም አድርሷቸው ተገናኙ መንርገ ምንኩስና ተቀብለው በጾም በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ጀመር ጾማቸውም ሥጋቸው አልፎ አጥንታቸው እስኪቆጠር ድረስ ነበር:: ሲጸልዩም በመንታቸው ገሎ መቆም እስኪያቅታቸው ድረስ እብዝተው ይሰግዱ ነበር::

አንድ ቀን መቁንናቸውን ተቀብለው ከወንድሞች ጋራ ወደ መንገድ ሲሄዱ ቤተክርስቲያን አግኝተው እጅ ሲነሱ ካህናቱ እየተቻኮሉ መጥተው ቅዳሴ ሊታጎልብን ነውና ከእናንተ የሚቻለው አንድ ሰው ይርዳን አሏቸው ሌሎቹ መቅኑናቸውን ተመገበው ነበርና አንችልም አሉ፣ እሳቸው ጠቅለለው የያዟት መቁንናቸውን ከቅጽሩ አስቀምጠው ገብተው ቀድሰውላቸዋል:: እኒያም ወልተው የቀደሱ መስሏቸው ለአባ ጰንጠሌዎን ነገሩ:: እርሳቸውም ሲመጡ መነኩሳቱን አድርጎትም ከሆነ እንዳያፍር ጥቂት እልፍ ብሉ አሏቸው:: አባ ገሪማ ይህን አውቀው ኀድገስ ሰብአ ዕፀው ወእዕፀን ያብሰሉ ለነ እንጨቶችና ደንጊያዎችም ይወገዱልን እንጂ አሉ:: በሁርያቸው የነበሩ እንጨቶችና ደንጊያዎች ሶስት ምዕራፍ ያህል ሸሽተዋል:: «እምገጸ ዕብዩ ሠናይ ወእምነ ግሩም ቃሉ፣ እዕፀን ተማህሉ ወዕፀው ለሰሉ» እንዲል አርኬ:: አባ ጰንጠሌዎን ያዩት የሰሙት ሁሉ ደንቋቸው ግሩም ግሩም ገሪማ ገረምከኒ ኦ ወልድየ ይስሐቅ ግሩም ድንቅ ልጄ ይስሐቅ አስገረምከኝ /አስደሰትከኝ/ አሉ ገሪማ የተባሉት ከዚህ በኋላ መነኮሳቱም አጥፍተናል ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል::

ከዚህ በኃላ መደራ ገብተው በዓት ሠርተው 23 ዓመት በትኅርምት ኑረዋል:: ጌታም ልዩ ሀብት ገቢረ

ተአምራት ሠጥቷቸዋል:: በነገህ ሰንዱ ዘርተው ዕለቱን ለመሥዋዕት አድርሰዋል:: ከመሥዋዕትነት የተረፈውንም በጠፍጣፏ ደንጊያ ቢወቅጡት 77 ቁና ዱቄት ሆኖላቸዋል:: በጎቱም ደንጊያ ላይም ወይን ተክለው አብቅለዋል:: አንድ ቀንም መጽሐፍ ሲጽፉ ውለው የጀመሩትን ሳይፈጽሙ ፀሐይ ልትገባ ስታቆለቁል ጸልየው የጀመሩትን እስኪፈጽሙ ድረስ ባለችበት እንድትቆይ አድርገዋል:: የሚጽፉበትም ብዕር ከእጃቸው ቢወድቅ ወዲያው አብቦ አፍርቶ ተገኝቷል::

ከዚህም የበዙ ተአምራትን ሲያደርጉ ኑረው በዚህ ዕለት በሠረገላ ብርሃን ተሠውረዋል:: ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ480 ዓ.ም ነው::

የሚያየውን ዓለም ባላየው ለውጠ
በላገለገለው ጌታን በተመሰጠ
ሕያው ሆኖ አለ በምቢጋና አጊጦ
ከተጉዘጉዘው ከአዱራት ወጥቶ
በትጎርምት ኖረ ከሞሻ ተከቶ
ዛፎች ቃሉን ሰምተው የተናገሩውን
ተንቃቅለው ሄዱ ለቀው በታቸውን

ደንጊያዎችም ቃሉን አክበሩለት
ደጠኩ ቢላቸው ራቁ ሸሹለት
ክብሩ እንዲገለጥ የአብ ገሪማ
አብቦ ተገኘች ብዕሩ ለምልማ
እንደ አባት ገሪማ የወንጌል መምህር
ሁሉን ትቶ ያደረ ለጌታው በምድር
ለለአንድ ፈንታ ያገኛል አሥር

ማቴ 19:20

## ሰኔ 20 ሕንጸተ ቤታ ለእግዝእትነ

እመቤታችን ባረገች በ4 ዓመት ጳውሎስና በርናባስ ፊልጶስዩስ ገብተው አስተማሩ፣ ሕዝቡም አምነው ተጠመቁ እንግዲህ ወደ ቤተ ጣዖት አትሔዱ አሏቸው የለመድነውን ከከለከላችሁንማ መካነ ጸሎት ስጡን አሏቸው:: እንዲህ ብንላቸው እንዲህ አሉን ብለው ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩ አልቦ ዘትገብሩ ወኢምንተኒ ዘእንበለ ትእዛዙ ወምክሩ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለጌታችን ፈቃድ አንዳች ልታደርጉ አይገባም እናንተም ጸልዩ እኛም እንጸልያለን ብለው ላኩባቸው:: ሱባዔ ሰጨርሱ በዚህ ዕለት ጌታ በሩቅም በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቱን በደመና ጠቅሶ ፊልጶስዩስ ሰበሰባቸው:: ዮሐንስ ጌታዬ ለምን ሰበሰብከን ብሎ ጠየቀ ጌታም በእናቴ ስም ጽንፍ እስከ ጽንፍ አብያተ ክርስቲያናት



እንዲታነጹ ፈቃዴ ነውና ሕንጻ ቤተክርስቲያን ላሳያችሁ ሥርዓት ላስተምራችሁ ነው አለው::

ይህንን ብሎ ወደ ምስራቅ ወሰዳቸው ተራርቀው የነበሩ 3 ደንጊያዎች ነበሩ፣ በተአምራት አቀራርቦ ቁመቱን ወርዱን መጥና ሠጣቸው ወአዕበነኒ ይለመልሙ በእዴሆሙ ይላል እሳት እንዳየው ሰም ከእጃቸው እየለመለሙ /እየተሳቡ/ ቁመቱን 24 ወርዱን 12 ክንድ አድርገው ሠርተውታል:: ወይእዜኒ አንትሙኒ ከመዝ ግበሩ እንግዲህ እናንተም እንዲህ አድርጋችሁ ሥሩ ብሏቸው ዐረገ::

በማግሥቱ እመቤታችንን መንበር ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጉ ቀድሶ አቁርቧቸዋል:: ዳግመኛም ወአርአሶ ለጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስን እጁን ጭኖ ፖትርያርክ አድርጎ ሾሞታል:: በዚህም ጊዜ ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ሐዋርያት አንድ ሆነው አመስግነዋል:: «በሠ

ላስ አዕባን ገጸ ሥላሴሁ ለአምሮ፡ ሐኒጸ ቤትኪ ድንግል ድኀረ ፈጸመ ሣርሮ፤ አመ ወረደ ለበዓል ምስሌኪ በአንብሮ፡ እንዘ ይብላ ቃለ ለዘምሮ ልዑል ቀደሰ ማኅደሮ፡ ደናግል ለጽጌኪ ዘበጣ ከበሮ» እንዲል አርኬ፤

➢ ታሪኩ የተፈጸመው በ53 ዓ.ም ነው

## ሊ. ኤልሳዕ ነቢይ /ከ852 – 798 ዓ.ዓ/

ኤልሳዕ ማለት ዐቃቤ ሀገር ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ይሳኮር ነው፣ አባቱ ዮሳፍጥ ይባላል 1ኛ ነገ 19፥16

መምህሩ ኤልያስ ከርሱ የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ካንተ ሳልወሰድ የምት ሻውን ለምን ብሎት ባንተ ያደረ መንፈስ እግዚአብሔር በኔ እጽፍ ድርብ ይሁን ብሎ ለምኖ አድሮበታል:: ይህም ሊታወቅ ኤልያስ አንድ ሙት ቢያስነሣ እርሱ 2 ሙታን አስነሥቷል ኤልያስ 1 ጊዜ ዮርዳኖስን ከፍሎ ቢሻገር እርሱ 2 ጊዜ ከፍሎ ተሻግሯል::

መምህሩን ሸኝቶ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሲመለስ ኢያሪኮ ከከተማ ገብቶ ሠናይ ንብረታ ለዛቲ ሀገር በዚህች ቦታ መኖር መልካም ነው አለ:: ሊቀበሉት የመጡ ደቂቀ ነቢያት ወማየ ብሑራብ እኩይ ውእቱ ውኃው ግን ወላድ የሚያመክን መካን የሚገድል ክፉ መራራ

ነው አሉት። በአዲስ ሸክላ ጨው አምጡልኝ አላቸው። አመጡለት ከምንጭ ላይ አድርጎ ከመ ዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፈወስክዎ ለዝንቱ ማይ ከመ አልቦ ዘይመክን እምኔሁ ወዘይመውት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከርሱ የሚመክን የሚሞትም እንዳይኖር ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ይላል ብሎ ቢጸልይበት ምሬቱ ጠፍቶ ጣፋጭ ሆኗል ምሳሌነቱን ከዘመነ ስብከት ታሪክ ተመልከት።

ከዚያ አልፎ ቤቴል ሲደርስ ሕፃናት ዕርግ በራህ ውጣ መላጣ እያሉ ዘበቱበት 2 ድባት አስነስቶ 42ቱን አስፈጃቸው 2 ነገ 21-25

በቀርሜሎስ ሳለ አንዲት ሴት መጥታ ነቢየ እግዚአብሔር ባሌ ቢሞት ባለ ዕዳ ልጄን ሊነጥቀኝ ነው ብላ ይረዳት ዘንድ ተማፀነችው ከቤትሽ ምን አለ? አላት ጥርኝ ዘይት አለችኝ አለችው። ከባልንጀሮችሽ ማድጋ ተውሰሽ ሙዪው አላት። ሶስት አራት ማድጋ ተውሳ ጠብ ጠብ ብታደርጋቸው በዘይት ተሞልተው ተገኙ። ይህን ሽጠሽ ዕዳሽን ክፈዪ የቀረውን ተመገቢ ብሏታል። 2 ነገ

በፍኖተ ሱናም በሚያልፍም ጊዜ በእንግድነት የምትቀበለው አንዲት ሱናማዊት ነበረች፤ ማረፊያ ሰገነት ሠርታለታለች። አንድ ቀን ደቀመዝሙሩ ግያዝን ምንእናድርግላት? አለው። እርሱም ልጅ ስለሌላት ታዝን ይሆናል አለ። አስጠርቶ የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ሕፃን ትታቀፊያለሽ አላት እንዳላትም በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለደች። ሕፃኑ ባደገ ጊዜ አባቱን ተከትሎ መስክ ወጥቶ ባለ ድንገት ሞተ። ሄዳ በውኑ ትወልጂያለሽ ብትለኝ እንጂ እኔ ለምኜ ነበርን? ብላ አለቀሰችበት ቢሄድ ከአልጋው ተኝቶ አገኘው፡ እጁን ከእጁ እግሩን ከእግሩ ገጥሞ እየወደቀ እየተነሣ ሲጸልይ በሰባተኛው ተነሥቶላታል። 2 ነገ 4:25-37

ከዚህ በኋላ ዘመነ ረሀብ ሆነ ደቂቀ ነቢያት ወደርሱ ተሰበሰቡ። ደቀመዝሙሩ ግያዝን ቅጠል ለቅመህ ቀቅለህ ስጣቸው አለው። እርሱም ሳይመርጥ ያገኘውን ሁሉ ቀቅሎ ሠጣቸው። ቀምሰው ቢመሩቸው ሕምዝ ባቲ ለልሕኩተ ነቢይ መርዝ አለበት አሉ። ዱቄት አላትሃ ስጣቸው አለው፤ አላትኖ ቢሰጣቸው ምሬቱ ጠፍቶላቸው ጣፍጧቸው ተመግበውታል 2 ነገ ምዕ 4 ምሳሌነቱን ከዘመነ ሰብከት እይ።



በጊዜው የነበረ የሶርያ ሊቀሠራዊት ንዕማን በፈረስ በሠረገላ ሆኖ ሠራዊት አስከትሎ ወደርሱ መጣ ስለምን ቢሉ ሰውነቱ በለምጽ ነዶ ነበርና ሚስቱ ሲገባ ሲወጣ እያየችው ታዝን ነበር ከእስራኤል የተማረከች አገልጋይ ነበረቻት በሀገራችን ደውይ የሚፈውሱ ሙት የሚያነሱ ነቢያት አሉ ከነርሱ ዘንድ ቢሄድ ይድን ነበር ብላ መከረቻት። ነገረችው እርሱም ንጉሡ ወልዱ አዴር አፈውሶ ለንዕማን ቀልዔየ ወዳጄ ንዕማንን እንዲፈወስ አድርገው ብሎ ለእስራኤሉ ንጉሥ ጽፎለት ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ንጉሡም መልእክቱን አንብቦ አሁን በምን ልጣላው ብሎ ነው እንጂ እኔ መግደል ማዳን የምችል አምላክ ነኝን? አለ ኤልሳዕ ይህ ተገልጾለት ወደኔ ላከው ብሎ ልኮበት በዚህ ምክንያት መጥቷል። ገና ከደጅ ቆሞ ሳለ በዮርዳኖስ ውኃ 7 ጊዜ ተጠመቅ አለው ነቢይ ሲባል በቃሉ ተናግሮ በእጁ ዳሶ የሚፈውስ መሰሎኝ እንጂ ውኃማ በሀገሬስ መች አጣሁ ብሎ ተቆጥቶ መለስ ሲል ነቢየ እግዚአብሔር የተናገረው አይቀርምና ያለህን አድርግ አሉት ሂዶ 7 ጊዜ ተጠምቆ ድኗል።

በሚሄድም ጊዜ 10 መክሊት ብር 6 ሺህ ወቄት ወርቅ 10 እጀ ጠባብ ይዞ ይህን ተቀበለኝ አለው እማሆጡኑ ለጼጋ እግዚአብሔር በወርቅ ወበብሩር የእግዚአብሔርን ስጦታ በወርቅ በብር አሸጠዋለሁ ብሎ እንቢ አለ። እንኪያስ ምን ላድርግልህ አለው። በእግዚአብሔር እመን ለሱም ብቻ ስገድ አለው። ለዚህማ ጌታዬ ከቤተ ጣዖት ሲገባ እኔን አስከትሎ ሲሰግድ ትከሻዬን ተደግፎ ነው ከፈቀድክልኝ ግን አፈር ጭኜ ወስጄ መደብ አሠርቼ እሱ ለጣዖቱ ሲሰግድ እኔ ስመ እግዚአብሔር ጠርቼ ልስገድ አለው። ይሁን አለው ጭኖ ወስዶ መደብ አሠርቶ ስመ እግዚአብሔር እየጠራ የሚሰግድ ሆኗል።

ግያዝ ወርቅ ብር አልቀበልም ሲል አይቶ ነበርና ሲሄድ ከወደ ኋላ ተከትሎ ነቢየ እግዚአብሔር እንግዶች መጥተውበት ወርቅ ብር ላክልኝ ብሏል አለው። አይሆንም ቢለኝ እንጂ ሁሉንስ ውሰድ ብዬ አልነበረምን ብሎ 2 መክሊት ብር 2 እጀ ጠባብ ሠጠው። ሲመለስ ከወዴት መጣህ አለው እዚሁ ነበርኩ አለ። ንዕማን ሊቀበልህ ከሠረገላው ሲወርድ ልቤ ካንተ ጋራ አልሄደምን ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ ወርቅ ብር ሽተህልና የርሱ ለምጽ ባንተና በቤተሰቦችህ ይሁን አለው በለምጽ ተመቶ እንደ በረዶ ነጥቶ ወጥቷል። 2 ነገ ምዕ 5

ደቂቀ ነቢያት ቦታ ጠበበን በዮርዳኖስ ቤት ሠርተን እንኑር አሉት እሺ ይሁን አላቸው:: በዮርዳኖስ ዳርቻ እንጨት ሲቆርጡ አንዱ ምሣሩ ከባሕሩ ገባበት የተበደርኩት ምሣር ገባ ብሎ አዘነ ኤልሳዕ ቅርፊት ልጦ በገባበት በኩል ቢጥል የማይዘቅጠው ቅርፊት ዘቅጦ የሚዘቅጠው ምሣር ተንሳፈፈ ያውልህ ብሎት እጁን ዘርግቶ ወስዶታል::

ከዚህ በኋላ ወልደ አዴር ንጉሠ ሶርያ እስራኤልን ሊጣላ ምሽግ መሽጎ ተቀመጠ:: ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ በዚህ ሂድ በዚህ አትሂድ ብሎ ላከበት ያም የማይሆንለት ቢሆን ምሥጢር የሚያወጣ አለን? አለ:: የምታስበውን የምትናገረውን እያወቀ የሚነግረው ነቢዩ ኤልሳዕ ነው አሉት ይዛችሁ አምጡልኝ ብሎ ሠራዊቱን ሰደደ:: ግያዝ በፈረስና በሠረገላ ሆነው ከበዋቸው ቢያይ ደነገጠ ኤልሳዕ ከኛ ጋር ያሉት ይበዛሉ አለው ቢወጣ በእነርሱ ወገን መላእክት በሠረገላ እሳት ሆነው ታዩት:: ኤልሳዕ ይህ ሕዝብ ዕውር ይሁን ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ:: ሁላቸውም ታወሩ:: ሂዶ ወዴት ትሄዳላችሁ ማንንስ ትፈልጋላችሁ? አላቸው:: የምንሄደው ዶይታን የምንፈልገው ኤልሳዕን ነው አሉት:: እንኪያስ መንገድ ስታቹህል ብሎ እየመራ ሰማርያ አድርሶ ዓይኖቻቸው የሚያዩ ይሁኑ ብሎ ጸለየ፡ አዩ:: የእስራኤል ንጉሥ አባቴ ልግደላቸውን? አለው:: የሚበሉት የሚጠጡትን ስጣቸው እንጂ ክፉ አታድርግባቸው አለው:: ኢትማእ ለእኩይ በእኩይ የምትል ሕገ ወንጌል እንድትሠራ አውቆ ጠላቶቹን አብልቶ አጠጥቶ ሸኝቷቸዋል:: እነዚያም ጠላቱን አገኝቶ አብልቶ አጠጥቶ የሚሸኝ አለን ብለው እያደነቁ ወደሀገራቸው ተመልሰው ብዙ ዘመን ሳይጣሉ ኖረዋል::

ኤልሳዕም እንዲህ ባለ ግብር 50 ዘመን አስተምሮ በሰላም ዐርፏል ካረፈም በኋላ እስራኤል በሞአባውያን የተገደለ የአንድ ሰው በድን ወስደው ከመቃብሩ ቢያኖሩት ተነሥቷል::
2 ነገ 13:20

## ሰኔ 21 ቅዳሴ ቤታ ለእግዝእትነ

በሰኔ 20 ቀን የተተረከውን ከገጽ ________ ተመልከት



## ሰኔ 23 ሰሎሞን ንጉሥ /ከ983 - 931 ዓ.ዓ/

ሰሎሞን ማለት መስተሳልም ማለት ነው:: አባቱ ዳዊት እስራኤልን 40 ዘመን ገዝቶ አረጀ፣ አዶንያስ ወልደ አጊት /የዳዊት ልጅ ነው/ አባቴ ዳዊት አረጀ አቤሴሎምም ሞተ ወንድሜ ሰሎሞን እንዳይነግሥ ሕፃን ነው የአባቴ መንግሥት ለኔ ይገባል ብሎ ከኢዮአብ ጋር ሰሙ ለኔ መብቱ ላንተ ይሁን ብሎ መክሮ ቅብዐ መንግሥት የሚቀባው አብያታርን ይዞ በኬልቲ ዘዘኤልቲ በዓል አድርጎ ነገ ሥሁ አለ::

ነቢዩ ናታን የአዶንያስ መንግሥት እንደማይጸና አውቆ የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን /የኦርዮ ሚስት የነበረች ኋላ ዳዊት ያገባት እስራኤላዊት/ ኢሰማዕኪኑ ከመ ነግሠ አዶንያስ ወልደ አጊት፡ አዶንያስ እንደነገሠ አልሰማሽምን አሁንም ሂደሽ ንጉሥን ተሐሰውኑ ቃልከ እግዚእየ ከመ ሰሎሞን ወልድየ ይነግሥ እምድኅሬየ በዪው እኔም መጥቼ ነገርሽን አጸናልሻለሁ አላት ሂዳ ጌታዬ ከኔ በኋላ ልጄ ሰሎሞን ይነግሣል ያልከው ቃልህ ታበለን? አለችው:: ወዲያውም ናታን መጣ እሷ ወደ እልፍኝ ገባች:: ምነው ደገኛ ልጅህ አዶናያስ ሲነግሥ ሳትጠራኝ ቀረህ? አለው ነገራቸው እንድ እንደሆነ አውቆ ቤርሳቤህን አስጠርቶ ሕያው እግዚአብሔርን ከኔ በኋላ ልጄ ሰሎሞን ይነግሣል አለችው:: ስለቱንም ነቢዩ ናታንን ካህኑ ሳዶቅን ብንያስ ወልደ ዮዳሄን ኬልቲ ፌልቲ የሚባሉ ጭፍሮችን ጠርቶ በበቅሎዬ አስቀምጣችሁ ግዮን ወደሚባል መናፈሻ ወስዳችሁ ቀብታችሁ አንግሡት አላቸው ወስደው ቀብተው አነገሡት ሕዝቡም ሕየው ወልደ ንጉሢ ሺህ ዓመት ያንግሥህ እያሉ በዕልልታ በሆታ ተቀበሉት::

የአብያታር ልጅ አኪማሆስ አባቱን ከነገር ሊያድን ወደ እነ አዶንያስ ሂዶ የሆነውን ነገራቸው ወእንዘ ይሠረቱ ጽውዓኒሁ ለአዶንያስ ይላል ታዳሚዎቹ አንድ አንድ እያሉ ከድተው ከሰሎሞን ገብተዋል:: አዶንያስ ኢዮአብና አብያታር ግን አቅርንተ ምሥዋዕ ይዘው ተማጸኑ ሰሎሞን ለጊዜው ምንም አላላቸውም::

ሰሎሞን ወደ ቤተመንግሥት ሲደርስ ዳዊት ከዙፋኑ አስቀምጦ እጁን በራሱ ጭኖ እግዚአ ኩነኔ ሀበ ለንጉሥ አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፡ ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ብሎ ጸለየለት፣

እርሱንም ኩንን በጽድቅ ሕዝብህን በእውነት ግዛ /ምራ/ ብሎ መከረው፤ ሕዝቡንም የ12 ዓመት ሕፃን ሸሙብን እንዳይሉ ወይ ወርድ ከመ ጢል ውስተ ፀምር - ጠል ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ ነገሩ ምክሩ ከሰው ልቡና ይስማማልና ብሎ መኸሯቸዋል:: 1 ነገ ምዕ 1 መዝ 71-1

ከዚህ በኋላ ዳዊት ዐረፈ እርሱም «ልጄ ሰው ሁን» /1ነገ/ ያለውን የአባቱን ቃል እያሰበ ደኃ እንዳይበድል ፍርድ እንዳያጓድል እየተጠነቀቀ መንግሥቱን ይመራ ጀመር:: በገባኦን መሥዋዕት የሠዋ ዕለት ጌታ ምን ትሻለህ?ሲለው፤ እሱም ጌታ ሆይ ድኃ እንዳልበድል ፍርድ እንዳላጓድል ጥበብንና ማስተዋልን ስጠኝ ቢለው እውነት እልሀለሁ ካንተ በፊት የነበሩ ያላገኙትን ካንተም በኋላ የሚነሡ የማያገኙትን ጥበብ ሠጥቼሀለሁ ያልለመንከኝ ሀብትንም የሚመስልህ የሌለ አድርጌ ሠጥቼሀለሁ:: እንደ አባትህ እንደ ዳዊት በፍጹም ልብህ ከኔ ጋር ብትሆን እኔም ካንተ ጋራ እሆናለሁ፤ ሲሊው ራዕይ አዩ:: እንዲያውም ድንቅ ጥበብንና ማስተዋልን አግኝቷል 1 ነገ 3 4:15

አንድ ቀን ንጉሥ ፍረድልን ብለው ሁለት ሴቶች ቀረቡ ምን ሆናቹኃል አላቸው አንዲቷ ንጉሥ ፍርድ ልብስ ሁለታችን ካንድ ቤት እንኖራለን፣ እኔ በወለድሁ በ3ኛ ቀን እርሷም ወለደች፣ እንቅልፍ ሲይዛት ሕፃኑን ተጭና ገደለችው፤ እኔም ተኝቼ ሳለሁ ልጄን ወስዳ የሷን ልጅ ከጎኔ አስተኛችው ልጄን አስመልስልኝ አለችው ሁለተኛይቱም ዋሸታለች የሞተው የርሷ ነው ይህ ልጂ ነው አለች:: እርሱም የሞተውማ አንድ ጊዜ ሞቷል ይሆን ያለውን ከፍላችሁ ሀቡ መንፈቆ ለዛቲ ወመንፈቆ ለእንታክቲ እኩ ሌታውን ለዚህች እኩሌታውን ደግሞ ለዚያች ስጡ ብሎ አዘዘ ያች አልወለደችውምና እሺ ብላ እጅ ነሳች ይህችኛዋ ግን ልጄስ ከሚሞት እሷ ትውሰደው አለች:: የዚያች ልጅ እንዳልሆነ አውቆ ለዚህች ሰጥቷታል: እስራኤልም ጥበቡን አድንቀዋል:: 1ነገ 3:16- 28

አባቱ ዳዊት ቤተ መቅደስ ልሥራ ባለ ጊዜ አኮ አንተ ዘትነድቅ ሊተ ቤተ አላ ወልድከ ዘወጽአ እምሐቌከ ውእቱ ይነድቅ ሊተ ቤተ በስምየ ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህ በስሜ ቤት ይሠራልኛል ብሎት ነበርና /2 ሳሙ 2:12/ ሰሎሞን ጌታ ጥበቡን ገልጦለት ከጢሮስ ዝግባና ጽድ እያስመጣ ቤተመቅደስ ሠርቷል::



| |
|---|
| በ586 ዓ.ዓ ሰልምናሰር ያፈረሰው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ነው |

ቤተመንግሥቱንም አብሮ በ20 ዓመት ውስጥ ሠርቷል:: 2 ዜና ፩:1

መንግሥቱን አጽንቶ ግዛቱን አስፋፍቶ የዳዊት ከተማ ጽዮንን አድሶ አስፍቶ ሲኖር በ4ቱ መዓዘናት ያሉ ነገሥታት ጥበቡን ለማየት እየመጡ ይጠይቁት እጅ መንሻም ይሰጡት ነበር:: ከነዚህም አንዷ የሀገራችን ንግሥት የነበረች ማክዳ ነበረች:: ታምሪን የተባለ ኢትዮጵያዊ ጥበቡን ነግሯት ልታየው ወደደች

| |
|---|
| ክብረ ነገሥት ገጽ 12 |

ለንግድበሚሄድ ጊዜ እኔ ወደርሱ እሄዳለሁና መንገድ እንድትመራኝ በቶሎ ተመለስ ብላ ለሰሎሞን የሚሰጥ ለርሱም የሚሆን ብዙ ወርቅና ብር ሰጠችው:: እርሱም ኢየሩሳሌም ደርሶ መልእክቱን አድርሶ በቶሎ ተመለሰ በሀገራችን ብቻ ያለ ሽቱ የዝሆን ጥርስ ዕንቁ፣ ወርቅና ብር ይዛ 500 ደናግል አስከትላ ሄደች:: ከእግሯ ላይ እንደ በግ እንደ ፍየል ዘርዛራ ፀጉር ነበረባት ስትገባ ከደጁ ወድቆ የነበረ ግንድ ቢነካው ተቀርፎ ወድቆላታል:: ገባሬ ተአምርነቱን ተረድተው እሱ በ 1 ብር እርሷም በ 1 ብር ለብጠው ከቤተመዛግብት ተቀመጠ

| |
|---|
| ከርሱ በኋላ የተነሱ 28 ነገሥታት በ1 በ1 ብር ለብጠውት አያሁድ 30 ውን ብር ለያሁዳ ሠጥተው በግንዱ ጌታን ሰቅለውታል:: |

ወይህገሯም እስክትመለስ ድረስ የሰባ እያረደ የጠራ እያወረደ ባማረ ቦታ አስቀምጧታል::

አንድ ቀን ግብር አግብቶ ካዳራሽ ተገኝቶ በቀኙ አስቀመጧት መኳንንት መሳፍንቱ ወይዛዝርቱ እንዳያዩአት መንጠላዕተ መጋረጃ ጋረዷት እርሷ ግን ታያቸዋለች ምግቧን ከርሱ ጋራ ጓልታ የአሳላፊዎቹን ሥርዓት የምግቡን ዓይነት ሌላውንም ጥበቡን ሁሉ አይታቸ ብዙም እንቆቅልሽ አምጥታ ጠየቀችው ወአልቦ ዘኢፈከረ ላቲ ወተሠወረ እምኔሁ ይላል ሳይመልሳት ተሠውሮት የቀረ የለም ሁሉን መለሰላት ጥበብህን ነግረውኝ መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ አላመንኩም ነበር፡ አሁን ግን ከሰማሁት እጅግ የሚበልጥ ጥበብህን አየሁ አንተን በእስራኤል

ዙፋን ያስቀመጠ አምላክህ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ብላ አመሰገነች::

ግብር ሲመለስ ወደ ማረፊያዬ ሂጄ እንዳርፍ አሰናብተኝ አለችው:: ዛሬማ ከዚህ እደሪ እንጂ ለምን ትሂጃለሽ? አላት ድንግል ስለሆንኩ በዚህ ለማደር እፈራለሁ ድንግልናዬንም ካልጠበቅሁ አባቴ ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ይፈርሳል አለች:: ስለምን? አላት ጥንቱን የሀገራችን ሰዎች ንጉሥ ነው እያሉ 400 ዘመን ለዘንዶ ሲገብሩ ይኖሩ ነበር የእኔ አባት አንጋቦስ ዘንዶውን ገድሎ ነገሠ:: በፍጻሜ ዘመኑ ሕዝቡን አረጀሁኝ ከኔ በኋላ ልጆቼን እንድታነግሡልኝ ቃል ግቡልኝ አላቸው እነርሱም ወንድ ልጅህ ወንድም ባይኖር ወንድ ሳታውቅ ሴት ልጅህን እናነግሣለሀለን አሉት እሱም ሲሞት እኔን አነገሱኝ አለችው:: እንዲህስ ከሆነ ተላልፌ አልነካሽም አላት:: ማልልኝ አለችው አንቺም ከሀብቴ ከንብረቴ እንዳትነኪብኝ ማይልኝ አላት ጥበበኛ ስትሆን እንዲህ ያለ ተራ ነገር ትናገራለህን ወርቅ ብር በሀገሬ ሞልቷል ወጻንተ መምጣቴ ጥበብህን ላይ እንጂ ወርቅ ብር ፈልጌ ነውን?አለችው፡ ግድየለም ማይልኝ አላት ማለችለት፡ እሱም አስቀድሞ መሐላ ላያፈርስ ማለ:: ደንገጡሯን ይዛ ተኛች::

ጥቂት ተኝታ ውኃ ጠማት ውኃ ጠማኝ ከኩስኩስቱ ቀድተሽ አምጪልኝ አለቻት ሰሎሞን ሲያንቀላፋ ዓይኑን ይገልፃል ሲነቃ ዓይኑን ይከድናል:: ዓይኑን ገልጾ ብታየው ንጉሥ ያየኛል አለቻት ሁለተኛ ጠምቶኛል አምጪልኝ አለቻት አይሆንም ያያል አለቻት:: ሶስተኛ አሁንስ አያይም አምጪልኝ አለች ሰሎሞን ከእንቅልፉ ነቅቶ ዓይኑን ከድኖ ነበር:: የተኛ መስሏት ቀድታ ሰጠቻት ስትጠጣ እጇን ይዞ ምነው መሐላሽን አፈረስሽ? አላት ውኃ ቢጠጡ መሐላ ይፈርሳልን አለችው ምድር በውኃ ላይ ጸንታለች አትክልት አዝርእት ዕፅዋት በውኃ ይበቅላሉ ያብባሉ ደግሞም እንጂ ውኃ ቢጠጡት ያረካል ቢታጠቡበት ያነጻል፡ ታዲያ ከዚህ የበለጠ ምን ሀብት አለ? አላት በዚህ ተረታች አብረው አደሩ::

በምትሄድ ጊዜ ጸንሻለሁና በወለድሁ ጊዜ ሴት ወይም ወንድ መሆኑን እንዳስታውቅህ ምልክት ስጠኝ አችው ወንድ የወለድሽ እንደሆነ ይህን ላኪልኝ ብሎ የወርቅ ቀለበት ሴት ከሆነችም ይህን ላኪልኝ ብሎ የብር ቀለት ሠጣት:: ይህንንም ምክንያት አድርገሽ ለእግዚአብሔር ስገጂ ብሎ ከታቦተ ጽዮን ሀብት 1 መጋረጃ ሰጣት



ይህን ይዛ በክብር በመዓረግ ወደ ሀገሯ ተመለሰች:: ስትሄድም ዓምደ ብርሀን ተከትሏት ሲሄድ አይቶ ክብር ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ብሏል::

መዋዕለ ጽንሷ ሲፈጸም ወንድ ልጅ ወለደች:: ስሙንም ዕብነሐኪም አለችው የብልህ ልጅ ማለት ነው:: የምስራቹንም የወርቁን ቀለበት ላከችለት:: ወንድ ልጅ አገኘሁ ብሎ ደስ አለው አይታችሁት ኑ ብሎም ባለሟሎቹን ብዙ ወርቅና ብር አሲዞ ላከ::

ዕብነ ሐኪም 19 ዓመት ሲሆነው አባቱን ሊያይ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ሰሎሞን መኳንንት መሳፍንቱን ልጄን ተቀበሉ ብሎ ልብሰ መንግሥቱን፣ ዘውዱንና የሚቀመጥበትን ሠረገላ አሲዞ ላከ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ በሠረገላው ሆኖ ሲገባ መልኩ አባቱን ይመስል ነበርና ንጉሥ ወዴት ሄዶ ነበር? አሉ ሲደርስም ምኒልክ እንደምን ዋልህ እንደምን አለህ ብሎ ሳመው ከዚህ በኋላ ስሙ ምኒልክ ተብሏል:: ምን ያምር ማለት ነው::

ከዚህ በኋላ ምኒልክ ሲወጣ ሰሎሞን እየመሰላቸው ተከትለውት ይወጣሉ ሲገባ ይገባሉ:: ይህ የሚያስቸግራቸው ቢሆን ለሁለት ጌታ መገዛት አይቻለንምና አንግሠህ ወደናቱ ሀገር ላከው አሉት:: እኔን የበኩር ልጅህን ላክ ካላችሁኝ እናንተም ወንድም ሆነ ሴት የበኩር የበኩር ልጆቻችሁን ከልጄ ጋራ ትልካላችሁ አላቸው እሺ ይሁን አሉ:: ሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ ልጁ አዛርያስን ሠጠ:: ሌሎቹም እንዲሁ የበኩር ልጆቻቸውን ሠጡ:: የካህናቱ ልጆች ሂዱ ካላችሁን ምክንያት አድርገን ለእግዚአብሔር እንስግድበት ዘንድ ከታቦተ ጽዮን ሀብት አንዱን ስጡን አሉ:: የታቦተ ጽዮን የውስጠኛው ልብሰ ይሰጣችሁ አላቸው:: እነርሱ ግን ከታቦተ ጽዮን መለየት አልወደዱምና አንድ አንድ ወቄት ወርቅ አዋጥተው በታቦተ ጽዮን ልክ ታቦት ቀርጸው በወርቅ ለብጠው በታቦት ጽዮን ቦታ አኑረው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሄዱ::

ከተማውን ለቀው ሲወጡ ኢየሩሳሌም ተናወጠች:: ሰሎሞን ሳዶቅን አስጠርቶ ይህ ልጅ በተነጻነሰባት ሌሊት ፀሐይ ከምድር ወርዳ በኢየሩሳሌም ጥቂት ስታበራ አይቻለሁ አሁንም ሄደህ ታቦተ ጽዮን መኖሯን ተመልከት አለው:: ቢገባ ልጆቻቸው የሠሯትን እንጂ ታቦተ ጽዮንን አጣት ደንገጠ ሄዶ የለችም ወስደዋታል አለው:: እንደ ነፋስ በሚበር ሠረገላ ሆኖ ተከተላቸው በ3 ቀን የሄዱትን በ1 ቀን ተጉዞ ዜናቸውን ቢጠይቅ ከኛ በሠለስት ተነሡ

ሲሄዱም ሠረገሎቻቸው ፈረሶቻቸው በንጉሥ ያህል መሬት ለቀው ይታዩ ነበር ይህን ጊዜም የ7 ቀን ጎዳና ተጉዘው ይደርሳሉ አሉት፣ እያሉ ተመለሰ:: እኒያም ብንነግረው መልሶ ለአባቱ ይሰጠናል ብለው ፈርተው አልነገሩትም ነበር:: የምንነግርህ አለ ለአባትህ መልሰህ እንዳትሰጠን ቃል ግባልን ብለው ቃል ከገባ በኋላ በቤተመቅደስ የነበሩ የሕግና የጥበብ መጻሕፍትንና ታቦተ ጽዮንን ይዘን መጥተናል አሉት:: ፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ ቢሆን ነው ብሎ እጅግ ደስ አለው::

ሲደርሱም እናቱ 40 ቀን የበገ እያረደች የጠራ እያወረደች ታላቅ አቀባበል አድርጋለታለች ታቦተ ጽዮንንም ቤተመቅደስ አሠርታ አስተምግባለች ለካህናቱም ርስት ጉለት ሰጥታቸዋለች:: ክብ ነገ

ሰሎሞን የጌታ ጎበዕ ስም የተቀረጸበት ግርማ ሞገሱ ትእምርተ መንግሥቱ የሆነ ቀለበት ነበረው አንድ ቀን ከዙፋኑ አስተምጦት ሳለ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ከነዙፋኑ ጠቅልሉ ወስዶ ከባሕር ጣለው ሰሎሞን ሊገባ ሲል ዙፋኑን ጠባቂው አትገባም ብሎ ከለከለው:: ኧረ ሰሎሞን ነኝ ቢለው ሰይጣን በምትሐት እሱን መስሎ በዙፋኑ ተቀምጦ ነበርና ሰሎሞን በዙፋኑ ተቀምጦ ሰሎሞን ነኝ ትላለህን? ብሎ ገፍቶ አስወጣው እርሱም ወጥቶ በከተማው 2 ሳምንት ያህል እየለመነ ሰነበተ አንድ ቀን ሰይጣን እየተከታተለ የሰውን ልብ እያጸናበት የሚመጻውተው አጥቶ ከባሕር ሄዶ ዓሣ አጥማጆችን ለመነ:: አንዱ ይህ ዘብዛባ ብሎ የሞተ ዓሣ ጣለለት ሆዱን ቢቀደው ቀለበቱን አገኘ ግርማ ሞገሱ ትእምርተ መንግሥቱ ነውና በዚያ የነበሩት ንጉሥን ከዚህ ምን አመጣው እያሉ ከበው አጅበው ከቤተመንግሥቱ አደረሱት:: ሰይጣኑ ወጥቼ አሄዳለሁ ሲል እንግዲህማ ወዴት ትሄዳለህ ብሎ ምድር አስቆፍሮ ቀበረው እንዳይወጣም መርበብተ ሰሎሞን የሚባል ሰመ አምላክ አትሞበታል:: ከዚህም ያደረሰው አንድ ቀን የራበው ችግረኛ ሲለምን ምን ሆኖ ነው ቢል ርቦት ብለውት በሞጊዝት አድጎ ኋላም በመንግሥት ሆኖ ረሀብን አያውቅምና ረሀብ ደግሞ ምንድር ነው? ብሎ ነበርና እንዲቀምሰው ነው::

ኋላ ግን መፍቀሬ አንስት ሆነ 700 ሚስቶች 300 ቅምጦች አስቀምጦ አረማውያት የሆኑት ለጣዖት እንዲሠዋ ልቡን አዘነበሉት ንጉሥ በመንግሥቱ ሲገቡበት እንደማይወድ ጌታም በአምላክነቱ ቢገቡበት አይወድምና መንግሥትህን ከልጅህ እጅ ከ12 እቀዳለሁ::



ለባሪያዬ ለዳዊት ስለማልኩት መሐላ ግን አንዱ እጅ ለልጅህና ለቤቱ ይሆናል አለው 1 ነገሥ.16.

በፍጻሜ ዘመኑ ንስሓ ገብቶ ይቅርታ ለመነ ጌታም ንስሓውን ተቀብሉ ኃጢአቱን ፋቀለት መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ዘር ከአዳም ባሕርይ ተከፍላ በሴት አካል ተቀርጻለች፣ ከሴት ሲወርድ ሲዋረድ በኖኅ በሴም ከሴምም ሲወርድ ሲዋረድ በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ፤ ከያዕቆብም ሲወርድ ሲዋረድ በዳዊት ከዳዊትም ባንተ ካንተም በሮብዓም አካል ተቀርጻለች ከርሷ አምላክ ይወለዳል እርሱም በሞቱ ዓለሙን ያድናል ብሎ የዓለምን የድኅነት ተስፋ ሌላውንም እስከ ምጽአት ድረስ የሚሆነውን ሁሉ ገልጾለታል:: ጥበባቱን ምሳሌያቱን ተግሣጻቱን በመጽሐፍ ጽፎ /አጽፎ/ በተወለደ በ52 በነገሠ በ40 ዓመቱ ዐርፏል::

## ሰኔ 24 ሙሴ ጸሊም

አባት እናቱ ፀሐይን ያመልኩ ነበር፤ ኃጢአት በሠራ ጊዜ ተው አምላካችን ፀሐይ ይጣላሀል ይሉታል:: ፀሐይማ አምላክ ቢሆን እስከዛሬም ባቃጠለኝ ነበር ይላቸዋል:: አንድ ቀን ፀሐይና ጨረቃን የሚያፈራርቀውን እውነኛውን አምላክ ባውቀው በወደድሁ አለ:: መንፈስ ቅዱስ አነሳስቶ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ወሰደው ካህን ለተልዕኮ ሲገባ አይቶት ሊፈጀን የመጣ ነው ብሎ ፈራው:: እርሱ ሄዶ አምላክ ማን እንደሆነ አስተምረኝ አለው ከመምህር ኢስድሮስ አገናኘው:: አስተምረው አጥምቀው ለመዓርገ ምንኩስና አበቁት::

እርባ ዘመን ከሰው ተለይቶ በዓቱን ዘግቶ ከኖረ በኋላ በ500 መነኮሳት ላይ አበምኔትነት ተሾመ:: ቀን ቀን ሲያስተምር ይውላል፣ ሌሊት ሌሊት ከበረሀ ወርዶ እንሥራ ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ለየመነኮሳቱ በየደጃፋቸው ያኖርላቸዋል:: እርሱ መሆኑን አያውቁም ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና አንድ ሌሊት እንሥራ ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ሲመለስ:: በደንጊያ መሀል አገዳውን መታው እርሱ ግን ጸብዕ መሆኑን ተረድቶ የበለጠ እንዲህ ባለ ትሩፋት የሚጋደል ሆኗል::

በዓል በሚያደርጉ ጊዜ አባታችን መዓርገ ቅስና ተቀብለህ ናዘን ብለው ወደ ሊቀጳጳስ ይዘውት ሄዱ ሊቀጳጳሳቱ እንዲህ

ያለውን ጠቋራ ታመጡብኛላችሁን አለ:: ሠናየ ገብሩ ብከ አ ጸሊም ዘኀሱም ገጽከ መልክህ የከፋ አንተ ጠቋራ ደግ አደረጉብህ እያለ ራሱን እየገሰሠጸ ወጣ:: እመቤታችን ለሊቀጳጳሳቱ ተገልጻ መልኩ ቢጠቁር ልቡ ይነጻ የለምን ብላ ገሠፀችው ደግ አላደረግሁም ብሎ አስጠርቶ ሾመው:: ይህም የእመቤታችን ቃል ኪዳኗ ዘማዊውን እንደ ድንግል ኃጥኡን ጻድቅ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል «ይትባረክ ጽጌኪ ማርያም ለልበየ ፍቅርኪ ዘከፈሉ፣ወእያር ኀቀ እምኔየ ለኪዳንኪ ሣህሉ፤ ትምህርተ ኪዳንኪ ይሁብ ለዘማውያን ተደንግሎ» እንዳለ ደራሲ:: የንስሓንም በቁዔት ይገልፃል ንስሓስ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመዘኢአበሰ» እንዲል::

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ 7ቱን አስከትሎ ወደ አባ መቃርስ ሄዶ ሳለ በርበር ገዳሙን ሊያቃጥሉ እነርሱንም ሊገድሉ መጡ:: ከናንተ የፈራ ይሽሽ አለ:: አባታችን አንተስ አትሸሽምን አሉት ሞት ፈርቼ ሰማዕትነት ጠልቼ እሸሻለሁን አለ:: ወዲያው በርበር ደረሱ በጎልማሳነቱ ጊዜ ደም አፍስሶ ነበርና ኢይነጽሕ ደም ዘእንበለዶም፣ደም ያለ ደም አይነጻምና የኔም ደም ይፍሰስ ብሎ አንገቱን ለሰይፍ ሰጠቶ በሰማዕትነት ዐርፏል:: ከደቀመዛሙርቱም 6ቱ እሱን ተከትለው አንተገታቸውን ለሰይፍ እየሰጡ ሞቱ:: አንዱ ግን ፈርቶ ከጥሻ ተደብቆ ነበር፤ መልአኩ ስምንት አክሊላት አምጥቶ 7ቱን ለሰባቱ ሲያቀዳጃቸው አንዱ ከእጁ ሲቀር አይቶ ከተደበቀበት ወጥቶ በሰማዕትነት ሞቶ ተቀዳጅቷል::

- የነበረው በ 4ኛው ም.ዓ ድ/ልክ ነው::

| | |
|---|---|
| የጸም ኅደኛዋ የጸሎት ወዳጅ | ሙሴ በጎ ሰው ነው እውነተኛ ምስመናን |
| የዋህ አባ ሙሴ በራሱ ፈራጅ | ለእምነቱ ቀንቶ ያፈሰሰ ደሙን |
| በንስሓ ታጥቦ ነጽቶ ከበረድ | ጻድቅ ሆኖ ሳለ ፍጹም የከበረ |
| በጽድቅ ጎዳና ሲሄድ ሲራመድ | ሁሌ በደለኛ ሰው ነኝ ይል ነበረ |
| ሰይጣን ተመቅኝቶ ሊያጠፋው ሲወድ | ምን በጎ ብንሠራ ከበደል ርቀን |
| እኃውን ሊረዳ ቢወጣ ቢወርድ | ከቶ አይገባንም ልንል ጻድቃን ነን |
| ሞገስን አገኘ በፈጣሪው ዘንድ | በሥራችን ሁሉ ፍጹም ሰላልሆን |

## ሰኔ 25 ይሁዳ ሐዋርያ /ረድዕ/

ይሁዳ ማለት ታማኝ ማለት ነው:: ቁጥሩ ከ 7ቱ አርድዕት ነው የጌታ አሳዳጊ የዮሴፍ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው:: ማቴ 13:55 ይሁዳ 1:1



ጌታ «ሑሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አሕናፈ ምድር» ማቴ 28:19 ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን ለዓለም እንዲሰብኩ ያዘዛቸውን አስቦ ሐዋርያትን መስሎ ሐዋርያትን አክሎ ዞሮ በማስተማር ብዙዎችን ከይሁዲነት ወደ ክርስቲያንነት ከአረማዊነት ወደ ምእመንነት መልሷል::

በፍፃሜ ዘመኑ ሀሳውያን ጸልተው ተመቅኝተው ከገሃ ቤት ጥለውት ሳለ ያስተማራቸው ምእመናን ከሃይማኖት እንዳይፋለሱ በኃጢአት እንዳይረከሱ ተግሣጻዊ መልእክት ጽፎ ልኮላቸዋል:: በመጨረሻም በችንካር ተቸንክሮ በመስቀል ተሰቅሎ ሀርፏል::

## ሰኔ 26 እያሱ ወልደ ነዌ

ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው አባቱ ነዌ የባላል:: መምህሩ ሙሴ በምድረ ሞአብ ካረፈ በኋላ ጌታ ባንተ እድሬ ሕዝቤ እስራኤልን ለወዳጆቼ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማልሁላቸው ምድር አገባቸዋለሁና በርታ ጽና ከባሪያዬ ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ካንተ ጋር እሆናለሁ አለው:: እርሱም ጠንክሮ ሕዝቡን ይመራ ያስተዳድር ጀመር::

ካሌብንና በልሞንን ኢያሪኮን ሰልሉ ብሎ ላካቸው:: ደጋ ደጋውን ሲሰልሉ ሰንብተው እያሪኮ ደረሱ የኢያሪኮ ንጉሥ እስራኤል ከግብጽ መውጣታቸውን ሰምቶ ሰባት የብረት ቅጽር ቀጽር ይኖር ነበር:: የሀገሩም ሰዎች ጠርጥረዋቸው ሊጣሏቸው መጡ:: ረፀብ/ ራኬብ/ ከምትባል ዘማ ቤት ገብተው ሠውሯን አሏት ከሰገነት አውጥታ በቀርከሃ ጠቅልላ አቆመቻቸው ተከታትለው መጥተው የእስራኤል ሰላዮች ከቤትሽ ገብተዋል አውጪ አሏት:: መግባትማ ገብተው ነበር:: ቁራሽ ቀምሰው ውኃ ተጉንጭተው ከናንተ ጥቂት ቀደም ብለው ወጥተው ሄዱ አለቻቸው:: መግባታቸውን ሰላልካደች መውጣታቸውን አምነውላት ተመልሰዋል:: ገብታ ትብውዑ ሀገረነ ወትቀትሉ ነገሥታቲነ ሀገራችን ትገባላችሁ ነገሥታቱን ትገድላላችሁ ይህም ሊታወቅ ኃያላኑ ያሸበራሉ ለ50 ለ60 የሚከፈተውም የብረት በር በገዛ እጁ ሲከፈት ሲዘጋ ያድራል ነገር ግን ወገኖቼ ተድላ ደስታ ሲያደርጉ

እኔ ኣላደረግሁምና አብራችሁ እንዳታጠፋኝ ቃል ግቡልኝ አለቻቸው። ቤተሰብሽን በቤትሽ ሰብስበሽ ከመስኮትሽ ሐር እንጠ ልጥለሽ ቀዩን ብለዋት ሄደው ያጋጣማቸውን ሁሉ ለኢያሱ ነገሩት።

ኢያሱ ታቦተ ጽዮንን አሲዞ ዮርዳኖስን ከፍሎ ተሻገሩ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ መና ከደመና እየወረደላቸው ውኃ ከጭንጫ እየፈለቀላቸው ይመገቡ ነበር። በኋላ ግን መናው ቀርቶ የከነዓንን ፍሬ የሚመገቡ ሆነዋል።

ኢያሪኮ ቅጽሯ ሰፊ አምባዋ ጽኑ ነውና 6 ቀን እየዞረ ከደረሰበት ሲሰፍር ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን ኃያላኑን በግራ በቀኝ አሰልፎ ካህናቱን አልባሰ ተክህኖ አልብሶ ግዕጠንታተ ብርት አሲዞ ታቦተ ጽዮንን በመሀል አድርጎ እሱም ከመሀል ሆኖ የነጋሪት ድምጽ ስትሰሙ አውኩ ደንፉ ብሏቸው ነበርና ቢደነፉ የኢያሪኮ ቅጽር ቅጥር ከምር በአራት ወገን ፈርሷል። ሬዓብንና ቤተሰቧን አስቀርቶ ሕዝቡን አጥፍቶ ሀገሪቱን ይዟል።

እስካሁን ያገኘነውን ለራሳችን ስናደርግ መጥተናል ከንግዲህ የምናገኘው ለእግዚአብሔር ይሁን ብሎ እስራኤል ያገኙትን ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር ሠጡ። ከጋይ ሰዎች ጋር ሲዋጉ ባንድ ጊዜ 36 እስራኤላውያን ተመቱ። ኢያሱ ወደ ጌታ ቢያመለክት ያልከውን ያስቀረ አለ አለው። ዕጣ ቢያጣጥል በአካን ወልደ ዛራ ወደቀ ከደበቀው ወርቅና ብር ጋር በደንጊያ ተወግሮ ደንጊያ ተከምሮበት ሞቷል። ከዚህ በኋላ ጌታ ጋይን አሳልፎ ሠጥቶታል።

ጋይን አልፈው ገባዖን ቢደርሱ 5 አሞራውያን ነገሥት ተባበሩት የቀረቡትን እርሱ በሰይፉ መታቸው የራቁትንም ጌታ በመብረቅ ፈጃቸው። ካሰበው ሳይደርስ ፀሐይ ልትገባበት ቢሆን ለትቆም ፀሐይ በገባዖን ወወርኀኒ በፈለገ ኤሉን ፀሐይ በገባዖን ትቁም ጨረቃም በኤሉን ወንዝ ብሎ ጸልዮ ካሰበው እስኪደርስ ድረስ ፀሐይን ካለችበት አቁሟታል። ኢያ 10:12

በፍፃሜ ዘመኑ እስራኤልን ሰብስቦ የሞአብን አምላክ ታመልኩ ወይስ እግዚአብሔርን አላቸው እግዚአብሔርን እንጂ የሞአብን አምላክ አናመልክም አሉት ምን ምስክር ይሁንባችሁ አላቸው፣ አንተ ያልከው ይሁን አሉ ሦስት ገጻት ያሏት ደንጊያ /ሐውልት/ ወስዶ በሴሎ በደብተራ አሪት አጠገብ ተከለ የወጣ የወረደው ያለፈ ያገደመው ሁሉ ኢያሱ ከእስራኤል ጋር የተማማለባት ሐውልት እያለ የሚያያት ሆኗል። እንዲህ ሆኖ ኖሮ በተወለደ 110 ዓመቱ ዐርፏል።



➢ የኖረው በ1500 – በ1400 ዓ.ዓ ገደማ ነው።

## ሰኔ 27 ያዕቆብ ዘሥሩግ /ከ 366 – 438 ዓ.ም/

ያዕቆብ ማለት አኃዚ አዕቃጺ ማለት ነው። አባቱ የሶርያ ሊቀካህናት ነበር። በተወለደ በ3 ዓመቱ እናቱ ወደ ቤተክርስቲያን ይዛው ሄደች። ልዑካን ሥጋውን ደሙን አቀብለው ሲመለሱ ከእናቱ ጭን ወርዶ ድንኩል ድንኩል እያለ ቤተመቅደስ ገባ። ሊቀጳጳሱ ጼጋ እግዚአብሔር እንደጠራው ከፍጹምነት እንደሚደርስ አውቆ ደሙን /ተረፋን/ በጽዋው 3 ጊዜ ጋተው ወዲያው ምሥጢር ተገልጾለት ሥጋህን ደምህን የሰጠኸኝ እያለ አመስግኗል። አያይዞም «አንብ አፈርህ ሠለስተ ግብራተ ወይእቲ ጸአተ ነፍስ እምሥጋ፤ ወተራክቦ ምስለ እግዚአብሔር ወጸአተ ፍትሕ ኅዕሬየ – ሶስት ነገሮችን እፈራለሁ እኒህም የነፍስ ከሥጋዬ መለየት፣ ከእግዚአብሔር ጋራ መገናኘትና ፍርድ መስማት ናቸው፤» እያለ ያለቅስ ጀመረ። ካህናቱም ምእመናኑም ጌታ እንጂ በዚህ ሕፃን አድሮ ወቀሰን ብለው አልቅሰዋል።

በ7 ዓመቱ ብሉይ ሐዲስ አጠና፤ በ12 ዓመቱ ድረሰት መድረስ ጀመረ 5 ያህል ጳጳሳት መጥተው ከፊታቸው ቆሞ ድርሰት እንዲደርስላቸው ጠየቁት። ትሕትና ልማዱ ነውና ከእናንተ ፊት ቆሜ እንኳ ድርሰት መድረስ ያጠናሁትንም አከናውኜ መናገር አይቻለኝም አላቸው እንኪያስ ይህን ተርጉመህ ንገረን ብለው የአራቱን እንስሳ ስዕል አሳዩት። ታሪኩን አምልቶ ምሥጢሩን አስፋፍቶ ተርጉሞላቸዋል። ከዚህም በኋላ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል ብዙ ድርሳናት ደርሷል።

በኤፍራጥስና በጤግሮስ መካከል በምትገኘው በሥሩግም ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ ሳለ ለጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት 'በሚል የልዮን ትምህርት ካህድበ ኬልቄዶን ጉባዔ

በ451 ዓ.ም የተደረገ የእኛ ቤተክርስቲያን የማትቀበለው ጉባኤ ካባት ተብሎ የሚጠራ ነው። የቤ.ክ. ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ

636 ኢጲስ ቆጶሳት የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ዲዮስቆሮስን አውግዘው በለዩት ጊዜ መናፍቃን በመሠልጠናቸው ዲዮስቆሮስም እውነተኛውን ሃይማኖት ይዞ ሳለ በመሰደዱ እዘን ልዮንም ይተባበረኛል ብሎ ምስለኝ ብሎ ላከበት። እርሱ ግን በጴጥሮስ መንበር ተቀምጠለሁ ብለሀልና ከሀደትህ ተመልሰህ ንስሓ ገብተህ አንድ ባሕርይ በሚል ሃይማኖት ጴጥሮስን ብትመስለው እኔም እመስልሀለሁ፤ ይህ ካልሆነ ግን አንተ ዲያብሎስ ነህ ተከታዮችህም አጋንንት ናቸው ብሎ ነቅፎታል።
እንዲህ ሆኖ ኖሮ በተወለደ በ72 በተሾመ በ10 ዓመቱ በ438 ዓ.ም ዐርፏል።

ብለደና ሐዲስ የተጻፈበት ገና በሶስት ዓመት በሕፃንነቱ
መዝገብ ነው ስሌዳ ያዕቆብ በእውነት አዝነው እለቀሱ ሕዝቡ ካህናቱ
ሞትና መቆምን በእግዚአብሔር ፊት ከሰሩት ርቀን በጎ እየሠራን
ጌታ ሲፈርድብኝ ፍርዱንም መሰማት የዓለም ተድላ ደስታ ሳይታልለን
ነፍሴን አስጨንቋት እኒህ ሶስት ግብራት እንዘን ወንድሞች ስለነፍሳችን
እያለ ሲያለቅስ በዕንባ ሲርስ ፊቱ የምንሞትባትን ቀኗን አስበን

ሲራ 28: 6፡3 መቃ 6:1

## ሰኔ 30 ልደቱ ለዮሐንስ መጥምቅ

የተፀነሰው በቅዱስ ገብርኤል ብስራት መስከረም 26 ቀን ነው:: በ6ኛው ወር እመቤታችን መልአኩ ኤልሳቤጥን እንተ እም እዝማድኪ ይዕቲኒ ጸንሰት ወረከበት ወልደ በልህቃቲሃ ወበርስአቲሃ ብኋት ነበርና ኤልሳቤጥን ልትጠይቃት መጣች ኤልሳቤጥ የሰላምታዋን ድምጽ ስትሠማ እንፈርዐፀ እጓል በውስተ ከርሣ ይላል ጽንሱ በማኅፀኗ ሰግዷል:: ኤልሳቤጥም መንፈስቅዱስ መልቶባት ቡርክት እንቲ እምአንስት ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ የማኅፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ ወምንትኑ አነ ከመትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚየ – የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ የሰላምታሽን ድምጽ ሰሰማ ጽንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሏልና ወብፅዕት እንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ተልከው የነገሩሽን ቃል እንዲሆን የምታምኚ ንዕድ ክብርት ነሽ ብላ አመሰግናታለች:: እመቤታችንም ከርሷ ተቀብላ ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ብላለች 3 ወርም ከርሷ ጋር ቆይታለች::

እመቤታችን ወደ ቤቷ ከተመለሰች በኋላ ብዙም ሳትቆይ በዚህ ዕለት ኤልሳቤጥ ወለደች በስምንተኛው ቀን ሊገዝሩት መጥተው ስሙን ማን እንበለው አሉ፤ ዮሐንስ ይባል አለች:: አልቦ እምአዝማድ ኪ ዘከማሁ ስሙ – ከዘመዶችሽ በዚህ ስም የተጠራ የለም:: እንደምን ይሆናል ብለው ዘካርያስን ማን ቢባል ትወዳለህ አሉት ብዕርና ክርታስ ሰጡት:: ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ ብሎ 10ሩን ፊደላት ጽፎ እንደበቱ ተፈትቶለት ተናገሯል:: ወዲያውም «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘተሣሃሎ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ» ብሎ ጌታን አመስግኗል፤ ሕፃኑንም ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ እስመ ተሐውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመትኢሕ ፍኖቶ - አንተም ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ትጠርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና ብሎ ትንቢት ተናግሮለታል:: ሉቃ 1:39 – 79

- ይህ የተፈጸመው 5500ው ዘመን ሊፈጸም መንፈቅ ሲቀረው /በ19.9 አጋማሽ/ ነው::



## ምዕራፍ 5

## ሐምሌ 2 ታዴዎስ ሐዋርያ

ቀዳሚ ስሙ ልብድዮስ ነው፣ ወልብድዮስ ዘተሰምየ ታዴዎስ እንዲል ልብድዮስም ማለት ልብድ ሠሪ ዓሣ አሥጋሪ ማለት ነው፤ ልበድዮስም ይለዋል ካህነ አምላክ ማለት ነው:: ታዴዎስ ማለት ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው አሪትን በዘር ወንጌል ን በመከር መስሎ አስተምሯልና በነግህም ስንዴ ዘርቶ ለመሥዋዕት አድርሷልና:: ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ለስብከት ወደ አፍራቅያ ሲሄዱ አንድ ገበሬ ዘር ሲዘራ አገኙ ራብን አብሳን ጠማን አጠማን አሉት ቀደም ብላችሁ ቢሆን ነበር እንጂ አሁንማ ስንቄን ጨርሻለሁ፣ እንዳላመጣላችሁም ቤቴ ሩቅ ነው አላቸው እንዳለህ ብለን ነው እንጂ ብለው መለስ መለስ ሲሉ ደግ አላደረግሁም ብሎ ቆዩኝ ላምጣላችሁ ብሏቸው ጥማዱን ፈቶ በሬዎቹን አሰማርቶ አገልግሉን መንቀሉን አንጠልሎ ወደ መንደር ሄደ:: ታዴዎስ እየዘራ እርሱ እያረሰ ሁት ሶስት ጥማድ የሚያውቀውን ዘሩን አበርክተው ዘርተው ቆዩት ምግባቸውን ይዞ ሲመጣ ዘሩ ተዘርቶ አሽቶ አፍርቶ በሬዎቹም ለምለም ሣር ሲነጩ ጥሩ ውኃ ሲጎነጩ አገኘ:: አግልክት ከሰማይ ወርደው ወደኔ መጥተዋል ብሎ እያደነቀ ያመጣውን መግቧቸው ጌቶቼ ወደ ቤት እንሂድ አላቸው:: እንመጣለን ቀድመህ ሂድ አሉት:: በሬዎቹን እየነዳ እሸቱን እየበላ ሲሄድ ጊዜው የዘር እሸቱን ከወዴት አገኘኸው? አሉት የሆነውን ሁሉ ነገራቸው ሰይጣን ከሐዋርያት ፊት ፊት እየሄደ በአሕዛብ ልብ እያደረ ትምህርታቸውን እንዳይቀበሉ እንዲያውም በእሳት ተኩሰው በደንጊያ ወግረው እንዲገድሏቸው ይመክር ነበር:: እኒህንም በክፉ ቅናት አነሣሣቸው:: የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ነን የሚሉት መሠርያን ይሆናሉ ካሉበት አድርሰን አሉት:: ይመጣላችኋል ከዚሁ ቆዩአቸው አሉ:: እኩሌቶቹ እነሱ ሙት የሚያነሱ ድውይ የሚፈውሱ ናቸውና ተው አይሆንልንም ያጠፉናል አሉ ሌሎች ግን በምክንያት እናችንፋቸዋለን ብለው አንዲት ዘማ በገንዘብ ገዝተው ራቁቷን ከከተማው በር አቆሙ እነርሱም ከዚያ ሲደርሱ ዕርቃኗን ጥላ ቢያዩአት ክፍታቸውን አውቀው በነፋስ አውታር ሲቅዘው እግዚኦ እግዚኦ አስብለዋታል:: አይሆንልንም ብለው የነበሩት አይሆንልንም ተው ስንል እንቢ ብላችሁ እኛንም ልታስጠፉን ነው ብለው ይሸበሩ ይታወኩ ጀመሩ::

ከሞተ ኃጢአት የምትድኑበትን ልናመለክታችሁ እንጂ ልናጠፋችሁ አልመጣንም ብለው አስተምረው አሳምነዋቸዋል:: ሴቲቱም ፍጻዋን ጨርሳ ወርዳለች ኋላም በተልዕኮ ስታገለግለው ኖራለች::

ቅዱስ ጴጥሮስ ከተመለሰም በኋላ በየሀገሩ እየዞረ በማስተማሩ ብዙዎችን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከክህደት ወደ ሃይማኖት መልሷል:: የሚመቀኘው አንድ መሠርይ ነበር:: አስተምሮ ያሳመነውን አንድ ባለጸጋ በክርስቶስ ማመንህ ምን አገኘለሁ ብለህ ነው? አለው ገነት መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ ብዬ ነዋ አለው:: ክርስቶስማ ባለጸጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል» ማቴ 19:24 እያለ እንዴት ትገባለህ አለው? እርሱም ነገሩ ደንቆት ታዲዎስን ባገኘው ጊዜ አባቴ እንዲህ ብለህ አስተምረሀልን? አለው አዎን አለ:: እንኪያስ አድርገህ አሳዮኝ አለው:: ያስተማረው አንጥረኛ ወዳጅ ነበረው:: መርፌ ስደድልኝ ብሎ ላከበት:: እርሱም ነገሩን አውቋልና ቀዳዳውን አስፍቶ ላከለት የመርፌ ቀዳዳ ምን ቢሰፋ ግመል ያሳልፋልን እንደነበረው አድርገህ ላክልኝ ብሎ መለሰው:: እንደነበረው አድርጎ ሰደደለት መርፌውን አቁም ግመሏን ያሳልፋልን 3 ጊዜ አመላልሶ አሳይቷቸዋል:: «ለትውልደ ትውልድ ኀሪት እስከ ተአምሩ ተጽሕፈ፤ ሰቀለ ብእሲተ በነፋስ ዘትዜሙ ዘልፈ፤ በስቁረት መርፍዕ ካዕበ – ገመለ አኀለፈ» እንዲል አርኬ:: እንዲህ ባለ ሲያስተምር ቆይቶ በመጨረሻ በደንጊያ ተወግሮ ሞቷል::

## ሐምሌ 3 ቅዱስ ቄርሎስ ሊቀ ጳ /ከ375 – 444 ዓ.ም/

ቄርሎስ ማለት ማኀቶት ማለት ነው:: ሀገሩ እስክንድርያ ነው ሊቀጳጳሳት ቴዎፍሎስ አጎቱ ነውና እያስተማረ አሳድጎታል፤ እርሱም መንፈስ ቅዱስ መርጦታልና ወሰበ ይሰምዖ ለቀለም ያጸንዖ በአሐዱ ጊዜ ወይመስል ከመዘቀዳሚ ተምህረ /ድርቄር/ ይባል ቀድሞ የተማረው እኪ መስል ድረስ የነገሩትን ቀለም ባንድ ጊዜ ይይዝ ነበር:: እንዲህ አድርጎ በ5 ዓመት ብሉይ ሐዲስ አጥንቷል:: ከዚህ በኋላ ከአባ ሰራብዮን ሥርዓተ ምንኩስና ተምሮ አንባቢነት ሾመው ኋላም እርሱ ሲሞት ንጽሕናውን ተረድተው:: በመንበረ



ማርቆስ 24ኛ ሊቀጳጳሳት አድርገው ሾመውታል:: ተሹሞም ሳለ ብዙ ድርሳናት፡፡ ደርሷል ብዙ ተግሣጽ ጽፏል ቅዳሴም ደርሷል::

በዘመኑም የቁስጥጥንያ ሊቀጳጳስ ንስጥሮስ «ሕሰው ኬ ትሰመይ ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ ወአማነ ትሰመይ ወላዲተ ሰብእ» በማለት የጌታን የአምላክነት የእመቤታችንን እመ አምላክነት ነቅፎ ተነሣ:: ንጉሡ ቴዎድስዮስ ዘይንዐስ በኤፌሶን ጉባዔ ይሁን ብሎ አወጀ:: 200 ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው በርሱ አፈ ጉባዔነት ተከራክረው አውግዘው ለይተውታል:: /በ431 ዓ.ም /

ንስጥሮስ ከተወገዘ በኋላ ላዕላይ ግብጽ ይኖር ነበር:: የወንድም ፍቅር አገብሮት ካለበት ድረስ ሄዶ ወንድሜ የሚጎዳ መስሎህ ከሆነ እኔ ልጎዳልህ ጌታን አምላክ ወልደ አምላክ እመቤቴንም ወላዲተ አምላክ በል አለው እኔስ ግብሬ ተሰማምቶኛል ይህን አልልም አለው:: እመቤቴን ላዋርድ እኔንም አልታዘዝ እንዳልክ ላንተም እንደበትህ አይታዘዝልህ ብሎ ረገመው ወጥቶ እንዘ ይነብብ ከመ ከልብ ይባል ምላሱ ተጎልጉሎ ወጥቶ ከደረቱ ተንጠልጥሎ እንደውሻ ህዝ ህዝ እያለ ደምና መግል እየተፋ ሞቷል::

እሱም እንዲህ ባለ ግብር ኑሮ ለሊቀጳጳስነት በተመረጠ በ43 ዓመቱ በዚህ ዕለት ዐርፏል::

ለሊቀጳጳሳት ቅዱስ ቄርሎስ
እስኪ እንደዐቱ ሰላምታ ታድርስ
መንፈስ ቅዱስ መርዖት [illegible]
ይተረጎም ነበር ምሥጢር በእንደዐቱ
አዝማሪት በረገመው በሰደንገል [illegible]
የመርዶት ሞት ሞተ ንስጥሮስ ኑፋሌ

ምላሱ እንደጠሩት ወጥቶ ተንጠልጥሎ
መዋረድን ሽቶ መጣል በሲኦል
አልመከር ያለ አሁንም ሞልቷል
ኃጢአት ሠርቼ ነፍሴ እንዳትጐዳ
አምላኪ እንዳስብህ በሠርክ በማለዳ
ቃልህን ጻፍልኝ በልቤ ሰሌዳ

## ሐምሌ 5 ጴጥሮስ ወጳውሎስ

### ሀ. ቅ. ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ማለት ኰኵሕ ሃይማኖት ማለት ነው አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጽ ለቤተክርስቲያንየ እንዲል ማቴ 16:18 በዕብራይስጥ ኬፋ ይለዋል:: ቀዳሚ ስሙ ስምዖን ነው፤ ትውልዱም

ከነገደ ሮቤል ነው:: አባቱ ዮና ይባላል:: የተወለደው በገሊላ አውራጃ በቤተ ሳይዳ ነው:: ጴርቴዋ የምትባል ሚስት ነበረችው የሚተዳደረው ዓሣ በማጥመድ ነበር:: ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር ዓሣ ከሚያጠምድበት ተጠርቶ ሐዋርያ ሆኗል:: ማቴ 4:19

የዋህ፣ ፈጣን ቁጡ ነበር:: የዋህነቱ ጌታ በባሕር ላይ ሲሄድ አይቶ ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንክ ወዳንተ እንድመጣ አሰናብተኝ ብሎ በባሕር ላይ ሊሄድ በመሞከሩ ማር 6: 45፣ ፈጣንነቱ ጌታ ደቀመዛሙርቱን በቂሣርያ ሰዎች ማን ይሉኛል ብሎ ጠ ይቋቸው ሙሴ ነው፣ ኤልያስ ነው ይሉሀል ባሉትና እርሱም መልሶ አንትሙስ መኑ ትብሉኒ – እኛን ተስ ማን ትሉኛላችሁ ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ጴጥሮስ ፈጥኖ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ ብሎ በመመለሱ ማቴ 16:16 ቁጡነቱም አይሁድ ጌታን በያዙት ጊዜ ተቆጥቶ የማልኮስን ጆሮ በሰይፍ በመቁረጡ ዮሐ 18:10 ታውቋል::

ጌታ «ይቀልል ይኅልፍ ገመል እንተ ስቁረተ መርፍዕ እምባዕል ይባዕ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ብሎ ሲያስተምር ጴጥሮስ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንልህ ዋጋችን ምንድር ነው? ብሎ ጠይቆ ነበር:: ጌታም አማን እብለክሙ አንትሙ እለተለውክሙኒ አመዳግም ልደት አመይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ አንትሙኒ ትነብሩ ዲበ ዐሠርቱ ወክሌኤቱ መናብርት ወትኬንኑ ዐሠርተ ወክልኤተ ሕዝበ እስራኤል ብሎ ከወንድሞቹ ከሐዋርያት ጋር የሚያገኘውን ክብር ነግሯቸዋል:: ማቴ 19:27 – 28::

ከሊያልይ ባንዱም ኢትነሡምኑ · ጌታዬ አትተኛምን አለው የሰንቁ ጽዋ ውኃ መልቶ ሰጠው፡ ሳይጠጣው እንቅልፍ ያዘው:: ጽዋው ከእጁ ወድቆ ተሰበረ ቢነቃ ጽዋው ተደቁሶ ውኃው ፈሶ አገኘ ደነገጠ:: እኔም ይህን ዓለም የያዝኩት በመሀል እጄ ነው፡ መተኛት ማንቀሳፋት ቢኖርብኝ ዓለሙ እንዲህ ተደቁሶ በጠፋ ነበር አለው እንደምን አድርገህ ትይዘዋለህ አለው? ዓለምን በመሀል እጁ ይዞ እሱን ከመሀል አድርጎ አይቴ ሀሎከ አ ስምዖን ወዴት አለህ? አለው፤ ኢየአምር እንዳአ እንጃ ያለሁበትን አላውቀውም ብሎታል::



ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ከሁሉ አስቀድሞ ቢከተለውም በሕማሙ ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ ክዶት ነበር:: ኋላ ግን በንስሓ የሚመለስ ሁኗል:: ማቴ 26:69 – 75 ጌታ ከማረጉም አስቀድሞ «ረዐይኬ አባግዕየ፣ ረዐይኬ መሐስዕየ፣ ረዐይኬ አባግዕትየ – በጎቼን ጠቦቶቼን ጠብቅ ብሎ በፍጹምነት በማዕከላዊነትና በወጣኒነት ያሉትን ሁሉ እንደ አባት ሆኖ እንዲንከባከባቸው አደራ ሠጥቶታል:: ዮሐ 20: 15 – 17 ካረገም በኋላ በ10ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የሚያውቀው ጸንቶለት የማያውቀው ተገልጾለት ባንድ ቀን ስብከት 3000 ሕዝብ አሳምኗል:: ሐዋ 2:41

ከጊዜያት ባንዱ ከዮሐንስ ጋር ለጸሎት ወደ ምኩራብ ሲገቡ እግሩ ልምሾ ሆኖ የተወለደ አንድ ሰው ስመ እግዚአብሔር ጠ ራባቸው:: ወርቅሰ ወብሩር አልብየ እምዘብየሰ እሁበከ – ወርቅና ብር የለኝም ያለኝን ግን እሰጥሀለሁ:: ናሁ በስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ተንሥእ ወሑር - በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥእ ተመላለስ አለው ድኖ ተነሥቷል:: ሐዋ 3:1 – 8

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ መዲናቸው ኢየሩሳሌምን 1 ዓመት በኅብረት ካስተማሩ በኋላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማድረስ ዓለምን ዕጻ በዕጻ በተከፋፈሉ ጊዜ ርእሰ ሐዋርያት ነውና ሮምን ደርበው ሠጥተውታል:: እርሱ ግን ለሁሉ አባት ነውና ሐዋርያትን ሁሉ ከሀገረ ስብከታቸው አድርሰ

ሐዋርያተ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ መዲናቸው ኢየሩሳሌምን 1 ዓመት በኅብረት ካስተማሩ በኋላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማድረስ ዓለሞን ዕጻ በዕጻ በተከፋፈሉ ጊዜ ርእሰ ሐዋርያት ነውና ሮምን ደርበው ሠጥተውታል:: እርሱ ግን ለሁሉ አባት ነውና ሐዋርያትን ሁሉ ከሀገረ ስብከታቸው አድርሶ
አለማምዶ ይመለስ ነበር:: በሮም 25 ዓመት አስተምሯል፣ ከዚህ በፊት ግን በሰማርያ፣ በልዳ፣ በኢዮጴ አንጾኪያ፣ በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያና በቢታንያ አስተምሯል:: በኢዮጴ ስምዖን ሰፋዬ አኅዕንን ሊቀ ሐራ ቆርኔሌዎስን አስተምሯል ጣቢታን ከሞተ አስነሥቷል ሐዋ 9:36 – 42 በልዳም ኤንያ የተባለ የ 8 ዓመት የአልጋ ቁራኛ ፈውሷል:: ሐዋ 9:32 – 34

በሰማርያም ሲያስተምር ሲሞን የሚባል መሠርይ ብዙ ወርቅና ብር አምጥቶ እኔም እጄን በጫንኩበት ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ ተአምር እንዲደረግ አድርጉልኝ አለ:: «ወርቅከሰ ወብሩርከ ይኩንከ ለከ ለሕርትምና ይመስለከኑ ዘበወርቅ ትሣየጠ ለጸጋ እግዚአብሔር - ጸጋ እግዚአብሔርን በወርቅ ትገዛለህን ወርቅና ብርህ ለጥፋትህ ይሁንልህ አልብከ ክፍል ውስተዝ ነገር – በዚህ ነገር ከኛ ጋራ እድል ፈንታ ተርታ የለህም በጽኑ ክህደት

ተደዘሀ አይሀለሁና አለው:: ያም የማይሆንለት ቢሆን አንጾኪያ ወርዶ ያስት ጀመረ:: ደቀመዛሙርትህን አሳተ ብለው ነገሩት:: ዮሐንስን አስከትሎ ወረደ:: መከራከር የማይቻለው ቢሆን ወደ ሮም ሄደ:: ተከተሉት ሕዝቡን ለማሳት ለመሥዋዕት የቀረበውን በሬ በጆሮው ቢያንሾካሽክበት ከሁለት ተከፈለ ቅዱስ ጴጥሮስ ጠርተህ አምጣው ብሎ ቢባርከው አፈፍ ብሎ ተነሥቶ እያዳፋ አምጥቶታል:: ያም በበኩሉ በምትሐት አጋንንትን ስቦ አንተን ቅስና አንተን ዲቁና ሹሜያቹሀለሁ ብሎ ለማረግ ሞከረ ጥቂት ከፍ ካለ በኋላ ጴጥሮስ ቢያማትብበት አጋንንት ጥለውት ሸሹ፣ እሱም ወድቆ ደቆ ቀርቷል:: ኋላም ተከታዮቹ ትንሣኤ ሙታን የለም ጌታ ነፍስ አልነሳም ምትሐት፣ ሕድረት እያሉ ቢያውኩ 11 ዱን ሐዋርያት 72 አርድዕት ቅዱስ ጳውሎስንና የዕቆብ እኀው እግዚእን በኢየሩሳሌም ሰብስቦ / በ50 ዓ.ም/ በያዕቆብ ሊቀመንበርነት 43ቱን አናቅጽ ዲድያስቅልያ እንዲወሰኑ አድርጓል:: ከዚህም ሌላ ያስተማሩቸው ምእመናን ከሃይማኖት ከምግባር እንዳይወጡ 2 መልእክቶችን ጽፎላቸዋል:: የመጀመሪያውን በ54 ዓ.ም በባቢሎን 2ኛውን በ60 ዓ.ም በሮም ጽፎታል::

ንጉሡ ኔሮን ቄሣር መምለኬ ጣዖት ነበረ:: በሃይማኖት ምክንያት አሰሮት ነበር:: አካይያ ዘምቶ ጠላቱን ድል ነሥቶ ሲመለስ ለጣዖት ስገድ ቢለው አልሰግድም አለ:: በችንካር ተቸንክሮ በመስቀል ተሰቅሎ ይሙት ብሎ ፈርደበት ከዚያ በፊት አሕዛብ ሊጣሉት ሲነሱ ወደ ጌታ ሲያመለከት እሳት ከሰማይ ወርዳ ታጠፋለት ነበር አሁንም እሳት ከሰማይ ወርዳ ትብላቸው ብሎ ወደ ጌታ ቢያመለከት ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ታየው ሰቀሉከኑ ዳግመ በሮም ዳግመኛ በሮም ሰቀሉህን? አለ አንተ ብትፈራ እንጂ ነዋ አለው:: ፈቃድህስ ከሆነ ብሎ እንደ ጌታዬ አቁማችሁ ሳይሆን ቁልቁል ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ አላቸው በራሱ ዘቅዝቀው ሰቅለውታል:: ሥጋውንም ደቀመዛሙሩ መርቄሎስ ከመስቀሉ አውርዶ በወተት በወይን አጥቦ ሽቱ ቀብቶ በነጭ ሐር ገንዞ እንዳይፈርስ በማር በተመላ ሣጥን አድርጎ ቀብሮታል::

መዋዕለ ስብከቱ 50 ዓመት ነው /ገድ ሐዋ ፣ ዜና ሐዋ/



## ለ. ቅዱስ ጳውሎስ

ጳውሎስ ማለት ንዋይ ኅሩይ ማለት ነው «ንዋየ ኅሩየ ረሰይክዎ» እንዲል ሐዋ 9:15 አንድም ብርሃን ማለት ነው ኢጳውሎስ ማለት ብርሃን እንደሆነ ዘጸ 14:2 አንድም መድቅሕ ማለት ነው:: ዶንጊያ በመዶሻ ተጠርቦ ለሕንፃ ሥራ እንዲውል አሕዛብም በርሱ ትምህርት ታንፀው ለገቢረጽድቅ ይበቃሉና ቀዳሚ ስሙ ሳውል ነው፤ ሳውልም ማለት ጸጋ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ትውልዱ ከነገደ ብንያም ነው:: ፊል 3:5 አባቱ ዮስአል ይባላል:: የተወለደው ጌታ በተወለደ በ5 ዓመት በጠርሴስ ነው:: ከ15ቱ ዓመቱ ጀምሮ ኢየሩሳሌም በታላቅ እንቱ ቤት ተቀምጦ ከመምህር ገማልያል ሕገ ኦሪትን መጻሕፍተ ነቢያትን ሲማር አድጓል ሐዋ 22:3 ለሕገ ኦሪት ቀናዒ ከመሆኑ የተነሣ ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ወንጌልን ዲቃላ ሕግ እያለ ሐዋርያትን ይቃወም ምእመናንን ያሳድድ ነበር:: በወንጌል ያመነው ጌታ ባረገ በ8ኛ ዓመት ነው:: «ወሳውልሰ ዓዲሁ ይትቄየም ይላል» ምእመናንን ለማሳደድ ከሊቀ ካህናት የሹመት ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ሲሄድ መብረቅ ጣለበት፤ ደንግጦ ወደቀ ወዲያውም ሳውል ሳውል ለምንት ትሰድደኒ ለምን ታሳድደኛለህ? የሚል ድምጽ ሰማ:: አንተ ማነህ አለ ምእመናንን ከዋሉበት አሳድር ካደሩበት አሳውል የምትልብኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ፤ ይብእሰከ ረጊጽ ውስተ ቀኖት በሊህ የተሳለውን ሰይፍ ቢረግጡት የረገጠው ሰው እንጂ ሰይፉ ይጐዳልን፣ አንተስ እኔን ብትከድ ምእመናንን ብታሳድድ አንተ እንጂ -እኔ እጐዳለሁን አለው:: አሁን ምን ላድርግ አለው ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባ የምታደርገውን ይነግሩሀል አለው:: ከርሱ ጋር የነበሩም ድምጹን ይሰማሉ መልኩን ግን አላዩም፤ ከወደቀበት ተነሥቶ ዓይኑ ጠፍቷልና ሰዎች እየመሩት ቤተ ይሁዳ አደረሱት እኅል ውኃ ሳይቀምስ:: 3 ቀን ውሎ አድሯል::

ከ 72 ቱ አርድዕት አንዱ ሐናንያ በደማስቆ ይኖር ነበር ጌታ በራዕይ ታይቶ ጳውሎስን አሳምነህ አጥምቀው አለው ምእመናንን ከዋሉበት አሳሳድር ካደሩበት አሳውል የሚል አይደለምን አለ:: እስመ ንዋየ ኅሩየ ሩሰይክዎ ሊተ - ምርጥ ዕቃ አድርጌዋለሁና ሂድ ይቀበልሀል አለው:: ሄዶ ወንድሜ ሳውል

በመንገድ የታየህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ያድርብህ ዘንድ ወዳንተ ልኮኛል ብሎ ቢዳስሰው ዓይኑን ሸፍኖት የነበረው እንደ ቅርፊት ተቀርፎ ወድቆለታል:: ሐዋ 9:1-19

ከዚህ በኋላ በክርስቶስ እመኑ እያለ ያስተምር ጀመረ አይሁድ ተደነቁበት በርናባስ በደማስቆ መጠራቱን በምኩራብ ማስተማሩን አይቶ ነበርና ከሐዋርያት ጋር አገናኝቶት ከርሱ ጋር የሚያስተምር ሆነ በልስጥራን ሲያስተምሩ ሽባ ሆኖ የተወለደ ሰው አግኝተው «ለከ እብለከ በስሙ ለእግዚአየ ኢየሱስ ክርስቶስ ተንሥእ ወቁም ቢለው እግሩ ጸንቶ ከወደቀበት ተነሥቶ ቆሟል ሕዝቡም ይህን አይተው «አማልክት ተመስሉ ሰብአ ወወረዱ ኀቤነ አማልክት ሰው መስለው ወደኛ መጥተዋል» ብለው መሥዋዕት ሊሠውላቸው ካላሙ ወፈረውን መርጠው አመጡ:: ልብሳቸውን ቀደው ትብያ ነስንሰው እንደእናንተ ሰዎች ነን አማልክት አይደለንም ብለው ከለከሏቸው መሥዋዕቱን ትተው በወንጌል አምነው ተጠምቀዋል:: ስማቸውን ለውጠው ጳውሎስን ሄርሜን በርባባስን ድያ ብለዋቸዋል ሐዋ 14:8 – 18

አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ነገር እየሠሩ ያሥሩት ይገርፉት ነበር:: በሶርያ በኪል ቅያ ሲያስተምር ሲላስን ጨምረው ገበያ ለገበያ እየጎተቱ ወስደው አሠሯቸው መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲዘምሩ «ወሶቤሃ ኮነ ዐቢይ ድልቅልቅ ወአንቀልቀሉ መሠረተ ቤተሞቅህ» ይላል የእስር ቤቱ መሠረት እስኪናጋ ድረስ ኃይለኛ መናወጥ ሆነ፤ ጠባቂው የመሠረቱን መናጋት የበሩን መከፈት አይቶ ወጥተው የሄዱ መስሎት የአለቆቹን ቁጣ ተሰቆ ራሱን ሊያጠፋ ሰይፉን መዘዘ፤ ቅ.ጳውሎስ ሁላችንም አለን፣ አንድ እንኳ የጠፋ ሳይኖር ራስህን ትገድላለህን አለው በዚህ ምክንያት አምኗል:: ሐዋ 16:19 – 34

ቅዱስ ጳውሎስ የሚያስተምረው በጥበብ ነበር፤ ጣዖት የሚያመልኩትን መምሰኬ ጣዖት መስሎ አስተምሯል «ወኮንክዎሙ ለእለ አልቦሙ ሕግ ከመ ዘአልቦ ሕግ» እንዲል 1 ቆሮ 9:21 ይህስ እንደምነው ነው ቢሉ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከየሀገረ ስብከታቸው ተመልሰው በኢየሩሳሌም ሳሉ ሄዳችሁ አንጾኪያ አስተምሩ አላቸው ዕረፍት ሽተው ነበርና በደመና አፋፍሶ አንጾኪያ አደረሳቸው:: ገብተው ሲያስተምሩ ሕዝቡ ፍቅረ ጣዖት አድሮባቸዋልና ጴጥሮስን ደብድበው ከእግረ ጣዖቱ፣ ዮሐንስን በደረቁ ላጭተው ከደጃፉ ጣሉት:: እሱ ካህነ ጣዖቱ የሚለብ ሰውን ለበብሶ እሱኑ መስሎ መጣ:: ዮሐንስን ከበር ወድቆ አገኘው አንተ ፍቁረ እግዚእ አይደለህምን ምነው ከዚህ ወድቀሀል አለው:: እኔን እፉክ እንጂ



ሊቀሐዋርያት ጴጥሮስም ተደብድቦ ከእግረ ጣዖቱ ወድቋል አለው ወደ ውስጥ ገብቶ መጥቶ ሙቶ ሕዝቡን ሰብስቦ ከቄሣር ተልኬ መጥቻለሁ እንዲህ እያሉ የሚያስተምሩ አሉና ይዛችሁ ስደዱልኝ ብሏል:: አላቸው:: እኛም እንጂ ይዘን ደብድበን ከዚህ ጥለናቸዋል አሉት:: ወዲህ አምጧቸው አለና መጡ:: ምን እያላችሁ ታስተምራላችሁ? አላቸው ጌታ ከሰማያት ወረደ ከድንግል ተወለደ ሞተ ተቀበረ ተነሣ ዐረገ ዳግመኛ ይመጣል ብለን አሉት:: ድንግል ልትወልድ ሙት ሊነሣ ይችላልን ቀጣፊ ብሎ ጴጥሮስን በጥፊ መታው :: ወደቀደመ ግብሩ የተመለሰ መስሎት ተመየጥኩ ጳውሊ ኀበ ዘቀዳሚ ግብርከ ወደ ቀደመው ግብህር ተመለስህን? አለ:: የምትሉት እውነት ከሆነ ሙት አስነሥታችሁ አሳዩን ብሉ የንጉሡ ልጅ ከሞተ 2 ወር ሆኖት ነበርና ከመቃብሩ ወሰዳቸው:: ጸሎት ጀመሩ:: እሱም በለሆሳስ ይጸልያል ሙቱ ተነሥቶ ማን አስነሣህ ሲሉት የቅዱስ ጳውሎስን መልክ ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ ልቅም አድርጎ ዘርዝሮ እርሱ አስነሣኝ ብሏል ተጠራጥረውት ስለነበር እንጂ የተነሣስ በሁሉም ጸሎት ነው በዚህም ሕዝቡ ሁሉ አምነው ተጠምቀዋል::

ሕሙማንንም ሕሙም መስሎ አስተምሯል:: «ወኮንክዎሙ ለድኩማን ከመድኩም ከመ እርብሖሙ ለድኩማን» እንዲል 1 ቆሮ 9:22 ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ታመምኩ ብሎ ከቤተ ሕሙማን ገብቶ 40 ቀን እኅል ውኃ ሳይቀምስ ሲጮህ ቆየ:: በ40 ቀኑ እናንተ በኢየሩሳሌም ተነሥቶ የነበረው ክርስቶስ ካመኑበት ያድናል ቢሉ ሰምቼ ነበር አላቸው:: እንኪያስ ካንተ የባሰበት የለምና እመንና ዳን አሉት፤ አመንኩ ብሎ ቢነሣ ሰውነቱ ተንቋቁቶለት ተጽናንቷል:: ይህን ይዘው አመነ በክርስቶስ እያሉ ከ 200 ያላነሱ ሕሙማን ድውያን ድነው ተነሥተዋል በወንጌልም አምነው ተጠምቀዋል::

ቃል ለቃል ከማስተማሩም ሌላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማዳረስ ከአንዱ ሀገር ወደሌላው ሲሄድ ምእመናን ከሃይማኖት እንዳይናወጹ ከገቢረ ጽድቅ እንዳይወጡ 14 መልእክታትን ጽፎላቸዋል::

ከዚህ በኋላ በ 69 ዓ.ም ሮም ገብቶ ሲያስተምር ንጉሡ ኔሮን ቄሣር አሥሮት ነበርና አካይያ ዘምቶ ጠላት ድል ነሥቶ ሲመለስ ጥሩት አለ፤ መስቀሉን በእጁ ይዞ ቀረበ፤ ተቆጥቶ በሰይፍ ቅጡት አለ፤ እንደ በግ እየነዱ ሲወስዱት የንጉሡ ልጅ አገኘቻቸው፤ እምና ነበርና መጐናጸፊያሽን ስጪኝ አላት ሰጠችው በዚያ ሸፋፍነው ሰይፈውታል:: ደሙም ሰማየ ሰማያት ወጥቶ ቀተሉኒ በዓመጸ እያለ

ተካሷቸዋል። «ደምከ ጴጥሮስ ወልደዮና በጽዋዐ መስቀል ተቀድሐ፤ ወደመ ጳውሎስ በማያተ ጸርሐ» እንዳለ ደራሲ እሱን ገድለው ሲመለሱ የንጉሥ ልጅ አገኘቻቸው ጳውሎስስ? አለቻቸው። በልብስሽ ሸፋፍነን በሰይፍ ጊያልነው አሏት። ልብሴን መልሶልኝ ከጴጥሮስ ጋር አሁን በዚህ ሲያልፍ እያየሁት ገደልነው ትሉኛላችሁን አለቻቸው ልብሷን አይተው አምነዋል። ተቆርጦ የወደቀ ራሱንም ከእንገቱ ቢያጋጥሙት እንደ ቀድሞው ሆኖላቸው ቀብረውታል። መዋዕለ ስብከቱ 42 ዓመት ሲሆን ሲያርፍ የ74 ዓመት አረጋዊ ነበር። /ገድ ሐዋ፤ ዜና ሐዋ/

➢ ቅ.ጴጥሮስና ቅ.ጳውሎስ የሞቱትም የተቀበሩትም ባንድ ቦታና ባንድ ቀን ነው። በብዙ መጻሕፍት ግን ያረፉት በ67 ዓ.ም እንደሆነ ተጽፏል ይህ ከሆነ ግን መዋዕለ ስብከታቸው ቀንሶ የጴጥሮስ 34 የጳውሎስ 26 ዓመት ብቻ ሊሆን ነው።

ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ጳውሎስ
ማደሪያዎች ናቸው ለመንፈስ ቅዱስ
የጠፉት ተገኙ ቀረቡ የራቁት
በጴጥሮስ ድንቅ ቃል በጳውሎስ ስብከት
ዓለም ተቀደሰች በነርሱ ትምህርት
ከጨለማ ወጣች ብርሃን ሆነላት
ወጥምቀት በቁርባን እኒህ ሐዋርያት
ከፈጣሪዋ ጋር ባያስታርቋት
ዓለም ትቀር ነበር ጨለማ ውሏት

እርሷ ግን አ... ...ቀም ወዳጅ ጠላቷን
ከእልፍኝ አስተምሣ በዛብዥ ባያቷን
ይጥፋልኝ ከፊቴ እልይ እነርሱን
ብላ ገፋቻቸው ጴጥሮስ ጳውሎስን
የወንጌልን ብርሃን ያበሩላትን
ከክህደት ገሞት ቤት ሰዎች እንዲወጡ
ቤዛ ሊሆኗቸው ነፍሳቸውን ሰጡ
ከንቱ ወረተኛ ናትና ዓለም
ለመልካም ሰው መልካም መቼም አትከፍል...

ዮሐ 15፡ 18 - 20 ፤ 17 ፡14

## ሐምሌ 6 ዕዝራ

ሱ.ቱ ኤልም ይለዋል፣ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው አባቱ አዛርያስ ይባላል በምርኮ ጊዜ ፋርስ ባቢሎን ይኖር ነበር። ሚጠትን ሲሻ ቀኖና ቢገባ የበለጠ የጌታ ሰው መሆን ተገልፆለት «አንበሳ ወጽአ እምገዳም ውእቱከ ወልድ ዋሕድ» ብሎ ተናግሯል። ዕዝ

አንድ ቀን በጀርባው ተንጋሎ የኢየሩሳሌምን ጥፋት የእስራኤልን መገፋት ሲያሰላስል ልቡ ታወከበት ስምህን የሚጠራ አንተን የሚፈራ እስራኤል ስምህን በማይጠሩ ቃልህን በማያከብሩ ዐላውያን መገፋቱ የእስራኤል ኃጢአት ከባቢሎናውያን ከፋት በልጦ ነውን? ተመዝኖ ቢታይ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እንኳ በልጦ ባልተገኘ ነበር አለ። ቅዱስ ዑራኤል መጥቶ ድሉ እሳተ በመድሉት ወስፍር ነፋስ በሳዳን አው ጸውዓ ለዕለት እንተ ትማልም ኀልፈት



እሳቱን በሚዛን መዝነህ ነፋሱን በሳዳን ሰፍረህ የትናንትናውን ቀን ዛሬ አድርገህ አሳየኝ አለው ሥጋ ለባሽ ይህ እንደምን ይቻለዋል? አለው እንዲሁ ባሕርየ እግዚአብሔርን በመመርመር ፕንዘብ ማድረግ የሚቻለው የለም አለው። ወዲያውም መጻእያት ኃላፍያቱን የሚታየውን የማይታየውን ሁሉ ገለጸለታል። ሱቱ . ዕዝ 21.

ከዚህ በኋላ 6 ቀን ቅጠል ቀምሶ ደንጊያ ተንተርሶ በምድረ በዳ ተቀ መጠ። ጌታ በራዕይ ይነጋገረዋል። በገኛው ቀን ጽዮንን በአምሳለ ብእሲት አይቷታል። ልብሷን ቀዳ አመድ ነስንሳ ታለቅሳለች፤ ምን ሆንሽ አላት 30 ዘመን መካን ሆኜ ልጅ አጥቼ ሳዝን አኖር ነበር፤ ከ 30 ዓመት በኋላ ጌታ ኀዘኔን አይቶ ወንድ ልጅ ሰጠኝ፣ እስከ መጠን ቢያደርስ ሚስት አጨሁለት፤ ወልደየ በአ ቤተ መርዓሁ ሰዓተ ወድቀ ወሞተ ወደ ጫጉላ ቤት ሲገባ ወድቆ ሞተብኝ በዚህ ምክንያት ሰዎኜ ከሀገሬ ወጥቼ ከወገኖቼ ተለይቼ ወደዚህ መጣሁ፤ እንግዲህም ከምግብ ተከልክዬ በዚሁ እኖራለሁ እንጂ ወደ ሀገሬ አልመለስም አለችው እኛ ታቦተ ጽዮን ጠፍታብን መምህራን ካህናት አልቀውብን እናዝናለን አንቺ ግን ለአንድ ልጅሽ ታለቅሺያለሽ፤ ይልቁን ወደ ሀገርሽ ተመለሺ አላት። ይህን ሲላት ድንገት አርአያዋ ተለውጦ መሠረቷ ጽኑ እንደ ፀሐይ የምታበራ ሀገር ሆና ታየችው። «አይቴ ሀሎከ አ መልአከ ዑራኤል - መልአኩ ዑራኤል ሆይ ወዴት አለህ? ብሎ ጮኸ። ቅዱስ ዑራኤል መጥቶ ከወደቀበት አንሥቶ ያየውን ራዕይ - ያየሃት ሴት ጽዮን ናት፣ 30 ዘመን ያለችህ መሥዋዕት ሳይሠዋበት የኖረችበት 3000 ዘመን ነው፤ ልጇ ከጫጉላ ቤት ወድቆ ሞተ ያለችህም ሰሎሞን የሠራው መሥዋዕተ እግዚአብሔር የሚሠዋበት ቤተ መቅደስ መመዝበሩን ስትነግርህ ነው፤ ኋላም ፊቷ እንደፀሐይ ሲያበራ ማየትህ ሁለተኛ መታነጿን ሲያጠይቅህ ነው ብሎ ተርጉሞበታል።

ከዚህ በኋላ ሕዝብህ ሕግህን እንዳያውቁ ሠርተው እንዳይጸድቁ መምህራን አለፉ መጻሕፍት ጠፉ ፈቃድህ ከሆነ ገለጽልኝና መጻሕፍቱን ላጽፍ ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ። ሕዝቡን ተሰናብተህ ሶርያን፣ ደርብያንን፣ ሰላምያን፣ ኢሉናንና አሳሄልን፣ አስከትለህ ተመለስ አለው። ሕዝቡን ተሰናብቶ እነ ሶርያን አስከትሎ መጥቶ ከዛፍ ሥር ተቀመጠ ቅዱስ ዑራኤል ዕዝራ ዕዝራ አርጉ አፉከ አፍህን ክፈት የምሰጥህንም ጠጣ ብሎ ጽዋዐ ሕይወት አጠጣው ያን ጠጥቶ ያለፈው የሚመጣው ሁሉ ተገለጸለት የብሉይ መጻሕፍትን በ40 ቀን አጽፏል። አንሰ በውዕቱን መዋዕል ኢበላዕኩ እክለ ወኢሰተይኩ ማየ እመንቱሰ መዓልተ ይጽሕፉ ወሠርከ ይዴረሩ ይላል እነሱ ቀን እየጻፉ ምሽት ይመገባሉ እርሱ ግን ሌሊት የሚያጽፋቸውን እያሰበ ቀን እየተናገረ ያጽፋቸው ነበርና እንጀራ ውሃ አልቀመሰም ከ40 ቀን በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ የጻፈውን አንብቦላቸው

ሥርዓት ሠርተላቸው ከፈጸመ በኋላ መላእክት በአካለ ሥጋ አሳርገው ብሔረ ሕያዋን አግብተውታል። ዕዝ. ሱቱ. ምዕ.13 በሙሉ

➢ የጻፈው ታሪክ በዘመኑ /ከ537 – 458 ዓ.ዓ / የተፈጸመውን ነው።

<u>ሐምሌ 7 – በዓለ ቅድስት ሥላሴ</u>

ሥላሴ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ቅድስት የሚለው ስያሜ ስም እንደተቀጸለላቸው፣ አንድነትና ሦስትነታቸው እንዴት እንደሆነ፣ በማይመረመር ጥበብ ፍጥረታትን መፍጠራቸውን፣ ባሕርያቸው በሕማም በሞት የማይለወጥ መሆኑንና በኖኅ ዘመን በንፍር ውኃ ከዚያም በኋላ በሰዶም በሎጥ ዘመንም በእሳት ዐመፀኞችን መቅጣታቸውን በክፍል 1 መጽሐፋችን መግለጻችን ይታወሳል። / ገጽ 144 / በዚህ ክፍል ደግሞ ወደ አብርሃም ቤት መግባታቸውን እንገልጻለን።

አብርሃም ቤቱን ከተመላቀለ ጎዳና ሠርቶ የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን እንግድነት ሲቀበል ይኖር ነበር። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ራሱን ገምሶ አጥንቱን ከስክሶ ከመንገድ ቆይቶ እንግዶቹን ወዴት ትሄዳላችሁ? ይላቸዋል፣ ርቦን ሊያበላን ጠምቶን ሊያጠጣን ከአብርሃም ዘንድ ይሉታል፣ የወትሮ አብርሃም መስሏችሁን እኔም እንደናንተ ርቦኝ ያበላኛል ጠምቶኝ ያጠጣኛል ብዬ ብሄድ ራሴን ገምሶ አጥንቴን ከስክሶ ሰደደኝ ይላቸዋል እያዘኑ በመጡበት ይመለሳሉ። እንዲህ አድርጎ 3 ቀን ሙሉ እንግዳ ከለከለበት እሱም ያለምስክር ማብር አላገባም ብሎ ሳይመገብ ቆይቷል።

በሦስተኛው ቀን በቀትር ከድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሥላሴ በአምሳለ አረው በመምሬ አድባር ዛፍ /

> በአብርሃም ወዳጅ በአሞራዊው መምሬ ስም የተሠየመ
> በኬብሮን አጠገብ ያለ ቃላቅ ዛፍ ዘፍ 13:18 ፤ 14:13

ሥር ተቀምጠው ታዩት። ሄዶ ከሁሉ አጋፅዝትየ ቢታ ገብርከ፡ አብርሃም ኋትፍ ከቤት ገብታችሁ እረፉ አላቸው። ደከምናልና ለዘለን አሉት። አንፉን አዝሎ ቢገባ ሁሉቱ በግብር አምላክ ገብተው ተገኝተዋል። እሱም ሰስት እንደሆኑ አውቆ ሳራን 3 መስፈሪያ ዱቄት ወስደሽ አንድ እንጎቻ አድርገሽ ጋግሪው አላት፣ ጋግራ አቀረበች፣ እርሱም ወይፈን አርዶላቸው ወተት አርጎ ጨምሮ አቅርቦላቸው ተመግበዋል፣ አቅረበ ሎሙ ሐሊበ ዐጸኑ ወዕጉለ ላህም / / እንዲል። መብላቸው ግን እሳት ቅቤ በላ እንደ ማለት ነው። ይህንንም ሲያጠይቅ አርኬ አወፊሮስ ያቀረበው ወይፈን ተንሥቶ «ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ» ብሎ አመስግኗል። «ድኅረ በላዕክሙ ላህመ አንበይኑ ፍቅረ ሰብአ ፍጹም፣ ወበኃይልክሙ ሐይወ ላህም፣ ሥላሴ ክቡራን በምእንግዳ ደራሲ።

በሚሄዱም ጊዜ ከዓመት እንዲሁ እግዚአብሔር ቃል እመ ከመዮም እንገባ ገጸከ የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ወዳንተ እመለሳለሁ ሚስትህ ሳራ ወንድ ልጅ



ትወልድልሃለች ብሎ ለጊዜው ልደተ ይስሐቅን ፍጻሜው ግን ሰው ሆኖ የሚያድነው መሆኑን ነግሯታል። ዘፍ 18: 1 – 15

➢ ታሪኩ የተፈጸመው በ200 እና በ1850 ዓ.ም መካከል ነው።

## ለ. ዕረፍቱ ለአባ ሲኖዳ

ሲኖዳ ማለት ተአምኒ ማለት ነው። ሀገሩ እስክንድርያ ነው። አባት እናቱ በንሳል የሚባል ቦታ ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን እናቱ ውኃ ልትቀዳ ስትሄድ አባ ከርሰላርዮስ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ሲሄድ አገኘት፣ ቡርክት አንቲ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ - ለቀደሙት ቅዱሳን ወንድማችው ለኋለኞችም አባታቸው የሚሆን ቡሩክ ፍሬ በማኅፀንሽ አለና የተባረክሽ ነሽ ብሎ 3 ጊዜ ራሷን ሳማት። ደቀመዛሙርቱ አባታችን ቤት አነጋገር አያውቅም ነበር ዛሬ ምን ሆኗል? አሉ ይህን አውቆ የልጇን ክብር ነገራቸዋል።

ያደገው ያባቱን በጎች ሲጠብቅ ነው። ሌሊት መንጋውን አሰማርቶ እሱ ከጉድጓድ ገብቶ ሲጸልይ ያድር ነበር። አንድ አረጋዊ ከጉድጓድ ገብቶ ሲጸልይ አሥሩ ጣቶቹ እንደፋና ሲያበሩ አይቶ አባት እናቱን እንዲህ ያለ ደግ የወለዳችሁ ምን ብፁዓን ናችሁ አላቸው እንዲህማ ከሆነ የእግዚአብሔር እንጂ የኛ አይደለም ብለው ለመምህር ሰጡት ሲሰጡትም ናሁ ይሰመይ አርስመቅሬዶስ ለኩሉ ዓለም እነሆ የባሕታውያን ራስ ይባላል የሚል ድምፅ ከወደላይ ተሰምቷል።

ከዚህ በኋላ እየተማረ እያገለገለ በጾም በጸሎት ተወስኖ በትኅርምት ኗሪ ቢሆን መልአኩ የኤልያስን አስኬማ የዮሐንስን ቅናት ሲሰጠው መምህሩ በራዕይ አየ፣ በማግሥቱም የሰጠሁህን ለሲኖዳ አልብሰው አለው መዓርገ ምንኩስና ሰጥቶታል። ኋላም እሱ ይህን መንፈሳዊ ሀብት ለሌላው የሚሰጥ ሆኗል።

በ431 ዓ.ም ለአውግዞተ ንስጥሮስ በቁስጥንጥንያ በተደረገው ጉባኤ ቅዱስ ቄርሎስን ተከትሎ ተገኝቷል። ንስጥሮስን አውግዘው ሃይማኖት መልሰው ሲመለሱ መርከበኞች ሲቀጸልሉት በተሳፈረበት መርከብ አትሳፈርም ብለው ከለከሉት፣ ጌታ ብሩህ ደመና አምጥቶ በዚያ ተጭኖ ሲሄድ በመርከቡ አንጻር ሲደርስ የመርከቡ ጣሪያ እንደመስታወት ሆኖላቸው እሱና ሲቀጸልሉት ተያይተው እጅ ተነሥተዋል። እኔም ክብሩን አይተው ደግ ሰው አስቀየምነ ብለው ተጸጽተዋል።

በመጨረሻም በሰሙ ጥርቅ ውኃ ለደጋ እስከሚበጠብጥ ድረስ በስሙ በነ የሠራውን እንደሚምርለት ጌታ ቃል ኪዳን ሠጥቶት ሕማም ድካም ሳይሰማው በተወለደ በ120 ዓመቱ ዐርፏል።

➢ የነበረው በ5ኛ ምዕ ዓመት ድ/ል/ክ ነው።

| | |
|---|---|
| ሰላም ለሲኖዳ ካህን ልዑል | መጋለት ደመና አምጣክ ልክለት |
| ቀኑም ተነሥቶ በዕለ ወንጌል | ፈተና እንዲያደርስው ከሚኖርበት |
| ዘወትር ሲተጋ ያነገቶ ልረፍት | ፈጣሪም አንደሰው ቢያቶ ደጋውን |
| ቀኑን ለተልዕኮ ሌሊት ለጸሎት | ምን ይሆን ነበር የአኛማ ነገሮ |
| አሥሩ ጣቶቹ ሆኑለት መብራት | ዛሬ ግን ሰው እንጂ እርሱ አይገኝም |
| በውስጥ የለበሰው የዐርያን ልብሱን | ይደጋገሙለታል ሊወድቅ ቢንገመገም |
| ሳይመለከቱ አይተው ቅናውን | ደጋን ስለላበሉ መንፍቅ አይቀርም |
| መርከብ ለመሳፈር ሰዎች ቢነፍጉት | ሰው በሥራው እንጂ በልብሱ አይለካም |

ምሳ 22:9 ሲራ 10:23

## ሐምሌ 8 - ዕረፍቱ ለአባ ብሶይ

እናታቸው ደግ ክርስቲያናዊት ነበረች፣ መልአክ ከልጆችሽ አንዱን ጌታውን እንዲያገለግለው ስጪኝ ሲላት፣ እርሷም ከ7ቱ የመረጥከውን ውሰድ ስትለው የብሶይን ራስ ይዞ «ዝ ውእቱ ኅሩዩ ለእግዚአብሔር» ሲላት ራዕይ አይቻለሁና ከቤት ርቀህ ንጽሕ ጠብቀህ ጌታህን አገልግል ብላ አሰናበተቻቸው:: ገዳመ አስቄጥስ ገብተው የአባ ባሞይ ረድዕ ሆነው በጾም በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ መናንያኑ በጸሎቱ ይጠብቀናል በትሩፋት ያጽድቀናል ብለው ለሹመት መርጠዋቸዋል::
ከገዳማውያን አንዱ ባሕርየ ሥላሴን ሲመራመር መንፈስ ቅዱስ የለም አለ እርሳቸው በምሳሌ አስተምረውት ተመልሷል:: አንድ ቀንም ሲጸልዩ ቆስጠንጢኖስ በአክናፈ እሳት ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሲያርጉ አይቶ በአካለ ነፍስ መጥቶ «ሰላም ለከሙ እ ብፁዓን መነኮሳት አላቸው፤ » አንተም እንጂ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሟልና ብፁዕ ነህ» አሉት የመነኮሳት ክብራችሁ እንዲህ መሆኑንስ ባውቅ መንግሥቴን ለቅቄ ከዚህ ወድቄ ዳዋ ጥሼ ቤዛ ልሼ በኖርሁ ነበር ብሎታል ከሄደ በኋላ ደቀመዛሙርቱ አባታችን ከማን ጋር ትነጋገር ነበር? አሉት ቆስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ እንዲህ አለኝ እኔም እንዲህ አልሁት ብለዋቸዋል:: ከትሩፋታቸውም የተነሣ ጌታ እንግዳ መስሎ መጥቶ እንግድነት ተቀብለውታል፤ እግሩንም አጥበዋል::
የነበሩት በ 5ኛው ም. ዓመት ድ/ል/ክ ነው::

## ሐምሌ 10 – ናትናኤል ሐዋርያ

ናትናኤል ማለት ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ቀዳሚ ስሙ ስምዖን ነው:: ትውልዱ ከነገደ ብንያም ነው:: የተወለደው በቃና ነው፤ ወስምዖን ቀነናዊ እንዲለው ማቴ 10:4 አብቱ ቀለዮጳ ይባላል:: ጌታ በተወለደበት ዘመን ተወልዷል:: ወደጌታ ያቀረበው ፊልጶስ ነው:: ሙሴ በኦሪት የጻፋለትን ነቢያት ትንቢት የተናገሩለትን መሲሕ ክርስቶስን አገኘነው አለው በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ሊገኝ ይችላልን አለው:: «ነዓ ትርአይ – መጥተህ እይ አለው:: ቢሄድ ጌታ «ነዋ ዘበአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሑት ውስተ ልቡ - ከዳት ተንኮል የሌለበት እስራኤላዊ እነሆ አለ:: ከወዴት ታውቀኛለህ አለው:: ሄሮድስ በጌታ ምክንያት በቤተልሔም 14 እልፍ ከ 4 ሺህ ሕፃናት ባስፈጀ ጊዜ እናቱ በቀፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ደብቃው ነበርና ያን ጊዜ ከሞት ያዳንኩህ እኔ ነኝ፤ የበለስ ቅጠል ሰፊ እንደሆነ ኃጢአት ሰፍኖብህ አንደነበር አውቅህለሁ ሲለው ነው:: እሱም «ረቢ በአማን አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ወንጉሠ እስራኤል



- በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ የእስራኤልም ንጉሥ ነህ» ብሎ አምኖ ተከትሎታል::
ሀገረ ስብከቱ ሰሜን አፍሪካን ይዞ ግብጽ ድረስ ነው:: ከዚያ ገብቶ ሲያስተምር ሕዝቡ ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አመኑ ተጠመቁ:: ጥቂት መፍቀርያነ ጣዖት ተመቅኝተውት ከንጉሥ እንድርያኖስ ነገር ሠርተው አጣሉት:: ጠርቶ ሲጠይቀው ሳይፈራ የጌታን ልደቱን ጥምቀቱን፣ ሞቱን ትንሣኤውን ፣ ዕርገቱን ዳግም ምጽአቱን ተርትሮ ዘርዝሮ ነገረው:: ማን ፈቀደልህ ብሎ ተቆጣበት፣ አንተንም እኔንም የፈጠረ እርሱ ነው አለው:: በዚህ ምክንያት በሰይፍ አስመትቶት ዐርፏል::

## ሐምሌ 12 በዓሉ ሊቀ - ሚካኤል ሊ.ቀ.መ

በዚህ ዕለት ሕዝቅያስን ሊረዳ ተልኳል
ወእመ ዐሠርቱ ወአርባዕቱ ዓመተ መንግሥቱ ለሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ዐርገ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ኀበ ሕዝቅያስ 2 ነገ 18:9 የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ በይሁዳ በነገሠ በ14 ዓመት የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ:: እስራኤል ኃጢአት እየሠሩ ጣዖት እያመለኩ እግዚአብሔርን አሳዝነውት ነበርና ሊያጠፉ ታዞ መጥቷል:: 2 ነገ 18:25 2 ነገ 19:25
ከዚህ በኋላ ራፋስቂስንና ራፋስርስን ላካቸው:: ከቅጽሩ ሆነው የሕዝቅያስ ብላቴና ብለው ተጣሩ፤ ሕዝቅያስ የሚናገሩትን ብቻ ሰምታችሁ ኑ ብሎ ሳምናስን ዮአስንና ኤልያቄምን ሰደደ::
በልዎ ለሕዝቅያስ በመኑ ተወኪለከ ዐለውከኒ በበትረ ባሕሩስኑ ቅጥቁጥ እንተ ግብጽ ወሰበ ተመርጉዘ ቦቱ ብእሲ ይሰብር ወይበውእ ሥርዌጸ ውስተ እዴሁ ወበሆ ይቀስል ወይመውት በማን ተማምነህል ሸንበቆ ቢመረኩዙት ተሰብሮ ስንጣሪው ከእጅ ገብቶ አቁስሎ ይገድላል፤ የግብጽ ንጉሥ ሳኀልም እንኳ ሌላውን ራሱንም አያድንም፤ አሁንም ሰግርያን እንዳጠፋሁ ኢየሩሳሌምንም አጠፋታለሁ ፈጣሪ አለኝ የምትለው ያድንህ መስሎህ ድንኳንህን ቀልፋህ ደጅህን ዘግተህ ቆየኝ ብሎሀል በሉት አሏቸው ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ገብተው ነገሩት እንዲህ ያለ ጠላት በጸሎት እንጂ በጦር አይመለስምና ሄዳችሁ ለነቢዩ ለኢሳይያስ ንገሩት አላቸው:: ነገሩት::
ኢሳይያስ ሲጸልይ የሚሆነው ተገልጾለት አይዞህ ከከተማ ሳይደርስ በመጣበት ይመለሳል ብሎ ወደ ሕዝቅያስ ላከ:: ከዚህ በኋላ ሰናክሬም እልፍ በለኪሶን ሰፈረ ሌሊቱን ቅዱስ ሚካል ሰይፈ መዓቱን መዞ ቢታያቸው ከ14 እልፍ 5 ሺህ የበዙ ሠራዊት እንቀላፍተው ተገኝተዋል:: እርሱንም መላእክት የነጋሪት ድምጽ የፈረስ ኮቴ እያሰሙት ሕዝቅያስ መጣብኝ ብሎ ልብሱን ዘውዱን ጥሎ እየሮጠ ወደ ሀገሩ

ተመልሷል:: ዘውዱን ነቢያት ከሀናት እማኘተውት ለሕዝቅያስ አቀዳጅተውታል::
ሰናክሬም ከቤቱ ደርሶ ለጣዖቱ ሲሰግድ ልጆቹ አድራማ ሌክና ሶርሶር ሠራዊቱን ወዴት ጥለህ መጣህ? አሉት፤ የሕዝቅያስ አምላክ ፈረደብኝ ሞቱ አላቸው ኃያላኑን ሁሉ ለቃቅሞ ወስዶ ነበርና ያን ያህል ሠራዊት አጥፍተህ ዳግመኛ በማን ላይ ልትነግሥ መጣህ? ብለው ወይከውን መቃብሪከ ታሕተ እግረ ሰብእከ ተብሎ ትንቢት ተነግሮበት ነበርና ከጣዖቱ ሥር እንዳለ በዘነዘና ቀጥቅጠው ገድለውታል:: «ወእንዘ ይሰግድ ውስተ ቤተ ሲድራክ አምላኩ፤ ቀተልዎ አድራማሌክ ወሶርሶር ዝኩ» እንዲል አርኪ::እንዲያጠፋ ታዞ ከመጣማ ለምን እንዲህ ሆነ ቢሉ ኃጥአኑን ሊያጠፋ እንጂ በእግዚአብሔርና በደጉ ንጉሥ ላይ እንዲገዳደር አልነበረምና ነው፤ ዳግመኛም ሕዝቅያስ ተመለስልኝ ብሎ 300 መክሊት ብር 30 መክሊት ወርቅ ከሰጠው በኋላ ሁለተኛ በማን ተማምነህል? ብሎ ዘብቶበታልና ስለዚህ ነው::

ታሪኩ የተፈጸመው በ 701 ዓ.ዓ ገደማ ነው::

ያላንዳች ጥርጥር በአምላክ መታመን
መገለጫው ይህ ነው የበጎው ምእመን
በእምነት ወደ አምላኩ እንገቱን ያቀና
ድል ያደርጋል እንጂ አይወድቅ በፈተና
በኃይልም በሠራዊት በሰይፍ በጦር
ፈጽሞ አይድንም የሰው ልጅ በምድር
ኅና በሃይማኖት የጸና ምእመን
ሳይዋጉ ይገድላቸዋል ባለጋራውን

ጠላት ተነሣብኝ ብለህ አትደንግጥ
ይልቅ ሆኅብህን ለአምላክህ ስጥ
እርሱ ያድንሀል ሳየዘገይ በቶሎ
ከቀፈረው ጉድጓድ ጠላትህን ጥሎ
ሹመት አለኝ ብሉ ከታበየ ሹሙ
በወርቅና በብር ከተመካ ሀብታሙ
ዝነኛም ከኩራ በዝነኛ ስሙ
እኒህ ራሳቸውን በውንም አይጠቅሙ
እንደ ነቀዘ ግንድ ሳይወድቁም አይከርሙ::

መዝ 36:35 ምሳ 16:5 ሲራ 10:9

## ሐምሌ 15 – ኤፍሬም ሶርያዊ /ከ306 – 373 ዓ.ዓ

ሀገሩ ሶርያ ነው የያዕቆብ ዘንጽቢን ደቀመዝሙር ነው:: ያዕቆብ ዘንጽቢን ለአውግዞተ አርዮስ ወደ ኒቅያ ሲሄድ አስከትሎት ሄዶ ነበር:: አርዮስን አውግዘው ሃይማኖት መልሰው ካደሩበት ሌሊት ዓምደ ብርሃን ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሉ ብርሃኑ በዓለሙ መልቶ ራዕይ አየ:: ባለቤቱን ግለጽልኝ ብሎ ቢያመለክት የታዘዘ መልአክ መጥቶ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ነው የሰውን ልቡና በትምህርቱ ብሩህ ያደርጋልና እንዲህ ባለ አርአያ አየኸው ለመረዳት ቂሣርያ ሄደ:: በወርቅ ወንበር ተቀምጦ በወርቅ አትሮንስ የወርቅ ወንጌል አዘርግቶ ኩፋር ጠምጥሞ ካባ ላንቃ ለብሶ እጀታው የወርቅ የሆነ የሐር መነሳንስ ይዞ ሲያስተምር አገኘው:: ወተሐዘቦ ልቡ ለኤፍሬም ከመሥጋዊ ውእቱ ይላል፤ እርሱ መሆኑን ተጠራጠረ አራት ነገር አይቶ ይረዳል:: መጀመሪያ ከአፉ ነጸብራቁ እስሳት እየወጣ ሕዝቡን ሲዋሀዳቸው ያያል ትምህርቱ ነው፤ ሁለተኛ ተሐዋስያን ከልብሱ ላይ እያረፉ እንደ ቀሉ ሲረግፉ፤ ሶስተኛ ነጭ ርግብ መጥታ በራሱ ላይ ስታርፍበት ያያል አራተኛ ስሙን ያውቅ ሀገሩን ያይጠይቅ ኤፍሬም ሶርያዊ ኤፍሬም ለብሐዊ ብላችሁ ጥሩልኝ ከማዕዘነ ቤተ. ክርስቲያን ባንዱ ቆሞ ይጸልይላቹህል ብሎ አስጠራው እያደነቀ ቀርቦ የባስልዮስ ቋንቋ ለኤፍሬም የኤፍሬም ቋንቋ ለባስልዮስ ተገልጾላቸው ሲጫዋወቱ አድረው ሲነጋ አሰናብተኝ ልሂድ አለው:: ልትኖር እንጂ ልትሄድ አምጥቶሀልን ብሎ ሕዝባዊ ነው ቢሉ ዲቁና ዲያቆን ነው ቢሉ ቅስና ሹሞ ከሀገረ ስብከቱ ሀገር ከፍሎ አስተምር ብሎ ሰጠው:: ባስልዮስ ይህን መልበሱ ስለ ክብረ. ወንጌል ነው:: ዛሬ ካህናት አክሊል ደፍተው ካባ ላንቃ ለብሰው ሥጋውን ደሙን እንዲያከብሩ እንዲለውጡ:: እሱ ግን በውስጠየሚለብሰው ማቅ ነበረ::
ለብሐዊ የተባለው ሞ ቢረሲ መርጠብ ብርጭቆ ኩዝ ካባ እየሰራ ሽጦ የዓመት ልብሱን የዕለት ጉርሱን እያስቀረ ሌላውን በእመቤታችን ስም ይመጸውት ስለነበር ነው:: እመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ የእመቤቴ ምስጋናዋ እንደ ሰማይ ከከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዝቶልኝ እንደ ልብስ ለብሼው እንደ ምግብ ተመግቤው ጠግቤው እንደውኃ ጠጥቼው ረከቸዉ እያለ ሲመኝ ይኖር ነበረ:: የሹትን መግለጽ ለመንፈስ ቅዱስ ልማዱ ነውና ገልጸለት እልፍ ካራት ሺህ ደርሶት ደርሷል:: አኃዝ እግዚአ መዋግደ ጸጋከ. እስኪል ድረስ:: ጸሎቱም ከወንጌለ ሉቃስ ወበሳድስ ወርኅን ጸሎተ እግዝእትነን አውጥቶ 64 ጊዜ ይደግም ነበር:: ከጊዜያት ባንዱ ዕለቱ ሰኑይ ጊዜው ነግህ ነው:: የነግህ ተግባሩን አድርሶ ከመካነ ግብሩ ተቀምጦ ሳለ እመቤታችን ትመጣለች የብርሃን ምንጻፍ ይነጸፋል የብርሃን ድባብ ይዘረጋል:: ከዚያ ላይ ሁና ሰላም ለከ ኢ.ፍቁርየ ወፍቁረ ወልድየ ኤፍሬም ትለዋለች ታጥቆ እጅ ነስቶ ይቆማል:: ወድሰኒ ትለዋለች:: እፎ እክል ወድሶ ተኪ ዘኢይክሉ ሰማያውያን ወምድራውያን ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ጻድቃን በማዕታት አንቺን ማመስገን የማይቻላቸው ለእኔ እንደምን ይቻለኛል አላት:: በከመ አለበወከ መንፈስ ቅዱስ – መንፈስ ቅዱስ እንዳቀበለህ ተናገር አለችው:: ባርከኒ ይላታል በረከተ ወልድየ ወአቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ይኅድር በላዕሌከ ትለዋለች:: ተባርኮ እንዳጸናው ቀለም ሰተት አድርጐ አመስግኗል:: ስታስደርሰውም በሰባት ክፍላ አስደርሳዋለች:: ምስጋናውም የሰባቱ ዕለታት ወዳሴ ማርያም ነው:: ዜማውን ቅዱስ ያሬድ ደርሶታል:: ገጽ - ተመልከት ሲጨርስም

በያዘችው መስቀሉ ብርሃን ባርካው ተስፋውን ነግራው ዐርጋለች። እሱም የበለጠ ሲያገለግላት ኑሮ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

ሰላም ላንተ ኤፍሬም ደገ አባት ቅዱብ
ከእሾህ ግንድ ላይ የበቀልህ በለስ
ፍሬም ደስ እንዲለን ጠጥተን ረክተን
ውዳሴ ማርያምን አፈለቅህልን
ከማርና ወተት የጣፈጠውን
የድንግል ውዳሴ ነውና ምግብህ

ጠንክረህ በመንፈስ ኃይልም አገኘህ
እስኪሸሽህ ፊርቶ ሰይጣን ጠላትህ
ወደርሱ እንዲያቀርብኝ አምላክ በምሕረት
በአንተ ልምና በአንተ ጸሎት
ልጅህ የዋህ ልሁን በልቤም ትሁት

ቆላ 3:12

## ሐምሌ 18 ለያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእን

ያዕቆብ ማለት አዕቃጺ ሰኩና ማለት ነው። በትምህርቱ የአይሁድን ትምክህት ምጽድቅ ይነቅፋልና እኁሁ ለእግዚእን ይሰዋል። ዝምድናውን አይቶ፣አልአዛር ቅስራንና ማትያንን ይወልዳል ቅስራ ኢያቄምን እያቄም እመቤታችንን እመቤታችን ጌታን ወልዳለች። በእንጻሩ ማትያን ዮሴፍን ዮሴፍ ያዕቆብን ወልዶታል። ዳግመኛም እመቤታችን ከቤተ ዮሴፍ ስትኖባ እናቱ ሙታበት በሐዋንነቱ አገኝታ ከጌታ ጋራ አንድ አድርጋ አሳድጋዋለችና አይሁድም አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለጸራቢ ወስማ ለእሙ ማርያም ወአኃ ዊሁኔ ያዕቆብ ወዮሳ ወስምዖን ወይሁዳ ማቴ 13:55 ማለታቸው ቅሉ ስለዚህ ነው። ወከነ እግሩ ከመ እግረ ነጌ ይላል ከገድል ጽናት የተነሣ እግሩ እንደ ሙቀጫ ተድበልብሎ ነበር። በዚያውም ላይ ምሁረ ኦሪት ነበርና የህገሩን ስርዶ በህገሩ በሬ እንዲሉ የአየሁድ ፀባያቸውን የሚያውቅ እሱ ነው እሱ ያስተምራቸው ብለው በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጰሰነት ሹመውታል።

ከዚህ በኋላ ብዙ አሳምኖ ብዙ አጥምቆ የሚኖር ቢሆን አይሁድ ለምቀኝነት አያርፍምና በምን ነገር እንጣላው ብለው ተነሣ ዐረገ ስለምትለው ስለ ኢየሱስ ናዝራዊ አስተምረን አሉት። ከደርቡ ወጥቶ መንበር አዘርግቶ ከዚያ ላይ ሁኖ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክነት ሲያስተምራቸው ኧረ ይህ ደፋር የማርያምን ልጅ አምላክ ይላል ብለው ጎትተው አውርደው ቀጥቅጠው ገድለውታል።

> ሰማዕት የሆነው በ 62 ዓ.ም ነው

## ሐምሌ 19 – በዓሉ ለቅዱስ ገብርኤል ሊቀ.መ

ገብርኤል ማለት እግዚእ ገብር ማለት መሆኑን ሊቀ መላእክት መጋቢ ሐዲስ አብሳሬ ትስብእት ፍጡነ ረድኤት መሆኑን በክፍል 1





መጽሐፋችን ተምረናል። በዚህም ዕለት ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት እየሉጣን ከእሳት ማዳኑን እንማራለን።

ቅዱስ ቂርቆስ ሀገሩ ሮም አንጌቤን ነው አባቱ ቆዝሞስ ይባላል እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ በትውልዷ ከአዝማደ ነገሥት ነች። ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ በ20 ዓመት በአባ ባጋሚዮስ ምክንያት «አብያተ ጣዖታት ይትራነዋ ወአብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ ብሎ አወጀ /በ303 ዓ.ም/ በዚህ ጊዜ እነሱንቹ ተሰደዱ ቅድስት ኢየሉጣም ልጇ የ 3 ዓመት ሕፃን ነበርና ለርሱ ብላ ወደ ኢቆንዮን ሸሸች።

መስፍኑ ብሔሩ እለእስክንድሮስ ክርስቶስን ካጂ ልጣዖት ስገጂ አላት ዓይን እያለው ለማያይ ጆሮ እያለው ለማይሰማ በቃልህ አዘህ በእጅህ ሠርተህ ለቆምከው ምስል አልሰግድም አለች። አይሆንም ካልሸማ በሰይፍ ትቀጪያለሽ ብሎ አስፈራራት። እስኪ ይሀን ሕፃን ጠይቀው አለችው። አንተ ሕፃን ወርቅ እሰጥሀለሁ ለዚህ ጣዖት ስገድ አለው መንፈስ ቅዱስ አድሮበታልና አንስ ኢይሰግድ ለእማልክቲከ ርኩሳን ዘኢይከሉ አድኅኖ ርእሶሙ ራሳቸውን እንኳ ማዳን ለማይችሉ ርሱሳን ጣዖታትህ አልሰግድም አለው ተበሳጨ በብረት ጋን ውኃ አፍልታችሁ ከዚያ ውስጥ ጣሏቸው አለ ዝፍት ተይ ጨምረው እንድደው በብሬት ጋን ውኃ አፈሉ ድምጸ ለጽሕርት ከመነጉድጋደ ከረምት ይላል የውኃው ፍላት እንደ ከረምት ነጐድጓድ 42 ምዕራፍ ድረስ ይሰማ ነበር። ሊከቷቸው ሲወስዷቸው ኢየሉጣ ልቧ በፍርሀት ታወከ እሱ ግን ፍርሃቷን አርቅላት እያለ ይጸልይላት እሷንም ጥብዒከ እምየ እምዝ ዳግመ ኢይ ረክበነ ሞት ሁለተኛ ሞት አያገኘንምና እናቴ ሆይ በርቺ ጨክኚ በዚያውስ ላይ ዘአድኅኖሙ ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ውእቱ ያድኅነነ አናንያ አዛርያ ሚሳኤልን ያዳነ እኛንስ ያድነን የለምን እያለ እያጽናናት ልብሷን እየጐተተ ከእሳቱ ቀረቡ ከዚህ በኋላ እሷም ጨክና በፍጹም ልብ ሆነው ተያይዘው ከእሳቱ ከውኃው ገብተዋል። በዚህ ጊዜም ከዐላውያን ነገሥታት ከዐላውያን መሳፍንት ገብተው የመሰከሩለት በስሙ መከራ የተቀበሉለት ጌታ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በበትረ መስቀሉ እሳቱን አጥፍቶ የፈላውን ውኃ አቀዝቅዞ አውጥቷቸዋል። በወጡም ጊዜ ልብሳቸው ሳይለበለብ ሰውነታቸው ሳይሸበሸብ ቢያዩ ከአሕዛብ ብዙዎቹ



እምነው አንገታቸውን ለሰለት ሥጋቸውን ለእሳት ሰጥተው በሰማዕትነት ዐርፈዋል።

ቂርቆስ ኢየሉጣ ቅዱሳን ሰማዕት
ከነፈረው ውኃ ዳኑ ከእሳት
በገብርኤል በትር ያላንዳች ጉዳት
ሀዋቆች ነን ባዮች አንተን ቢከዱህ
ለሦስት ዓመት ሕፃን ምሥጢርን ገልፀህ
እምላክነትህን መሰከረልህ።
እንዲህ ነው ልጅ ማለት ወደ ዓለም መድኅን

በርቺ እናቴ እያለ የሚመራ እናቱን
እየጐትተቱ ገብተው ከዕቶን
ኀብኘተውት ወጡ የውኃውን ጋን
እምነት የሌለው ሰው ጌታውን የናቀ
መንግሥቱን እንጃ እንዴ ከወደቀ
ሃይማኖት ያለው ግን ተሸንፎ አያወድቅም
ጊንጡን ቢረግጥ እንኳ እንዳች አይጐዳውም

ማር 16፡15 ቆላ 2፡7

## ሐምሌ 24 አባ ኖብ ጻድቅ

ኖብ ማለት ጽሩይ ወርቅ ማለት ነው ሀገራቸው ደቡብ ግብጽ ንሂሳ ነው። በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ዓላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ሲያፈርሱ የምእመናን ደማቸውን ሲያፈሱ በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣስተው ለመመስከር ወደ ገምኑዲ ሄዱ የጣዖትን ከንቱነት የእግዚአብሔርን አምላክነት ሲመሰክሩ መስፍኑ ብሔሩ ሉክዮስ ፈጣሪህን ክደህ ለጣዖት ስገድ አላቸው። ፈጣሪዬን አልክድም ለጣዖትም አልሰግድም አሉ። በሰይፍ እቀጣሀለሁ አላቸው ከዚህ ሁሉ አምላክ እንደሚያድነኝ አምናለሁ። አሉት ያገኛቸው መርከብ ሲሳፈር ነበርና በመርከቡ ምሰሶ ቀልቀል አስቅሎ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አስገረፋቸው።

ከዚህ በኋላ ብላቴኖቹ ምግቡን መጠጡን አቀረቡለት ። እመገባለሁ ቢል ደንጊያ ሆኖበታል። ብላቴኖቹም ዓይናቸው ታውሯል። እሳቸውን ግን የታዘዘ መልአክ ፈውሶ ከስቅላት አውርዷቸዋል። ምድረ. እትሪክ ሲደርሱ ወደ ጌታ ቢያመለክቱ ብላቴኖቹ ዓይኖቻቸው በርተውላቸዋል። በአምላካቸው አምነው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕትነት አርፈዋል። አባ ኖብን ግን ሥቃዩ ይጽናበት ብሎ በብረት አልጋ በብረት ችንካር ቸንክሮ እሳት አስነደደባቸው መልአኩ መጥቶ ፈወሳቸው። የተቀበሉት መከራ ይህ ብቻ አይደለም። ዓይን ከማየት ጆሮ ከማስማት እንዳያቋርጥ እሳቸውም ስመ እግዚአብሔር ጠርተው አምላክነቱን መስክረው ከመሠቃየት ያረፉበት ጊዜ የለም። ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ በቃል ኪዳናቸው የተማጸነውን ሁሉ እሳቸው ከገቡበት መካነ ዕረፍት እንዲያገባቸው ተስፋቸውን ነግሯቸው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕትነት ዐርፈዋል። በሺህ የሚቆጠሩ አማንያንም አሠራቸውን ተከትለው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕታት ዐርፈዋል።

- የነበሩት በ4 ኛው ም/ዓመት ድ/ል/ክ ሲሆን በሀገራችን ቡልጋ ውስጥ እቲሳ አካባቢ በስማቸው የታነጸ ቤተክርስቲያን አለ።

## ሐምሌ 26 ዕረፍቱ ለዮሴፍ ጻድቅ /ከ 5440 ዓ.ዓ - 44 ዓ.ም/

ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ከቤተ ዳዊት ነው:: አባቱ ያዕቆብ ይባላል:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ለሰው የሚራራ ደግ ሰው ነበር:: ማቴዎስ ወዮሴፍ ፈኃሪሃ እስመ ጻድቅ ውእቱ ኢፈቀደ ይክሥታ ሲል መስክሮለታል:: ማቴ 1:19 ድግር ጠርቦ ጥርብ አለዝቦ ሸጦ ይኖር ነበር:: ጌታም አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለጸራቢ መባሉ ቅሉ ስለዚህ ነው:: ማቴ 13:54 ያዕቆብ ዮሳ ስምዖን ይሁዳ የተባሉ አራት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች ወልዷል:: ሚስቱ ከሞተችበት በኋላ እይሁድ በእመቤታችን ላይ በጠላትነት ተነስተው ከቤተ መቅደስ ትውጣልን ባሉ ጊዜ ልማደ ሥሉስ ጥሩ በሥሉስ እንዲሉ በሶስት ነገር ተመስክሮለት እመቤታችንን ወስዶ ከቤቱ አስቀምጧታል:: ከዚህ በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በደስታዋም በኀዘንዋም ጊዜ አልተለያትም:: ጌታን በወለደች ጊዜ ዳስ ሠርቶ ግርግም አዘጋጅቶ አገልግሏታል::

ልጇን ከሄሮድስ ሰይፍ ለማዳን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ረሀቡን ጽሙን ሐሩሩ ቆሪ ሌሊቱን ታግሣ በረሀ ለበረሀ በተንከራተተችበትም ወቅት አልተለያትም::

«አልቦ እንበለ ሰሎሜ ዘያስተብርየኪ ለኪ፣ ወዮሴፍ አረጋዊ ዘይጸውር ስንቀኪ» እንዳለ ደራሲ::

ከሚጠቅም በኋላ ጌታን እንደ አባት ሆኖ አሳድጎታል:: አይሁድ ጌታን ወልደ ዮሴፍ ማለታቸው ቅሉ ይህን ይዘው ነው:: ያረፈው በ104 ዓመቱ ነው:: መላእክቱን አስከትሎ ደቀመዛሙርቱን በደመና አምጥቶ ካለበት ሰብስቦ ክብርት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ አሳርጓታል:: ሥጋውንም በእጁ ዳሶ እንዳይፈርስ እንዳይበሰብስ አድርጎታል::

ሰው ሁሉ ባወቀው ታማኝነትህ
ኢየሱስ ክርስቶስ ቸሩ ፈጣሪህ
ከደጋጎች ሁሉ አንተኑ መርጦህ
ድንግል ወላዲቱን እደራ ሰጠህ
አረጋዊ ዮሴፍ አንተስ ብፁዕ ነህ
ጽድቅህ እንዲታወቅ ፍጹምነትህ
ጻድቅ ሰው ነው ብሎ መሰከረልህ
ማቴዎስ በወንጌል ተረድቶት ክብርህ
አባ ሕርያቆስም የመንፈስ ልጅህ

ጽኗል እንዳሆነ ንጽሕና ሀብትህ
ድንግል ደስ ቢላት አንተም ደስ ብሎህ
ሲከፋት ተከፍተህ ስታዝን አዝነህ
ስትራብ ተርበህ ሲጠማት ጠምቶህ
መከራዋን ሁሉ አንተም ተቀብለህ
እመቤትነቷን እምላክ ገልጦልህ
ዮሴፍ ጻድቅ ሆኖ ክብርን የወረሰው
ጌታን ከእናቱ ጋር በማገልገሉ ነው
እኛም እናገልግል ድንግልን በሐቅ
ባለሟል እንድንሆን ለአምላክ ጽድቅ::

ምሳ 22:9 ሲራ 10:23

## ሌ. ዕረፍቱ ለአቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/
/ከ328 – 350 ዓ.ም መቀ ሢመት/



የትውልድ ሀገራቸው ሶርያ ነው:: ቀዳሚ ስማቸው ፍሬምናጦስ ነው:: የመጀመሪያው ጳጳስና በትምህርታቸው በትሩፋታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከዝቢረ ኃጢአት ወደ ዝቢረ ጽድቅ የመለሱ ሐዋርያዊ ናቸው:: «ሰላማ ኆኅተ ዘምሕረት ወተሣህሎ፤ አሥረቀ በኢትዮጵያ ሰብርሃነ ክርስቶስ ጸዳሎ፣እንዘ ያዕሊሃ ጽልመት ወቆባርሁ» እንዲል አርኬ-

ሀገራቸው ሶርያ ከሆነማ ወዲህ ምን አመጣቸው? ትለኝ እንደሆነ በፈቃደ እግዚአብሔር መጥተዋል:: መረዳዎስ የሚባል ነጋዴ ዘመድ ነበራቸው:: እሳቸውንና ሲድራኮስን አስከትሎ ለንግድ ወደ ሀገራችን መጥቶ ሲመለስ ከመንገድ ወንበዴዎች ደብድበው ገደሉት ሕፃናቱን ማርከው ለመንግሥት ሰጧቸው:: ንጉሡ አይዛና ይባላል:: የአብርሃ ወአጽብሃ አባት ነው:: ስነ. ምግባራቸውን ጽንዐ. ኃይላቸውን አይቶ ሲድራኮስን ከቤተ.መንግሥት ፍሬምናጦስን ከቤተ መዛግብት አስገባቸው:: ፍሬምናጦስ ከዝበዘ አክሱም ከእንበረም ብሉይ ሲማሩ አድገዋል:: አንድ ቀን የሀገሬቸውንን ሥርዓት አጽንተው እምነት ብከመ ግዝረት ብከመ ጥምቀትሰ ወቀረበ ቁርባን አልብከሙ እምናቹሀል ተገዝራቹሀል ጥምቀትና ቁርባን ግን የላችሁም አሉት:: ግዝረትንማ አባቶቻችን ሊዋውያን አምጥተውልናል እምነትንም የሕንደኬ በጅሮንድ አስተምሮን አምነናል:: ለዝንቱሰ ኢተፈነወ ለነ ሐዋርያ ለጥምቀት ለቁርባን ግን ሐዋርያ አልተላከልንም አሳቸው:: ምነው እስክንድርያ ቅርብ አይደለችምን ሄዳችሁ አታመጡምን አሉት:: ከቤተ. መንግሥት ተማክር አንተ ባወቅህ አምጣልን ብለው 500 ወቄት ወርቅ ሰጥተው ሰደዷቸው ቢሄዱ ሊቀ ጳጳሳቱ አባ እለ እስክንድሮስ ለጉባዔ ኒቅያ ሄዶ አገኙ:: ተከትለው ሄደው ሠለስቱ ምዕት አርዮስን አውግዘው ሲለያዩ አገኝተው ነገሩት:: ይህማ ደግ ነገር ነው ሳላማክር አደርገዋለሁን ብሎ ሠለስቱ ምዕትን ሰብስቦ አንዲት ያለ ሐዋርያ ያመነች ሀገር አለች አላቸው:: ያንተ ዕጽ ናትና አንተን መስላ ትደር አንተ ሹምላት አሉት:: እሱም ከጉባዔ ከተመለሰ በኋላ አልሰነበተም::ከሱ ቀጥሎ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ተሾመ:: ባህላቸውን የለመደ ቋንቋቸውን ያወቀ ካንተ ሌላ ወዴት ይገኛል ብሎ አምስት ዓመት ሐዲስ አስተምሮ አባ ሰላማ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘከሉ ኢትዮጵያ ብሎ ሾሞ ልኳቸዋል:: ሰላማ ማለት ሰላማዊ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው::

ከዚህ በኋላ ከእንበረም ጀምረው ቀሳውስትን ዲያቆናትን ሾመው ዙረው ተዟዙረው አስተምረዋል:: መጻሕፍት ቅዱሳትንም ከሱርስት ከጽርዕ ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል:: የሳባውያንንም የፊደል አቀማመጥ የለወጡትና ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብን ዘዴ ያስገኙ እሳቸው ናቸው:: በዚህ አኳኋን ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን በትጋት ሲፈጽሙ ኑረው በዚህ ዕለት በሰላም ዐርፈዋል::

ሐዋርያ ወንጌል ደግ አባት ሰላማ
የተዋሕዶ ሩና የኢትዮጵያ ገርማ
ሀገሬ ኢትዮጵያ መሙም አትረሳህ
በአምላክ ሰም ተጠምቃ ቆርባለች በእጅህ
አባ በስራትህ በትሩፋትህ
የታመሙ ድነው ቆሙ በፊትህ

ፍጹም መንፈሳዊ ፍቅር አንብሮህ
ወተተህ ተራራውን ቆላውን ወርደህ
ምቀኛ ጣዖትን ነቃቅለህ ጥለህ
በሰውና በአምላክ ዕርቅን አደረግህ
ስለዚህም በእውነት ሰላማ ተባልህ
ሰውን ከአምላክ የሚያስታርቅ መካር
በሕይወት ይኖራል በሰማያት ክብር

ማቴ 5:9 2ቆር 5:20

## ምዕራፍ 6

### ነሐሴ 1 አቦሊ ሰማዕት

ሀገሩ አንጾኪያ ነው፡፡ አቤቱ ዮስጦስ እናቱ ታውክልያ ይባላሉ፡፡ ዮስጦስ የንጉሥ ኑማርያኖስ ልጅ ነው፡፡ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ እያለ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥል መጻሕፍትን ሲቀነጽል ሰይፉን መዞ ሊጣላው ሲሄድ ፋሲለደስ ስለ ሃይማኖትማ በሰይፍ ልንሞት እንጂ ልንገድል አይገባም ተው ብሎ መልሶታል፡፡ ዲዮቅልጥያኖስ ሰይፉን ቢመዝበት ፈርቶ ወደ ማጀት ሸሽቶ ነበር፡፡ ከቁጣው ሲመለስ መጥቶ ሃይማኖትህን ከደህ ለአጽሉን ሰግደህ እኔን መስለህ እኔን አክለህ አትኖርምን አለው፡፡ አይሆንም አለው፡፡ አጎቱን አግብቼ ከመንግሥቱ ገብቼ እንዴት ልጣላው ብሎ ሚስቱ ታውክልያንና ልጁ አቦሊን ጨምሮ ወደ እስክንድርያ ላካቸው፡፡ መስፍኑ ሄርሜኔዎስ ይባላል፡፡ የንጉሥ ልጅ ንጉሥ እንዴት ብዬ እናገረዋለሁ ብሎ ክፉም በጐም አልተናገረውም፡፡ ለያያቸው የሚል ትእዛዝ ደረሰው፡፡ አንድ አንድ ብላቴና እየሰጠ ዮስጦስን ወደ አንዲናው ታውክልያን ወደ ፃ ሰደዳቸው መከራውን ተቀብለው በሰማዕትነት ዐርፈዋል፡፡ አቦሊንም ወደ ብስጣ ሰዶታል፡፡ መስፍኑ ለጣዖቱ ስገድ አለው፡፡ አይሆንም አለ በደንጊያ አስወግሮ በእሳት አስተኩሶ ገደለው፡፡ የታዘዘ መልአክ መጥቶ አንስቶታል፡፡ ብዙዎች በእውነት መግደል ማዳን የሚችል የክርስቲያን አምላክ ነው ብለው አምነው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰውነታቸውን ለእሳት እየሰጡ በሰማዕትነት አርፈዋል፡፡ እሱን ግን መከራው ይጽናበት ብሎ ቆዳውን አስገፍፎ በጨው ሆምጣጤ የተዘፈዘፈ ጨርቅ ጠቅልሎ ቆዳውን አሸክሞ ዝብያ ለዝብያ አዙሮታል፡፡ መከራው ቢፀናበት ወደ ጌታ አመለከተ፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተልኮ መጥቶ ፈውሶታል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደ ቶማስ ዘሕንደኬ በስልቻው ሕሙማንን እየፈወሰ ሙታንን እያስነሳ አሕዛብን በወንጌል እንዲያምኑ ክርስትና እንዲቀበሉ ከዝሊረ ጽድቅ እንዲመለሱ አድርጓል፡፡

አበስኪሮስ የሚባል ባለጸጋ ሕንፃ ያሰራ ነበር፡፡ ከሕንፃው ጽኑዕ ደንጊያ ወድቆ ሁለቱ ልጆቹንና 12 ብላቴኖቹን ራሳቸውን ነምሶ አጥንታቸውን ከስክሶ ገደላቸው፡፡ ልብሱን ቀዶ ትቢያ ነስንሶ ዋይ ዋይ ይል ጀመር፡፡ እነሆን ሙታን ባስነሳልህ በአምላኬ አታምንምን አለው፡፡ አምናለሁ አለ፡፡ በስመ ለእግዚእየ እየሱስ ክርስቶስ ወልደ.



እግዚአብሔር ሕያው ተንሥኡ ሕያዋ ኒክሙ እያለ ስልቻውን ቢያስነካቸው ተነስተውለታል፡፡ አበስኪሮስም ከነቤተሰቡ በወንጌል አምኗል፡፡

መስፍኑ ይህን ቢያፍር አንገቱን በሰይፍ አስመትቶት በሰማዕትነት ዐርፏል፡ ከዚህም አስቀድሞ ጌታ በተሰፋህ ያመነውን በኪዳንህ የተማጸነውን ሁሉ ከገባህበት ውሳጤ መንጦላዕት አገባዋለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮታል፡፡

➢ ሰማዕትነት የተቀበለው በ4ኛው ም.ዓመት ድ/ል/ክ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

### ነሐሴ 2 ቅድስት አትናስያ

ሀገሯ መኑፍ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ለሰው የምትራራ ደግ ሴት ነበረች፡፡ ከደግነቷም የተነሣ ቤቷን ክፍት አድርጋ የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን እንግድነት ስትቀበል ትኖር ነበር፡፡ ያላትን ሰጥታ ስትጨርስ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ፍትረ ዝሙት አሳደረባት እዚ በጀ ቢዩን ምሂላትን ሁሉ ግባ በይው የምትል ሆነች፡፡ ከመንኮሳት አንዱ ዮሐንስ ሐጺር እዘና ተከዞ ሄደ፡፡ አልጋዋን እንጸፉ ከዚያ ላይ ሁና ና ከኑኔ ተቀመጥ አለችው፡፡ ከፊቷ በወንበር ተቀምጦ እያያት ያለቅስ ጀመር፡፡ የመጣህበትን ትተህ ያልመጣህበትን ምን ያስለቅስሀል አለችው፡፡ ከዝሊረ ጽድቅ ወደ ዝሊረ ኃጢአት ተመለሰች ብለውኝ አዝኜ ተክዤ ብመጣ ሰይጣናት በራስሽ ላይ ሆነው ሲሳለቁብሽ እያየሁ ይሀ አያሳዝንምን አላት፡፡ እንኪያስ ምን ይሻለኛል አለችው ድንኩቷ.ኑፍስ ከፈለገሽ ተከተይኝ ብሏት ወጣ፡፡ ሀብቱን ንብረቱን ትጥቁን ማቁን ሳትል ተከተለችው እሱ ፊት ፊት ይሄዳል እሷ ኋላ ኋላ ትሮጣለች፡፡ አባቴ ቀየኝ ትለዋለች ድረሽብኝ ይላታል፡፡ ሸኩ ጋሬጣው ሲወጋት ባለ ንብር ቀሚሷን እየቀደደች እግሯን እያሰረች ተከተለችው፡፡

ከበዓቱ ሲደርሱ አሷን ከምንዳደ እሳተ ትተ ቢጸልይ አድሯል፡፡ የብርሃን መሰላል ተተክሎ መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ አይቷል ሲነጋ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ያመጣሀት ሴት አርፋለችና እናብስት መቃብሯን ይቆፍሩልሀል ገንዘሀ ቅበራት አለው፡፡ ያስ ይሁን ይሀን ያሀል ስትወጡ ስትወርዱ ያደራችሁት ለምንድን ነው አለው፡፡ ነፍሷን ስናሰርግ ነው አለው፡፡ ተቀበላትን አለው እሷንማ ትጥቁን ማቁን ሳትል ከቤቷ ወጥታ በተከተለችህ ጊዜ ነው የማራት አለው፡፡ ቢሄድ ዐርፋ አገኛት፡፡ እናብስት መቃብሯን ቆፍረውለት ቀብሯታል፡፡

የነበረችው በ ኛው ክ.ዘ ድ/ል/ክ ነው፡፡

ቅድስት አትናስያ አምላክ ያደላት
ወደ ሕይወት ገባች አምልጣ ከሞት
ከዓለም ተድላ ይልቅ ያንድእፍታ ደስታ
ከአምላክ ጋር መኖር መሻሉን ተረድታ
ወደርሱ ዘንድ ሄደች ቤቷን ክፍቱን ትታ
ሮጣ ያልጠገበች ገና ቀንጆ ሳለች
ሁሉን ነገር ትታ አምላኳን ፈለገች
ዮሐንስ መምህሯን እየተከተለች

ወደገዳም ስትሄድ እምራ እያነባች
ምድሩን እራበችው ደሟን እያዘራች፡፡
ከፈጣሪም ዘንድ አገኘታ ምሕረት
የቅዱሳንን ሞት ደከማ ስትሞት
በጥዑም ዝማሬ በቃለ ማኅሌት
በክብር አሳረጉ ነፍሷን መላእክት
የኃጥእ መመለስ ወደ አምላኩ ፊት
ደስታቸው ነውና ለነርሱ በእውነት

ማቴ 18፡13 ሉቃ 15፡7

## ነሐሴ 6 ማርያም መግደላዊት

ማርያም ማለት የዋሂት ርኅርኅት ማለት ነው። ቀጥሯ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ነው። መልከ መልካም ተወዳጅ እህት ነበረቻት። ወዲህ መውሰድ ወዲህ መወደድ እያለች ትቀናባታለች። በዚህ ምክንያት 7 አጋንንት አድረውባት ነበር። መንፈሰ ትዕቢት፣ መንፈሰ ጽርፈት /ስድብ/፣ መንፈሰ ቅንዓት፣ መንፈሰ ትውዝፍት /የምንዝር ጌጥ ማድረግ/ መንፈሰ ዝሙት፣ መንፈሰ ሐሜት፣ መንፈሰ ሐሰት ናቸው። ጌታን አምና በተከተለችው ጊዜ ይህን ሁሉ አጥፍቶላታል። ጌታም ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ መጀመሪያ የታየው ለእሷ ነው። ወተንሢኦ በጽባሕ በእሁድ ሰንበት አስተርአያ ቅድመ ለማርያም መግደላዊት እንተ እምኔሃ አውጽአ ሰብአተ አጋንንተ እንዲል ማር 6:9 ከዕርገቱም በኋላ ሐዋርያትን በተልዕኮ ስታገለግላቸው ኑራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች።

## ነሐሴ 7 ጽንሰታ ለእግዝትነ

እያቄም ቴክታ በጥሪያ ይባላሉ። ብዙ የወንድ ባሪያ የሴት ባሪያ የቀንድ ከብት፣ የጋማ ከብት የነበራቸው ባለጸጎች ነበሩ። ከወርቅ በዛት የተነሣ እንደ ቀለበት እንደ አምባር እያሰሩ ከበሬው ከላሙ ቀንድ እያደረጉ ይህን ያህል የወርቅ ቀንድ ይህን ያህል የብር ቀንድ አለን ይሉ ነበር። አንድ ቀን ቴክታ ከቤተ መዛግብት ገብቶ ወርቁ ብሩ ተዝረክርኮ አይቶ በጥሪቃ ሀብታችን ብዙ ንብረታችን ብዙ ነገር ግን የወለድነው ያሳደግነው ልጅ የለንም ለማን ይሆናል አላት። እግዚአብሔር እንጂ ከኔ ባይሰጥህ ከሌላ ይሰጥህ ይሆናል አግብተህ አትወልድምን አለቻው። ሕያው እግዚአብሔርን አላደረገውም አላት። በዚህ ጊዜ አዘኑ ሌሊት በሕልሟ እንቦሳ ከበረታቸው ስትወጣ እንቦሳይቱ እንቦሳ እየወለደች እስከ ስድስት ስትደርስ ስድስተኛይቱ ጨረቃን ጨረቃ ፀሐይን ስትወልድ አይታ እንዲህ ያለ ሕልም አለምሁ አለቻው። ከመተርጐመ ሕልም ሄደው ቢጠይቁ ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ ጨረቃይቱ ከፍጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ትወልዳላችሁ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለጸልኝም እንደ ነቢይ እንደ ንጉሥ ያለ ይሆናል አላቸው። ጊዜ ይተርጉመው ብለውት ሄዱ ከዚህ በኋላ አንስት ወለደች ስሟን ረከብኩ በዕለትየ ስትል ሄኤሜን አለቻት። ሄኤሜን ዴርዴን፣ ዴርዴ ቶናን፣ ቶና ሲካርን፣ ሲካር ሄርሜላን፣ ሄርሜላ ሐናን ወለደች። ሐናም ዕሡተ ማኅፀን ሁና ልጅ አጥታ በኃዘን ትኖር ነበር። ዘማዊት ጉረቤት አለቻት። አንድ ቀን ሐና ልብሴ ቆሸሿል እንጂ እመለስ ነበር አለች። ልብስማ የኔ ልብስ ማጥን መልቶ ተርፎ የለምን እንዱን ለብሰሽ አትሄጂምን አለቻት። ያንቺ ልብስ በአሰበ ዝሙት የተሰበሰበ ነው ንፁሐ ባሕርይ ጌታ ንፁሕ ነገር ይወዳልና ይህን ለብሼ ብለምነው አይሰማኝም ብዬ ነዋ አለቻት። ሐና እኔስ ጌታ ስለምን ልጅ ነሣት እያልኩ ሳዝንልሽ እኖር ነበር። ለካስ በዚህ ክፋትሽ ነው እንደ ድንጊያ አጠጥሮ እንደ ግንድ ገትሮ ያስቀረሽ አለቻት። በዚህ አዘነለች።

ሊቀ ካህናቱ ሮቤል ይባላል። እናንተ እንጂ ወኢይትዌከፍ መባዕም ለመካናት ይላል። ብዙኑ ወተባዝኁ ያለውን ያስቀረባችሁ ርጉማን ብትሆኑ አይደለምን መባችሁን አልቀበልም አላቸው። ሁለተኛም ወላድያን የሚመዘኑት ተረፈ መበዋዕት ነበረ። ያን ከልኪያቸው እያዘኑ ሲመለሱ ከዛፍ ጥላ ሥር አረፉ። ሐና አእዋፍ ከልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ አይታ አእዋፍን ከባሕርያቸው እንዲራቡ ዕጽዋትን እንዲያፈሩ ስታደርግ ሐና ባሪያህን በምን ነገር ልጅ ነሳሀት በውኑ ተፈጥሮዬ ከደንጊያ ነውን ብላ አዘነች። ከቤት ሲደርሱ ወንድ ልጅ ብንወልድ አርፍ አርቆ ተከል አዕድቆ ይርዳን አንልም። ለቤተ እግዚአብሔር ምንጻፍ አንጣፊ መጋረጃ ጋራጅ ይሆናል እንጂ ሴትም ብንወልድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም መሶብ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ ቤተ እግዚአብሔር ታገለግል እንጂ ብለው ብፅዓት ገብተዋል።

ሐምሌ 30 እሷ ለርሱ ግምጃ ሲያስታጥቁት መቋሚያው አፍርታ ፍጥረት ፍሬዋን ሲመገቡ እሱ ለእሷ ነጭ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በቀኝ ጆሮዋ ገብታ በማኅፀንዋ ስታድር ሕልም አለሙ። ሄደው ለመፈከረ ሕልም ነገሩት። የከበረች ልጅ ትወልዳላችሁ አላቸው። የማይመስላቸው ቢሆን ጊዜ ይፍታው እንጂ አንተስ አልፈታኸውም ብለውት ተመለሱ። ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ በሕሊና አምላክ ታስባ ትኖር የነበረች እመቤታችን የተነገረላት ትንቢት ሊፈጸም የአባት የእናቷ ራዕይ ሊተረጐም ጌታ የፈቀደበት ጊዜ ሲደርስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ኢያቄምን ሚስትህ ሐና ትፀንሳለች ደግ ልጅም ትወልዳለች አለው። ዝሙት ይሆንብናል ብለው ምንጻፍ ለይተው ይኖሩ ነበር። ፈቃዱስ ከሆነ ብለው በአንድ ምንጻፍ አድረዋል። እመቤታችን በዚሁ ሌሊት ተፀንሳለች።

ታሪኩ የተፈጸመው በ16 ዓ.ዓ ነው።

በገብርኤል ብሥራት ከእያቄም ከሐና
ድንግል ተወለደች የንጽሕ ሁሉ ጨና
ሁሉም ይደንቀኛል መምረጧ በደትን
የሰው ሁሉ እናት ሆና በማኅፀን።
ዳሩ ግን ለበጎዕት ሆነች እርሷ ያቸው
ዋጋ እንዲያገኙበት ከቸር አምላካቸው።
መድኃኒትነቷ እንዲታወቅ ኀልቶ
ክብሯን መሰከረ የሞተው ተነሥቶ
ሕሙማንም ዋሉ እያመሰገኑ
የሐና ማኅፀኗን ላሰው እየዳኑ

ነገረ ማር

## ነሐሴ 9 አልዓዛር ካህን

ከምርኮ መልስ በ169 ዓ.ዓ ገደማ/ ከሀገት ከምስፍና ደርሶ ይዞ ይኖር ነበረ። ስምዖን አልፍዮስ መባልስ የሚባሉ ንዑሳን ካህናት ነበሩ። ሹመት

በተርታ ሥጋ በገበታ እንዲሉ ፊንታችንን እንሾም ስጠን አሉት:: ለሕዝቡ አስታውቃችሁ ተሾሙ አላቸው:: ሕዝቡን ሰብስበው ፊንታችንን እንሾም ሹመቱን ስጡን አሏቸው:: እሱ ከእግዚአብሔር አግኝቶ ተሹሞታል:: እናንተም ከእግዚአብሔር አግኝታችሁ ተሾሙ አሏቸው:: ይህማ ለርሱ ማድላታቸው ነው ብለው ጽርዕ ወርደው ንጉሡ እንጥያኮስን የዳዊት የሰሎሞን መንግሥት የሚዳኛት አጥታ ምናምንቴ ካህን ይናኝበታል ሄደህ እጅ አታደርጋትምን በዚያውስ ላይ እንጂ የዛሬን አያድርገውና አባትህ እስክንድር በእጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጐ ይገዛት ነበረ አሉት:: እስራኤል ሰዎቹ ጽኑዓን እምባቸው ጽኑ ፈጣሪያቸውም ይረዳቸዋል ሲሉ ሰምቼ እንጂ ሳላስበው የቀረሁ ይመስላችኋልን አላቸው:: ይህማ ቀላል ነገር ነው አመንሁ ብለህ አዋጅ እያስነገረህ እርያ ከኋላህ ላም በግ ከፊትህ አድርገህ ና ብለው መከረውት ተመለሱ:: ከየት መጣችሁ አሏቸው እናንተ ከሁለት ሹመት አንዱን ስጡን ብንላችሁ አይሆንም አላችሁ:: እኛ ግን ጽርዕ ወርደን እንጥያኮስን ያህል ገናና ንጉሥ ሃይማኖት ከምግባር አስተምረን መጣን አሏቸው::
እንጥያኮስም እርያውን ከኋላ ላሙን በጉን ከፊት አድርጐ ከዋለበት ካደረበት ሁሉ አዋጅ እያስነገረ መጥቶ እምባ ከፈቱልኝ መሥዋዕታችሁን ልሠዋ በዓላችሁን በዓል ላድርግ አላቸው:: አሪት ኢይባእ ምእባዊ ወአሞናዊ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ብላለች ብለው አይሆንም አሉት:: ነገሩን ለማስወደድ አይሆንም ካላችሁማ ብሎ ፊቱን መለሰ:: ሶስቱ ካህናት እያችሁ ገና ለገና ርስት ይጠበናል ብለው በእግዚአብሔር ያመነውን ሲከለክሉት እያሉ ይለፍፉ ጀመር:: እውነት መስሏቸው ይግባ እንጂ አሉ:: ጥቂት ራስህን ሁነህ ገብተህ ሂድ ሠውተህ አሉት:: ፊታውራሪዉን ቢትወደዱን በጅሮንዱን እያለ ሠራዊቱን ሁሉ ይዞ ገባ::
የሠራዊቱን መብዛት የሕዝቡን ማነስ አይቶ አልዓዛርን አስጠርቶ አንተ መንቻካ ለእኔና ላንተ በግ ሠዋ በግራ እጅህ የእርያ ሥጋ በቀኝ እጅህ ቢላዋ ይዘህ የበላህ መስለህ ሕዝቡን አሳምንልኝ አለው ጌታዬ የበኩ አብነት አደረገኝ እንጂ የከፋ አብነት አድርጐኛልን አይሆንም አለው:: ይመለሳል ብሎ ለክህነት የደረሱ 7 ልጆቹን ከፊቱ አሰልፎ በሰይፍ መታቸው: ብሎ ለክህነት የማይመለስ ሆነ ሚስቱ መክብዩ ትባላለች በጡትና በጡቷ መካከል በብረት አስቅዞ ሰቀላት: አሁንም አልተመለስም በቁመቱ ልክ ሻሽ አስጠ ምጥሞ ሰም አስነክሮ ብረት ምጣዱን አግሎ በራሱ ላይ ደፋበት ተንጨርጭሮ ሞቷል::
የእኒያስ ፍጻሜያቸው እንደም ነው ቢሉ ንዋያቱን ዘርፎ ሕዝቡን ማርኮ ከተመለሰ በኋላ ለወገኖቻችሁ ያልሆናችሁ ለኔ ምን ልትሆኑኝ ነው ብሎ አንዱን በሰይፍ አስመት ቶታል:: አንዱን በርጥብ ቆዳ አስጠቅልሎ ገደል ጥሎታል:: አንዱን ግን ከምን እንዳደረሰው አልታወቀም:: እሱም አልተጠቀመም:: ቡኒ ወለተ ዱራ ላግባሽ ስላላት ተናዳ የነቀዘ እንጨት በረበረበችበት ጉድጋድ ውስጥ ወድቆ ከዚያም ሰይጣ ን ጢቅ ብሎበት ሽቶ ተልቶ ሞቷል::

መከራና ሥቃይ የማይለውጡት
ያ ዳግ አልአዛር ካህን ነው በእውነት
እንጥያኮስ ቢለው አንተ ሙት ካህን
ሕዝቡ እንዲቀበሉ ዳጉን አምላኪን
የኔን መሥዋዕት ሠዋ ትተህ ያንተውን፣
እንዲህ ሲል መለሰ ሳይርበተበት
አምላኬ የቀባኝ የሰጠኝ ክህነት
እንድህን ነው እንጂ በጎ አብነት
አይደለም እንድሆን ሕዝቡን እንዳስት
ከሙማም አሁን መሥዋዕት ለጣዖት
ና ትጣኝ በሰይፍህ ይሻለኛል ሞት
እንጥያኮስ መስሎት ፈርቶ የሚከድ
ሚስቱን አስቀላት በጡቷ ከግንድ

ሰባት ልጆቹን እንድም ሳያተርፍ
ከፊቱ አቁሞ ፈጃቸው በሰይፍ
ይህ ሁሉ ግን እርሱን አላሸበረው
ይልቅስ ለእምነቱ ጽናትን ሠጠው
እንጥያኮስ አይቶ በእምነቱ መጽናቱን
ሲቀጣው ወሰነ አብዝቶ ሥቃዩን
በጨርቅ ጠቅልሉ በሰም ውስጥም ነከሮ
የጋለውን ምጣድ በራሱ አኑሮ
እንደቅቤ በእሳት ሞተ ተንጨርጭሮ
ዳሩ ግን አልቀረም ደሙ እንዳፈሰሰ
አምላኩ ስለርሱ ጠላቱን ወቀሰ
ክፉው እንጥያኮስ ሳይተመለሰ
ሽቶ ተልቶ ሞተ በቁሙ በስብሶ

ዘሌ 19:18 ዘዳ 32:35 ሮሜ 12:19

## ነሐሴ 13 ደብረ ታቦር

ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ ነው:: ምን አድርጐበታል ቢሉ ብርሃነ መለኮቱን ለሐዋርያት በደብረ ታቦር ገልጾበታል:: ደብር ተራራ፤ ታቦር የተራራ ስም ነው ጌታ በመዋዕለ ስብከቱ ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው ተአምራት የሚያደርገው በተራራ ላይ ነበር:: በዚህም ዕለት ዘጠኙን ከእግሩ ደብር ትቶ ሶስቱ ጴጥሮስን ዮሐንስንና ያዕቆብን አስከትሎ ከርእሰ ደብር ወጣ:: ወተወለጠ ራዕዩ በቅድሜሆሙ ወአብርሀ ገጹ ከመ ፀሐይ ወአልባሲሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ. በረድ ይላል አርአያው ተለውጦ ፊቱ እንደ ፀሐይ አብርቶ ልብሱ እንደ በረድ ነጽቶ ሙሴና ኤልያስ በቀኝ በግራው ሆነው ታዩአቸው:: ሙሴን ኤልያስን መምረጡ ስለምንድርነው ቢሉ ሙሴ 570 ጊዜ ቃል ለቃል ተነጋግሮ ባይህ እወዳለሁ አለው:: አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ እሐተ ሰዓተ እምዘሕይወቱ በዲበ ምድር ፊቴን አይቶ አንድ ሰዓት እንኳ መቆም መቆየት የሚቻለው የለም አለው:: ይህ ካልሆነማ ባለሟል መባሌ ምኑ ላይ ነው::
ቢለው ድኅረሰ ትሬኢ ገጽየ መሥዋዕት ሁኜ በምቀርብበት ጊዜ እታይሀለሁ ብሎት ነበርና /ዘጸ 33:18+23/ ነው:: ያን ለመፈጸም ኤልያስም እንዲሁ ተሰፋ ነበረውና አንድም ጌታ ዕውር ቢያበራ ሙት ቢያነሳ ሙሴ ቱው ኤልያስ ነው ብለውት ነበርና የኛን ጌታ ግን ሙሴ ኤልያስ ይልሀል የሙሴ የኤልያስ ጌታ ይበሉህ እንጂ ብለው እንዲመሰክሩ አምጥቷቸዋል:: ፍጻሜውው ግን ደብረ ታቦር

የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። ሕጋውያንም ደናግልም እንዲመርጧት ለማጠየቅ ከሕጋውያን ሙሴን ከደናግል ኤልያስን አመጣ። ኋላ ግን በማየት ተመኝተው ብርሃን መለኮቱን ቢገልጽላቸው ከፊቱ መቆም ተሳናቸው ሙሴ ትጎይሲ መታበርና ብሏል። ኤልያስም ወደ ሥርዓቱ ተመልሰዋል።

ጴጥሮስ እመብ ትሌትድ ንነበር ዝም ወንገበር መለበተ ማኀደረ ለሕዝ ለሕዝ ለሙሴ ወሕዝ ለኤልያስ ብትወድስ አንዱን ላንተ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ ሰለት ጎጆ ሠርተን በዚህ እንኑር አለ። መጽሐፍ ደመና ብሩህ መሐለው ይለል ይህን ሲናገር ብሩህ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው። ወሊያውም ድምፅ ወእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ ቢሉ ደስ ፡ ሪለኝ ልጄ ይህ ነው እሱን ስሙት የሚል ድምጽ ከመደላይ ተሰምቷል። እነ ጴጥሮስ ደንግጠው ወደቁ ተንሥኡ ወኢትፍርሁ ብሎ አነሣቸዋል ከርእስ ደብር ሲወርዱም ያዩትን የሰውትን እሱ ትንሣኤው ለማንም እንዳይናገሩ አዟቸዋል። ማቴ 17፡3፡9

ዘመኑን በእግረ ደብር ትቶ ሰዎቱን አስቢትሉ መመጣቱ በለምግድር ነው ቢሉ ከዘመኑ ብርሃን መለኮቱን ሊያይ የማይቻለው ይሁዳ ነበርና ትቶትም ቢሄድ ለምን ዓለ ነበርና እንደም ጴጥሮስ እምታለሁ እንዴላሁ ብለው ካንተ ይሬት ብሎት ነበርና እሱን ሰውት የሚለውን እንዲሰማ አምጥቶታል፡ ዮሐንስና ያዕቆብንም በመንግሥቱ በመጣ ጊዜ በቀኝ በግራ መቀመጥን ሽተው ነበርና ነው። ያስ ቢሆን ከተራሮች ሁሉ ታቦርን በለምን መረጠ ብሉ ዳዊት «ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ» መዝ 87፡12 ብሉ ነበርና ያን ለመፈጸም ነው።

እንዴ ደብረ ታቦር ምንኛ ታደልሽ
ጌታ መለኮቱን የገለጠብሽ
ያው ያዕቆብ ሁሉን ሰብስበሽ
በብርሃን ተመልተሽ በመገኘትሽ
ለመንግሥተ ሰማይ ምሳሌ ሆንሽ
ንጉሥ እንዲያምንበት በአምላክነቱ
እንዲ በታቦር ታየ ጌትነቱ
እብ መለኮቱለት በደመና አሎት
የምወደው ልጄ ይህ ነው ሰውት ብሎ
መስና ኤልያስ ካለበት መጥተው
ቆመው መሰከሩ በቀኝ በግራው
ሐዋና የሐንስ ያዕቆብ ሁላችሁ
ጌታ ጌትነቱን ገልጦ ያሳያችሁ
የሰበሩ ናቸው ያዩ ጌርናቸው
እኛም በልባችን ንጹሓን እንሁን
እንደ ሐዋርያት እንድናይ ክብሩን።

ምዕ 23፡4 ማቴ 5፡8

## ንሐሴ 16 ፍልሰተ ሥጋዋ ለእግዝእትነ

እመቤታችን ጥር ሃያ አንድ እሁድ ቀን ግሬዋን በከፍል 1 መጽሐፋችን ተምረናል። ሐዋርያት ሊቀብሯት ቀባር አድርገው ወደ ጌቴ ሴማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ተድሞ ልጇን ተነሣ በረገ አያሉ ሲያውኩን ይናፈራሉ። አሁን ደግሞ እሷን ተነሣች ዐረገች እያሉ ሊያውኩን አይደለምን ንሱ ናምኒ ሥጋዋ ለማርያም ሥጋዋን እናቃጥል ብለው በጠላትነት ተነሡ። ከነሱ አንዱ ታውፋንያ ተራምዶ አልጋውን ጠልፈው የታዘዘ መልአክ ሁለት እጆን በሰይፍ ቀጣው። ከአገጎች ተንጠልጥሎ ቀረ። በድያለሁ ማረኝ ብሎ ቢማልዳት ሬሷን ሆንለ አድርጋ ጴጥሮስን እንደነበረው አድርጋዋት አለቻው። ቢመለሰው ደና ተነሥቷል። ከዚህ በኋላ የሐንስን ጨምሮ ከመካከላቸው ነጥቆ ገነት በዕፀ ሕይወት ሥር አኑሯታል፤የሐንስን እንደምን ሆንች አሉት። ገነት በዕፀ



ሕይወት ሥር አኑሯታል አላቸው። ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው ከነሐሴ ማባቻ ጀምረው ሱባዔ ገቡ። ሁለት ሱባዔ ሲጨርሱ 14 እምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል፣ ማኅተም ተነሥታለች ። ቶማስ አልነበረምና ደመና ጠቅሶ ከሀገረ ስብከቱ ሲመጣ ስታርግ አገኛት። ወሬቀደ ይደቅ እምደመናሁ ይላል ተድሞ የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ አሁን ደግሞ ያንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁን ብሎ ተናደደ እኒያ ትንሣኤዋን ዕርገቷን አላዩም አንተ ግን አይተሀል አሁንም ሄደህ ተነሣች ዐረገች በላቸው ብላ ሰበኗን ሰጠችው። ሄዶ የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ? አላቸው። አግኝተን ቀበርናት አሉት። ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር ለሰሚም አያምር ተውደህ ነገር አይመስለኝም አላቸው። ጴጥሮስ አንተን እንጂ መጠርጠር ልማድህ ነው ተጠራጥርህ ሰውን ስታጠራጥር ትኖራለህ አለው። ጴጥሮስ ተቆጥቶ ፊት ፊት እየሮጠ እነሱ እየተከተሉ ጌቴ ሰማኔ ከመቃብሯ ደረሱ። ቢከፍተው አጣት ደንግጦ ቆመ አታምኑኝም ብዬ እንጂ እመቤታችንስ ተነሣች ዐረገች አላቸው። ምን ይዘሀል አሉት። በዚህ ሰበን አልገባችሁምን አላቸው። ትንሣኤ ዕርገቷን አምነው ሰበኑን ለበረከት ተካፍለውታል።

በዓመቱ ቶማስ አይቶ እኛ ሳናይ እንቀራለንን ብለው ሱባኤ ገቡ። በአሥራ ስድስተኛው ቀን ጌታ ከሰማያት ወርዶ እመቤታችንን መንበር ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን አስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ አቁርቧቸዋል።

የእመቤታችን ያረገችው በ 49 ዓ.ም ነው።

ይገርማል ይደንቃል የድንግል ዕረፍት
የአምላክ እናት ሆና ሞትን ስትሞት
ለድሳ አራት ዓመት በዚህች ዓለም ስትኖር
ደስታ አልነበራትም ከመከራ በቀር
ገና ስትወጣ እንኳ ከሰናቿ ማኅፀን
ዓለም ያዘቻት ነበረ ሰዶትን
በመንፈስ ቅዱስ ግብር ልጇንም ስትወልድ
ታሳድዳት ነበር በበረቱ በጉዱድ
ገቢት በመናትን ከሆናችም ኋላ
ደግሞ አስከፋቻት ልጇን በሕንጨት ሰቅለ
ያየችው መከራ ድንግል በዚያች ዕለት
ሌላም አያልቅም ቢወራ እንኳ ዓመት
ምንም ብትሞትና እዲታ ትንሣኤውን
ታዘንበር ሁሉ በለጋምእን መሳን
አይደረሻትም ወይ ታዲያ የአምላክ ሥራው

እጅግ የበለረች ንጽሕት ማደሪያው
እንደለው ሳትኖር ስትሞት እንደሰው።
ለሁተድላ በደስታ ሳትኖር ለማለት ነው፤
ጥር ሃያ አንድ ቀን በዛም ዕለት
ተቀምጣ ሳለች በዮሐንስ ቤት
ጌታ በክብር መጥቶ ለእምታ መጣት።
ከዓለም ሊያሳርፋት መምጣቱን ስትሰማ
አላችው እንደምን ደምና ይሆን
ወሊያው በተመበሙ ገለጠ አሳያት
ለማት በሊአለ ያሉትን ነፍሳት።
ነፍሳትን በሊአለ ሲመጣቸ አይታ
እኔ ሌላት አለች ለበድርቡ ፈንታ።
ጌታም ሲምራላት ቃል ኪዳኑን ገብቶ
ነፍሷን አሳረገ ከሥጋ ለይቶ።
ነፍሳት ገነት ገቡ ከሞት ጉድጓድ ወጥተው
የድንግል ዕረፍቷ መድኃኒት ሆኗቸው
ሐዋርያት ሽተው ሥጋውን ሊቀብሩ
ወደጌቴ ሴማን ይዘዋት አመሩ
ደግሞ እንደ ልጇ ትነሣለች ብለው
አይሁድ ሊያቃጥሏት መጡ ተሰብስበው
ታውፋንያ ዘሎ አልጋውን ሲይዘው
የታዘዘ መልአክ እጆቹን ቀረጠው
ለርሷ ግን ደግነት ልማዷ ነውና
በክብር ተነጠቀች እጆቹን አድና።
ዮሐንስ ሲመለስ ልቡን ደስ እንዳለው
በዕፀ ሕይወት ሥር መሆኗን ነግሯቸው
ሱባዔ ጀመሩ ሊያዩአት ተመኝተው
ሁለት ሱባዔ ጾመው ነሐሴን
እምጥቶ ሠጣቸው ጌታ ሥጋዋን
እነርሱም ቀበሯት በጌቴ ሴማን።
በሶስተኛውም ቀን በዕለተ ሠሉስ
ከሙታን ተነሣች እንደ ክርስቶስ
በመላእክት አጀብ በጥዑም ማኅሌት
ቶማስ በደመና ስታርግ አያት
ዕርገቷን ከቶማስ ሐዋርያት ሰምተው
በዓመቱም በአንድነት በሱባዔ ተግተው
በአሥራ ስድስት ቀን ጌታ መጥቶላቸው
በርሷ መንበርነት ቀድሶ አቁርቧቸው
ዕርገቷን ሰበኩ በዓለም ሁሉ ዞረው።
ወትቀውም ንግሥት እንዳለ ዳዊት
ሕያው ሆና አለች ዛሬም የእኛ እናት
በልጇ ቀኝ ሆና ከብራ በስብሐት
ለፍጥረቱ ሁሉ ስታሠጥ ምሕረት

## ለ. /ፍልሰታ ሥጋሁ ለቅዱስ ጊዮርጊስ/

ፀሐይ ከመመላለስ ማይ ከማፍሰስ እንደማያቋርጥ ክርስቶስን አልክድም የሚል አንድ እንኳ በጠፋበት ጊዜ በክርስቶስ አምላክነት የጣዖትን ከንቱነት በመመስከር ያለማቋረጥ 7 ዓመት ሲሰቃይ 3 ጊዜ ሲሞት ሲነሣ ቆይቶ በ4ኛው ሚያዚያ 23 ቀን ዐርፏል:: ጌታም እንደወደደው ወዶታልና እንዳከበረው አክብሮታል ና ዕረፍቱን እሱ ለቤዛ ብዙኃን በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ባረፈባት ዕለተ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት እንዳደረገለት ፍልሰተ ሥጋውንም ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕርገተ ሥጋ ጋር አንድ አድርገው እንዲያከብሩት በዚሁ ዕለት በሀገረ ሙላዱ ልዳ በስሙ ወደነጹለት ቤተ ክርስቲያን እንዲያፈልሱት አድርጓል::

## ሐ. ዕረፍቱ ለጊጋር መስፍን ሶርያ

መስፍነ ሶርያ ነበረ:: እመቤታችን ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ ከቤቱ እንግድነት ሰንብታለች:: ወጥታ ከሄደች በኋላ የሄሮድስ ብላቴኖች መጥተው እንዲህ ያሉ ሰዎች ከቤትህ ገብተዋል:: አውጣ አሉት:: እኔ በእጃችሁ ቤቴ ከፊታችሁ ገብታችሁ ማየት ትችሉ የለምን አላቸው:: ገብተው ፈልገው ቢያጧቸው ደብቀሃቸው ነው እንጂ ብለው ባሰይፍ መተውታል::

➢ ሰማዕት የሆነው በ 2 ዓ.ም ነው::

## ነሐሴ 22 ዕረፍቱ ለሚኪያስ ነቢይ

ሚኪያስ ማለት መኑ ከመ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው:: ቁጥሩ ከ 12 ደቂቀ ነቢያት ነው:: ንጉሡ አክዓብ ይባላል:: የይሁዳውን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ከኔ ጋራ ወደ ሬማት ዘገለዓድ አትወጣምን አለው:: ያስ ቢሆን ፈቃደ እግዚአብሔር ሳንጠይቅ ይሆናልን አለው:: ደግ ነገር አይናገርልኝም እንጂ ሚኪያስ ወልደይምላ ነበር አለው:: ጥሩት አለ: ነቢየ እግዚአብሔር ወደሬማት ዘገለዓድ ልውጣን አለው:: እስራኤል ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ሲቅበዘበዙ አይቻለሁና ሂድ ተከናወን አለው ይኸውልሃ ክፉ እንጂ ደግ ነገር አይናገርልኝም አላልሁምን አለው:: አንተ ከነቢያት ሁሉ የተለየህ ነህን አሉት:: አሊያንማ ጌታ አክዓብን ወደሬማት ዘገለዓድ እንዲወጣ የሚያታልል ማነው ቢል ከመናፍስት አንዱ እኔ በነቢያቱ አፍ መንፈስ ሐሰት



አለው:: ሴዴቅያስ ዘሉ ፊቱን ጸፋው:: አክዐብም በደኅና እስክመለስ ድረስ የመከራ እንጀራ እየመገብህ እኑረው ብሎ ወደ ኢዮአስ ሰደደው:: ያም አልቀረ አክዓብ በጦር ተወግቶ ሙቷል:: እስራኤል ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ተቅበዝብዘዋል:: 2 ዜና 18:1 – 3

ከዚህም የበለጠ የሥጋዌ ነገር ተገልጾለት ወአንቲኒ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቴሀቲ እምነገሥተ ይሁዳ እስመ እምኔኪ ይወድእ ንጉሥ ዘይሬእዮሙ ለሕዝብየ እስራኤል ሲል የጌታን ከሰማያት መወረድ በቤተልሔም መወለድ እንድም ቤተልሔም ቤተ ኅብስት ከተባለች እመቤታችን እንደሚወለድ ትንቢት ተናግሯል:: ሚክ 5:2

ከዚህም በኋላ እስከ ሕዝቅያስ ዋልደ.አ ካዝ ንጉሠ እስራኤል ድረስ አስተምሯል::

➢ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 735 – 688 ዓ.ም ነው::

## ነሐሴ 24 ዕረፍቱ ለቶማስ ዘመርዓስ

በመርዓስ ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሟል ሲያስተምር ዐላውያን ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ ዐጽቅ ዐጽቁን እየቆረጡ ለጣዖት ሲያጥኑት ኑረዋል::

ከዚህ በኋላ ዘመነ.ሰደት አልፎ በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ቀርነሃይማኖት ቆሞ ባለ አርዮስ ወልድ ፍጡር ብሎ ተነሣ:: ንጉሡ በኒቅያ ጉባዔ ይሁን ብሎ አዋጅ ነገረ:: ደቀመዛሙርቱ በቅርጫት አድርገው በአህያ ጭነው ሲሄዱ ካደረሱት ቦታ አርዮሳውያን ሌሊት ካደረበት አህዮቹን አንገት አንገታቸውን ቆርጠው ጣሏቸው:: እሱም በጸጋ አውቆ ኀዘ ሳይቀድ ተነሥተ ልጆቼ ጫኑ አላቸው:: ቢሄዱ ተቆራርጠው አገኟቸው ምኑን ጫነው እንዲህ አድርገዋቸዋል አሉት:: ራሳቸውን ካንገታቸው ግጠሙ አላቸው:: አህዮቹ አንዲቷ ጥቁር አንዲቷ ነጭ ነበሩ:: የነጭነቱን ከጥቁሬት የጥቁሬቱን ከነጭቱ አድርገው ገጠሙት:: ቢባርካቸው ተነሥተዋል:: ከዚያም ሲደርስ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ ስነ. ጽድቁን ተረድቶ አባቴ በረከትህ ይድረሰኝ እያለ ከሰይፍ የቀረ ሰውነቱን ዳሰታል:: አርዮስን አውግዞ ሃይማኖት መልሶ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ብዙም አልቆየም በዚህ ዕለት ዐርፏል::

## ለ. ዕረፍቱ ለአቡነ ተክለሃማኖት/ከ 1215-1313/

ተክለሃይማኖት ማለት ተክለ.አብ ተክለ.ወልድ ተክለ.መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው:: ብሔረ ሙላቸው ጽላልሽ /ዞረሬ/ ነው:: አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእ ኀረያ ይባላሉ:: ቀዳሚ ስማቸው ፍስሓ ጽዮን ነው:: ዓመት ከሰስት ወር ሲሆናቸው በምድረ.ሽዋ ይልቁንም በጽላልሽ ረሀብ ሆነ:: እግዚእ ኀርያ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ሲታጎልብን ነው? እያለች ስታለቅስ እንባዋን ጠረጉላት የቅዱስ ሚካኤል በዓል ሊታጎልብኝ እንደሆን እያውቅ ምን ይለኛል ብላ ጡቷን አጎረሰቻቸው:: መጥባቱን ትተው ወደ ቤት እንድታገባቸው አመለከቷት:: ይዛቸው ገባች:: እፍኝ የስንዱ ዱቄት ያለበት እንቅብ ነበረ:: እጃቸውን ቢጭኑበት መልቶ ፈሰሰ:: ዘጠኝ እንቅብ አስመጥታ አቀረበችላቸው:: እየዘገኑ ጠብ ጠብ ቢያደርጉበት ዘጠኙም መልተው ተገኝተዋል:: የቅቤውንም ማሰሮ

አስመጥታ እጃቸውን ብትከተው ከእሳት እንደ ጣዱት ፈልቶ መልቷል፡፡ ሌላውንም የሚያስፈልጋትን ሁሉ በእጃቸው እየዳሰሱ አበርክተውላታል፡፡ ይህንንም በዓይነቱ አዘጋጅተው መጋቢት 12 ቀን በቅዱስ ሚካኤል ስም የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን ሁሉ ሲያበሉ ሲያጠጡ ውለዋል፡፡ እነሱም እንዲ የረሀቡ ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ሲመግቡት ኑረዋል፡፡

ሰባት አመትቢሆናቸው አባት እናታቸው ሕይወት ብነበጽዮን ለሚባል መምህር ሰጧቸው፡፡ ጌታ ልቡናቸውን ብሩህ ልሳናቸውን በሊህ አድርጓቸው መምህራቸው ከሚነግራቸው ሌላ መጻፍትን እንብበው ምሥጢር የሚተረጉሙ ሁነዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ጸጋ ዘአብ ዲቁና ሊያሾሟቸው ከአባ ጊርሎስ ይዘዋቸው ሄዱ፡፡ ቅዱስ ሚካኤል እስመናሁ ይመጽእ ኀቤከ ወልድ ኅሩይ ዘኢይከውኑ ሰማይ ወምድር ሜጢአሑቲ ሥዕርተ ርእሱ ሰማይና ምድር የአንዲት ጸጉሩ ዋጋ የማይሆኑ የእግዚአብሔር ምርጥ መጥቷልና ተቀበለህ መዓርገ ዲቁና ስጥተህ አሰናብተው አላቸው፡፡ እሳቸው ተደስተው እነሱንም አስደስተው ተቀብለው መዓርገ ዲቁና ሰጥተው አሰናብተዋቸዋል፡፡

ሲመለሱ ጊዜው መሽቶባቸው ስንቅ አልቆባቸው ከመንደር ገብተው ሰላም ለእናንተ ይሁን አሏቸው፡፡ እናንተሀን ሰላም ይንሳት ምን ልትሆን መጥተሀል አሏቸው፡፡ ይልቁንም እንዱ ፊታቸውን ጸፋቸው፡፡ ወደጌታ ቢያመለክቱ ቅዱስ ሚካኤል በአውታረ ነፋስ ውሃርበእስዋጢ እሳት እየነረፈ ማረኝ ማረኝ አስብሉታል፡፡ መጻጻተን አይተው ጸልየው አሠርደውታል፡፡

መሠርያን መሰለውት ጸልቷቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ከቤቱ አስገብቶ ማዕድ ሠርቶ መግቧቸዋል፡፡ ሚስትና ልጁ ድውያን ነበሩ፡፡ የእጃቸውን የእግራቸውን እጣቢ ቢረጯቸው ድነው ተነስተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የ15 ዓመት ልጅ ነበሩ፡፡ አካለ መጠን ሲያደርሱ ሚስት አጭተው አመጡላቸው፡፡ ሸሽተው ሄደዋል፡፡ ከዚያም ዘንድ ከዳለሱ ከአቡነ ጌርሎስ ሄደው መዓርገ ቅስና ተቀብለው ለቀ ካህናት ዘምድረ ሸዋ ተብለዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አባት እናታቸው በ 5 ቀን ልዩነት ተከታትለው ዐረፉ፡፡ ዕዓሲ ማውታ ሁኜ ቀረሁ ብለው አዘኑ፡፡ አንድ ቀን ሲያድኑ ወደ ዱር ሄዱ፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ለካህናት የማይረባውን አይን ልታድን መጣህን አላቸው፡፡ ወዲያውም ጌታ በቅዱስ ሚካኤል ከንፍ አርፎ ኢፍቀርየ ፍስሓጽዮን ናሁ ኅረይኩከ ከመ ትኩን ሐዲስ ሐዋርያ -ሐዲስ ሐዋርያ እንድትሆን መረጥሁህ እምይእዜሰ ኢትንሰው አራዊተ አላ ትንዑነፍሳተ እንግዲህም ነፍሳትን እንጂ እንስሳ አታድንም ስምከስ ይኩን ተክለሃይማኖት ስምህም ተክለ ሃይማኖት ይባላል ብሏቸዋል፡፡ እሳቸውም ይህን ከሰሙ በኋላ ልዋል ልደር አላሉም፡፡ ለሱቱን ቤታቸውን ከፍቱን ትተው ማስተማር ጀምረዋል፡፡ ጣያታቱን እያፈራረሱ ኢጋንንቱን እየደመሰሱ ከተታ ደረሱ በወንጌል እመኑ ክርስትና ተቀበሉ አሏቸው፡፡ አምላካችንን ትተን አይሆንም አሉ፡፡ ማንን ታመልካላችሁ? አሏቸው፡፡ ብንቸገር የሚረዳን ብንታመም የሚያድነን ታላቅ ዛፍ አለ አሏቸው፡፡ እንግዲያስ እኔም እንድሰግድለት ካለበት አድርሱኝ አሏቸው፡፡ ይዘዋቸውሄዱ፡፡ ሲደርሱ ሶስት ምዕራፍ ሲቀራቸው በዚያ ያደረ ሰይጣን ተክለሃይማኖትን መልስኝ እያለ ይጮህ ጀመር፡፡ ስምህ እንግዳ ምግባርህ እንግዳ አምላኬን አልወደደህም ከዚህ ቆይ አሏቸው፡፡ ወደጌታ ቢያመለክቱ ዛፉ ተንቅሎ መጥቶ ከፊታቸው ቆመ፡፡ ሰይጣኑንም ቅዱስ ሚካኤል በሐጹ እሳት እየነደፈ አባርሮታል፡፡ ዛፉ ሲነቀል ከሥሩ ጎዝበስ ቀና ሲሉ የነበሩ ሰዎች





ሞተው ነበር፡፡ ቀድሞ ከሞቱትም 15ቱን ጨምረው አስነስተዋቸዋል፡፡ በዚህም በዚህም ከስምንት እልፍ ያላነሱ ነፍሳት አምነው ተጠምቀዋል፡፡
መሰፍን ብሔሩ ድል አሰግድ ይባላል፡፡ በዚህ ዛፍ ምክንያት በቀን 100 ወቄት ያገኝ ነበር፡፡ እንግዲህማ ይህ ሁሉ ሲቀርብኝ አይደለምን ብሎ ብላቴኖቹን አስከትሎ ሄደ፡፡ እሳቸው ለመፍቀደ ደብር ይሆነኛል ብለው ያን ዛፍ ያስፈልጡ ነበር፡፡ እጣላቸዋለሁ ብሎ ሲንደረደር የአንገቤት ሰንባሪ ከዓይኑ ገብታ እንደ እሳት ጠበሰችው፡፡ ዋይ አለ ፈውሰውት ከነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል፡፡
ከዚህ በኋላ ምድረ ዳሞት ገቡ፡፡ ንጉሡ ሞተሰሚ ነው፡፡ ከወዴት መጥተሀል አላቸው፡ እግልከትህን እንዳጠፋ ከጌታ ተልኬ መጥቻለሁ አሉት፡፡ አንተን እንድናመልክህ መጥተሀ ብሎ በቀፎ አድርጎ ጠመግራር ከሚባል ገደል አስጣላቸው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ከንጉሥ ፊት አደረሳቸው፡፡ ሁለተኛ አስጣላቸው፡፡ የጣሏቸውን ብላቴናች ቀድመው ከደጁ ተገኙ፡፡ ይህ መሠርይ ብሎ ሰይፉን ቢወረውር ከእጁ ተጠቅልላ ቀረች፡፡ ሁለተኛም ቢወረውር ከእጁ ተጠቅልላ ቀረች ሥቃዩ ጸናበት፡፡ ዋይ አለ፡፡ ያድኑኛል ይጠብቁኛል የምትላቸው ካህናተ ጣዖትህ አያድኑህምን አሉት አስጠርቶ አድኑኝ አላቸው፡፡ የዚህን ሥራይ መፍታት እንደምን ይቻለናል አሉ፡፡ እኔ ካዳንኩህ እነሱኝ ካላዳንኩህ እኔን እንድትቀጣ ቃል ግባልኝ አሉት፡፡ ቃል ገባላቸው፡፡ ጸልየው አድነውታል፡፡ ይልቁንም ከ 25 አመት በፊት እናታቸው እግዚእ ኃሊያን እግለሁ ብሎ ከጣዖቱ ፊት ባቆማት ጊዜ በተፈጸመው ግሩም ርእይ ልቡን እጥቶ አንድ ጊዜ ገደሉት አንድ ጊዜ አድኑት ከአየር ላይ ቤት ስሩልኝ ከምድር በታች ዘር ዝሩልኝ ሲል ይኖር ነበር ከዚህ ሁሉ ጅውሰውታል፡፡ካህናተ ጣዖቱ ንዘሰዶፍ አስፈጅቷቸዋል፡፡

እሱም አምና ተጠምቋል። ከዚህም የበዙ ተአምራትን እያደረጉ እያስተማሩ አብያተ ክርስትያናት እያሠሩ 12 ዓመት ኑረዋል።

ከ 12 ዓመት በኋላ ወደ ምድረ እምሐራ ሄደው ከአባ በጾሎተ ሚካኤል ገዳም እህል እየፈጩ ውሃ እየቀዱ እንጨት እሰበሩ ይልቁንም ሕሙም እየፈወሱ አጋንንትን እየደመሰሱ 10 ዓመት ኑረዋል። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ሐይቅን እንደ ደንጊያ እንደ ብረት አጽንቶላቸዋው በእግራቸው እየተራመዱ ከአባ ኢየሱስ ሞአ ገብተው ልብሰ ምንኩስና ለብሰው በጾም በጸሎት ተወስነው 10 ዓመት ኑረዋል። ከ10 ዓመት በኋላ ደብረ ዳሞ ገብተው ከአባ ዮሐኒ አስኬማ ምንኩስና ተቀብለው 10 ዓመት አገልግለዋል። በሄዱ ጊዜ ሰይጣን ለምቀኝነት እያርፍምና ይሙት በቃ ብሎ የሚጠርዱበትን ገመድ ከሥሩ ነቀለባቸው። ጌታ በግራ በቀኝ ስስት ስስት /ስድስት/ እክናፍ ሠጥቷቸው በዚያ በረው ወርደዋል።

ኢየሩሳሌም ደርሺ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነስቼ ልምጣ ብለው በሠረገላ ብርሃን ተጭነው ሲሄዱ በጽንፈ ኤርትራ አንድ ሙት አገኙ። አንተ ምውት ለእመ ኮንከ ክርስቲያናዌ ተንሥእ እብለከ በስሙ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ተንሥ አሉት። ተንሥቷል። ምን ሆነህ ሞትክ አሉት። ኢየሩሳሌም ሄጄ እጅ ነስቼ እመጣለሁ ብዬ ከዚህ ስደርስ ውኃ ጽም ጸንቶብኝ ሞትኩ አላቸው። አስከትለውት ሄደው ቅዱሳት መካናትን ተሣልመው ሲቀጳጳሳቱ ዮሐንስ ይባላል እጅ ነስተውት ተመለሱ። በዚህ ዓመት ሶስት ጊዜ ኢየሩሳሌም ደርሰው ተመልሰዋል። ሲቀጳጳሳቱ መነኮስ በዓት ሠርቶ ብፅዓት ገብቶ በጽሙና በብትሕውና ይኖራል እንጂ ይዞራልን በዓት ሰርተህ ብፅዓት ገብተህ በጽሙና በብህትውና ኑር አላቸው። ከኤርትራ ጀምረው እያስተማሩ ተመልሰው በደብረ ሊባኖስ በዓት ሠርተው ብፅዓት ገብተው ተቀምጠዋል። በዚህም ላይ አጋንንቱን መሠርያኑን በኃይለ እግዚአብሔር ድል ነስተው እሕዛብን በሃይማኖት ወልደው በምግባር አሳድገው የሚኖሩ ሁነዋል። ካመኑት ብዙዎቹ አሣቸውን ተከትለው ከወገኖቻቸው ተለይተው ሥርዓተ ምንኩስና ተምረው በጽሙና በብሕትውና የሚኖሩ ሁነዋል። ከሳቸውም ፍጹምነት የተነሣ ደቀመዛሙርቶቻቸው ወንዶችም ሴቶችም በማብረ ኃጢአት ሳይተዋወቁ ባንድ ላይ ያድሩ ነበር።

ከዚህ በኋላ ከበዓታቸው ገብተው ወደፊት ወደኋላ ቁጭ ብድግ እንዳይሉ ከፊት ከኋላቸው ከግራ ከቀኛቸው ስምንት ጦር ተክለው ሱባዔ ያዙ። ከቁመት ብዛት ከገድል ጽናት የተነሣ አንድ እግራቸው ጥር 24 ቀን (13 06 ዓ.ም) ተቆርጦ ወድቋል። ከዚህም በኋላ ባንድ እግራቸው ቆመው 7 ዓመት ኑረዋል። ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ እመቤታችንን መላእክትን ነቢያትን ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትን አስከትሎ መጥቶ ኢፍቁርየ ተክለሃይማኖት ወዳጄ ተክለሃይማኖት ሆይ ሰማዕኩ ጸሎተከ ወስእለተከ ልመናህን ሰምቼ ወናሁ አእርፈከ አምብዙኅ ጻማ ከድካምህ ሳሳርፍህ መጣሁ ነበ ሀሎ ፍስሐ ህየ አነብረከ መንፈሳዊ ደስታ ካለበት አሳርፍሀለሁ እምዝ ዳግመ ኢይሬክበከ ሞት እንግዲህም ሁለተኛ ሞት አያገኝህም በተስፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማጸነውን ሥጋህን የቆረስክበትን ደምህን ያፈሰስክበትንም ቦታ እጅ የነሣውን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም አድንልሀለሁ በዚህችም ቦታ በተስፋህ ጸንተው በኪዳንህ ተማጽነው የሚኖሩ ልጆችህን እንደ ሰማይ ከዋክብትእንደ ባሕር አሸዋ አበዛልሀለሁ ብሎ ተስፋቸውን ነግሯቸዋል። ከዚህ በኋላ ሕማመ ብድበድ ለሞታቸው ምክንያት ሁኗቸው በተወለዱ በ 99 ዓመት ከ 10 ወር ከ 10 ቀናቸው በዚህ ዕለት ዐርፈዋል።



አባ ተክለሃይማኖት ክቡር ወቅዱስ ከክህደተ ከተማ ከአጋንንት ግዛት
ሐዲስ ሐዋርያ ሱታፌ ቶማስ። በወንጌል ቃል ማርከ ነፍሳትን ከሞት
እርሱን ለምስጋና ጌታ ቢመርጠው እጅ መንሻ አቀረበ በአምላኩ ፊት
ገና የእናቱን ጡት ጠብቶ ሳይጠግበው ጻድቃንን እናከብር ስንኖር በምድር
ቅዱስ ቅዱስ ብሎ አመሰገነው። እንደተናገረው ዳዊት በመዝሙር
በጥዑም ምስጋናው በሥሙር ጸሎቱ ዳግ ጻድቅ አባት የሕግ መምህር
በአምላክ በረከት ተመላች ምድሪቱ። በረከት ያሰጣል መንፈሳዊ ክብር።
መንፈስ ቅዱስ በርሱ ስላደረበት

መዝ 53:6 ማቴ 10:41

## ሊ. ዕረፍታ ለ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ

ሀገሯ ቡልጋ ቅዱስጌ ነው። አባቷ ደርባኒ እናቷ ዕሌኒ ይባላሉ አካለ መጠን ስታደርስ ሠምረ ጊዮርጊስ ለሚባል ደግ ካህን ዳሯት። ሁለት ልጆች ወልዳለታለች። ንጉሡ አፄ ገብረመስቀል የልቧን ቅንነት የግብሯን ደግነት ሰምተው የምትለብሰው የምታነጽፈው እልባሲ ወርቅ ወጥተው ወርደው የሚያገለግሏት 174 ብላቴኖች ሰደውላታል። እንዲቷ በጠባዩአዋ በሥራዋም ታስቆጣት ነበር። አንድ ቀን ከአሳት ዳር ሳለች አገኝ አጣውን እየቀባጠረች ብታስጨንቃት ፍህሙን በአፏ ታፍና ከአፏ ጣለችባት። ክብላ ሞታለች። ሕገ እግዚአብሔር አፍርሼከኔታዬ ተጣልቼ የምሸልክበት ቀዳዳ የምርጥበት ሜዳ አጥቼ ቀረ ሁን ብላ ታስቅ ስ ጀመር ወዲያውም ይህች ብላቴና ብታነሳልኝ ከዓለም ተለይቼ ገዳም ገብቼ ባገለገልሁህ ነበር አለች። ተነስታለች። ከዚህ በኋላ አልባሰ ምንኩስና አዘጋጅታ ሕፃኑን ወንድ ከዚህ አይቀርም ቢሏት ከአንቀፁ ትታ ገብታለች። ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ሄሮድስ ካስፈጃቸው 14 እልፍ ከ4 ሺህ ሕፃናት ደብሮታል። እሷንም በክንፉ ተሸክሞ ጽንፈ ጣና አድርሷታል።

ከመከራዋ ብዛት ከገድሏ ጽናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የዓሣ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባሕሩ ገብታ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ሳትል 12 ዓመት ኑራለች። ጌታ መጥቶ ምን እንዳደርግልሽ ትወጃለሽ አላት። ከእንጨት የማይጠስ ከብረት የማይዝግ ከሰውም የማይበድል የሰምና ውሉደ አዳም እንዳይስቁ ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው። ምሕረትን ቸርነትን አይሻም እንጂ ከሆነልሽስ ጠርተሽ አምጪው አላት። ቅዱስ ሚካኤል ወስዶ ጽንፈ ሲኦል አደረሳት። ጌታ ምሬሐለሁ ብሏልና ና ውጣ አለችው። በምድር ፈልጌ ባጣሽ ሳዝን እኖር ነበር አሁንማ ከቤቱ መጣሽልኝ ብሎ ጎትቶ አስገባት። ቅዱስ ሚካኤል ተከትሎ ገብቶ በክንፉ ነጥቆ አውጥቷታል። ስትወጣም ስለመከራዋ ብዛት ስለ ገድሏ ጽናት 6 ክንፍ ተሰጥቷት ነበር። በዚያ ነፍሳትን ማርካ ወጥታለች።

ከዚህ በኋላ ዜና ገድሏ ስነ ጸድቋ በየአህጉሩ ተሰምቶ ከ 1279 ያላነሱ ደናግል ተሰብስበውላት ጽሙና ብሕትውና የምታስተምራቸው ሆናለች። በፍጻሜ ዘመኗ በቁመቷ ልክ በዓት ሠርታ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ 12 ጦር ተክላ ወዲያ ወዲህ ሳትል ቆማ 12 ዓመት ኑራለች። ከዚያውም ዘንድ እሰግዳለሁ እያለች ጎንበስ ቀና ስትል ሥጋዋ በጦር ተወግቶ ተፈትቶ አልቋል። ጌታም ይህን ሁሉ መከራዋን እንደመሥዋዕት ቆጥሮላት አእላፍ መላእክቱን አስከትሎ መጥቶ በተስፋዋ ያመነውን በቃል ኪዳኗ የተማጸነውን እስክ

10 ትውልድ ድረስ እንዲምርላት ተስፋዋን ነግሯት ክብርት ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ በዎሊአቅርንት በዝማሬ መላእክት አሳር ጎታል

በሰምታ ይድረሳት ለክርስቶስ ሠምራ
ሰውን የምታስምር ራሷ ተምራ፡፡
ቤት ንብረት ልጆቿን ትታ ዘመዶቿን
ጋሻዋ አድርጋ መከታ አምላኳን
በትህርምት ኖረች ለአያሌ ዘመን፡
በጽናት መኖረድ መረገጥ በዲይን
ነፍሷ ተጨንቃባት ተሰምቷት ኀዘን
ይተወዋል ብላ ስቶ ማላቱን
ያንን ከንቱ ፍጡር ዓመጸኛውን

ትተከው ውሳኔ የላት ማቱን
ካስታርቅህ አስችው ከአምላክህ አሁን፡፡
እርሱ ግን ወርደቱን ቀጥርት እንደክብር
አልወደደም ከአምላክ ታርቶ ለመኖር
ድርም አይጥማትም ለአህያ ማር፡፡
ከፈጣሪ ጋራ ተጣልቶ መኖር
እያዩ መግባት ነው ወደእሳት ባሕር፡፡
ይልቅስ ይሻላል መታረቅ በቶሎ
ዋይ ዋይ ላለማለት በሲኦል ተጥሎ፡፡

ሐዋ 9:5 2 ቆሮ 5:16-21

## ነሐሴ 28. ተዝካሮሙ ለአብርሃም ወይስሐቅ ወያዕቆብ /ከ 2000 - 1825 ዓ.ዓ/ከ 1900 1720 ዓ.ዓ እና ከ 1840 1693 ዓ.ዓ/

አብርሃም ማለት አባብዙኃን ማለት ነው፡፡ ትውልዱ ከነገደ ሴም ነው፡፡ አባቱ ታራ ይባላል፤ ከጥፋት ውኃ በኋላ ሃያ አንደኛ ትውልድ ነው፡፡ ሚስቱ የሚባል ወንድም ነበረው ኢያ 24፡2 ሚስቱም ሣራ ትባላለች፡፡ አባቱ ታራ ጣዖት እየቀረጸ የሚሸጥ ነበር፡፡ አንድ ቀን ሽጠህ ና ብሎ ጣዖት ሰጠው፡፡ ከመንገድ ራበኝ አብላኝ ጠማኝ አጠጣኝ አለው፡፡ ዝም አለው ያም ባይሆን አጫውተኝ አለው፡፡ ዝም አለው፡፡ ከዚያ ሲደርስ ዓይን እያለው የማያየው እግር ሳለው የማይሄድ እጅ ሳለው የማይዳስስ አምላክ አለላችሁ ማለት ነው፡፡ የማያውቁት እሱ ያቀረጸውን ግን ይገዛቸዋል ብሎ ይደክማል ብለው አደነቁበት የማያውቁትም አብርሃም ዛሬስ አለምርውን አባ ብለው ዘበቱበት የሚገዙ እንቶ ይዞ ሲመለስ ራበኝ አብላኝ ጠማኝ አጠጣኝ ያም ባይሆን አጫውተኝ አለው፤ ዝም አለው፡፡ አላዋቂነቱ እንጂ አንተማ በፍጡር እጅ የተሰራህ እንጨት አይደለህምን ብሎ ከላይ ዳገቱ ከታች ደገቱ አድርጎ ቀጥቅጦ ሰበረታል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ሰማይ ብሎ አምላኩን ይፈልግ ጀመረ፡፡ ነፋስ ረቂቅ ነው የሚሄድበት የሚመጣበት አይታወቅም እሱን ሳማይ አለ፡፡ ቢመረምረው ግድግዳ ተራራ ሲከለክለው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት፡፡ እሱን ትቶ ውኃ ቢታጠቡት ያነጻል ቢጠጡት ያረካል እሱን ሰማይ አለ፡፡ ቢመረምረው አፈር ጠጠር ሲገድበው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት፡፡ እሱን ትቶ ፀሐይ ብርሃኑ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳል የረጠበውን ያደርቃል እሱን ሰማይ ብሎ አለ፡፡ ቢመረምረው ቀንና ሌሊት ሲፈራረቀው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት፡፡ ከዚህ በኋላ አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ የፀሐይ አምላክ ተናገረኝ አለ፡፡ ጌታም ሃይማኖቱን ለማጽናት አብርሃም አብርሃም ጻእ እምሀገርከ ወተፈለጥ እምአዝማዲከ ከወገኖችህ ተለይተህ ከሀገርህ ወጥተህ እኔ በማሳይህ ቦታ ተቀመጥ አለው፡፡ አባቱ ሞቶ ነበር ሚስቱና የእኅቱ ልጅ ሎጥን አስከትሎ ከበቱን ነድቶ ሄዶ በከነዓን ተቀመጠ፡፡

በዘመኑ ረሀብ ቢሆን ወደ ግብጽ ተሰደደ፡፡ ሚስቱ ሣራ ከሰማር ጥፍሯ እስከራሷ ጸጉሯ ድረስ ደም ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ነበረች፡፡ እኅቴ እንቺን ሲሉ እኔን እንዳይገድሉኝ እህቱ ነች እላለሁ ወንድሜ ነው በይ አላት፡፡ እሺ አለችው፡፡ ፈርዖን እሱን ከአገልጋዩ ግሬሬያ አስቀምጦ እርሷን ወደ እልፍኝ አስገባት፡፡ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ነጥሎው በተሰቡንም መቅሰፍት መታቸው፡፡ ጠርቶ ስለምን ሸሸግከኝ አለው፡፡ ብሬሬ አለው የወንድ ባሪያ የሴት ባሪያ ወርቅ ብር ከብት ሰጥቶ አሰናበተው፡፡ ዘፍ፡ 12፡10-20 ከዚህም በኋላ ባለጸጋ ሁኖ በኬብሮን ይኖር ነበር፡፡ ከደግነቱም የተነሣ ቤቱን ከተመሰቀለ ጎዳና ሠርቶ... ብለህ ከዚያ - ተርከ ተጨማሪ ከዚያ በራት አብርሃም ልጅ አጥቶ ሲያዝን ይኖር ነበር ከሰያሌይ ባንዱ ወደ ሜዳ ወስዶ ኮከብን ከምትቆጥር የሰማይ ከዋክብትን ቁጥር አለው ሊቆጠሩ ቁጥር ቆቶሙ አይቻለኝም አለ፡፡ ከማሁ ይከውኑ ዘርዕከ ዘርህ እንዲሁ ይበዛሉ ብሎታል፡፡ ከዋናትም ባንዱ ከባሕር ወስዶ ኆጻት ኆጻባሕር የባሕርን አሸዋ ቁጥር አለው፡፡ ሊደክል ኆልቆቶሙ አይቻለኝም አለ፡፡ ከማሁ ይከውኑ ዘርዕከ ዘርህ እንዲሁ ይበዛሉ ብሎታል፡፡ ወተአመነ በኩሉ ልቡ ከመ ይከል ገቢረ ኵሉ እግዚአብሔር ይላል እኔ መቶት ልምላሜ ተለይቶኛል ሚስቴም ልማደ አንስት አልፎባታል፡ ሳይል ይህን ሁሉ እግዚአብሔር ሊያደርግላት እንደሚችል በፍጹም ልቡ አመነ ማመኑም ጽድቅ ሆኖ ተቆጥሮለታል፡፡ ዘፍ 15፡1-7 ሮሜ 4፡ 17-24

ከዚህ በኋላ ዘመነ ረሀብ ቢሆን በምድረ ጌራራ መጻተኛ ሁኖ ተቀመጠ፡፡ ንጉሡ አቤሜሌክ ይባላል፡፡ ምንህ ናት አለው፡፡ እኅቴ አለ፡፡ የሰባ እርዶ የጸራ አውርዶ ሲበሉ ሲጠጡ ቆይተው ሲመሽ ወደ እልፍኝ ይዟት ገባ ባታ ብልቱን በእሳጭ ቀመታው፡ ዋይ አለ፡፡ ሰባለቤቷ ካልመለስክ ትሞታለህ አለው፡፡ አስጠርቶ ስለምን እኅቴ ናት አልክ አለው ብሬሬ አለው፡፡ ጸልዮ መቅሰፍቱን አርቆለታል፡ ለርሱም ሚስቱን መልሶለታል፡፡ የሚኖርበትን ቦታ የሚተዳደርበትን ከብትና የወንድ የሴት ባርያ ሰጥቶታል፡ ዘፍ 20፡1-18 ከዚህ በኋላ ጌታ የሚያደርገውን አይናገር የተናገረውን አያስቀር ወንድ ልጅ ሰጥቶታል፡፡ስሙን ይስሐቅ ብሎታል፡፡ ትፍሥሕት ማለት ነው፡፡ በ8 ቀን ግዝረት ፈጽሟል፡፡ ዘፍ 21፡ 1-4

ከጊዜ በኋላ ባንዱ ጌታ ብዙ እርከ በዲቢምድር አብርሃም ፍቁርየ በምድር ላይ አብርሃም ወዳጅ አለኝ አለ፡፡ መላእክትም ተቀብለው አብርሃም ፍቁረ እግዚአብሔር አብርሃም እርከ እግዚአብሔር ብለው አመሰገኑ፡፡ ሰይጣን ሰምቀኝነት አያርፍምና እንዲያው ወዳጁ ትለዋለህ እንጂ ካረጀ ካፈጀ በኋላ የወለደው ልጁን ሠዋልኝ ብትለው አይሠዋልህም አለ ጌታም የአብርሃም ጽድቁን የሰይጣን ሐሰቱን ለመግለጽ አብርሃም አብርሃም ሠዕ ሊተ ይስሐቅሃ ወልደከ ይስሐቅ ልጅህን ሠዋልኝ አለው፡፡ ቆይ ዛሬ ነገ ስትል ታዘናጋኛለች ብሎ ለሣራ ሳይነግራት እንጨቱን በአህያ ጭኖ ብላቴኖቹን አስከትሎ ወደ ሞርያም ሄደ፡፡ ከአግረ ደብር ሲደርስ እኔና ልጄ መሥዋዕት ሠውተን እንመጣለን ከዚህ ቆዩኝ ብሎ ብላቴኖቹን ከዚያ ትቶ እንጨቱን ለይስሐቅ አሸክሞ እሳቱን ቢላውን እሱ ይዞ ከርእሰ ደብር ወጡ፡፡ አባቴ እኔ እንጨቱን ይዣለሁ አንተ እሳቱን ቢላውን ይዘሀል የሚሰዋው በግ ወዴት አለ? አለው?፡፡ ልጄ በጉን ጌታ ያዘጋጀል አለው፡፡ ሁለተኛ መልሶ አባቴ የሚሠዋው በግ ወዴት አለ? አለው፡፡ ልጄ በጉን ጌታ ያዘጋጀል አለው፡፡ ከሰስቱ ተራሮች ባንዱ የብርሃን ዓላማ ተተክሎ ሲጠቅሰው አየ፡፡ ከዚህ ሠዋ ሲለኝ ነው

ብሎ ደንጊያውን ይጸፈጽፍ እንጨቱን ይረበርብ ጀመር። በጉ ሳይገኝ ደንጊያ መጸፍጸፍህ እንጨት መረብረብህ ስለምንድር ነው አለው። ልጄ በጉን ጌታ ያዘጋጃል አላልኩህምን አለው። እንግዲህ በጉ ከምን ተገኝቶ እኔን ልትሠዋኝ ይሆናል እንጅ አለው። ያስ ቢሆንትጠቀምበታለህ እንጅ ትጎዳበታለህን አለው። እንግዲያስ ጎልማሳ ነኝና ጸእረ.ሞት ይዘኝ ስንፈራገጥ ልብ እራስህን እንዳልልህ እጅ እግሬን አስረኝ አለው። አሥረው ዐይኔ ከብል ከብለል ቢል አይተህ ራርተህ እንዳትተወኝ በሆዱ አስተኛኝ አለው። ወአስከቦ በከብዱ ይላል በሆዱ አስተኛው ቢላውን አንሥቶ ካንገቱ ሲያሳርፈው ጌታ አብርሃም አብርሃም ኢታከብድ ኤደከ በላዕለ.ወልድከ ይስሐቅ እስመ አኮ ዘይድኅን ዓለም በደመ.ወልድከ አላ በደምየ /በደመወልድየ/ ዓለም የሚድን በኔ ደም /በኔ ልጅ ደም/ እንጅ በልጅህ ደም አይደምና እጅህን በልጅህ ላይ አትዘርጋው አለው። ወረደ ሉቱ ቤዛሁ በግዕዘእንጉዝ አቅርንቲሁ በዕፀ. ሳቤቅ ይላል መለስ ቢል ጸዓዳ በግዕ በሀረግሬሳ ተይዞ አግኝቶ ሠውቷል። ሁለተኛም መልአኩ ይቤ እግዚአብሔር መሐልኩ ለከ በርእስየ እባርከከ በበረከትየ ወእበዝሆ ለዘርዕከ ከመ.ኮከበ.ሰማይ ወከመ.ኖጻ ዘድንጋጌ. ባሕር እስመ ኢከልአከኒ ወልደከ አንድ ልጅህን አልነሳህኝምና በበረከቴ አባርከሀለሁ ዘርህንም እንደሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ ብሎሰታል። ዘፍ፡-22፡1-24

ሚስቱ ሣራ በተወለደች በ127 ዓመቷ ዐረፈች። በዓተ.ክዕበት ይላታል እልፍኝ ከአዳራሽነት ያላት መቃብር ገዝቶ ቀብሯታል። ዘፍ፡- 23፡1-28

አብርሃም ከይስሐቅ ሌላ 7 ልጆች ወልዷል። የመጀመሪያው እስማኤል ነው። ከአጋር ወልዶታል። ዘፍ፡- 16፡15 6ቱን ከኬጡራ ወልዷል። ዘፍ፡ 25፡1 አቀውም ኪዳንየ ዘምስሌሁ ተብሎ የተነገረለት ግን ይስሐቅ ነውና ለሌሎች ድርሻ ድርሻቸውን ሰጥቶ አሰናብቶ ይስሐቅን ርብቃ ወለተ.ባቱኤልን አጋብቶ በሁቡቱ በንብረቱ አሥልጥኖት በተወለደ በ160 ዓመቱ ዐርፏል። ዘፍ፡- 25፡ 5-11

ስለእምነቱ ፍቅር ሁሉን እየጣለ — ብሎ ቃል ገባለት ጌታ ለአብርሃም
የፈጣሪን ፈቃድ ስለተከተለ — ሆኖ ስላገኘው ታማኝ ቢጤ ፍጹም።
የብዙኃን አባት አብርሃም ተባለ። — ሰጥቷት ዘመኑ ለምታልፍ በቶሎ
አብርሃምአብርሃም የቅዱሳን ራስ — ሕንጻ አላነጸም ቤት አልሠራምብሎ።
የተወለደ ለት ከዘሩ ክርስቶስ። — በድንኳን ውስጥ ኖረ ያጣ ደጋመስሎ
ዘመዶቹን ሁሉ ወገኖቹን ትቶ — አብርሃም አብርሃም ደግ አባት መባሉ
ሩቅ ሀገር ሄዶ ከሀገሩ ወጥቶ — እንግዳን በፍቅር ነው በመቀበሉ
በአባቱ ፈንታ እምላኩን ቲክቶ። — ጌታ ደግነቱን ቸርነቱን አይቶ
ዘርህ እንደ አሸዋ እንደ ኮከብ በዝቶ — ከዚያች ከድንኳኑ እንደእንግዳ ገብቶ
ስምህን ይጠራል ምድርን ሁሉ መልቶ፣ ባጭሩ አስደሰተው ወራሽ ልጅም ሠጥቶ።

የይስሐቅን ነገር ከዚህ ይዋቈታል አባቱ ከዕረፍቱ አስቀድሞ ኢያውብር የሚባል ሎሌውን ጠርቶ ልጄን ከወገኖቼ ልጆች እንጅ ከከነዓን ሴቶች እንዳታጋባው ማልልኝ አለው። ሕያው እግዚአብሔርን እንዳልክው ይሆናል ብሎ ከወርቁ የጸራውን መርጦ 10 ግመል ጭኖ ወደ መስጴጦምያ ሄደ። ወደማታ ከውሃ ዳር ተቀምጦ ያወጣ ያወርድ ጀመር። ውኃ ለሚቀዱት ብላቴኖች ከጌታዬ ዘመዶች ወገን ሁና መልክ ከደምግባት አስተባብራ የያዘች ውኃ አጠጭኝ ብያት አጠጥታኝ ግመሎቼንም ብታጠጣልኝ ኪያሃ አስተዳሉከ ለገብርከ ይስሐቅ ለብርያህ ይስሐቅ አዘጋጀሁት ባልኩ ነበር አለ። ይህን ተናግሮ ሳይፈጽም ርብቃ ባጭር ታጥቃ



ማድጋዋን ነጥቃ መጣች። ቀድታ ስትነሳ ውኃ አጠጭኝ አላት። ደስ አለው። የማን ልጅ ነሽ አላት የናኮር ልጅ የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችው። ከቤትሽ ማደሪያ አይገኝምን አላት ምን ታጥቶ ስንኳ ሳንተ ለግመሎችህ የሚበሉት ገፈራ የሚያድሩበት ጋጥ አለን አለችው። ለጣቷ ቀለበት ለጆሮዋ ጉትቻ ሰጥቶ አስጌጦ ሰደዳት። ላባ የሚባል ወንድም አላት። ማን ሰጠሽ አላት። እንዲህ ያለ ሰው አለችው። የሚሰጠው የሚያስጌጠው መስሎት ሄደ። አንተን ያህል ክቡር ከዚህ ተቀምጠህልን ብሎ ግመሎቹን ነድቶ እሱን መርቶ ይዞ ገባ። እግርህን ታጥብህ እህል ቀምስህ ዐረፍ በል አሉት። ጌታዬ የላከኝን ሳልናገር አይሆንም አለ። በል ተናገር አሉት ጌታዬ አብርሃምን አልቆ አከብርታል። ካረጀ በኋላ የወለደው የሚወደው ልጅ አለው። ከሶርያ ልጆች እንጂ ከከነዓን ልጆች እንዳታጋባው ብሎ አስምሉኛል። ገንዘብ ይዤ መጥቼ ከውኃ ዳር ተቀምጬ ሳወጣ ሳወርድ ይህችን ብላቴና መጣች። እንደምታዩት አስጊጬ ሰደድኳት ለጌታዬ ልጅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ስጡኝ እናንተም ገንዘባችሁን ተቀበሉኝ አላቸው። ንህነሰ ኢንክል ተናግሮ ኢሠናየ ወኢእኩየ ይህማ ከወደእግዚአብሔር የመጣ አይደለምን ምን ማለት እንችላለን አሉት። ቁረጡልኝ አላቸው። ይሁን ተቀመጥ አሉት። አደረ። ሲነጋ አሰናብቱኝ ገንዘባችሁን ተቀበሉኝ ልጅቷን ስጡኝ አለ። 10 ቀን ትሰንብት አሉት። እግዚአብሔር አቅንቶልኝ ሳለ አታሰናክሉኝ ለላቸው። ባይሆን እሷን እንጠይቃት ብለው ቢጠይቋት እሄዳለሁ አለች። ገንዘቡን ሰጥቶ ይዞ ሲመለስ ይስሐቅ ወንዝዳ እንዳይጣላቸው ብሎ መንገደኛ መስሎ ይሰልል ነበር። አሻግራ አይታ ያ ማን ነው አለችው። የምትሄጅለት የጌታዬ ልጅ ነው አላት። ተራ ልብስ ለብሳ ነበርና አውርዱኝ ብላ አጌጣ ቆየች። ይሏቸው ሄዷል። በዚህ ጊዜ ይስሐቅ የ 40 ዓመት ጎበዝ ነበር። ዘፍ፡- 24፡1- 66 ዘፍ 25፡20

ርብቃ እፁተ ማኅፀን ነበረች። አዝኖ ተክዞ ወደ ጌታ ቢያመለክት ምክንት ተወግዶላት ጸንሳለች። ጽንሱም በማኅፀኗ እየታወከ ቢያስቸግራት ወሖረት ትሰአል ቃለ እግዚአብሔር ይላል ቃለ እግዚአብሔር ልትጠይቅ ወደ መከነ ራዕይ ሄደች። ክልዔቱ ሕዘብ ሀለው ውስተ ከርሥኪ ወክልዔቱ አንጋድ ይወጽኡ እማኅፀንኪ ሕዝብ ዘየዓቢ እምሕዝብ ይተቀነይ ለዘይንዕስ ሁለት ሕዝብ በማኅፀንሽ አሉ። ትልቁ ለትንሹ ይገዛል ብሏታል። መዋዕለ ጽንስ ሲፈጸም ሁለት ልጆች ወልዳለች። የመጀመሪያው ዔሳው ሁለተኛው ያዕቆብ ነው። ያዕቆብ ማለት አኃዜ ሰኩና አዕቃጺ ማለት ነው። የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ተወልዷልና በዚህ ጊዜ ይስሐቅ የ65 ዓመት ሰው ነበር። ዘፍ 25፡26

እንደ አባቱ በዘመኑ ጽኑ ረሀብ ሆኖ ወደ ጌራራ ሄዶ አቢሜሌክ ዘንድ እንግድነት ተቀምጦ ፍልስጥኤማውያን እስኪቀኑበት ድረስ ዘር ዘርቶ ከብቶ አርብቶ ከበረ በኋላ አቤሜሌክ በሰላም አሰናብቶት ተመልሷል። ዘፍ 26፡1 – 17

ወኮነ ይስሐቅ ያፈቅሮ ለዔሳው እስመ ዘውእቱ ነዓወ ይሴሰይ ወያዕቆብ ንጹሕ እምዝንቱ ይላል ዔሳው ያውሬ ሥጋ እያደነ ይመግበው ነበር። አንድ ቀን ልጄ ዛሬ በረከት የማድልባት ቀን ናትና ሳልሞት እንድመርቅህ እንደምወደው አድርገህ አምጣልኝ አለው። ሲፎከል ልብሱን ትቶ ሄደ። ርብቃ ግን ያዕቆብን ትወድ ነበር። ልጄ ዛሬ አባትህ በረከት የሚያድልባት ቀን ናትና እንዲመርቅህ ሁለት ጠቦት አምጥተህ እረድልኝ ። እንደሚወደው አድርጌ ሰርቼ እሰጥሀለሁ

ጌታ የአብርሃም ሲገለጠው ዝድቀን
ጠርቶ እንዲህ አለው አንት የኔ ምእመን
ሙሃላን ልጅህን የምትወደውን።
አብርሃም ተነሣ ሲሊሽም ትእዛዙን
ልጁን አስከትሎ ገሠገሠ ሦስት ቀን
በጎዳና ጎሉ ሲጓዝ እንደንጉት
ይልኛል አቅረብ ተያቄ በደንጎት
አባቴ አንተ አሉት ቻተኩን ይሆሉ
እንጨቱንም እኔ እሸከማለሁ
የመሥዋዕቱ በግ ከወዴት ይመጣል
አብርሃምም አለው ልጄ ሆይ ፈጥነህ
ጌታ ይመጋልና ሆኑ ያሰቡን
ጌታ ያመቻልና በጉ ያለበትን።
ተራራውን ወጥተው ከዛው ሲደርሱ
መሠዊያውንም ሠርተው ሲጨርሱ
ደግሞ አቀረበ ተያቄ ወደርሱ።
አሁን አንዴ ለኛነር አባቴ ስማኝ
ወሳን አስረኸኝ በኋ ላይ ጣለኝ
አንዴ የምትወድህ እኔን መጠለኝ
አብርሃምም እሱ ይዞው ነው እውነት

እንቱባለቱም አንተ ነህ መሥዋዕቱ
ሊሠዋ መሆኑን ከሰማ በኋላ
ደለለት አለበለም ወደ አለውሱ ገዘ
ሌለትም ለእርሳሱ መሥዋቱን ሽቶ
ከበላል ከበላ ሲል ዓይኑን ተመልክቶ
ዓይለውው እንዲደፋር ለበሰው ራርቶ
አሥር በደረቱ ደፋቶ አሰተኝቶ
በተሉ እንዲሠዋው መጨረሻ አለንቶ
አብርሃምም እሥር እጆና እግሩን
ደፋቶ አስተኝቶ እንደ በግ ልጁን
ካነሣቱ አስረሐ በለት ቻተሉን
ጌታም ተመለከቶ ታማኝነቱን
አብርሃም ተው አለው አትረድ ልጁን
እንደያ ልጅህን ለኔ መሠዋትህ
በመሆኑ እኔን ስለመውደድህ
የበረ ይሁን ይሰረክ ዘርህ
አብርሃምም ልጁን ከእሥራቱ ፈቶ
ጌታ የሰጠውን ነውን በግ መሠቶ
ወደ ቤቱ ገባ ከልጁ ተደስቶ።

መንገዱው ትመሪታለህ አለችው። መከፈለት ሲሹ መቅመሙት እንዲሉ በረከት ለሻ መርገም ሲደርስብኝስ ወንድሜ ጌሳው ጸጉር ነው እኔ ጸጉር የለኝ በጆ ዳስ አደቶ ዛሬብ ዓይኔ ደከሙና ዘበተብኝ ብሎ ይረገመኝ የለም? ገአላት። ወልደኝ መርገሙስ ይከን ላለ ልጄ መርገምህ በኔ ይሁን አለችው። አምጥቶ በጣት። እንደሚወደው አድርጋ ሠርታ የበንን ጸጉር በደመ እየሸከረች ከሬቱ ከደረቱ ከትከሻው አግብታ ጌሳው እደን ሲሄድ የሚለብሳትን ለብስ አለብስ ምግቡን አሲዶ ለደደችው አባቱ እንዲምትወደው አድርጌ አምጥቼለሁህ በልተህ መርቀኝ አለው። አንተ ማነህ አለው ጌሳው ወልድህ በኩርህ ጌሳው ነኝ አለው። በጁ ዳሰ አደቶ ጸጉርስ ዘጌሳው ወቃልስ ዘያዕቆብ ጸጉርህ የጌሳው ቃልህ የያዕቆብ እኔ ምን አገደኝ ሁሉታችሁም ልጆቼ ናችሁ ብሎ በልቶ አምጠሉ ለበግዴ ወእምበሩሉ ለምድር ይከን በረከትከ ከማ እግዚእ ለአንከ በረከትህ ከበግዴ ጠል ከምድር ሰብ ይብዛ ለመንደምህ ጌታ ሁነው ብሎ መርቆታል።

ያዕቆብ ከመጣ በኋላ ጌሳው መጥቶ አባቴ እንደምትወደው አድርጌ አምጥቼልሀሁ በልተህ መርቀኝ አለው። አንተ ማነህ አለው። ጌሳው ወልድከ ዘበኩርከ ጌሳው ነኝ አለው አሁን እንደምወደው አድርጎ መንገዱን የመረቀሁት ማነው በሶስከ መሰሉ ብሶስ ነው ያዕቆብ ነሥአ በረከትከ በኩረቶ በረከትህን ያዕቆብ ወሰደብት አለው። ቀደም ብኩርናየን አሁን በረከቴን ነሥቶኝን ብሎ ያዕቆብ ጀመረ አለቀሰ አባ በረከትከ ወእለውኑ ዘአትረፈከ ሊተ አባቴ በረከትህ እንዲት ናትን ለኔ ያስቀረኸው የለምን አለው። በጁ ዳሰ ናሁ ኄር አለምሲሁ ለወልደኝ ጥቶ ምንቶተ ከመሄና ገዥ ሠርዕክ አምላክ ቃለእግዚአብሔር እምጠሉ ለበግዴ ወእምበሩሉ ለምድር ይከን በረከትከ አንተ በቀስትከ ወበአመከ ፈተድከ ታቅለል ገድ አድንን

ርእሰ ከ - በረከትህ ከበግዴ ጠል ከምድር ሰብ ይብዛ በቀስትህ ኑር ለመንደምህ ተገዥ ብሎታል። ዘፍ 27፡1 – 40

ከዚህ በኋላ ቀድሞ ብኩርናውን አሁን በረከቱን ነሥቶኝ ይቶራልን ለብ ራሱን ብሎ እንደሰማለው እያለ ቀን ሲቆጥር እናቱ ወንድምህ ሊገድህ ይሻልና ቀጣው እስከበርድ ለርያ ከላን ሀገር ተቀመጥ አለችው ሊሄድ መሸኑለት ከመንገዱ አልፎ ብሎ ድንጊያ ተንተርሶ ተኛ። ሌሊት በሕልሙ የወርቅ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት በላይ ዙፋን ተዘርግቶበት በዛ ንጉሥ ተቀምጦበት አየ። ሊነጋ ዛሬ ይለቀሮዋታ ለሰማይ ደጅ ይችሐበዝ ቤተ እግዚአብሔር ብሎ ድንጊያውን አቁሞ ዘይት አፍስሶበት ሄደ። ለርያ ሲደርስ ከአፈ-ማይ ተቀምጦ ላለ የላባ ልጅ ራሔል በጎቿን እየነዳች መጣች። የምን ልጅ ናት አለ። የላባ አሉት እትዬ አድርጎ ሳማት። ከወዴት ታመቀቻለህ አለችው የላባ እኅት የርብቃ ልጅ ያዕቆብ ነኝ አላት። ሄዳ ለአባቷ ነገረችው። ደስ አሰኝቶ ተቀብሎታል።

የሥጋን ቁራጭ የአጥንቱን ፍቅር ለዘንቶ እንግዲህ ብሎ የምትወደውን ንገረኝ አለው። በራሔል 7 ዓመት ላገለግለህ አለው። ይሁን ከሰ 7 ዓመት አገለገሉ ሚስቱን በወኝ አለው። የበላ እርዳ የሬሬ አውርዶ ዘመድ አዝማድ ጠርቶ ሲበላ ሲጠጣ ወለው ሊመሽ ልያን አስገባለት፡ ይህች ልያ ናት ልያ ነበረች። ሊነጋ መንቶ ለለ ራሔል እንጂ ለለ ልያ ነውን ለለምንድር እንዲህ አደረግኸኝ አለው። በሀገራችን ለማድ ታናሽ ሳለች ታላቋ አትዳርም ይሁን ሳምንት ጠብቆ ራሔልን ደግሞ እሰጥሃለሁ። ለለ ርያም 7 ዓመት ትገዛልኛለህ አለው። ይሁን አለ።

ሳምንቱን ጠብቆ ራሔልን ሰጠው። ይህ ቀረሽ የምትባል መአከ መስዕም ነበረች ከዚያ ይልቅ እሷን ወደደ።

ከዚህ በኋላ እናቴኔን ለያዕ አለው። 14 ዓመት ብትገዛኝ ሁለቱ ልጆቼን ሰጠሁህ ለ 6 ዓመት ምን ለትገዛህ አለው። ከመንጋህ ሽመለመሌ የመሰሉን የተዥጎረጎረውን ለኔ ለመድ አለው። ይሁን አለ። ወን ሲጠጡ ሽመለመሌ በትር ሲያሥጥው በጎች ሁሉ ሽመለመሌ የመሰለ የተዥጎረጎረ ወለዱ። የጋውን እያየመለ ሲያዥጎረጉሩ ወርቅ ባደረ ጠጠር ከዛለ በለረ አረር እንዲሉ አባታችሁ መሰሉም ባይርገዳት ከኔ አደረገብኝ ጌታም ወደ ተመለከተኝ ሀገር ሄደ አለኝ። ምን ይመስላችኋል አላቸው። እኛ ከአባታችን እድል ፈንታ ዐዋ ተርታ የለንም እኛና ሁሉ የጋችንን ተቀብሎ የለምን ያለውን አድርግ አሉት። ሚስቶቹን ልጆቹን በገመል ጭኖ ከብቱን ነዳቶ ገባቶ ገሠገሠ ገጽ።

ላባ መተዳደሩን የሰማው በሦስተኛው ቀን ነው። ብትከተለው አባቶቹሉ በደረሰ ሰባት ሁሉ የገለዓድ ቀን መንገድ በሁ ቀን ተገዞ ደረሰበት። የቃለ መለአክ ከሆነ አንዳችንግረው እሰት አለው። ልጆቼን እንዳሰጠም ማደርገኝ መለሰም ነውን አጋለበትን መሰረ ትህ ለለምንድን ነው አለው። ድንገላ ገዛ ከሬትህ አደራሰሆን አትለውኛም አለው። የሠረቀችው ራሔል ነበረች። ከኮርቻ ሥር ደበቃ ተቀመጠችበት። ሌላን በርብር አለ። ልጆቼ ልጆቹ በገን ነገር አጣኘሁሉ ብሎ ለመሉት በም ለ እቅም መርቋቸው ተመለሰ። ዘፍ ከም ፡ 29 – 31

ያዕቆብም ለጌሳው ከብት ከፍለ ሃያ ሃያውን ከሙ 40 ከበሬው 10ሩን ከግመል 30ውን ከአህያው 20 እጅ መንሻ ለዶ ሚስቶቹንና ልጆቹን ሌላ ያሳን አሻገር እሱ በቻውን አደረ። ሌሊት በሕልሙ ጌታ በሰውነት ወርዶ ተይዞ ሆኖ ሲታገለው

ሹለዳው ሲደንገዝዝ አትላላ ልቀቀኝ ቢለው ካልባረክኸኝ አለቅህም ሲለው ስምህ ማነው ቢለው ያዕቆብ፣ ከሰውም ከእግዚአብሔርም ታግለህ አቸንፈሀልና ስምህ እስራኤል ይሁን ሲለው ራዕይ አየ። ሲነጋ ዔሳው 400 መቶ ራሱን ሁኖ ሊቀበለው መጣ። አንገት ላንገት ተቃቅፈው ተላቀሱ። እሊህ ምናችህ ናቸው አለው። ጌታዬ ለባሪያህ የሰጠኝ ልጆቼ ናቸው። አለው ከፊትህ ያለፉትስ አለው። በፊትህ ሞገስ አገኘቼ እንደሆን ትቀበለኝ ዘንድ የላኩልህ ነው አለው። ወንድሜ ለኔ ብዙ አለኝ ያንተ ላንተ ይሁን አለው። ግድ አለው። ተቀብሎ እንሂድ አለው። ሕፃናቱን እንስሳቱን እንደምን አድርጌ አንተ ቅደም አለው።

ሶኮት ሲደርስ ከልያ የወለዳት ልጁ ዲና ወደመስክ ወጣች ሲኬም ወልደ ኤሞር አገኝቷት ግድ ብሎ ከክብር አሳነሳት። አባቱን ይህችን ብላቴና ካላጋባኸኝ አለው። ተያይዘው ሄደው ልጅህን ለልጄ ስጥልኝ አለው። ስምዖንና ሌዊ እኅታችንን ለኢግዙር እንሰጣለንን ብለው ካልተገረዛችሁ አንሰጥም አሉ። ይህማ ቀላል አይደለምን ብለው ሕዝቡን መክረው ተገረዙ። በ3ኛው ቀን ቁስለው መሄድ አቅቷቸው ሳሉ ሰይፍ ሰይፋቸውን ማዘው ሄደው እነሱን ፈጅተው እኅታቸውን ይዘው ተመልሰዋል። ዘፍ 34:1-30

ጌታ ወደቤቴል ውጣ አለው። ከልያ ከራሄል ያሉትን አማልክት ቀብሮ ሄደ። ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ትወርሳለህ ዘርህንም እንደ ሰማይ እንደባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ አለው። ሐውልት ተክሎ ዘይት አፍስሶበት ስሙን ቤቴል ብሎታል። ምድረ ኤፍራታ ሲደርሱ ራሄል ብንያምን ስትወልድ በምጥ ተጨንቃ ሞተች። እሷን ቀብሮ ወደ አባት እናቱ ገብቷል።
ከከብቱ ብዛት የተነሣ አንድ ላይ መኖር የማይችሉ ሲሆኑ ዔሳውወደ ሴይር ሄደ። ርብቃ ይስሐቅን ያዕቆብ፤ እንኳ በከብታችን በከብቱ ናዙብት እዘዙብት ይለናል ዔሳው ግን ስንኳ በከብቱ በከብታችን አያሳዝዘንም ምን ይመስልሀል አለችው። አሁንማ በዔሳው ያደረ ሰይጣን በያዕቆብ ያደረ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አውቄ ልቤ ወደ ያዕቆብ ተመልሷል አላት። እንዲህ ከሆነማ እናስታርቃቸው አለችው። ጠርተው አስታረቋቸው ከዚህ በኋላ ይስሐቅ በ180 ዓመቱ ዐረፈ። ዘፍ 35:28

የዔሳው ልጆች ዕርቁን አልወደዱምና ተቆጥተው ያዕቆብን ሊጣሉ ተነሱ እርሱም አብሮ ሊጣላው ጦር ሠርቶ ሄደ ወንድምህ ጦር ሁኖ መጣብህ አሉት። ታርቀን የለምን? ሚስቴ ልያ መሞቷን ሰምቶ ሊያላቅሰኝ ይሆናል እንጂ አላቸው። ጦር ሰብቆ ሸተል መዞ ነው የመጣው አሉት። አመጣጥህ በሰላም ነውን ብሎ ላከበት። ሰላም ይንሳህ ከእንግዲህ የኔና ያንተ ሰላም ውሻ ቀንድ ቢያወጣ ከል የገባ ቢነጣ ነው ብሎ መለሰለት። 200 ራሱን ሁኖ ገጠመው። ይሁዳ የዔሳው ልብ ለቀስት ተመችቶ ታየው የአባትን ታላቅ ወንድም መግደል አባትን መግደል አይደለምን? ቢገድለውም ቢያድነውም እሱ እንደወደደ ያድርገው ብሎ አመቻችቶ ሰጠው። ቢሰብ ልቡን መቶታል። ጦፉም «አውራ የሌለው ንህብ አለቃ የሌለው ሕዝብ» እንዲሉ ተበታትነዋል። እነ ያዕቆብ እየተከተሉ ፈለገ ኤፍራጥስ ድረስ አሳደዋቸዋል። እንግዲህስ ተውን እንገብር አሏቸው ተውአቸው ይገብሩ አላቸው። ከዚህ በኋላ እስከ በእተ. ግብጽ ድረስ 15 ዓመት ገብረውላቸዋል። ሕዝብ ዘየዓ(ሊ እምዘዝብ ይትቀነይ ለዘይንዕስ ያለው በዚህ ተፈጽሟል።

ያዕቆብ የወለዳቸው ልጆች 13 ናቸው መጽሐፍ ትውልደ አንስት ስለማይቆጥር ዲናንትቶ 12 ብሎ ይቆጥርለታል። 6ቱን ከልያ ወልዷቸዋል። ሮቤል ስምዖን ሌዊ ይሁዳ ይሳኮርና ዛብሎን ናቸው። 2ቱን ከራሄል ወልዷቸዋል።



ቱን ከራሔል ባርያ ከባላ ወልዷቸዋል። ዳንና ንፍታሌም ናቸው። 2 ቱን ከልያ ባርያ ከዘለፋ ወልዷቸዋል። ጋድና አሴር ናቸው። ዲናን ከልያ ወልዳታል። ዘፍ 35:23 ሁለት ሚስት ሳለው ከባርያ መወለዱ በለምንድር ነው ቢሉ ልያ 3 ልጅ ስትወልድ ራሔል ዕቀቱ ማገዘን ሁና ትኖር ነበር። ልጅ ካልሰጠኸኝ እሞታለሁ አለችው። ልጅ መስጠት መንሳት የሚቻለኝ እግዜር ነኝን? አላት። የወለደችው ለኔ ይሁን ብላ ባሪያዋ ባላን ሰጠችው ወልዳለታለች ልያም መውለድ ብታቆም የወለደችው ለኔ ይሁን ብላ ባሪያዋ ዘለፋን ሰጠችው። ወልዳለታለች። ዘፍ 30:1 – 13

ይኸውም ምሳሌ ነው። ያዕቆብ የትምህርተ ወንጌል ልያ ራሔል የምእመናን እስራኤል ባላ ዘለፋ የምእመናን አሕዛብ ሕፃናቱ የጸድቃን ስጋዕት ምሳሌ ከባላ ከዘለፋ መውለዱ ወንጌል ከአሕዛብ ደርሳ ከምእመናን አሕዛብ ጻድቃን ስጋዕት ለመገኘታቸው ምሳሌ ነው።

| | |
|---|---|
| የደጋጎቹ ልጅ ደጉ ያዕቆብ | ሌሊት በራእይ ራሔልን አይቶ |
| ከርሱ ወጣ በውነር የጸድቃ ክበብ። | አለለትም እለ ካልባረከኝ ትቶ |
| ለሙን እልመራቸው ለበጎነም | ጌታም ፍቱም ዋቅፍን እቶ ዓርኮ |
| ከዘሩ ተወልዶ ደንግል ማርያም። | ሁለም ለዋለ እስራኤል እለው |
| አንድ ቀን ተዘርተው አንድ ቀን ታጭደው | እንደ ዓለር እየ ሁሉን እየሞ |
| ለርሱ ተገዝተው ወንድሙ ዔሳው። | ገር የዋህ ነዋና ያለው ቅንነት |
| ልጆቹም ዝናሩ ለዘሩ በምድር | አሥራ ሁለት ልጆች ለርሱ ተሰጥተ |
| ለምትወለድ ድንግል ከርሱ ዘር | በርሱ እንዲሆን የአለዋ እባቶ |

ከ15 ዓመት በኋላ ዘመን ረሀብ ቢሆን በዮሴፍ ጥሪ ሰባ ራሱን ሆኖ ግብጽ ወርዷል ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ የዮሴፍ እናቱ ራሔል ሁለተኛ ልጇ ብንያምን ስትወልድ በምድረ ሉዛ ዐርፋለች። ራሔልን ስለመውደዱ እሱን ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር። ከመውደዱም የተነሣ በአራት ኅብር በአምስተኛ ወርቅ የተሠራ ልብስ አልብሶት ልብስ አልብሶት ነበር። ወንድሞቹ በዚህ ቀንተውበታል።

ከለያልይ ባንዱ የወንድሞቹ ነዶ ለሱ ነዶ ሲሰግዱ ሕልም አይቶ ለአባቱ ነገረው። በእህል ምክንያት ይገዙልህ ይሆናል አለው። ሁለተኛ ፀሐይ ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብት ላንድ ኮከብ ሲሰግዱ አየ ፀሐይና ጨረቃ የተባሉን እኔና እናትህ ነን አሥራ አንድ ከዋክብት አሥራ አንዱ ወንድሞችህ ናቸው አንድ ኮከብ አንተ ነህ የኋላ የኋላ ይገዙልህ ይሆናል ነገር ግን ወንድሞችህ ከሰሙ ይጣሉሃልና አትንገራቸው አለው።

ከብቶቻቸውን ይዘው ለምለም ሳር ጥሩ ውኃ ካለበት ይኖራሉ ስንቃቸውን አቢዮ ሰጥተሃቸው ና ብሎ ሰደደው። ሲፈልጋቸው ስንቢቶ አጥቶው የታዘዘ መልአክ በአምሳለ ብእሲ ሆኖ ደይታን አሉልህ አለው ሄደ። ከሩቅ አይተውት ባለ ሕልሙ መጣ ወግረን እንግደለው ከዚያ በኋላ ደኅንነቱን እንደሆነ እናያለን አሉ። ያመጣላቸውን ተቀብለው ከዚህ ይመክሩት ጀመር ሮቤል ምንም ቢሆን ያጥገታችን ፍሬ የሥጋችን ቁራጭ አይደለምን ተው ብሎ አስጣላቸው። ከዚህ በኋላ እሱን ከጉድጓድ ከተው ይመክሩ ጀመር። ሮቤል ከብት ሊመልስ ሄዶ ሳለ እስማኤላውያን

ሞቱ ይሁዳ ወንድሞቻችንን ብንገድለው ምን እንጠቀማለን እንሽጠው አላቸው። በ20 ብር ሸጠውታል። ሮቤል ተመልሶ ቢያጣው እንደሸጡት አውቆ ልብሱን ቀዶ አመድ ነስንሶ ያለቅስ ጀመረ። ጠቦት አርደው ልብሱን በደም ጠምቀው ምን ብላቱና ወደ አባቸው ነበርን አውሬም በልቶት እንደሆነ ልብሱን እንዲሁ ሆኖ አገኘነው ብለው ላባቶት ልጆን ክፉ አውሬ በልቶታል እያለ ግብጽ እስኪወርድ ድረስ ሲያለቅስ ኑሯል። ዘፍ 37፡1 -36

እኒያም እስማኤላውያን ግብጽ ገብተው ከፈርዖን የጦር አበጋዞች ለአንዱ ለጲጥፋራ በሠላሳ ብር ሸጠውለታል። ጲጥፋራ በዮሴፍ ምክንያት ከበረ። ይህ ዕብራዊ ከመጣ ገንዘቤ በዛ ብሎ በቤቱ ላይ አሠለጠነው ወደ የት አዕይንን ቲሃ በእሲተ እግዚኡ ደላል የጲጥፋራ ሚስት ገደኛን ማለችበት አንድ ቀን ነዓ ስዕበ ምስሌየ ና ከኔ ጋር ተኛ ብላ በግልጽ ነገረችው። ጌታዬ በሁቡቱ በንብረቱ ሲያሰለጥነኝ ባንቺ ላይ አላሰለጠነኝም ብሏት ወጣ። በሌላ ጊዜ ለሥራ ገምጃ ቤት ገብቶ ባለ አንተ ባሪያ ዛሬስ አለቅህም ብላ ተራምዳ የዘችው ነጥቆ እሄላለሁ ሲል ቀሚሱ ከወገቧላው ተቀደደ። ብታዋር ቀሚሷን ከወደፊቷ ቀዳ መጣች። ምን ሆንሽ አላት። ይህ ቀጋበኛ ባሪያ ልደፈርሽ አለኝ። አይሆንም ብለው ቀሚሱን ቀዳት ሄደ አለቻቸው። ፈቃዱስ ያንቺ ይመስላል። ይህ ባይሆን ያንቺ ከፊትሽ የሱም ከኋላው ባልተቀደደ ነበር ብለው ለጊዜው ደስ ይበላት ብለው አሠሩት።

ጲጥ ፋራም ለሚስቱ አድልቶ ከፈርዖን እስረኞች ደረበው። ወኢገደፈ ዘእንበለ ሚመት እንዲል ያለሙት አላደረም ከዚያም ሹሙ እስረኞች ጥንተ ቃል ይደሩ ብሎ መብት ሰጥቶታል። የፈርዖን ጠጅ አሳላፊና ሥጋ መልከኛ ታሥረው ነበር። ሕልም አይተው የሚተረጉምላቸው አጥተው ሲያዝኑ ወሐደ ሲሞቅ ቀደቶ ገብቶ ምነው አዝናችኋል አላቸው። ሕልም አይተን የሚተረጉምልን አጥተን አሉት የገለጸለት ይተረጉማል ንገሩኝ አላቸው እንጀራ አበዛው! በ3 መሶብ ነው እንጀራ ይዤ ወደ ቤተመንግሥት ስገባ አዕዋፍ ከላዬ ገልብጠውት ሲመገቡት አየሁ። አለው። እስከ 7 ቀን ፈርዖን ይሰቅልሃል አዕዋፍ ይመገቡሃል አለው። ጠጅ አሳላፊው 3 የወይን ዘለላ በጽዋ አድርጌ ለፈርዖን ስሰጠው አየሁ አለ። እስከ 3 ቀን ወደ ሹመትህ ትመለሳለህ ብሎ ተርጉሞላቸዋል። ጠጅ አሳላፊውንም እኔም ተድሞ በግፍ ተሸጬአለሁ። አሁንም በግፍ ታስሬአለሁና ከፈርዖን ፊት አስታውሰኝ አለው። ተስፋውን በሰው በማድረጉ ጌታ ተጨማሪ 2 ዓመት በግዞት እንዲቆይ አድርጉታል። ትርጓሜ በ3ኛው ቀን ፈርዖን የልደት በዓሉን ሲያከብር መኳንንቱ ገብተው እጅ ነሡ እንደምን ውላችኋል አላቸው። በደህና ውለናል የተድሞውን ጠጅ አሳላፊ የዛሬውን እንጀራ አበዛ ለሹመት የተድሞውን እንጀራ አበዛ



የዛሬውን ጠጅ አሳላፊ ለትዋት ብሰናል አሉት። ያን ወደ ሹመት መልሶታል። እንጀራ አበዛውን አሰቅሎታል።

ያም ወደሹመት ከተመለሰ በኋላ እስከ 2 ዓመት ድረስ አላስተወሰውም። ከ2 ዓመት በኋላ ፈርዖን ሕልም አየ ከወንዝ ዳር ያለ ይመስለዋል 7 የወፈሩ ያማሩ ላሞች ወተተው ሲሰማሩ 7 የከሱ የከሰሱ ላሞች ወተተው ውጠዋቸው ያልተመቹ ሲመስሉ ሁለተኛ 7 ያፈሩ ያማሩ እሸቶች ሲወጡ 7 የደረቁ የደቀቁ እሸቶች ወተተው ውጠዋቸው ያልተመቹ ሲመስሉ ያያል። ጠበብቱን ጠርቶ ተርጉሙልኝ አላቸው። አልቻሉም በዚህን ጊዜ ያ ጠጅ አሳላፊ ሀጥያቴ እኔና ባለንጀራዬ በእስር ሳለን ሕልም አይተን የጲጥፋራ ባሪያ ተርጉመልን እንደነገረን እኔ ወደ እኔም ወደ ሹመት ተመለስኩ እሱ ይተረጉምልሃል አለው። አስጠርቶ ሕልሙን ነገረው።ደግ ምላሹ እንደሰው ሰማጠየቅ ይጋገምሃል 7 የወፈሩ ያማሩ ላሞች 7 የሚያፈሩ ያማሩ እሸቶች 7 አዝመን ጽጋብ ናቸው። 7 የከሱ የከሰሱ ላሞች 7 የደረቁ የደቀቁ እሸቶች 7 አዝመን ረሀብ ናቸው፣ ውጠዋቸው ያልተመቹ መዋጣቸው 7ቱን የጥጋብ ዓመታት የሚያስከረው 7 የረሀብ ዘመናት ይመጣሉ ብሎ ተርጉሞለታል። ፈርዖንም ሲተወደዱ አድርጎ ሹሞታል።

ከዚህ በኋላ የሴፍ የወርቅየብር ግብሩ እህል ይሁን ብሎ አዋጅ አስነገር የ7 ዓመት እህል በትቱሩ አከማቸ።

7 የጽጋብ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ በምድር ላይ ጽኑ ረሃብ ሆነ። የሴፍ በግብፅ እህል እንዳለ ሰምቶሉና ሽምታችሁ ኑ ብሎ ልጆቹን ሰደዳቸው። የሴፍ አይቶ አወቃቸው ምንድር ናችሁ? ብላችሁ ጠይቋቸው አለ። ሰማዮች ነን አሉ። ሐሰት ሰላዮች ናችሁ አላቸው። ሰላይ ከሆነ ተወጣቶ ይመጣል። እኛ ግን ያንድ ሰው ልጆች ነን አሉት ሐሰት አንድ ሰው አሥር ይወልዳልን አላቸው። ኧረ አሥራ ሁለት ነበርን አሉት። ሁለቱ የት ሄደዋል አላቸው። አንዱ ሕፃን ሆኖ ከቤት ቀርቷል። አንዱን ግን አውሬ በልቶታል አሉት። እንግዲያስ ከቤት ያለውን ካመጣችሁት ሰማኞች መሆናችሁን አውቃለሁ። ከዚያ በኋላ ተመላለሳችሁ ትሸምታላችሁ። ያለበለዚያ ግን ሰላዮች መሆናችሁን በዚህ አውቃለሁ ብሎ ስምዖንን አስቀርቶ ስንዴውን ከወርቃቸው ጋር በየአይበታቸው አድርጎ አሰናበታቸው።

ከቤታቸው ደርሰው አይበታቸውን ሲፈቱ ወርቃቸውን አገኙ አባቱ ለአንዱ ሊተፀ ገብአተኒ ወርቅየ ይል ጀመረ ስምዖን አላቸው የሆነ ገዥ አስጠ ብቆታል አሉት።

ያን በልተው ሲጨርሱ ሄዳችሁ ሸምቱ አላቸው ብንያምን ካላመጣችሁ አይሆንላችሁም ብሎናል እሱን ስጠን አሉት። የሴፍን አውሬ በላው ስምዖንን አስጠበቀው አላችሁኝ አሁን ደግሞ ብንያምን እንውሰደው ብላችሁ አንድ ነገር ቢሆን በኀዘን ወደ መቃብር ልታወርዱኝ ነው አላቸው። ይሁዳ እኔ ይህና ባልመልሰው እዳው በእኔ ይሁን አለ። ስጣቸው ይዘውት ሄዱ። እናመጣዋለን ያላችሁት ወንድማችሁ ይህ ነውን አላቸው አዎን አሉት ሸማግሌ አባታችሁስ ደህና

እሱን እላቸው እምን ሰደምና ነው እሉት በሩብ በእሌሁ የተዓረከ ሰው እለ እለታችንን እመጠበስ ብለው እጅ ነሱ ሾመን ከፈርያን ደርጊ መጫ ከመንደተቸው እገናቸው ብሎት ጉድ። በመሰደነው ወርቅ ሊያገኙን ነው ብለው ተደናግ የመሰደነውን ወርቅ ሊለምወርቅ ይዞን መተናል አሉ። የእቢታችሁ እምላክ [illegible] አሳልፎ እንጂ እላቸው።

ከለርያን ደርሶ ሊመክር ግለድ እመርቶ ከበሉ ከወጡ በኋላ በሰበዉ እንደ ወዲ ዘሰበ አንድ ምን ሁነው ሊመጡት ብንያም ገዝ አለ። ምንው እትመጡት ምን ብለው ክለው መተርጉመንው። እሊህ ልይበት ያባሊት ልጅ ሁሉቱ ያባሊት ልጅ ሁለቱ ያባሊት ልጆች ናቸው። ብለው ወንድም ነበረኝ አሙሬ ብለው አለው አለው። ሹሙ ቀድሞ የመሰደነን ወርቅ ለለም ይዞን ያለ ወርቅ ይዞው መተናል አለው። ወርቃቸውን እትገል እለሰን ሰዋቸው ከትገዙ ልጅ እሰበት ዘገኑን እደርግሁ ልጅን እንደ ተበለሁ መልሰ እምላኳ አለው እንዲሁ አደርጎ ከዎቸው በኋላ ግትት እሉና ሊሉ ተቀትሉ ሄደ ወርቅ ብደረሬ ጠመር እህል ብደረሬ እሌር እንዲሉ ጌታዬ ደግ ሊያደርግላቸሁ ክፉ ታደርጉብኛላችሁን ስለምን ዘንዉን ሠረቃችሁ? አላቸው ኸሬ እኛ እለመሰደንም የተገኘበት ይሙት እሉ ምንግ ለምን ይሙት ባሪያ ሆኖ ይገዛ እንጂ [illegible] ከበርሊ [illegible] ከብንያም ተገኘ [illegible] ስሉን እስናቀትለኝ አለው። ለምን የተገኘበትን ትቼ ያልተገኘበትን እሰራለሁ አለው። የሴፍ ይህን ግድሬን እሉን እንዲሁ እሰንስ ትትውት ደደሉ ይሆን ብሎ ነው ይሁዳ እቅቶ እንዲሁ ቢል [illegible] ሊሞት እለደም እኔ ለስሉ ልንሽ እለ የተገኘበትን ትቼ ያልተገኘበትን እሰራለሁ እለው ከዚህ በኋላ ይህ ሁሉ የመንደሞቹን ጉዳ ነው ያየንታችንን ዋጋው የመገቸችን ቀሪው ሾተው ይሳላ ጀመር። በመተርጉም ይነጋገሩ ስለነበር የሚሰሙቸው አይመስላቸውም። ወደ እለዋቸ ይሂቸው ገብቶ እነ መልቶ የሴፍ [illegible] የሴፍ እሉ ነኝ እላቸው። ደነገጡ እደገችሁ እትደንገጡ እናንተ ለበጎ ብታደርጉት ጌታ ለበጎ እደርገታል። ይህ ባደሁን ይህ ሁሉ ከሆት ይመጣ ነበር ብሎ ለብዙ ሰንቶ ሰተቶ ለእባቴም ለብሱን በንቀን የሚመጡበትን መሪያ ሰተቶ እሰሱን በብሌሬ ባለ ያገኙትን ክብር ነገሩችሁ እምጡልኝ ብሎ ሰደዳቸው።

ያዕቆብ የየሴፍን በሕይወት መኖር ሲሰማ ደስ እለው። ወዲ ራሱን ሆኖ ግብጽ ወረደ የሴፍ ፈርዖን እሰፈቃደ በምድሬ ገሰም እሰፈረው። ጌሴ ሰርፍቀ ሲደርስ ልጄ በእባቶቹ ሀገር በእባቶቹ መቃብር እንጂ በእሕዛብ ሀገር እንዳትቀብረኝ እለው። ዘፍጥረት 47፡22-31 ከዚህ በኋላ ደከም ብለ የሴፍ ልጆቹ ምናሴና ኤፍሬምን በቀኙ በግራው እቀም እሱን ልጆቹን ባርካቸው እለው። ወእስተኃለፈ እደዊሁ ለባርከ ኤፍሬም ወምናሴ ይለል እጆቹን እለዋወጠ ቀኝ እጅን በግራው የቆመው ኤፍሬም ላይ ግራውን በቀኝ የቆመው ምናሴ ላይ አደረገ። የሴፍ እባቱ በሉሬ እሱ ይህ ነው እለ ምናሴን። ልጄ ሁለቱም ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ ታናሹ ግን ይበልጣል ብሎ ባርኳቸዋል ትንቢትም ተናገሬባቸዋል። ትንቢቱ ለ[illegible] ልጆች ሁሉ ነው። እንዲሁ ሆኖ ኖሮ በ147 ዓመቱ ሞሬ። የሴፍ በመሬቱ ቃሉ በእባቶቹ እውቶ በዘያን በእባቶቹ መቃብር ተቀበሬታል። ዘፍ ምዕ 48-49 የሴፍም በ110 ዓመቱ እርፎ ሥጋውን ሰደው [illegible] ቀብሮው እሳቸው እሮሮው [illegible] [illegible] እሰራኤል ከግብጽ ሰወጡ ይዘውት ወጥተዋል። መታሰቢያው ጥር 28 ቀን ነው።

ያዕቆብ ከልጁ እጅግ የሚወደው
የሴፍ የተባለ ታናሽ ልጅ ነበረው።
ስርሱ ወንድሞቹ እንዲጠሉት
በምጣኬ እና ሕልም በሌሊት።
ወንድሞቹ ሁሉ ይህንን ሰምተው
ጠሉት ተመቀኙት እሉ አንድው
ክብት ሊጠብቁ ከሚዳ ሁነው
እንዳይመጥጉ በንት ጠርበው
ያዕቆብ በፍቅሩ የሴፍን ላከው።
እሱም ያሰበትን ሲፈልግ ቀይቶ
ዶታይን እገኛቸው ብሎ ተንከራቶ
በንቀን ተቀብለው ዘራያውን ከዘው
በጉድጓድ ዉርግጉ መቀት ጨክነው
ይነገሥበን እንደሁ ዋቶ ሆኖ በደን
እስኪ እናያለን የዚህ ሰው ሕልሙን።
እየተቀበሉ በእርሱ እየዘበቱ
ሊሰበረበት እስኪዝዞ ጉልበቱ
የሴፍ ገራ ገሙ ታወከ ሕይወቱ።
ሲገዛ ሲገዛበልፍ ሩቀው በዘቀበት
ከቀበር ጉድጓድ እሱን ከተውት
ምግባውን በሉ ሆነው እንድገነት
እሱን ግን ከመጫው ቀራኘ ኳኔትን።
በሉተው ሲጠርሱ የሰባቸውን
የደሁሳን ምከር ሰምተው ሁሉን
በሃያ ብር ሸጡት ለእንድያን።
ለእቢታቸውም ምክን ሊያረሩት
ለብሱን በዐሞት ደም ነክረው ላኩለት
ያዕቆብ እሱ ወደቀ ከመሬት
ልጄ ልጄ እያለ እለቀሰለት
የሴፍም ተሸጦ በግብጽ ሀገር
እያገለገለ ከሙ ቤት ሲኖር
ሥጋዊ ፈቃዱን እለፈጸም ብሎተ
በግፍ እመሬቸው የእስሩቤው ሚስት።
እሱ ግን ንጹሕ ሰው ነውና ትሑት
በዎች ቢጠሉትም በምቀኝነት
እምላክ እልተወውም ለእንዲት ቅጽበት።
ከእሥር ጎመት በኋላ ከገዎት ተጠርቶ
የፈርዖን ሕልሙን ተርጉሞና ፈትቶ
በግብጽ ተሾመ ሞገስን አግኝቶ።
ሕልሙን ሲተረጉም የሴፍ እንዳለው።
በዓቱ የዘጋብ እመታት እለፈው
የረኀብ ዘመን መጣ በተራው።
ያዕቆብ በማና ሰንዴ መግፋን
ወደ ግብጽ ላካቸው እሥር ልጆቹን
የሴፍ ወንድሞቹን እይቶ እወቃቸው
ነገር ግን እልሻተም እንዲበቀላቸው።
በፍቅሩት በፍቅር ቀተ እያያቸው
ከወዲት መጣችሁ ማናችሁ እላቸው
ከእንድ ሰው ተወለደን እሥሬ ሁለት ነን
እንዱም ከቤት እለ እኛም እሥራችን
እንዱን እሥሬ በሌቶት እሳቋል ሕይወቱን
ብለው ሠቃ ሳይሞት እረዱት ሞቱን።
እሱም ሳይቀየም በጥንት በደላቸው
ሰማቸው ሰንደውን ከስጋዝባቸው
ሊገዙ ሲመጡ ደግመው ተመላለሰው
ወንድማቸው የሴፍ መሆኑን ነገርቸው
ተወቶ እሊሩ በክፉ ሥራቸው
ያዕቆብ ደስ እለው ሰልጁ መኖር
ምስጋና እቀረበ ለእግዚአብሔር
ሊረሀብ ምክንያት ስለልጅም ፍቅር
ቢተበሰን ይሆ እንድ እንኳን ሳይቀር
ከየሴፍ ጋር ኖሬ በግብጽ ምድር
ሰውንድም ላይ ክፉ ማድሬግ መጨከን
ያዕታል እንጂ እይሰጥም ጤናን
ክፉውን በክፉ መመለስ ነውር
ክፉውን በበጎ መመለስ ግን ክብር

ማቴ 5፡45 ሮሜ 13፡19

## ምዕራፍ 7

## 2 - ቅንጭጌን ዕረፍቱ ለቲቶ

ቲቶ ማለት ሠርቅ ማለት ነው። ሀገሩ ቀርጤስ ነው። እባት እናቱ አረማውያን ነበሩ። እሱም ለሰው የሚራራ የተቸገረ የሚረዳ ደግ ነበረ። ዘኢእምን ሙሴኢተ ጠምቀ ይደየን ማር 16፡16 ያለ ነውና ሲሊት በራዕይ ሥር የሌለው ዛፍ

ዓምድ የለለው አጸራሽ ሊጸና ይችላልን ካላመንክ ካለተጠመቅህ ምግባር ብቻ አያድንህም አለው። ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ቅዱስ ጳውሎስ ቀርጤስ ደርሶ ሲያስተምር ሙት ሲያነሣ እውር ሲያበራ አይቶ ተከተለው። ከፍጹምነት እንዲደርስ አውቆ ሳየገሪዝ አስከትሎታል። ወቲቶስ ዘምስሌየ እንዘ አሬግዊ ውእቱ ኢየዘበርከም ይትዘከር እንዲል፡-

ኋላም ከፍጹምነት እንደደረሰ አውቆ በቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስነት ሹሞት ሄዷል። ናቆጽል በሚባል በታም ሳለ እንዲህ አድርግ እንዲህ አታድርግ ሲል በአርጣግ በእጅ መልእክት ልኮለታል።

እሱም ወንጌል ካልደረሰበት ሲያደርስ አሕዛብን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ሲመልስ መጻሕፍት ገልጸው የማያስተምሯቸው ቀድሰው የማያቆርቧቸው ቀሳውስትን ዲያቆናትን ሲሾምላቸው ቆይቶ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

## ጳጉሜን 3 በዓሉ ለቅዱስ ሩፋኤል ሊቀ መላእክት

ሩፋኤል ማለት ፈታሔ ማኅፀን ማለት ነው። ግእባይ ሊቀ መላእክት ነው። ለሄኖክ ወልደ ያሬድ 6 ዓመት በእግረ ኀትት ወድቆ ሳለ ኅበዓቱን ከሡታቱን አሳይቶታል ሄኖ 8:15

ወደ ጦቢት ተልኮ ዓይኑን ፈውሶታል። ቤቱን በበረከት መልቶታል። በዚህ ዕለት ተዝካረ በዓሉ መደረጉ ስለ ሁለት ነገር ነው። የመጀመሪያው በዓል ሢመቱ ስለሆነ ነው።

ሁለተኛው ቅዳሴ ቤቱ የተከበረበት ነው። የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባቴዎፍሎስ እምከመረከብከ ምገብ በቅድመ እምላኪየ ኢየኀድግ ለዝንቱ አድራማሊክ ቢል እልእርታ አስከብትራለት ሦስት ድስት ሙሉ ወርቅ ወርቅ አግኝቶ በአንዱ በድስት ሙሉ ወርቅ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት አሰርቷል። በቅዱስ ሩፋኤል ስም በዛበነ ዐንበሪ ዐቢይ ቤተክርስቲያን አሰርቶ በዚህ ዕለት ቀድሶታል። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ዐንበሪውን ወዲያ ወዲህ አናወፀው። ወደ ጌታ ቢያመለክት ቅዱስ ሩፋኤል መጥቶ በትዕዛዙ ለእግዚአብሔር ቀም ወኢትትሀወክ እመካንከ ከቦታህ አትንቀሳቀስ ብሎ በዘንጉ ቢነካው ባለበት ጸንቶ ቀርቷል።

## ለ. ተዝካረ በዓሉ ለመ ልከጼዴቅ ካህን

መልከ ጼዴቅ ማለት ንጉሠ ሰላም / ሳሌም / ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ካም ነው። አባቱ ቃይናን ይባላል። እያቱ ኖኅ ጊዜ ዕረፍቱ ሲደርስ ሴምን ከሰም ወገን ደግ ልጅ ተወልዷልና ከዘመዶቹ አሲ... ናብተህ እኒህን ንዋያትና አጽመ አዳምን አስጠብቀው በንጽሕና በቅድስና እንዲኖር ሥርዓት ሠራበት



አለው። ንዋያቱ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሩፋኤል ከገነት አምጥተው ለአዳም የሰጡት ኋላም ሰብአ. ሰገል ለጌታ የገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤ ናቸው።

ከዘመዶቹ አሰናብቶ ከቤት አትድረስ ጻባ ልበስ ፀጉርህን አትላጭ ጥፍርህን አትቁረጥ ሥጋ አትብላ ጠጅ አትጠጣ በሰንዱ በወይን አስታኩት ብሎ ሥርዓት ሠርቶ በዱዳሴም /ማዕከለ ምድር/ ንዋያቱንና አጽመ አዳምን አስጠብቆታል።

አብርሃም ለአምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራቱ ነገሥተ ከሉዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ደስ ቢለው በመዋዕል የኑ ትፌኑ ቃለከ ወሚመ ታርእየኒሁ ኪያሃ ዕለተ አው አልቦ ልጅህን በትሰብዕት የምትልከው በዘመኔ ነውን ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ። እሱን አታየውም ነገር ግን ምሳሌውን ታየለህ ሑር እድዎ ለዮርዳኖስ - ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው። ቢሄድ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ አኰቴት ጽዋዐ በረከት ይዞ ተቀብሎታል። ወርቅ ዕጣን ከርቤውንም በዚህ ጊዜ ሰጥቶታል። ዘፍ 14:17-18

ከዚህ በኋላ የሀገሩ ሰዎች ሄደው ንጉሥልን አሉት ያስጠበቀኝን ትቼ አይሆንም አላቸው። ሉጣሉ አስታርቀን ሲከራከሩ ፍረድልን እያሉት ያስታርቃቸው ይፈርድላቸው ነበር። ፍርድ የማያጓድል ደኃ የማይበድል የተጣላ የሚያስታርቅ የተበደለ የሚያስከስ ቢሆን ንጉሠ ጽድቅ ንጉሠ ሠላም ብለውታል።

መልከ ጼዴቅ የተመረጠ ክህነትም የተሰጠው ከእግዚአብሔር ነው። ወሰመዮ እግዚአብሔር ሊቀካህናት ዘለዓለም በከመሢመቱ ለመለከጼዴቅ እንዲል የሕይወቱ መጀመያ እንዳልታወቀ የሕይወቱ ፍጻሜም አልታወቀም። ማለት እንደ ሌሎች ነቢያት ካህናት በዚህ ጊዜ ተወለደ በዚህ ጊዜ ሞተ ተብሎ አልተነገረለትም። እስከ ምጽአት ድረስ ሕያው ሆኖ ይኖራል። ምጽአት ሲደርስ ግን ከእነ ኤልያስ ጋር መጥቶ መስክሮ በሰማዕትነት ይሞታል። ገጽ ________ ተመልከት። ቅዱስ ጳውሎስ አልቦ ጥንት ለመዋዕሊሁ ወኢማኅለቅት ለመንግሥቱ አምሳሊሁ ለወልደ እግዚአብሔር ይነብር ክህነቱ ለዝሉፋ ማለቱ ስለዚህ ነው። ዕብ 7: 1-13

## ጳጉሜን 5 አሞጽ ነቢይ

አሞጽ ማለት ጸር /ሸክም/ ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ቁጥሩ ከ12 ደቂቀ ነቢያት ነው። ከብት እያረባ በቴቁሔ ይኖር ነበር። ሚስቱ ወንድ ልጅ ስትወልድለት ሀብተ ትንቢት ተሠጥቶት ዐቢይ ነቢይ እንደሚሆን ተረድቶ ኢሳይያስ ብሎታል። ኢሳይያስ ማለት መድኀኒት ማለት ነው።

ንጉሡ ዮርብዓም ወልደ ዮአስ እግዚአብሔርን የማፈራ ነበርና በሰይፍ ከመሞት እስራኤልም ከመማረክ አይቀሩም እያለ ትንቢት ሲናገር ሊቀካህናቱ አሜርያስ ቤቴል የንጉሥ ቤትና ቤተመቅደስ ናትና ወደ ይሁዳ ሄደህ በዚያ ትንቢት ተናገር አለው። ላም ጠባቂ ዋርካ ለቃሚ እንጂ ራዕይ የማይ ትንቢት የምናገር ነቢይ ነኝን ብሎ አይሆንም አለ። ማስተማሩንም ቀጠለ። ትንቢቱም አልቀረ ንጉሡ በሰይፍ ሞቷል እስራኤልም ተማርከዋል። መዋዕለ ትንቢቱ 50 ዘመን ነው። የነበረው በ760 ዓ.ም. ገደማ ነው።

## ታላቁ የቅኔ መምህር መምህር መንግሥቱ ዘለዓለም ከዘረፉቸው በርቃታ ቅኔዎች መካከል፡-

### መወድስ

1. ሃይማኖት ወይን ዘዘሐዋርያ ሠረገላ ሥቃይ ወገድል ማትያስ መዘምር
   ኢተርፈ በከ ወኢተከዕወ በምድር
   ሃይማኖት ወይኑ ሐዋርያ አኮኑ መዓር
   ቅድሜሆሙ ለማኅበር ጳውሊ ወጴጥሮስ ዘታውጉሉስ አብትር
   ኢፈተወኒ ከመይስተይ ዘኢያስክር
   ወይነ ቤተ ማትያስ ሃይማኖተ ይሁዳ ዘዮንሥር
   እስመ ቀዲሙ ተብህለ ኢይጥዕሞ በምዕር
   ምዓር ለይሁዳ እድገ ሲኦል ሠቃብር

2. መደንግጸ ሕዝበ ለሳሌም ሠረገላ ሙሴ
   ኖላዌ ኢያሱ ወአሮን አባግዐ ብንያም ዘተዐውቀ
   በኀበ ዕብራዊ ንፍታሌም ስሙዐ ርሑቅ ርሑቀ
   ጸራቅሊጦስ ነጕድጓደ ራማ ዘለብሰ መብረቀ
   ዘናዝሬት ዘገሊላ ዘበሰሎሜ ወዮሴፍ ነፋሳተ ብሂል ረቂቀ
   በዮሴፍ ዮሴፍሃ ዘብዙኃን አጥመቀ
   አድለቅለቀ አድለቅለቀ አድለቅለቀ አድለቀለቀ
   ዘኢ በጽሑ ሄኖክ ወመልከ ጼዴቅ መንፈቀ
   ምሥራቀ ወምዕራበ ምዕራበ ወምሥራቀ

3. **ዕጣኑ ሞገር (ዕዝል)**

   ሰማዔ ትእዛዙ ለእብ ግብሬ ኩሉ ፍጥረት
   አብርሃም ወልድ ዘየሐትት
   እኩየ ወሠናየ በዘቀደሙት አሪት
   ምዕራፈ እለ በዝኑ ነቢያት
   አናግደ ሳሌም ወጽአ ቀዲሙ እምነ ሀገሩ ስቅለት
   ወተፈልጠ እምነ አዝማዱ መቃብር ወሞት
   አብርሀ ለነ መቃርዮስ ብርሃነ ካህናት ቀደምት
   እስመ በእማን አንተ ለኩሉ ዘኢይጠፍዕ ማኅቶት
   ይትቄደስኒ ወይትአኰት
   ስምከ ሕያው ዘኢይመውት
   እስመ ለከ ይደሉ ስብሐት



#### ከሊቀ ጠበብት ሰሎሞን አያሌ (ዘደ/ት/ቅ/ሚካኤል)

ዓይነ መሀይል ጠቢት ሠናይተ ራእይ
እንዘኒ ትተዋነይ ዘምስለ ዑረት መፍቀሪሃ
ፍጡነ ርእት መንገለ ብርሃን ጽርሐ
እምአንጻር አምጣነ እልጸቀ ሩፋኤል አቡሃ
ከመ ኢይርገጸ ለፍቁራ ወከመዓዲ በኃይል ኢይትቆጣዕ ላዕሌሃ
ዑረትሰ ፈራሀ ልበ እምድኅረ ገብአ ቅድሜሃ
ለፍቅርት ዓይነ ጠቢት ኢወአለ በፍሥሓ
ከመ በትፍሥሕት ኢየአል እንዘ ይተዋነይ ምስሌሃ
እስመ ኮነ ማዕቀፎ ሩፋኤል ወላዲሃ

#### ከመምህር ዓምደወርቅ ደሴ (ዘቤ/ብ/ኪዳነ ምሕረት)

ዋዜ. ሥጋ እም እቤረ ክብር መፍቀሬ ብሂል አዐቢ
መላእክተ ሰማይ ኄራነ
ላዕለ ዝሀር ሊቀ ቤተ ሙሴ መአዝዘ ኮነ
እስመ እም እግዚእ ተውህበ ዕርገተ ሰማይ ዘመነ
ሥጋ እምሂ እቤር ዘአስተኀዘነ
ሕገ ሙሴ ዕፄ ዝሀር መነነ

ወመ ሐሰስተ ነቢያት ቀደምት ለመልከጼዴቅ ላዕካኑ
መና ወወይን ቅድሳኑ
ለፋኑኤል እመሰምዑ ትርጓሜ ፋኑኤል ቦኑ
ውስተ ደብረ ኢዮር ዘተሐጽኑ
ገዳመ ሱቱኤል ቦኑ ዋሕድና ወገበ ዳንኤል ኮኑ
እስመ ጽድቀ ዘካርያስሃ ዓለመ መነኑ
ሐንጽተ ጠ ቢባን ካህናት ወእሉ ሊቃውንተ ያሬድ ዝኑ
ማኅሌተ ሰሎሞን ቤት ዘዘቦ ብርሃነ መስቀል ብርሃኑ
ይከውን እንከ ለለዘመኑ
እምጣነ ጠፈሩ ጽኑዕ በበአምጣኑ
ውኅሩይ ቅዱሴ ክዳኑ

#### ከመምህር ኢየሱ ሀብለፋ (ዘደብረ ሊባኖስ)

መወድስ ባዕለ ጸጋ አብርሃም እምዘተዘምዱከ
እንከሰ ለትኅሥሥ ሐራሲ ስመ ሕይወት
አምጣነ መጥባሀት ወልድከ ዘውስተ ቤት
ኢየሐውር እምነ ኮሣዱ ለይስሐቅ ገራህት
በይነ ዘለመደ ተዋንዮ ተዋንዮ ፍቅር ምትረተ ምስለ ወለተ አብ በግዕት
ያዕቆብሂ ዘየዐቅቦ ለአጸድከ ሐውልት

ይውእል በሰኪም ሰዋሰው ዘኢብርት
ወ እንዘ ይቀድሕ ዘይተ ማየ ፈለገ ዳን ርህቅት
ለዘየሐንጹ ማኅደረ ምሳሌ ድንግል መላእክት

## ከመጽሐፉ አዘጋጅ

**መወድስ**


1. በውእቱ ሉቃስ ነገደ ተጋድሎ
ይስሕቅ ኔሮን ለስልምናሶር ጸታሁ
እስመ ማህተ ሄኖክ ማይ እንበለ ይቀረብ ቅድሜሁ
ውስተ ሰይፍ ማዕደ ሮምያ ፈነወ እደዊሁ
ወይትፌእም በጉጉአ ኀበይምን ወጽግም እንዘኢይሬኢናሁ
ሉቃስሰ ድኅሬፈጸመ በሊበምትረት ምሳሁ
ፈቀደ ለሰኪብ እመንክር ምስክቢሁ
ሕማማትስ አግብርት እለነጸሩ ቀማሁ
ሰአልዎ ለሉቃስ ይሕጽቡ እገሪሁ

2 ወልደ አብ አንተ መምህረ ሱላሜ
ፍጡነ ገሥጽ ማየዳኖስ ወለተከ
አምጣነ አፍአ ትውእል ምስለ ዮሐንስ ረድዕከ
ውስተ ቤት ቀለየ ገሊላ አንቢራ ኪያከ
ወእም ዮም ኢገሠጽካ ወለትከ ማይ ትወጽእ ኅዕሌከ
እለሂ እምካልዓን አጽናዕኮሙ ቅድሜከ
እግብርቲከ ድንጋጌ ኢዐቀቡ አጸደከ
አኮኑ አርመሙ እንዘ ይጸርሑ ብከ
መላእክት ሕጻናቲሁ ለአብ ፍቁርከ

3 <u>ዕጣነ ሞገር (ዕዝል)</u>
እምከመ ሀሉ ጸዊም ጽጌ ምድረ ገነት ሥሙር
እምልሳነ ጴጥሮስ ንህብ ዘበኢነውር
ኢይትኃጣእ በምንትኒ <u>ወንጌል</u> መንግሥት መዓር
ወሥጋ ማርያም ጥቡሐ ክብር
እምከመ ተጠብሐ ሞተ በሊሐ መጥባሕት በምድር
ኢይሄወር እም አዕይንቲሁ ለዕርገት ንስር
ማርያም ፋቅርት ዘጳውሎስ መተርጉመ ዘቃል ምሥጢር
የሀልው ዘልፈ በደብረ ትጉሃን ዘበኩር
ሥርጉተ ስብሐት ዕንቁሰንፔር
ከመ በሠናይ ይልሐቁ ማዕከለ አብትር
ውሉድኪ ሱላሜ ወፍቅር

ዋቢ መጻሕፍት


1. የኢት.ኦ.ቅ ማኅበር - መጽሐፍ ቅዱስ /81/ - 1980 አ.አ
2. ት/ቤት አሳታሚ - መጻሕፍተ ትርጓሜያት - /ወንጌል፣ ጳውሎስ - መልእክትና ቅዳሴ/
3. - ስንክሳር - ብራና
4. - ዜና አበው - ብራና
5. - ገድለ ሐዋርያት - ብራና
6. ኅሩይ ወ.ሥ.ብ. ጌታ - ዜና ሐዋርያት - 1923 ዓ.ም አ.አ
7. - ድርሳናትና ገድላት - ሕትመትና ብራና
8. - ግብረ ሕማማት
9. አባ ጎርጎርዮስ ሊቀጳጳስ - የቤ/ክ ታሪክ በዓለም መድረክ - 1978 አ.አ
10. አባ ጎርጎርዮስ ሊቀጳጳስ - የኢት ቤ/ክ ታሪክ - 1986 ዓ.ም አ.አ
11. ሉሌ መልአኩ - የቤ/ክ ታሪክ - 1986 አ.አ
12. - ፍትሐ ነገሥት - አሥመራ
13. - ክብረ ነገሥት -
14. -
15. - New catholic Encyclopedia - vol I - XI
16. -
17. እን ዶ/ር ሥርግው - የቤ/ክ መዝገበ ቃላት I – III - ጀርመን
18 የኢ. ኦ.ቅ ማኅበር - የኦ.ቅ መዝገበ ቃላት - 19 አ.አ




መምህር ኅሩይ ኤርምያስ

ፖ.ሣ.ቁ 588/1033

ስ.ቁ 0911 16 42 49


## ከዚህ በፊት የታተሙ የጸሐፊው ሥራዎች

### ድርሰት

- መዝገበ ታሪክ ክፍል ፩
- መዝገበ ታሪክ ክፍል ፪
- መልካም ዜጋ ማን ነው ?
- መርኆ ምሥጢር

### ትርጉም

- Daily Prayer / የዘወትር ጸሎት/
- ገድለ ቂርቆስ
- ገድለ ፋሲለደስ


እሌኒ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ.

ዋጋ ብር 35.00